# የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው

ጽሑፍ፡- ብሩስና ካሮል ብሪተን

ትርጉም፡- ጌቱ ግዛው

እርማት፡-

ፈቃዱ ገብሬ፥ ዓለማየሁ ማሞና ወርቁ ኃ/ማርያም

1ኛ እትም በ1993 ዓ.ም፥ 2ኛ እትም በ1995 ዓ.ም

ይህ መጽሐፍ ጋብቻቸው የሞቀና አስደሳች እንዲሆንላቸው ለሚፈልጉ አዋቂዎች ያገለግላል።

በእስያ፥ አውስትራሊያ፥ አፍሪካ፥ አሜሪካና አውሮፓ ባልና ሚስቶች ለትዳራቸው የሚሆኑ መልሶችን ከዚህ መጽሐፍ አግኝተውበታል። እርስዎም እንዲሁ!

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

Copyright ©1998 by SIM Ehiopia, Addis Ababa. Orginally published in English under the title of **ANSWERS FOR YOUR MARRIAGE** third edition by Bruce & Carol Britten © 1998 by World Wide Books, Florida, 1710, South Africa. All rights reserved.

# ለባሎችና ለሚስቶች የሚሆን መጽሐፍ

ከብዙ ዓመታት በፊት በጉርምስና ዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች የሚሆን መጽሐፍ "LOVE AND MARRIAGE" «ፍቅርና ጋብቻ» በሚል ርእስ ጽፌን ነበር። የዚያ መጽሐፍ ዓላማ እግዚአብሔር ለጋብቻ ያቀደውን ድንቅ ዓላማ ለወጣቶች ማሳየት ነበር። በመጽሐፋችን ውስጥ እግዚአብሔር ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንደማይፈቅድ አመልክተናል። መጽሐፉ የተዘጋጀው በጉርምስና ዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ስለነበር በጋብቻ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግሮች ምንም አላነሣንም ነበር።

"LOVE AND MARRIAGE" (ፍቅርና ጋብቻ) የተባለው መጽሐፋችን በብዙ አገሮች ታትሞ ስለተሠራጨ በሺህ የሚቆጠሩ ደብዳቤዎች ከአንባቢዎች ደርሰውናል። ከደረሱን ደብዳቤዎች ጥቂቶቹ በጉርምስና ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶች ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን ከአዋቂዎች ነበር። ከእነዚህ አዋቂዎች መካከል አብዛኛዎቹ በጋብቻ ውስጥ ስላለ ፍቅርና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከባድ ጥያቄዎች የነበሯቸው ናቸው።

በመጨረሻ ለአዋቂዎች የሚሆን መጽሐፍ መጻፍ እንዳለብን ተገነዘብን። ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መጻፍ የሚያሳፍር ቢሆንም በዓለም ዙሪያ ያሉ ባለትዳሮች በጋብቻ ውስጥ ከፍተኛ ትግል የሚያደርጉባቸውን ጥያቄዎች መመለስ አለብን።

«የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው» "ANSWERS FOR YOUR MARRIAGE" የተባለውን መጽሐፍ የጻፍነውም ስለዚህ ነው።

የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ እትም ያነበበች አንዲት ሴት እንዲህ አለችን፡—

«የትዳር ሕይወቴ ጭንቅ ስለነበር ፍቺን ብቸኛ ምርጫ አድርጌ ነበር። "ANSWERS FOR YOUR MARRIAGE" «የጋብቻ እንቆቅልሾችና መፍትሔዎቻቸው» የተባለውን መጽሐፍ አነበብኩ። ከመጽሐፉ ለትዳሬ መልሶችን አገኘሁ። በእርግጥም ያ መጽሐፍ መልሶች ነበሩት። አንድ አሜሪካዊ ባልና ሚስት ለእኔ የትዳር ችግሮች በሆኑት ጉዳዮች ላይ ለመጻፍ መቻላቸው አስደንቆኛል»።

* ኮሎምቢያ፥ ኮትዲቭዋር፥ ሕንድ፥ ኬንያ፥ ኮሪያ፥ ላይቤሪያ፥ ማላዊ፥ ናይጄሪያ፥ ፖርቱጋል፥ ስሎቫኪያ፥ ደቡብ አፍሪካ፥ ታንዛኒያ፥ ኡጋንዳ፥ ዛምቢያና ዚምባብዌ።

# ማውጫ


ምዕራፍ 1 ፍቅራችን ከሰመ....................................1
ምዕራፍ 2 ከሠርግ ቀን በኋላ....................................10
ምዕራፍ 3 በትዳር ሕይወት ፍቅርን ማዳበር....................................13
ምዕራፍ 4 መግባባት አቃተን....................................19
ምዕራፍ 5 ጥቂት ስለ ራሳችን ትዳር....................................28
ምዕራፍ 6 ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አምስት እውነታዎች....................................35
ምዕራፍ 7 የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስልቶች....................................42
ምዕራፍ 8 የሠርግ ቀን ምሽት....................................57


## ደብዳቤዎችና መልሶቻቸው

### ዝሙት፥ ስካርና ዱላ


ዮሴፍ፡- ለአንድ ጊዜ ብቻ ከእርሱ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እፈልጋለሁ....................................70
ኤውጂን፡- ሚስቱ ዝሙትን እየተለማመደች ነው....................................71
ራሔል፡- ከባሌ ጋር መኖር የሚገባኝ ለምንድን ነው? ....................................73
ዳዊት፡- ልጆቻችን ያንን ኃጢአተኛ ሰው ይመስሉብን ይሆንን? ....................................74
ጁሊያ፡- ባሌ ከእርሷ ጋር ተኝቶ አገኘሁት....................................75
ፍሬድ፡- እንድትወደኝ መተት አስደረግሁባት....................................77
ሊና፡- ዱላው ሰለቸኝ....................................77


### የልጆች አስተዳደግ


ጆሴፊን፡- ልጃገረድ እንደመሆኔ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እጠይቅ ነበር...79
ቢትሪስ፡- ለሴት ልጄ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መናገር ይገባኛል?....................................80
ካረን፡- እናቴ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የነገረችኝ እጅግ ዘግይታ ነው ......82
አንዲ፡- እስኪያገቡ ድረስ ድንግል ሆነው መቆየት ይችላሉን? ....................................82
ጌዴዎን፡- ልጆቻችን ለምን ምግባረ ብልሹ ሆኑብን? ....................................82
ጢሞቴዎስ፡- ባለቤቴ ሥራዋን አቆመች....................................85
ክሪስታቤል፡- «ልጆችን በዱላ መምታት ፈጽሞ አያስፈልግም» ትላለች ....86
አውስቲን፡- አባቴን ፈራሁት....................................86
ግላዲስ፡- ልጄ እርባና-ቢስነት እንዳይሰማው ልረዳው እችላለሁን?....................................87
ሙሬል፡- ወደ ቤት ወደ ባሌ ዘንድ መመለስ ያስጠላኛል....................................89
ኢሳይያስ፡- ብልቱ በከፊል መቆረጥ አለበት....................................90


### እርግዝና


ክርስቲን፡- በእርግዝና ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንችላለን?....................................90

ሚሪየም፡- የወንድ የዘር ፈሳሽ በማህፀን ያለውን ፅንሴን
ይጎዳው ይሆንን? ........ 91
ብሬንዳ፡- ጡቶቼ ትንንሽ ስለሆኑ በቂ ወተት አይይዙም ........ 91
ኢቴል፡- የጡቴን ወተት ምን ሊመርዘው ይችላል? ........ 92
ጂን፡- አራርቄ መውለድ እፈልጋለሁ ........ 92
ሳምሶን፡- የቤተሰብ ምጣኔ መልካም ነውን? ........ 93
ኢሊየት፡- እዚያው አልጋዬ ላይ እንድቆይ ነገረችኝ ........ 94
ራያን፡- ባለቤቴ አታረግዝም ........ 95
ሄለን፡- በወር አበባዬ ወቅት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት
ብፈጽም ላረግዝ እችላለሁ? ........ 107
ዶርቲ፡- ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔን እጠቀማለሁ ........ 107
እነዚህን ገጾች የራሳችሁን ሠንጠረዥ ለመሥራት ተጠቀሙባቸው
ቤቲ፡- ጡት ማጥባት እርግዝናን ይከላከላልን? ........ 111
ክሌመንት፡- የፍትወተ ሥጋ ተግባርን ማዘግየት የተሻለ ያደርገዋል ........ 111
ዴኒስ፡- የወንድ ዘር ፈሳሼን ውጭ ባፈሰውም እንኳ አረገዘች ........ 111
አውን፡- የፍትወተ ሥጋ ፍላጎቷ ይቀንስ ይሆንን? ........ 112
አማኑኤል፡- የቤተሰብ ምጣኔ ለእኛ አዲስ አይደለም ........ 112
ካሌብ፡- አራት ሴቶች ልጆች ቢኖሩንም እንኳ አሁን
ወንድ ልጅ እንፈልጋለን ........ 113
ማርጋሬት፡- ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በኋላ የዘር ፈሳሹ
በብልቴ ውስጥ አይቆይም። ........ 115
አሚሊያ፡- አርጅቻለሁ። ማርገዝ እችል ይሆንን? ........
ኢራስመስ፡- ወደ ሐኪም ቤት መሄድ ተገቢ ነውን? ........ 115
በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች
ሮዝሜሪ፡- አልጋችን ይጮኻል ........ 116
ማርክና ዶሪስ፡- ሴትን ለወሲብ የሚቀሰቅሱ ነገሮች ምንድን
ናቸው? ........ 117
ሸርሊ፡- በሥራ ከመድከሜ የተነሣ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት
መፈጸም ያቅተኛል። ........ 119
ሊድያ፡- ለባለቤቴ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወቅትም ፍቅሩን
እንዴት ሊገልጥልኝ እንደሚችል አሳየሁት። ........ 119
ቪክቶር፡- የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የትኞቹን
አቅጣጫዎች መጠቀም እንችል ይሆን? ........ 120
ኢለን፡- በእርግዝና ወቅት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም
የትኛው አቅጣጫ ይሻላል? ........ 121
ትሮይ፡- ቫዝሊን መጠቀም አለብኝን? ........ 122

ግሎሪያ፡- ባለቤቴ ከፍተኛ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት አለው ....122
ሳሙኤል፡- አዘውትሬ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እፈልጋለሁ....124
አግነስ፡- የግብረ ሥጋ ግንኙነት አያስደስተኝም....125
እዝራ፡- በአንዳንድ አቅጣጫዎች ወደ ከፍተኛ የእርካታ ደረጃ አትደርስም...126
አሞጽ፡- ወደ ከፍተኛ የእርካታ ደረጃ ባትደርስም እንኳ በግብረ ሥጋ
ግንኙነት ትደሰታለች....126
ኮሪኒ፡- ልጃገረዶችን ያሳድዳል?....127
ቪንሰንት፡- የፍትወተ ሥጋ ፍላጎትን የሚጨምሩ መድኃኒቶች
የትኞቹ ናቸው? ....127
አንጄላ፡- የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን አስደሳች የሚያደርጉ
ተግባራት ምን ምን ናቸው? ....128
ቬሮኒካ፡- ከእንግዲህ ብልቱ ሊቆምለት አይችልም....131
ጳውሎስ፡- ሲጋራ ማጤስ የወሲብን ኃይል ያደክማልን?....134
ዳንኤል፡- የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸሚያ ዕድሜያችን
አልፎአል....134
ቲኦ፡- በወሲብ ፍላጎቴ ቀዝቀዝ የሚያደርገኝ መድኃኒት ምንድን ነው? ....134
አልፍሬድ፡- ጠጪዎች በወሲብ የላቀ ይደሰታሉን? ....136
ሉቃስ፡- ብልቴ ትንሽ ነው....136
ሩት፡- እስካገባ ድረስ ድንግልናዬን ጠብቄ እቆያለሁ ....137
ኤድጋር፡- የሴት ጓደኛዬ አረገዘችብኝ....138
ሊድያ፡- ያለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ የእርካታ ደረጃ ላይ
መድረስን ተለማምጄያለሁ። እግዚአብሔር በዚህ ይቆጣ ይሆንን? ...139
ዳግላስ፡- ባለቤቴ የቀድሞ የወንድ ጓደኛዋን ታፈቅራለች....140
ማርታ፡- የልጆቼን አባት ላገባው ይገባኛልን? ....142
ኢያሱ፡- ከዚህ ቀደም የፈጸምኩትን የፍትወተ ሥጋ
ኃጢአት ይቅር ልትለኝ አልቻለችም ....143
ሳሮን፡- ከመጋቢያችን ጋር ፍቅር ይዞኛል ....144
እንድርያስ፡- ሚስት አለችኝ፥ የከንፈር ወዳጅ እፈልጋለሁ....145
ጵርስቅላ፡- ኤድስ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መተላለፉ እርግጥ
ነውን? ....146
ኑኃሚን፡- በኤድስ የተለከፉ ሰዎች ምን ይሆናሉ? ....146
አብኔር፡- በኤድስ የተያዙ ሰዎችን መርዳት እንፈልጋለን ....147
ያዕቆብ፡- በኤድስ እንዳልያዝ ምን ማድረግ እችላለሁ? ....148
ዲቦራ፡- ለነርሶች «ንጹሕ ያልተበከለ መርፌ
እንዲጠቀሙ» እነግራቸዋለሁ ....152

ዶርቃ፡- በኃጢአቴ ጥፋተኛ መሆኔን ለሴቶቹ ነገረቻቸው ........................ 153
ኔሊ፡- ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የተነሣ ሊይዙኝ
የሚችሉ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ........................ 153
ጌሪ፡- ኃጢአት ባለ ትዳር ልጅ አልባ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላልን? ........................ 155
ናታን፡- የፍትወተ ሥጋ ፍላጎቶቼ በጣም ያይሉብኛል ........................ 156
አቤሴሎም፡- ልብሷን ለማውለቅ እፈተናለሁ ........................ 157

## አዲስ ባለትዳሮችና በቅርቡ ትዳር የሚፈጽሙ

ጴጥሮስ፡- እግር ኳስ ተጫዋች መሆኔን የማትወድ ይመስለኝ ነበር ........................ 158
ዮሐናም፡- ጓደኛዬ አይደለም። የፍትወተ ሥጋ ፍላጎትም የለኝም ........................ 159
አንቶኒ፡- ባለቤቴን እንዴት ልለውጣት እችላለሁ? ........................ 160
ኢዮኤል፡- ክርስቲያኖች መሆን አለብን? ........................ 161
አቤል፡- የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንድንፈጽም ላስገድዳትን? ........................ 162
ቶማስ፡- የፍትወተ ሥጋ ችግሮች ፍቅርን ያጠፋሉን? ........................ 163
ኤልያስ፡- ማሪዋና ወይም ሐሺሽ ማጨስ የፍትወተ ሥጋ
ተግባርን ያሻሽላል? ........................ 164
ኤማንዳ፡- በቤቱ መኖር ልጀምርን? ........................ 164
ኤውንቄ፡- በአዳዲስ የሴት ጓደኞቼ ተጠምዷልና ጊዜም የለውም ........................ 165
ሔኖክ፡- ባለቤቴን ወይስ እናቴን? ........................ 166
ሜርሲ፡- ከወላጆቼ ጋር መኖር አልፈልግም ........................ 167
መጋቢ ኤን፡- ባለቤቷ ልጃገረዲቱን አስረገዘ ........................ 168
ስምዖን፡- ፈታት ........................ 169
ሲንቲያ፡- ባለቤቴን ለመውደድ ወሰንኩ ........................ 171
ሉይስ፡-ላግባ ወይስ ላጤ ሆኜ ልቅር? ........................ 171
የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በሕይወቴ ........................ 173

# መቅድም

ይህ በዓይነቱና በአቀራረቡ የመጀመሪያ የሆነው መጽሐፍ ከአንባቢዎች ልዩ ልዩ አስተያየቶች እንደሚገጥሙት ይጠበቃል። ምናልባትም ከአስተያየቶቹ በርካታዎቹ ጎሽ! እንኳን ይህን መጽሐፍ ጻፋችሁልን! ለመናገር የምንፈራውን፤ ለመጠየቅ የምናፍረውን፤ የቤታችንና የጓዳችን ምሥጢር የሆነውን እንዲሁም የመኝታ ስፍራ እንቅቅልሾቻችንን ሁሉ የነካና የዳሰስ በመሆኑ እጅግ ተጠቅመናል የሚሉ እንደሚሆኑ ምንም ጥርጥር የለንም።

ጥቂቶቹ ደግሞ እንዲህ ግልጥ መሆን ከባህላችን ጋር ይገጥማል ብላችሁ ነው? ትንሽ ድንበር አላለፋችሁም? አልበዛም? የሚሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሁለቱም አስተያየቶች መሠረታዊ መነሻ አላቸው። ጎሽ፥ እንኳን የሚሉን ብዙ ችግሮችን በጋብቻ ዙሪያ ያዩ፥ ብዙ እንቆቅልሾች የተፈራረቁባቸውና መፍትሔም ለመሻት መውጫ መግቢያው የጠፋባቸው ናቸው። አሁን እንዲህ የልብ ጥያቄን የሚመልስና የመኝታ ቤት ጨዋታንና የትዳር ጓደኛሞችን ፍቅር አስደሳች የሚያደርግ መጽሐፍ በእጅ ላይ ሲገኝ እጅግ ደስ ያሰኛልና ደስታው ተገቢ ነው እላለሁ።

በአንጻሩ ደግሞ ግልጽነቱ አልበዛም ወይ? ከባህላችን ጋርስ አይጋጭም ወይ? የሚሉንም ቢሆኑ ምክንያታቸው ማለፊያ ነው። የኢትዮጵያ ባሕል ብዙ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ሁሉ አንዳንድ ደካማ ጎኖችም እንዳሉት አሌ የማይባል ነው። በተለይም ድብቅ መሆናችን፥ የምንፈልገውን አለመናገራችን፥ በትዳራችን ውስጥ የሚያስቸግረንን በግልጥ መጨዋወት አለመቻላችን፥ የጾታ ትምህርትን ከልጅነት ጀምሮ አለመማራችን፥ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሂደቶችን አስመልክቶ ሥነ-ምግባር የሞላበትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ትምህርት ማጣታችን ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ስለሆነም፥ የዚህ ጽሑፍ አቀራረብ ባህላችንን ያገናዘበ፥ ችግሮቻችን ላይም ያተኮረና እንዲሁም በትዳር እንቆቅልሾቻችን ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ማናቸውም አስተያየት ሰጪ ተጠቃሚ እንደሚሆን እምናለሁ።

የጋብቻ ዝግጅት በማድረግ ላይ ያሉ፥ በቅርቡ የሚጋቡና የተጋቡ፥ እንዲሁም በትዳር ዓመታትን ያስቆጠሩ ሁሉ ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

ስለሆነም፥ ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ አንባብያን ሁሉ ያለኝ ማሳሰቢያ በደስታ፥ በተከፈተ ልብና አዕምሮ፥ ከባህል እሥራት ነፃ በሆነ መንገድ የአስደሳች ጋብቻ ባለቤት ለመሆን በመዘጋጀት ያነብቡት ዘንድ ነው።

## ምዕራፍ 1

# ፍቅራችን ከሰመ

የተወደዳችሁ አቶ ብሪተንና ወ/ሮ ብሪተን

እኔና ባለቤቴ ክርስቲያኖች ነን። የጋብቻ ሕይወታችን ግን አንድ ችግር ገጥሞታል። ፍቅራችን እንደ በረዶ ቀዝቅዟል። ብዙ ጊዜ እንጣላለን። በእኔ አስተሳሰብ እውነተኛው ችግር የፍቅራችን መክሰም ነው።

ጋብቻችንን በፈጸምንበት ወቅት አንዳችን ለሌላችን ጽኑ መተሳሰብ ያለበት ፍቅር ነበረን። አሁን ግን የእነዚያ ቀናት ስሜቶች ደብዛቸው ጠፍቷል።

አሁን ወዳጅነታችን ቀርቷል። በአንድነት በምናሳልፋቸው ጊዜያት ደስተኞች አይደለንም። በችግሮቻችን ላይ አንነጋገርም። እንዲያውም የምንነጋገረው አልፎ አልፎ ብቻ ነው።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችን የሚያስደስተን ሳይሆን በግድ የምንፈጽመው ተግባር ሆኗል።

እኔም ሆንኩ እርሷ ሌላ ሰው አላፈቀርንም። ነገር ግን በመካከላችን የነበረው ፍቅር ከስሟል።

ሕይወቴን በሙሉ በፍቅር አልባ ትዳር ማጥፋት አልፈልግም። በመካከላችን የነበረው ፍቅር ከስሞ እያለ አብረን መቆየት ይገባናልን? ከፍቅር አልባ ትዳር ፍች አይሻልምን? እኔም ሆንኩ እርሷ በእርግጥ የምንወደውን ሌላ የሕይወት ጓደኛ ፈልገን ማግባት አይሻለንምን?

እባካችሁን በዚህ ትዳር እንድቆይ አትንገሩኝ። ይህ ትዳር ደስተኛ ሊሆን እንደማይችል አውቃለሁ። ፍቅራችን ከስሟል።

ምን ጊዜም የእናንተው፥

ኤሪክ

እኔና ካሮል ለኤሪክ ደብዳቤ መልስ ስንሰጥ አሁን ያለበት ትዳር አስደሳች ሊሆን ስለመቻሉና በአስደናቂ ሁኔታ እርካታና ሐሤት የሚገኝበት እንደሚሆን አበሰርንለት።

እኔና ካሮል የኤሪክን ችግር ተረድተን ነበር። ከብዙ ዓመታት በፊት በትዳራችን ውስጥ ተመሳሳይ ችግር ነበረብን። በዚህ መጽሐፍ ስለትዳራችን ወደፊት እንናገራለን፥ አሁን ግን የኤሪክን ፍቅር አልባ የትዳር ሕይወት እንመልከት።

የኤሪክ የመጀመሪያ ችግር ፍቅር ምን እንደሆነ አለማወቁ ነው። የፍቅርን ምንነት የሚያውቅ ይመስለዋል፥ ነገር ግን ተምታቶበታል።

ብዙ ሰዎች ስለ ፍቅር እውቀት እንደሌላቸው እርግጥ ነው። በየትም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች (በአሜሪካ፥ በአፍሪካ፥ በአውሮፓ፥ በአውስትራሊያ ወይም በእስያ) ስለ ፍቅር ሲናገሩ ትሰማላችሁ፥ ምንነቱን ግን በትክክል አልተረዱትም።

ብዙ የጋብቻ ችግሮች የሚነሡት ባልና ሚስት እርስ በርስ ባለመዋደዳቸው ነው። እንዲያውም ፍቅር ራሱ ምን እንደሆነ አያውቁትም።

ፍቅር ምንድን ነው? መልሱ ቀላል ነው። *ፍቅር የደግነት ተግባራት ነው።* ፍቅር የምናደርገው ነገር ነው። ፍቅር ስሜት አይደለም። ፍቅር የደግነት ተግባራትን ማድረግና መልካም ቃሎችን መናገር ነው። ፍቅር ስንል መስጠትና ይቅር ማለት ነው። ፍቅር መርዳት፥ ማመስገን፥ ፈገግ ማለትና ማገዝ ነው። ፍቅር እነዚህ ሁሉ ተግባራትና ከዚህም በላይ ሌሎች ሺህ ተግባራት ናቸው።

ኤሪክ ግን ይህን ተረድቶ ነበርን? ሰው ሁሉ ይህን ይረዳልን? አይረዳም! ብዙ ሰዎች ፍቅር የሚጠፋ ነገር እንደሆነ በማሰብ ይሳሳታሉ። ኤሪክ ሲጽፍ «ፍቅራችን ከሰመ» ይላል።




እውነቱ ግን ፍቅር የማይከስም መሆኑ ነው።

ቁልፍ ሊጠፋ ይችላል። በቅርቡ የቤቴ ቁልፍ ጠፋብኝ። ምንም ብለፋ ላገኘው አልቻልኩም። ፍቅር ግን ሊጠፋብኝ አይችልም። ከፈለግኩ ሁልጊዜ ማፍቀር እችላለሁ። ማፍቀር የምችለው ፍቅር ተግባር ስለሆነና ተግባራቴን መምረጥ ስለምችል ነው።

ደግና ረዳት መሆንን ከመረጥኩ ማፍቀርን መረጥኩ ማለት ነው። አለማፍቀርንም መምረጥ እችላለሁ። ትዕግሥት- የለሽና ይቅርታ-ቢስ መሆን እችላለሁ።

ላለመውደድ ምርጫ ካደረግሁኝ ፍቅሬ ጠፋብኝ ወይም «ከሰመ» ማለት አልችልም። ባለቤቴን ካልወደድኳት ጥፋቱ የራሴ ነው። የእኔ ኃላፊነት ባለቤቴን መውደድ ነው። ይህ ግዴታዬ ነው። ካልወደድኳት ምክንያቱ የፍቅር መጥፋት ወይም መከሰም አይደለም። ነገር ግን *በጎና መልካም ተግባራትን* ላደርግላት ባለመምረጤ ነው።

## የፍቅር ስሜት

ፍቅር ምን እንደሆነ ተነጋግረናል፥ አሁን ወደ ሌላ ርእስ እንተላለፍ። ይህም «የፍቅር ስሜት» የሚል ነው። እባካችሁ *የፍቅር ስሜት ከማፍቀር* ጋር አንድ እንዳልሆነ ልብ በሉ።

«የፍቅር ስሜት» ምንድን ነው? የዚህን ጥያቄ መልስ ሁሉም ሰው ሳያውቀው አይቀርም። የፍቅር ስሜት አስደናቂ፥ አስደሳች ስሜት ነው..... ‹ትወደኛለችና እወዳታለሁ› የምንለው ስሜት ነው። ይህ የፍቅር ስሜት እጅግ አስደናቂ ከመሆኑ የተነሣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዘፈኖች ተዘፍነውለታል፤ ግጥሞችም ተገጥመውለታል።

ዳሩ ግን ስለ ፍቅር ስሜት ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚረዱት አንድ እውነታ አለ። ይህ እውነታ *የፍቅር ስሜት የሚመጣና የሚሄድ መሆኑ ነው*። አንድ ሰው ዛሬ ጠንካራ የፍቅር ስሜት ሊኖረው ይችላል። ይህ ስሜት ነገ ሲጠፋ ከነገወዲያ ሲመለስ ከዚያ በኋላ ሲጠፋ ቆይቶ ደግሞ እንደገና ሊከሰት ይችላል። ለምን? ምክንያቱም የፍቅር ስሜት፥ ስሜት ብቻ ስለሆነ ነው፥ ስሜቶቻችን ደግሞ ይቀያየራሉ።

እኛ ሰዎች ብዙ የተለያዩ ስሜቶች አሉን። አንድ ቀን ልናዝን በሌላ ጊዜ ደግሞ ልንደሰት እንችላለን። አንዳንድ ቀናት ሐሤት ልናደርግ በሌላ ጊዜያት ልንቆጣ፥ አንዳንድ ጊዜ ብቸኝነት ሊሰማን በሌላ ጊዜ ደግሞ በፍቅር እንደተከበብን ሊሰማን ይችላል። ነገር ግን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ስሜት ሊኖረን አይችልም።

ለአንድ ወር ሙሉ በየዕለቱ የደስተኛነት ስሜት ተሰምቶህ ያውቃልን? ሊሆን አይችልም። የደስተኛነት ጉዳይ ስሜት ስለሆነ ይመጣል ይሄዳል። ስሜቶቻችን ሁሉ ብልጭ፥ ጥፍት ይላሉ፥ ደግሞ እንደገና ብቅ ይላሉ። ይህም የፍቅርን ስሜት ይጨምራል።

## ከሠርግ ቀን በኋላ

*ሙሽሪትና ሙሽራው* በሠርጋቸው ቀን እስከ ሞት ድረስ ለመዋደድ *ቃል* ኪዳን ይገባሉ። ይህ ማለት በየዕለቱ *የፍቅር ስሜት* እንዲኖራቸው *ቃል* ገቡ ማለት ነውን? አይደለም። *ለመዋደድ ቃል* ሲገቡ *የፍቅር ተግባራትን ለመፈጸም ቃል* መግባታቸው ነበር። ደግ፥ ርኅሩኅ፥ ረዳት፥ ተገንዛቢ፥ ይቅር ባይ፥ ወዘተ... ለመሆን *ቃል* መግባታቸው ነው።

የፍቅር ስሜት ይኖራቸዋልን? አዎን፥ ነገር ግን ሁልጊዜ አይደለም። አንዳንድ ቀናት ትኩስ የፍቅር ስሜት ይኖራቸዋል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በምትኩ ሌላ ስሜት ሊኖራቸው ይችላል። የጭንቀትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ምንም ዓይነት የፍቅር ስሜት ላይኖራቸውም ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ምንም አይደለም። እግዚአብሔር አንዳንድ የተወሰኑ ስሜቶች እንዲኖሩን አላዘዘም። ያዘዘን እንድንዋደድ ነው።

ስለዚህ ባልና ሚስት በበጎና መልካም ተግባራት ያለማቋረጥ መዋደድ አለባቸው። ስሜቶቻቸው ይመጣሉ ይሄዳሉ፥ ስለዚህ መስጋት የለባቸውም። ሥራቸው በመልካም፥ በጎ ቃላትና ተግባሮች መዋደድና ያንንም በየዕለቱ መፈጸም ነው (1ኛ ቆሮ. 13፡4ን ተመልከት)።

ስሜቶቻችንን መቆጣጠር አንችልም፥ ነገር ግን ተግባሮቻችንን መቆጣጠር እንችላለን። አንዳንድ ስሜቶች እንዲኖሩን የመምረጥ መብት የለንም። ነገር ግን አንዳንድ ተግባራትን ለመፈጸም መምረጥ እንችላለን። ለምሳሌ በባለቤቴ ላይ እንድጮኽባት ብፈተንና ይህን ፈተና አሸንፌ በመልካምና በርኅራኄ ቃላት ብናገራት ልወዳት መረጥኩ ማለት ነው።

እራሴን የመውደድ ስሜት በሚይዘኝ ወቅት እንኳ ለትዳር ጓደኛዬ እንክብካቤ ማድረግን ልመርጥ እችላለሁ። ስለ ችግሮችዋ በምትናገርበት ወቅት ልሰማትና ልረዳት መጣር እችላለሁ። እርሷን ማጽናናትና ማረጋጋትን ልመርጥ እችላለሁ። ስሜቶቼ ስስታምና ቂመኛ እንድሆን በሚግጠሩኝ ወቅት እንኳ ፍቅር የሞላባቸው ነገሮችን መፈጸምን መምረጥ እችላለሁ።

አንዳንድ ጊዜ የትዳር ጓደኛዬን እንዳገለግል ሲሰማኝ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ እራሴን በማስደሰቱ ላይ እንዳተኩር ሊሰማኝ ይችላል። ፍቅር ማለት በማይሰማኝ ወቅት እንኳ የትዳር ጓደኛዬን ማገልገልን መምረጥ ማለት ነው።

የትዳር ጓደኛዬን ለማገልገል በምመርጥበት ወቅት በዚያን ቅጽበት ያሉትን ስሜቶቼን እየታዘዝሁ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በሠርጋችን ዕለት የገባሁትን ቃል ኪዳን እየፈጸምኩ ነው።

በዚያ ቀን እስከ ሞት ድረስ ባለቤቴን ልወዳት ቃል ገብቻለሁ። ያንን ቃል ኪዳኔን መጠበቅ እችላለሁ። ማፍቀርን መምረጥ እችላለሁ። ማፍቀር ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነ ነገር አይደለም። «ፍቅሬ ከሰመ» ወይም «ፍቅሬ ጠፋ» ልል ፈጽሞ አልችልም።

## የኤሪክ የጋብቻ ሕይወት ተስፋ አለውን?

ኤሪክ «ፍቅሬ ከሰመ ወይም ጠፋ» ይላል። እግዚአብሔር ደግሞ «ሚስትህን ውደድ» ይላል።

ኤሪክ ሚስቱን መውደድን ሊመርጥ ይችላል። ደግ፥ ታጋሽ፥ ለጋስ.... በመሆን እግዚአብሔርን መታዘዝ ሊመርጥ ይችላል።

«የፍቅር ስሜትን» በተመለከተስ? የኤሪክ ጋብቻ ከእንግዲህ አስደናቂ፥ ሞቅ ያለና አስደሳች የፍቅር ስሜት ሊኖረው ይችላልን? በሚገባ!

በዚህ ቅጽበት ኤሪክ የፍቅር ስሜት የለውም። በጤነኛ የትዳር ሕይወት ውስጥ የፍቅር ስሜት ይመጣል፥ ይሄዳል፤ በኤሪክ የጋብቻ ሕይወት ግን ይህ ስሜት ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል። ለሚስቱ የፍቅር ስሜት የሚሰማባቸው ቀናት እጅግ ርቀውታል።

ነገር ግን ያ ሊለወጥ ይችላል!

ለኤሪክ ትዳር– ለአንተም/ለአንቺም ቢሆን–ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ትእዛዝና የተስፋ ቃል ቀጥሎ ተሰጥቷል።

**ትእዛዝ**

የፍቅር ስሜትህ/ሽ የጠፋ ቢሆንም እንኳ የትዳር ጓደኛህ/ሽን ውደድ/ጂ። የትዳር ጓደኛህን/ሽን በመልካም ተግባራት ውደድ/ጂ። አጋዥ፥ ትሑት፥ ለጋስ፥ ታማኝና ራስን አሳልፎ የሚሰጥ ለመሆን ጥንቃቄ አድርግ/ጊ።

ይህ ከባድ ትእዛዝ ነው፥ አይደል እንዴ? ነገር ግን ታገሥ፤ ቀጥሎ አስደናቂ የተስፋ ቃል ታገኛለህ።

**የተስፋ ቃል**

የፍቅር ተግባራትህን ያለሚቋረጥ ስትፈጽም ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን ወይም ወዲያውኑ የፍቅር ስሜትህ ይመለሳል! ልክ ነው፥ በቀረው ዘመንህ በፍቅር አልባ ስሜት መቀጠል የለብህም። ያ አስደናቂ ስሜት ሊመለስ ይችላል። የፍቅር ተግባራትን መምረጥ ስትቀጥል ይመለሳል።

የፍቅር ስሜት ስሜት ብቻ መሆኑ እርግጥ ነው። በየዕለቱ ላይኖርህ ይችላል። ይመጣል፥ ይሄዳል። ነገር ግን አትጨነቅ.....የፍቅር ተግባራትን ለማድረግ መምረጥህን ከቀጠልክ የፍቅር ስሜት ለረጅም ጊዜ አይሸሽህም።

አስታውሱ፥ ኤሪክ ደብዳቤውን ያጠቃለለው «የጋብቻ ሕይወታችን ከቶውንም ደስተኛ ሊሆን አይችልም...ፍቅራችን ከስሟል (ጠፍቷል)» በማለት ነበር። እውነቱ ግን የከሰመው ወይም የጠፋው የፍቅር ስሜታቸው ብቻ መሆኑ ነው። ያ የፍቅር ስሜት ደግሞ የፍቅር ተግባራትን መፈጸም ሲጀምሩ ይመለሳል። አስቀድመው የፍቅር ተግባራትን መፈጸም መጀመር አለባቸው፥ ከዚያም የፍቅር ስሜቶቻቸው ይመለሳሉ።

## የፍቅር ስሜታቸው የጠፋባቸው ለምንድን ነው?

ኤሪክና ባለቤቱ የፍቅር ስሜታቸውን ያጡት እንዴት ነበር? መልሱ የሚከተለው ለመሆኑ ጥርጥር የለንም፤ የፍቅር ተግባራትን መፈጸም ስላቆሙ የፍቅር ስሜቶቻቸው አሽቆለቆሉ።

ምናልባት በጋብቻ ሕይወታቸው መጀመሪያ አካባቢ አንዳቸው ለሌላቸው በጣም ትሑትና ደግ ነበሩ። ነገር ግን ቆይተው አንዳቸው ለሌላቸው የሚያደርጉትን የፍቅር እንክብካቤ አቁመው ተቺዎች፥ ተሳዳቢዎች ወይም

ርኅራኄ የጎደላቸው ሆኑ። ይህም የፍቅር ስሜት ከልባቸው እየራቀ መሄዱ የማይታበል ነው።

ሆኖም ግን የፍቅር ተግባራትን ለመምረጥ ከወሰኑ ያ እስደሳች የፍቅር ስሜታቸው ይመለሳል።

## ተግባራችን ስሜታችንን ይቅደም!

ዛሬ አንድ ባል ለተወዳጅ ሚስቱ አስደናቂ የፍቅር ስሜት አለው እንበል። እጅግ ግሩም ተወዳጅና ውብ ሴት ሆና ትታየዋለች።

አንድ የሚያበሳጭ ነገር አደረገችበት እንበል። በዚህ ተግባሯ እንዴት እንዳስቀየመችው ሲያስብ በልቡ የነበረው የፍቅር ስሜት በቁጣ ይተካል።

አሁን ምርጫ ማድረግ ያለበት ሁኔታ ውስጥ ይወድቃል። ከፈለገ ትዕግሥቱ ተሟጥጦ ሊጮኽባት ይችላል። ወይም ደግሞ እንዴት እንዳሳዘነችው በዝግታ ሊያስረዳት ይችላል። ከዚያም ይቅርታ አድርጎላት ለእርሷ ባለው መልካምነት ሊቀጥል ይችላል።

ምርጫው የእርሱ ነው... ከፈለገ ሊወዳት ይችላል።

ቀጥሎ ምን እንደሚሆን መገመት ትችላላችሁን? ትዕግሥቱ እንዲሟጠጥ ፈቅዶ ከጮኸባት የፍቅር ስሜቱ ይቀንሳል፤ በፍቅር ተግባራቱ ግን ሊቀጥል ከፈቀደ የፍቅር ስሜቱ ያድጋል።

ፍቅር እንደዚህ ነው። የፍቅር ተግባራትን ለመፈጸም ስንፈቅድ ወዲያውኑ የፍቅር ስሜቶቻችንን እናገኛቸዋለን።

## የፍቅርን ስሜት እንዴት መልሰን እንደምናገኝ

ኤውንቄ ማርቲንን በማግባቷ በጣም ደስተኛ ነበረች። እንደዚህ ዓይነት አስደናቂ ክርስቲያን ባል በማግኘቷ እግዚአብሔርን እጅግ አመስግና ነበር!

ከጋብቻቸው ጥቂት ቀናት በኋላ «ባል ለምን ሰጠኸኝ? ለምንስ እርሱን?» የሚል እግዚአብሔርን የሚከስ ጥያቄ በውስጧ ተፈጥሮ ስታገኝ መደናገጥ ውስጥ ገባች።

ማርቲን የምትፈልገውን ያህል ሁልጊዜ ማራኪ እንዳልሆነ ተገነዘበች፥ ስለዚህም ለእርሱ ያላት ስሜት እየቀዘቀዘ መጣ። በዚህ መካከል ኤውንቄ በሠርጓ ቀን መጋቢዋ «ይህን ሰው ልትወጂው ቃል ትገቢያለሽን?» በማለት የጠየቃት ጥያቄ ትዝ አላት።

ቀስ በቀስ «ማርቲንን መውደድ አለብኝ» የሚል ግንዛቤ ውስጥ ገባች። የማይስማማና ስስታም በሚሆንበት ጊዜም እንኳ መውደድ አለብኝ... ከእርሱ ጋር አብሬ እኖር ዘንድ እጅግ አስቸጋሪ በምሆንበት ጊዜ እንኳ እንደሚወደኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለች።

ስለዚህም ለእራሷ እንዲህ አለች፡- «አሁኑኑ አንድ የፍቅር ተግባር ልፈጽምለት ይገባል፥ በጣም የሚወደውን ምግብ አዘጋጅለታለሁ!»

ምግቡን እያዘጋጀችለት ሳለ ስሜቷ መለወጥ ጀመረ። ለእርሱ የነበራት የፍቅር ስሜት እንደገና ይቀጣጠል ጀመር!

ለእርሱ የነበራትን የፍቅር ስሜት እንደገና ያመጣላት የፍቅር ተግባሯ ነበር፥ (ማለትም የሚወደውን ምግብ ማዘጋጀቷ)።

**በተግባር የተገለጠ ፍቅር የፍቅርን ስሜት እንደገና ያመጣል።**

የሚያሳዝነው ነገር ይህን የሚረዱ ባልና ሚስት ጥቂቶች መሆናቸው ነው። ብዙዎች እንደ ኤሪክ ናቸው። የፍቅር ስሜት ሳይኖር ሲቀር ፍቅራቸው የከሰመና የጠፋ ስለዚህም የትዳር ሕይወታቸው ተስፋ ቢስ የሆነ ይመስላቸዋል።

ዛሬ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ባልና ሚስቶች በሙሉ ስለ *ፍቅርና* ስለ *ፍቅር ስሜት* የሚከተለውን መረዳት አለባቸው።

| | |
|---|---|
| 1ኛ እውነታ<br>*ፍቅር ተግባር ነው።* የጨዋነት፥ የአርቆ አሳቢነት፥ የታጋሽነት ወዘተ... ተግባር ነው። ማፍቀርን ምርጫህ ማድረግ ትችላለህ። | 2ኛ እውነታ<br>*የፍቅር ስሜት፥* ስሜት ብቻ ነው። ስለዚህ ይመጣል ይሄዳል፥ አንዳንድ ጊዜ ይኖራል፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ አይኖርም። |
| 3ኛ እውነታ<br>በተግባር ማፍቀርን ስትተው የፍቅር ስሜትህ መጥፋት ወይም መከሰም ይጀምራል። | 4ኛ እውነታ<br>የፍቅር ስሜትህ ከጠፋ መልስህ አግኘው። እንዴት? በተግባር ማፍቀርን ምረጥ። ጀምር! |

## ፍች

ኤሪክ በደብዳቤው ሚስቱን ሊፈታት እንደሚፈልግ ተናግሯል። እኔና ካሮል «ፍች» የሚለውን ቃል ስንሰማ ለታላቅ ወንድሜ የሚከተለውን የውሳኔ አሳቧን የተናገረች የአንዲት ወጣት ሴት ታሪክ ትዝ ይለናል፥ «ባለቤቴን መፍታት እፈልጋለሁ። በዚህም አሳርረዋለሁ» ትለዋለች።

ታላቅ ወንድሟም «ጥሩ ነው። ደኅና አድርገሽ እንዴት እንደምታሳርሪው እነግርሻለሁ። በመጀመሪያ ያስደስተዋል የምትዪውን ነገር ሁሉ ማድረግ ጀምሪ። ለእርሱ ልታደርጊ የምትችይውን ተጨማሪ በጎ ነገሮች አስቢ። ሁልጊዜ በአክብሮት አነጋግሪው። ማጉረምረም አቁሚ። ወዲያውኑ ያለ አንቺ መኖር ያለመቻሉን በማሰብ አጥብቆ ይፈልግሻል። ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ፍቺውን ፈጽሚ። ይህ በእርግጥ ያሳርረዋል» የሚል መልስ ሲሰጣት በጣም ነበር የተገረመችው።

ከጥቂት ወራት በኋላ «የመጀመሪያውን እርምጃ ወስጄአለሁ» በማለት ለወንድሟ ነገረችው።

ወንድሟም መልሶ «በጣም ጥሩ ነው። ፍችሽን መፈጸም ያለብሽ ጊዜ አሁን ነው» አላት።

አድናቆት በሞላበት ሁኔታ «ፍች! አልችልም፤ አሁን በፍቅሩ ተይዤአለሁ» አለችው።

የፍቅር ተግባራት የፍቅር ስሜቶችን መልሰው እንደሚያመጡ ተገነዘበች። ብዙ የትዳር ጓደኞች ይህን እውነት ሳይገነዘቡ መቅረታቸው እንዴት የሚያሳዝን ነው! «የፍቅር ስሜታችንን አጥተናል። ስለዚህ ለዚህ ትዳር ምንም ተስፋ አልቀረለትም። መፋታት አለብን» ይላሉ።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- መውደድን(ፍቅርን) ምረጡ... ፍቺን አትምረጡ። «ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም» (1ኛ ቆሮ. 13፡8)። «እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ» ( ዮሐ. 15፡17)። «ባሎች ሆይ! ...ሚስቶቻችሁን ውደዱ» (ኤፌ. 5፡25፥26)። «እኔ ግን፥ እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል» (ማቴ. 19፡9)።

## ለኤሪክ የሰጠነው መልስ

ውድ ኤሪክ፥

በሠርግህ ቀን ሞት እስከሚለያችሁ ድረስ ሚስትህን እንደምትወድ ቃል ገብተሃል። ይህ ቃል ኪዳን ለእግዚአብሔር የሰጠኸው መሐላ ነበር። ስለዚህ ልትጠብቀው ይገባል።

«ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ» (መክ. 5፡4)።

መውደድ ቀላል ነገር አይደለም። ነገር ግን ሚስትህን ለመውደድ ቃል ገብተሃልና በእግዚአብሔር ርዳታ ልትፈጽመው ይገባሃል።

በተግባር ማፍቀር ስትጀምር ወዲያውኑ ወይም ጥቂት ቆይቶ ስሜትህ ሲመለስ በማየት ደስተኛ ትሆናለህ። አዎን «ፍቅር ይዞኛል!»

ብለህ እንድትጮህና እንድትዘምር የሚያደርግህን አስደናቂ ስሜት እንደገና ታገኛለህ።

ከዚያም በኋላ ቢሆን ስሜትህ ከፍና ዝቅ ማለቱ የማይቀር ነው። ስሜትህ በዕለቱ ከፍ ወይም ዝቅ ቢል እንኳ የአንተ ተግባር ሚስትህን መውደድ ነው።

በተግባር የማፍቀርን መልካም ሥራ ከፈጸምክ ዓመታት ባሳለፍክ ቁጥር በጋብቻ ውስጥ የሚኖረው የፍቅር ስሜት የበለጠ አስደናቂ እየሆነ ይሄዳል። የስሜት ከፍና ዝቅ ማለት ሁልጊዜ ይኖራል፥ ነገር ግን ዝቅታው እየቀነሰ ከፍታው የበለጠ አስደሳች እየሆነ ይሄዳል።

«ከፍቅር አልባ ትዳር ፍች አይሻልምን?» ብለህ ጠይቀሃል። መልሱ ሁለቱም አይሻልም ነው። ሚስትህን አትፍታ፤ ፍቅር አልባ የሆነ የትዳር ሕይወትህንም አትቀጥል። ማፍቀርን ምርጫህ አድርግ። በእግዚአብሔር ርዳታ የትዳር ሕይወትህ ሞቅ ያለና የፍቅር ስሜት የሞላበት ይሆናል። ታዲያ ፍች ከዚህ ይሻላልን?

ምዕራፍ 2

# ከሠርግ ቀን በኋላ

ውድ ብሩስና ካሮል፥

ትክክለኛዋን ሴት ካገባሁ እወዳት ዘንድ እጅግ ቀላል እንደሚሆን አስብ ነበር። በዚሁ መሠረት ኤውንቄ የተባለች መልካም ክርስቲያን ሴት አገባሁ። ከተጋባን ስድስት ወራት ሆኖናል። እኔ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ባላውቅም እርሷ ስለምትሄድ ደስ ይለኛል። እርሷ ጥሩ ሚስት ብትሆንም እንኳ በየዕለቱ ስጮኽባት ራሴን አገኛለሁ። ለመሻሻል ብጥርም አቃተኝ። ችግሬ ምን ይሆን?

የእናንተው፥

ስምዖን

---

ውድ ስምዖን፥

መውደድ ቀላል አይደለም። እኛ ሰዎች በተፈጥሮአችን ስስታሞች ነን። ብዙ ጊዜ ፍቅር የጎደላቸው ተግባራትን መፈጸምና መነጋገር ይቀናናል።

እግዚአብሔር ሊረዳን ይፈልጋል፥ ነገር ግን ችግር አለ። ኃጢአታችን ከእግዚአብሔር ይለየናል። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ የሚያስፈልገን ኃጢአታችንን የሚያስወግድልንን ሰው ማግኘት ነው።

ይህን ማድረግ የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው።

ስምዖን፥ ስለዚህ ኃጢአተኛ መሆንህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ። በአንተ ስፍራ ተሠቃይቶ መሞቱን እመን። አዳኝህ እንዲሆን ጠይቀው። የዘላለም ሕይወትን ይሰጥሃል።

አፍቃሪ ባል መሆንን እግዚአብሔር ቀላል ያደርግልሃልን? አያደርግልህም። ማፍቀር ቀላል ነገር አይደለም። ክርስቶስን ከተቀበልክ በኋላ ግን የእግዚአብሔር ኃይል በአንተ ውስጥ ስለሚሆን ድልን መቀዳጀት ትጀምራለህ።

---

### ከሠርግ ቀን በፊትና ....በኋላ

ትክክለኛ የትዳር ጓደኛ ከመረጥኩ ማፍቀር ቀላል ይሆንልኛል በማለት የሚያስቡ እንደ ስምዖን ያሉ ሰዎች በርካታ ናቸው። ከሠርጋቸው ቀን በኋላ ማፍቀር ቀላል እንዳልሆነ ለመገንዘብ ረጅም ጊዜ አይወስድባቸውም።

ለወጣት ወንድና ሴት ከሠርግ ቀናቸው በፊትና....በኋላ ያሉት ጊዜያት በአብዛኛው ምን እንደሚመስሉ እንመልከት።

አንድ ወጣት ወንድ በአንዲት ወጣት ሴት ላይ ልዩ ስሜት ሲያድርበት ያለውን ሁሉ ሊሰጣትና በትሕትና ሊቀርባት ጥንቃቄ የተሞላባቸውን እርምጃዎች ይወስዳል። እርሷም ደግሞ የምትፈልገው ከሆነ እንዳታስቆጣውና ትዕግሥቱን እንዳታስጨርሰው በመጠንቀቅ መልካም ሴት ሆና ትቀርበዋለች።

እነዚህ የፍቅር ተግባራት ለወራት ይቀጥላሉ። እናም ወደ ሠርጋቸው ቀን ያደርሷቸውና ይጋባሉ። ከዚያ በኋላ ምን ይሆናል?

ችላ ማለት ይጀምራሉ!

ሴቲቱም እንዲህ ብላ ታስባለች። «አሁን ባል አለኝ፥ ሕይወቴን በሴተ ላጤነት እገፋው ይሆን የሚል ስጋት የለብኝም። ስለዚህ ዘና ማለት እችላለሁ።» ችላ ማለት ምን ማለት ነው? ለባሏ ጥሩ ሆና ለመገኘት ብዙ አትጨነቅም ማለት ነው።

ባለቤቷም እንደዚሁ ነው። ከሠርጉ ቀን በኋላ እንዲህ ማለት ይጀምራል። «አሁን ሚስቴ ሆናለች፥ አሁን የራሴ ሴት ናት» እናም እንደማንኛውም ሴት ሊያያት ይጀምራል። ስለሚያስፈልጋት ነገር መጨነቅ ያቆምና መዝናናት ይጀምራል። ባደረገችው አንድ ነገር ሲጎዳ ይቅርታ ማድረግ ያቅተዋል። እናም እርሷን በሚጎዳ ነገር ምላሹን ለመስጠት ይሞክራል።

እርሷም ተመሳሳይ ድርጊት ትፈጽምበታለች። ስለዚህ መጎዳዳቱ እያደገ ይመጣል።

ከሁለት አንዳቸው «ጌታ ሆይ፥ የትዳር ጓደኛዬ ለእኔ መልካምና ደግ በማይሆንበት ጊዜ እንኳ በአንተ ርዳታ ደግና መልካም እሆንለታለሁ» ብለው ቢጸልዩ የትዳር ሕይወታቸው ሊሻሻል ይችላል። ይህን ማለት ግን ከባድ ነው። ስለዚህ አያደርጉትም። ይልቁኑ ችላ ማለትን ይቀጥሉበታል።

ወዲያውኑ *የፍቅር ስሜታቸው* እየወረደ ይመጣል። ከመጋባታቸው በፊት ሁለቱም አስደናቂ የፍቅር ስሜት ነበራቸው። በእነዚያ ቀናት *«በዓለም ላይ ከሁሉም የላቀ ሥርዓት ያለው፥ ደግ፥ አስደናቂ ሰው ሆኖ ሳለ ሊያገባኝ እኔን መረጠ»* ብላ ታስብ ስለነበር በሐሤት ትኖር ነበር። እርሱም ከፍተኛ ደስታ ነበረው። ምክንያቱም *«በምድር ላይ ከሁሉም የላቀች መልካም ሴት»* ለማግባት እየተዘጋጀ ነበርና። አሁን ግን አንዳቸው ለሌላቸው የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ይቀንሳሉ....የፍቅር ስሜታቸው እየከሰመ ይሄዳል እናም እያንዳንዳቸው *«ለምንድን ነው ብዙ ጊዜ የምንጋጨው? በልባችን የነበረው የፍቅር ስሜት የት ደረሰ? ምናልባት ፍቅራችን ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ ይሆናል»* ይላሉ።

እግዚአብሔር የሚሰጣቸው መልስ «እርስ በእርሳችሁ እንድትዋደዱ አዝዣችኋለሁ» የሚል ነው። ይህ ማለት ከሠርጋቸው ቀን በኋላ አንዳቸው ለሌላቸው የፍቅር ተግባራትን ማድረግን መቀጠል አለባቸው ማለት ነው።

ትዕግሥት ማድረግን፥ . . . ደግነታቸውንና ቸርነታቸውን፥ እና የመሳሰሉትን ማቆም የለባቸውም።

ይህን ማለት ከሠርጋቸው ቀን በኋላ *ችላ ማለት የለባቸውም* ማለት ነውን? አዎን እንደዚያ ማለት ነው!

በየዕለቱ የፍቅር ተግባራቸውን ለመቀጠል *ጥንቁቅ* መሆን አለባቸው። ተግተው *መሥራት* አለባቸው። ችላ ማለት የለባቸውም።

«ነገር ግን ክርስቶስ በእኔ ከኖረና ኃይሉን ከሰጠኝ ዘና ማለት አልችልምን?» አትችልም፥ ከክርስቶስ ጋር *መሥራት* አለብህ። አብሮ በመሥራት ድልን ማግኘት ይቻላል።

እንዴ እስቲ ጥቂት እናስብ! የትዳር ጓደኛዬን ለማፍቀር ተግቼ *መሥራት* ካለብኝ ይህ ጉዳይ ትዳርን ቀዝቃዛና ስሜት አልባ አያደርገውምን?

አያደርገውም። ሞክርና እየው! ዛሬውኑ ጀምር የትዳር ጓደኛህን በማፍቀር። ትጋ፤ በልዩ እንክብካቤ ለመያዝ ተጨማሪ ጥንቃቄ ውሰድ/ጂ። ክርስቶስ እንዲረዳህ ጠይቅ። *የትዳር ሕይወታችሁ በፍቅር ያደገ...የመኝታ ጊዜያችሁም ተናፋቂና አስደሳች ይሆናል!*

በሚቀጥለው ምዕራፍ አንተና የትዳር ጓደኛህ አንዳችሁ ለሌላችሁ ፍቅር የምትገልጹባቸውን ሦስት ጠቃሚ መንገዶች ትመለከታላችሁ።

ምዕራፍ 3

# በትዳር ሕይወት ፍቅርን ማዳበር

በትዳር ሕይወት ውስጥ ፍቅርን ለማዳበር እንዲቻል የሚያደርጉ ተግባራዊ ልምምዶችን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

ከትዳር ጓደኞቻችሁ ጋር የምትዋደዱባቸው ሦስት ተግባራዊ የሆኑ ነገሮች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል።

1) የአድናቆት ቃላትን መጠቀም

ሰው ሁሉ አድናቆትን ይፈልጋል። ሁላችንም የሚከተሉትን ዓይነት አባባሎች መስማት እንወዳለን፥ «መልካምነትህን/ሽን አደንቃለሁ፥ እንደ አባት/ እናት ለልጆቻችን የምታደርገው/ጊው መልካም ሥራዎች ያስደስቱኛል።»

ለተግባራችን አድናቆት ካላገኘን እንጎዳለን። አንዲት የቤት እመቤት እንዲህ ብላ ጻፈች፥ «ባለቤቴ ቤቱ ንጹሕ መሆኑን፥ ሸሚዞቹ በሚገባ መተኮሳቸውን ልብ የሚል አይመስለኝም፥ ብቻ ከዋለበት ወደ ቤት ሲገባ እራት እስካሁን አልደረሰም? ይላል።»

አድናቆታችንን በግል ብቻ ሳይሆን ሌሎች ባሉበትም መግለጽ አለብን።

ካሌብና ራሔል የእርሱን ዘመዶች ጥየቃ በተገኙበት ቦታ፥ «በመኪናህ ወደ ሱቅ ታደርሰኛለህ? ለልጃችን ተጨማሪ የአንገት መሃረብ መግዛት እፈልጋለሁ» ብላ ጠየቀችው።

ካሌብም መለሰና «ለምንድን ነው በሚገባ የተቀናጀ ሥራ የማትሠሪው? አስቀድሞ ማቀድ መቼ ትማሪ ይሆን?» በማለት ወረፋት።

ካሌብ ይህን የተናገረው በዘመዶቹ ፊት ነው...። ይህም ከየትም በታ ይልቅ ራሔል መልካም ነገር እንዲነገርላት የምትፈልግበት ስፍራ ማለት ነበር።

በዘመዶቹ ፊት ስለ እርሷ መልካም ነገር ተናግሮ ቢሆን ኖሮ ራሔል ምን ያህል እንደተወደደች ይሰማት እንደነበር አስቡ!

አንድ ባል ስለ ሚስቱ በግልም ሆነ በሕዝብ ፊት መልካም ነገሮችን ለመናገር አጋጣሚዎችን መፈለግ ይገባዋል። ሚስትም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ባሏ መናገር መቻል አለባት።

አንድን ሰው ላደንቀው በፍጹም ሳልፈልግ ማድነቅ ግብዝነት አይሆንምን? አድናቆት እንዲሁ የሚመጣ ተፈጥሮአዊ ነገር አይደለምን? መልሱ አይደለም ነው። አድናቆት እንዲሁ በተፈጥሮ የሚመጣ አይደለም። የእኛ የሰው ልጆች ተፈጥሮ ራስ ወዳድነት ነው። ስግብግቡ ተፈጥሮዬ አድናቆት ማግኘት እንዳለብኝ መንገሩ ተፈጥሮዊ ቢሆንም አድናቆትን ለሌሎች እንድሰጥ ግን አይነግረኝም።

አድናቆትን መስጠት የማፍቀር አንዱ መንገድ ነው። ማፍቀር ደግሞ ቀላል አይደለም። ለማፍቀር መትጋት እንጂ ዘና ማለት አያዋጣም።

**እንዴት እንደምንጀምር።**

ዛሬ የትዳር ጓደኛህን ማድነቅ ልትጀምር ትችላለህን፥ እራስህን ሁለት ጥያቄዎችን ብቻ ጠይቅ።

ሀ. ስለትዳር ጓደኛዬ በእውነት ደስተኛ የምሆንበት ምን ጉዳይ አለ?

ለ. አድናቆቴን እንዴት ላሳያት እችላለሁ?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሁሉ የተሻለው መንገድ መልሱን ወረቀት ላይ መጻፍ ነው።

*መጀመሪያ፥* የትዳር ጓደኛህ ጠንካራ ጎኖች ናቸው የምትላቸውን አምስት ነገሮች ጻፍ። (ስለ እርሷ/ እርሱ የማትወደው/የማትወጂው በርካታ ነገሮች ቢኖሩ እንኳ አምስት ጠንካራ ጎኖች መኖራቸው አይቀርም።)

በሁለተኛ ደረጃ፥ እነዚህን ጠንካራ ጎኖች የምታደንቅበትን አንድ መንገድ ጻፍ።

ከታች የተሰጠውን ምሳሌ ተመልከት።

አሁኑኑ ይህን መጽሐፍ አጥፈህ አስቀምጠህ በምሳሌው እንደተሰጠው ዓይነት *ለትዳር ጓደኛህ* ጻፍ።

አሁኑኑ አድርገው። በዚህ ደስተኛ እንደምትሆን እናረጋግጥልሃለን።

## ይሻሻላል/ትሻሻላለች።

የትዳር ጓደኛህን/ሽን አድናቆትን በማሳየት ካፈቀርክ/ሽ ደካማ ጎኖች *ይሻሻላሉ!*

የትዳር ጓደኛን ደካማ ጎን ለማሻሻል ነቀፋና ትችት ፈጽሞ አይረዳም። በእርግጥ የሚረዳው አድናቆት ነው።

ለምሳሌ፥ ባለቤትሽ ለልጆቹ የሚያደርገው እንክብካቤ በጣም እንደሚያስደስትሽ በመግለጽ ብታደንቂው ለልጆቹ የሚያደርገው እንክብካቤ ይጨምራል።

| ስለ ትዳር ጓደኛዬ የምወዳቸው ነገሮች | አድናቆቴን እንዴት እንደምገልጥ |
|---|---|
| 1. ለልጆቻችን ግሩም እንክብካቤ ታደርጋለች። | 1. እርሷ እየሰማች ልጆቹን እንዲህ ልላቸው እችላለሁ። ልጆች «በጣም የምትወዳችሁ እናት ስላለቻችሁ እድለኞች ናችሁ»። |

| | |
|---|---|
| 2. ለእንግዶቻችን የሚያረካ አቀባበል ታደርጋለች። | «እንግዶቻችን ቤታችን እንደ ቤታቸው እንዲሰማቸው የምታደርጊበትን አቀባበልሽን አደንቃለሁ» ልላት እችላለሁ። |
| 3. ለወላጆቼ ደግ ናት። | 3. ለእነርሱ አንድ ነገር ባደረገች ቁጥር ተጨማሪ አድናቆት ልገልጥ እችላለሁ። |
| 4. በእሑድ ት/ቤት በማስተማር በታማኝነት ታገለግላለች። | 4. እግዚአብሔርን ለማገልገል በቂ ጊዜ በመስጠቷ ደስተኛ እንደሆንኩ ልነግራት እችላለሁ። |
| 5. ተጫዋችና ተግባቢ ስለሆነች ሰዎች ይወዷታል። | 5. የአክስቴ ልጅ እንደዚህ ዓይነት ተግባቢ ሚስት ስላለህ ዕድለኛ ነህ አለችኝ ብዬ ልነግራት እችላለሁ። |

በቅርብ ጊዜ ስድስት መቶ አስተማሪዎች የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራቸው ተግተው ይሠሩ ዘንድ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተጠይቀው ነበር። የብዙዎቹ መልስ ለጥረቶቻችን አድናቆት መስጠት ይገባቸዋል የሚል ነበር።

አዎን አድናቆት መምህራን ጥረታቸውን እንዲያሻሽሉ ይረዳቸዋል፥ ለትዳር ጓደኛም ይህ መንገድ በሚገባ የሚሠራ ነው? እስቲ ሞክሩት። ዛሬውኑ አድናቆታችሁን ከሌላ ጊዜ በበለጠ መግለጥ ጀምሩና ምን እንደሚሆን ተመልከቱ!

## 2. የደግነት ተግባራትን ፈጽሙ።

ፍቅርን በተግባር የመግለጥ ሁለተኛው መንገድ የደግነትን ተግባራት መፈጸም ነው። በትዳር ሕይወታችሁ መጀመሪያ አካባቢ በርካታ የደግነት ተግባራት ለመፈጸም ጥንቁቅ የነበራችሁ ይሆናል።

ያንን አሁን አቁማችኋልን?

ዛሬም ቢሆን ለትዳር ጓደኞቻችሁ ልትፈጽሙ ከምትችሉት የደግነት ተግባራት የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

**ባሎች ሆይ**

* ለሚስቶቻችሁ «እወድሻለሁ» ማለትን አትዘንጉ። ይህን ስታደርጉ ግልጥ የሆነ ምክንያታችሁንም ተናገሩ። ለሚስቶቻችሁ ደስ የምትሰኙበትን ነገር ስትናገሩ የሚስቶቻችሁ ፊት ይፈካል።

* ከሚስቶቻችሁ ጋር በእግር ጉዞ በማድረግ ተንሸራሸሩ። እንደዚህ ዓይነት ድርጊት አብራችሁ የምታጠፉት ጊዜ ደስ እንደሚያሰኛችሁ ለሚስቶቻችሁ ማረጋገጫ ይሆንላቸዋል።

* ስጦታ ስጧቸው። ስጦታ በምትሰጡበት ወቅት ምክንያታችሁ «ስለምትወዷቸው» ብቻ መሆኑን ንገሯቸው። ስጦታውን ያመጣችሁት በዚያን ቀን ምሽት በመኝታችሁ የተለየ ቸሮታ በማድረግ እንዲከፍሏችሁ አስባችሁ እንዳይደለ ግለጹላቸው።

* በምትቆጡበት ጊዜ እንዴት እንደምትናገሩ ተጠንቀቁ።

* በቤት ውስጥ ሥራ ዕርዷቸው። እንዴት እንደምትጠነቀቁላቸው ልጆቻችሁ ሲያዩ ያከብሩአችኋል፥ ደግሞም ቤቱ በፍቅር እንደተሞላ ስለሚሰማቸው የዋስትና ስሜት ይኖራቸዋል።

* ለወላጆቻ ልጃቸውን እንዴት እንደምታደንቋት ንገሯቸው።

* አብራችሁ ቁጭ ብላችሁ ለመጫወትና ለመነጋገር ጊዜ ውሰዱ። አሳባችሁንና ስሜታችሁን ትወቁ።

* በየዕለቱ በሁለት መንገዶች ጸሎት አድርጉ፡-

ሀ) ከልጆቻችሁ ጋር፥

ለ) ከሚስቶቻችሁ ጋር ብቻ።

## ሚስቶች ሆይ

* ባሎቻችሁ ከሥራ በሚመጡበት ወቅት በፈገግታና በመልካም ንግግር ተቀበሏቸው። በጠቆረ ፊት አትቀበሏቸው። ባሎቻችሁን ማየት ደስ እንደሚያሰኛችሁ ይወቁ።

* መልካም ነገር ሲያደርጉላችሁ አመስግኑአቸው! ተወዳጅ የሆነ አንድ ቃል ቢኖር «አመሰግናለሁ» ነው።

* ለልጆቻችሁ አባታቸውን እንዴት እንደምታደንቁ ንገሯቸው። አንድ ባል ከሥራ እጅግ ደክሞ ወደ ቤቱ ሲመጣ ትንሽ ሴት ልጁ እንዲህ አለችው «አባዬ፥ ለእኛ መልካም እንክብካቤ ለማድረግ በጣም እንደምትሠራ እማዬ ነገረችኝ።» በዚህ አነጋገር እርሱም ወዲያውኑ ድካሙን ረሳው!

* የሚወዱትን ዓይነት ልብስ ልበሱ። የለበሳችሁት ልብስ ምርጫችሁ የሆነው ባሎቻችሁ ስለሚወዱት እንደሆነ ንገሩአቸው።

* ጠንካራ ጎናቸውን በመፈለግ እነዚያን ደጋግማችሁ ግለጹላቸው።

* ሌሎች ሰዎች ስለ ባሎቻችሁ መልካም ነገር ሲናገሩ ከሰማችሁ ንገሩአቸው። ይቃበያሉ ብላችሁ አትፍሩ።

ከእነዚህ አሳቦች አንዳንዶቹን አትወዱቸው ይሆናል። የ ምንም አይደለም። ከባሕላችሁና ከስብዕናችሁ ጋር የሚጣጣሙትን... የራሳችሁንም አስቡ።

በእያንዳንዱ ቀን ለትዳር ጓደኛሽ አንድ መልካም ነገር ለማድረግ ዐቅጂ። ይህ ጥረትን የሚጠይቅ ነው። የሚደረጉ ነገሮችን ለማሰብና ለማድረግ ጥረት ይጠይቃል። አዎን ሰውን ማፍቀር ከባድ ሥራ ነው። ነገር ግን አስደናቂ ደስታን ወደ ቤታችሁ ይዞ ያመጣል!

3) የትዳር ጓደኞቻችሁን ተቀበሉ

የማፍቀር ሦስተኛው ተግባራዊ መንገድ የትዳር ጓደኛን ከነደካማ ጎኑ መቀበል ነው።

በእርግጥ ልንቀበላቸው የማንችላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፥ የትዳር ጓደኛችሁ ብታመነዝር ወይም ቢያመነዝር ያንን መቀበል አይቻልም። እንዲያውም ለዚህ አስነዋሪ ተግባር እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። (ገጽ 72–80 ተመልከቱ)

በትዳር ሕይወት ውስጥ ልንቀባበል የምንችላቸውና ግዴታም የሚሆኑ በርካታ ነገሮች አሉ። ቀጥሎ አንድ ምሳሌ ተሰጥቷል።

*ውድ ብሩስና ካሮል፥*

*ባለቤቴ በጣም ያበሳጨኛል! በየቀኑ ጋዜጣ ካነበበ በኋላ ወለሉ ላይ ይጥለዋል። እኔ እስካላነሣሁት ድረስ ጋዜጣው ወለል ላይ ይቆያል። ምን ባደርግ ይሻለኛል?*

ውድ ፍሎረንስ፥

መጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል» ይላል (1ኛ ጴጥ. 4፡8)፥ በሌላ አባባል ፍቅር ብዙ ድካም ይሸፍናል።

ፍሎረንስ፥ ስለዚህ ባለቤትሽን ደካማ ጎኑን በመሸፈን ተቀበዪው። ጋዜጣውን ከመሬት በማያነሣበት ወቅት እንኳ ለእርሱ ደግና ፈገግተኛ ሁኚለት።

እንዲያሻሽልም ልታበረታቺው ትችያለሽ። በጥሩ አነጋገር ለምን ጋዜጣውን እንደማያነሣ ጠይቂው። በሚያነሣበት ጊዜ ደግሞ አድናቆትሽን ግለጪለት። ባያነሣውም እንኳ ከደካማ ጎኑ ጋር በመቀበል ውደጂው። ምናልባትም እርሱ ሊቀበለው የሚገባ ደካማ ነጥብ አንቺም ሳይኖርሽ አይቀርምና።

አንቺና ባለቤትሽ እንዳችሁ ለሌላችሁ ደግ ሆናችሁ ደካማ ጎናችሁን ልትሸፋፈኑ ከወሰናችሁ ቤታችሁ ሰላም የሞላበት ይሆናል።

ፍሎረንስ፥ ከዚህ ቀደም ጋዜጣውን ማንሣት በነበረብሽ ሰዓት ሁሉ በቁጣ ትነጂ ነበር። «ይህን ደካማ ጎኑን መቀበል አለብኝ። ክርስቶስ ባሌን እንደሚወደው እኔም ልወደው ይገባል። ይህን ጋዜጣ የማንሣት ጉዳይ ከባድ አይደለም። በደስታ አደርገዋለሁ።» ብትዪ በቤታችሁ ያለው ሁኔታ እንዴት የተሻሻለ እንደሚሆን አስቢ (ቆላ. 3:13ን ተመልከቺ)።

## ፍቅርን ባትቀበሉም እንኳ ስጡ

ብዙ ሰዎች «አድናቆትን የምገልጽበት፥ የደግነትን ተግባር የማሳይበትና ደካማ ጎንን የምቀበልበት ምክንያት ምንድን ነው? የትዳር ጓደኛዬ ከእነዚህ አንዱንም ለእኔ አያደርግም/አታደርግም፤ ታዲያ እኔ ለእርሱ/ለእርሷ ይህን ለምን አደርጋለሁ?» ይላሉ።

ሆኖም ግን ክርስቶስ ከትዳር ጓደኞቻችን የተቀበልነው ፍቅር ጥቂት ቢሆንም ወይም ምንም ፍቅር ባንቀበልም እንኳ እንድንወዳቸው አዝዞናል።

«እኔ ግን እላችኋለሁ....

ጠላቶቻችሁን ውደዱ...

የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ?»

(ማቴ. 5:44-46)

ይህን ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው። ፍቅርን በማንቀበልበት ሰዓት እንኳ ፍቅርን በመስጠት እንድንቀጥል ኃይልን የሚሰጠን ክርስቶስ ብቻ ነው።

«ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።» (ፊልጵ.4:13)

ምዕራፍ 4

# መግባባት አቃታን

ውድ ብሩስና ካሮል፥

ባለቤቴ እንዲያነጋግረኝ ምኞቴ ከፍተኛ ነው። በየዕለቱ ከሥራ መልስ የቀን ውሎዬ እንዴት እንደነበር ልነግረውና የእርሱም ውሎ እንዴት እንደነበር እንዲነግረኝ በጣም እፈልጋለሁ። ነገር ግን አንዳችም ነገር አይጠይቀኝም፥ ስለምሠራው ሥራም ሆነ ስለሚሰማኝ ስሜት ደንታ የለውም። ውሎው እንዴት እንደነበር ስጠይቀው በታቻለ መጠን በጣም አጭር መልስ ይሰጠኛል። ባለፈው ሳምንት ከአምስት ቀን የሥራ ጉዞ ሲመለስ ያሳለፈው ጊዜ እንዴት እንደነበር ስጠይቀው፥ «አይከፋም» የሚል መልስ ሰጠኝ። ማመን ትችላላችሁ? ከአምስት ቀን በኋላ ያገኘሁት አንድ ቃል ብቻ ነው።

ብዙውን ጊዜ አብረን አናሳልፍም። ቅዳሜ ጠዋት ከጓደኞቹ ጋር ቴኒስ ይጫወታል፥ እሑድ ዕለት አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናሳልፈው በቤተ ክርስቲያን ነው። አብረን በምንሆንባቸው ምሽት ከመጫወትና ከመነጋገር ይልቅ «ሻይ አምጪልኝ» ወይም «ያንን ልጅ ዝም አሰኘው» በማለት ይነግረኛል።

ፈጽሞ የማንነጋገርባቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው። የገንዘብ ጉዳይ ስለሚያስቆጣው እንሥቼበት አላውቅም። ስለ ፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ጉዳይ ምንም ለማለት እፈራለሁ። እውነቱ ግን ከእርሱ ጋር የምፈጽመው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ምንም አያስደስተኝም። ለምን? ቢባል እንደማይወደኝ ስለሚሰማኝ ነው። ለሰው የሚገባውን ያህል እንክብካቤ አያደርግልኝም። ነገር ግን እራሱን ለማርካት ሰውነቴን መጠቀም ያስደስተዋል።

ጥሩ ሚስት ለመሆን እየሞከርኩ ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በጠየቀኝ ጊዜ ሁሉ የፈቀደውን አደርጋለሁ። ሁልጊዜ በሁለት ደቂቃ ውስጥ ያጠናቅቅና ወዲያውኑ ይተኛል። በዚያን ጊዜ ጮኽ ማልቀስ ነው የሚቃጣኝ፥ ምክንያቱም ባለቤቴ እኔን በውስጡ ስብዕና የሌለው አካል አድርጎ ስለሚያስብ።

ስለዚህ ብዙ ጊዜ እራሴን እንዲህ በማለት እጠይቃለሁ። «ባለቤቴ ከእኔ ጋር መነጋገር የማያስደስተው ለምንድን ነው? አስተሳሰቡንና ስሜቱን ከእኔ ለምን ይደብቃል? ስለ አስተሳሰቤና ስሜቴስ ጠይቆኝ የማያውቀው ለምንድን ነው? ስለ እኔ ይገደዋልን? ከእርሱ ብለይ የተሻለ ሕይወት አልኖርምን? ብሩስና ካሮል፥ ብለየው ትልቅ ስሕተት መሥራት ይሆንብኛል ብላችሁ ታስባላችሁ?

የእናንተው ታማኝ፥

ሳሊ

የሳሊ የጋብቻ ሕይወት ቀዝቃዛና ብቸኝነት የሞላበት ነው። ምክንያቱም በእርሷና በባለቤቷ መካከል ያለው መግባባት በጣም አነስተኛ ነው። መግባባት ማለት በነፃነትና በታማኝነት እርስ በርስ መነጋገር ማለት ነው። ሁለት ሰዎች

መግባባት አላቸው ስንል ስለ ችግሮቻቸው፥ ደስታቸው፥ ሃዘናቸው፥ ስሜቶቻቸውና አሳቦቻቸው በግልጽ ይነጋገራሉ ማለት ነው። ባልና ሚስት የማይግባቡ ከሆነ ትዳራቸው የሁለት ብቸኛ ሰዎች በአንድ ቤት በደባልነት የመኖር ያህል ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸውም ባል እራሱን አርክቶ ልጆችን የሚያፈራበት መንገድ ብቻ ይሆናል።

በነፃነት እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩ ባልና ሚስት ምንኛ ደስተኛ ናቸው! ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባል ለሚስቱ እንዲህ ይላታል፡-

«ቃልሽ መልካም ፊትሽም ያማረ ነውና

መልክሽን አሳዩኝ፥

ድምፅሽንም አሰሚኝ።»

(መኃ. 2፡14)

ዛሬ በምድር ላይ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት ሰው ሠራሽ ባሕል እንዲህ ይለናል። «እውነተኛ ወንድ ከሚስቱ ጋር ንግግር ያበዛልን?»

ሆኖም ግን በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ (በወንድም ሆነ በሴት) የመግባባት/የመነጋገር ጥብቅ ፍላጎት አለ። ሁላችንም በነፃነት የምናጫውተውና፥ እንዴት እንደሚሰማን የሚያውቅልን የቅርብ ወዳጅ እንፈልጋለን፤ ሌላው ሰው እንዴት እንደሚሰማውም ማወቅ እንፈልጋለን። በሌላ አባባል መነጋገር እንፈልጋለን።

ይህ ፍላጎት ከእግዚአብሔር የሚመጣ ነው።

እግዚአብሔር የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ሰጥቶናል። ከምዕራፍ 6-8 ስለ ፍትወተ ሥጋ እንነጋገራለን። በዚህ ምዕራፍ ግን እኩል አስፈላጊ በሆነ ርእስ ላይ እንነጋገራለን። ይህም መግባባትን ከማድረግ አንጻር ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ፍላጎት እንዴት እንደሚያሟላ ነው።

ባልና ሚስት የአሳብ ግንኙነት ለማድረግ አንዱ የሌላውን ፍላጎት የማያሟላ ከሆነ በጋብቻቸው ውስጥ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸው ቀዝቃዛና የማያስደስት ይሆናል።

## የመግባባት ደረጃዎች

ምናልባት አሁን ጋብቻችሁ በጣም አነስተኛ መግባባት የሚደረግበት ቢሆን አትጨነቁ፥ ምክንያቱም ሊሻሻል ይችላልና።




## የመግባባት ደረጃዎች

ሦስት የመግባባት ደረጃዎች አሉ። የሁሉም ባለትዳር ዓላማ 3ኛው ደረጃ ላይ መድረስ መሆን አለበት። የትዳር ጓደኞች ከ1ኛው ደረጃ ጀምረው በእግዚአብሔር እርዳታ ወደ 2ኛው ደረጃና 3ኛው ደረጃ ያልፋሉ።

3ኛው ደረጃ ላይ የደረሱ ባለትዳሮች እጅግ የተቀራረቡና የሚዋደዱ ጓደኞች የሚኖራቸውን አስደናቂ ደስታ ይለማመዳሉ።

ሦስቱንም ደረጃዎች እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ እንመልከት።

1ኛ ደረጃ – ስለተፈጸሙ ነገሮች መነጋገር፡– ቀላሉ የመግባቢያ ዓይነት በየዕለቱ በተፈጸሙ ድርጊቶች ላይ መነጋገር ነው። ለምሳሌ፥ አንድ ባል ከሥራ ወደ ቤቱ ሲመለስ በዚያ ቀን አለቃው ጠጥቶ እንደመጣ ለሚስቱ ሊነግራት ይችላል። እርሷ ደግሞ ቆንጆ አድርጋ ስለጋገረችው ድፎ ዳቦ ልትነግረው ትችላለች። ወይም ስትጋግረው ቢበላሽባትም እንኳ ልትነግረው ትችላለች።

የሚያሳዝነው ነገር ብዙ የትዳር ጓደኞች በዚህ በቀላሉ ደረጃ እንኳ መግባባት አያደርጉም። በቀኑ መገባደጃ በቤታቸው ሲገናኙ ጥቂት ነገር ብቻ ይነጋገራሉ፥ ወይም ተለጉመው ያመሻሉ።

አንተና/ቺና የትዳር ጓደኛህ/ሽ እንዲህ ዓይነት ችግር ካለባችሁ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ በመጠየቅ ዛሬውኑ መነጋገር ጀምሩ! በየዕለቱ አንዳችሁ ለሌላችሁ በዚያን ቀን ስለሆነው ነገር ተነጋገሩ። በመጀመሪያ ይህ

እንደ ከባድ ሥራ ሊመስል ይችላል፥ ከጥቂት ሳምንት በኋላ ግን ልማድ ይሆንና ደስ ትሰኙበታላችሁ።

የራሳችሁ የቀን ውሎ ምን እንደሚመስል መናገር ብቻ ሳይሆን የትዳር ጓደኞችሁ የእርሱን/የእርሷን ደግሞ እንዲነግራችሁ ጠይቁ። መጠያየቅ አስፈላጊ ነገር ነው። ባል ወደ ቤቱ በሚመጣበት ጊዜ እንዴት እንደዋለ ሚስቱ የማትጠይቅ ከሆነ ግድ የሌላት ያስመስላታል። ባልም ሚስቱን ስለ ውሎዋ የማይጠይቃት ከሆነ እንደማይወዳት ማሰብ ትጀምራለች።

ሰዎች ስለ እኛ ግድ እንደሚላቸው የሚያመለክቱንን ቅን ጥያቄዎች ሲጠይቁን በጣም ደስ ይለናል። ማንኛውም ሰው ስለ ሥራዬ ወይም ስለ አሳቦቼ ሲጠይቀኝ ይህ ምንኛ ተግባቢ ሰው ነው ብዬ አስባለሁ።

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን እንደሚገደን የሚያሳዩ ጥያቄዎችን መጠያየቅ አለብን።

በዕለቱ ስለተፈጸሙ ነገሮች ጥያቄዎች መጠያየቅና ምልልስ ማድረግ የመግባቢያ ጥሩ ጅምር ነው፥ ነገር ግን እዚያ ላይ መቆም የለበትም። በእግዚአብሔር ዕርዳታ ወደሚቀጥለው ደረጃ ማለፍ እንችላለን።

2ኛ ደረጃ፤ በጋራ ጉዳይ ላይ መነጋገር፡— ይኸውም ስለ ገንዘባችን፥ ስለ ልጆቻችን፥ ስለ ዘመዶቻችንና ወደፊት ስላለን ዕቅድ። ለምሳሌ፥ ባል ከሚስቱ ጋር የሚከተሉትን በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ መነጋገር አለበት። ልጆቻችን የት ቢማሩ ይሻላል? የአክስቴ ልጅ ከእኛ ጋር እንዲኖር እንጠይቀው? አዲስ መኪና መግዛት አለብን ወይ?

በጋራ ጉዳዮቻችን ላይ ስለምንወስዳቸው ውሳኔዎች ስንነጋገር ላንስማማ እንችላለን። ያለመስማማታችን ግን መግባባታችንን እንዲያስተጓጉል መፍቀድ የለብንም። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ወደ መስማማት እስክንደርስ ድረስ ውይይታችንን መቀጠል አለብን።

አንድ ቀን አብኔርና ልድያ በእናቱ ጉዳይ ላይ መነጋገር ጀምረው ተጣሉና ውይይታቸውን ለግጭታቸው መፍትሔ ከመስጠታቸው በፊት በማቆም ስሕተት ሠሩ። ከዚያ በኋላ ግጭትን ለማስቀረት «የእናቱን ጉዳይ» ላለማንሣት ሁለቱም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ጀመሩ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በገንዘብ ጉዳይ ተጣሉና ግጭታቸው መፍትሔ ሳይፈለግለት ያንንም ርእስ ማንሣት ተው።

በመጨረሻም የማይነጋገሩባቸው ጉዳዮች ዝርዝር በጣም ብዙ ሆነ። ይህም መግባባታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ችግር ላይ ጣለው።

ግጭት መግባባትን እንዲገድል ከመፍቀድ ይልቅ መግባባትን ግጭቶችን ለማርገብና መፍትሔውን ለማግኘት ልንጠቀምበት ይገባል። ይህንን ማድረግ የምንችለው ውይይቶችን ፍቅር በተሞላበት መንገድ አንዳችን ሌላችንን መረዳት እስክንችል ድረስ እኛ በውሳኔም እስክንስማማ ለመቀጠል ቆራጥ በመሆን ነው።

ግጭቶችን በውይይት ስንፈታ ማንኛውንም ርእስ ለመነጋገር ነፃ እንሆናለን።

ቀጥሎ ወደ ሦስተኛው ደረጃ ለማለፍ ዝግጁዎች እንሆናለን።

3ኛ ደረጃ– ስለ ጋራ ስሜቶቻችሁ መነጋገር፦ እዚህ ደረጃ ላይ ስሜቶቻችንን እንጋራለን፤ የልቦቻችንን በር በመክፈት የትዳር ጓደኞቻችን የውስጣችንን እንዲያዩና እርግጠኛ ማንነታችንን እንዲያውቁ እናደርጋለን።

አስጢፋኖስ ለባለቤቱ እንዲህ በማለት ተናገራት፦ «ዛሬ ወንድሜ ተቆጥቶ ጮኸብኝ፤ አባቴም እርሱን ደገፈው።» እንደ እነዚህ ዓይነቶቹን የተፈጸሙ ድርጊቶችን መነጋገር 1ኛ ደረጃ መግባባት በመባል ይታወቃል።

በመቀጠል አስጢፋኖስ ባለቤቱ ይህ ከዘመዶቹ ጋር ያጋጠመው ችግር እንዴት ሊቃለል እንደሚችል ተነጋገሩ። ይህ 2ኛ ደረጃ መግባባት ነው። ምክንያቱም እኛና ዘመዶቻችን በማለት የሚነጋገሩበት የጋራ ጉዳይ ነው።

ከዚያ በኋላ ባለቤቱ «ስለ ወንድምህና ስለ አባትህ አሁን የሚሰማህ ስሜት ምንድን ነው?» በማለት ጠየቀችው።

አስጢፋኖስም ሲመልስ «የቤተሰቦቼ መልካም ግንኙነት እንዳይበላሽ ስለምፈራ እየተጨነቅሁ ነው» አላት።

እንደዚህ ዓይነቱ ስሜትን መጋራት ጉዳይ ሦስተኛው ደረጃ መግባባት ነው።

በሦስተኛ ደረጃ መግባባት ላይ ስንደርስ የጋብቻ ሕይወት ግሩም ይሆናል። በአንዳችን ላይ የሆነው አስደሳች ነገር የጋራችን ደስታ ነውና በዚያ ደረጃ መግባባት ስናደርግ ደስታችን እጥፍ ይሆናል። ሸክሙን ስለምንከፋፈል ችግሮቻችን በግማሽ ይቀንሳሉ።

## ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለም

አሮን እራሱን ክርስቲያን ብሎ የሚጠራና ከባለቤቱ ጋር ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ሰው ነው። ነገር ግን ችግር ሲያጋጥመው ለራሱ እንዲህ ይላል። «ዛሬ እንዴት ዓይነት ተስፋ አስቆራጭ ነገር እንደገጠመኝ ለባለቤቴ አልነግራትም። ምክንያቱም ወንድ ነኝ፤ ችግሬን ለማቃለል የማልችል ደካማ ሰው አድርጋ ልትቆጥረኝ አይገባም።»

አሮን የሚከተለውን ጥቅስ ትርጉም አልተረዳም።

«ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን

ረዳት እንፍጠርለት።» (ዘፍጥ. 2፡18)

ማንኛውም ሰው ስለ ስሜቶቹ ከባለቤቱ ጋር ለመነጋገር ማፈር የለበትም። አትንቀውም። እንዲያውም የበለጠ ትወደዋለች።

ስሜቶቻችንን እርስ በርስ ስንከፋፈል በከፍተኛ ደረጃ እንግባባለን፥ ትዳራችንም የከበረ ቅርበት ስለሚኖረው የሚያስደስት ይሆናል።

### የመግባባት ዕንቅፋቶች

በምድር ላይ በሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ብዙ ባለትዳሮች በ3ኛው ደረጃ መግባባት ለማድረግ ያለመቻላቸው አሳዛኝ እውነታ ነው። አንዳንዶች 1ኛ ደረጃ መግባባትን እንኳ አያደርጉም። ለምን? ምክንያቱም የመግባባት ዕንቅፋት የሆኑ ነገሮች አሉ። አንዳንድ ባለትዳሮች እነዚህ ዕንቅፋቶች ከመግባባት እንዲገቷቸው ይፈቅዳሉ።

እያንዳንዱን የመግባባት ዕንቅፋት በአጭሩ እንመልከት።

## ፍርሃት

አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸው እንዲፈሩአቸው ያደርጋሉ። ይህ የሚያሳዝን ነገር ነው። ፍርሃት ጥልቅ መግባባትን ያጠፋል። ሚስት ባሏን አለ አግባብ የምትፈራ ከሆነ ተገቢ መግባባት ማድረግ አይችሉም።

መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ባሏን ታክብር እንጂ አለ አግባብ ትፍራ አይልም።

«ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ።»

(ቆላ. 3:18)

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም።» (1ኛ ዮሐ. 4:18)

## ያለማዳመጥ

የመግባባት ሌላው ችግር ያለመደማመጥ ነው። ካልተደማመጥን (በእርግጥ ካልተደማመጥን) ማለት ነው መግባባት ሊኖር አይችልም።

አንዳንድ ጊዜ የትዳር ጓደኛዬ ስትናገር እኔ ቀጥዬ የምናገረውን ነገር አስባለሁ። የምትናገረውን እስክትጨርስ እታገሥና ወደ ራሴ ትልቅ አሳብ ዘልዬ እገባለሁ። እየጠበቅኋት ሳለሁ ግን አላዳምጣትም!

ወይም አንዳንድ ጊዜ እርሷ ስትናገር ከዝርዝር ጉዳዮች በአናሳው ስሕተት እንደሠራች እያለሁ። እየተናገረች እያለች እርሷን ለማረም የምጠቀማቸውን ቃላት በማቀድ እጠመዳለሁ። ይህን ሳደርግ ማዳመጡ ያመልጠኛል።

የትዳር ጓደኛዬ በምትናገርበት ጊዜ በምትናገረው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ አለብኝ። ምን ማለቷ እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆንኩ «እንዲህ ነው ያልሽው? ወይም እንደዚህ ማለትሽ ነውን?» በማለት መጠየቅ ይገባኛል።

ማዳመጥ ሥራ ነው። ስለዚህ የማዳመጥን ተግባር ተግተን መፈጸም አለብን።

> በጥንቃቄ ማዳመጥ ካልቻልን የትዳር ጓደኛችንን ከመግባባት እንድትታቀብ እናደርጋታለን።

## የሥራ ብዛት

ኤርነስት «እኔና ባለቤቴ በሥራና በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ተጠምደናል። አብረን የምንሆንበት ጊዜ እጅግ አነስተኛ ነው። ስለዚህ እንዴት መግባባት እንችላለን?» አለ።

ምክራችን፡- አንዳንድ ሥራዎቻችሁን በመቀነስ አብራችሁ የምታሳልፉትን ጊዜ አሳድጉ። ትዳራችሁ እጅግ አስፈላጊና ዋናው ነገር ነው። ባልና ሚስት ለመግባባት/ለመነጋገር እስኪቸገሩ ድረስ በሥራ ከተጠመዱ እግዚአብሔር ከሚፈልጋቸው በላይ በሥራ ተጠምደዋል ማለት ነው።

## የአባትነት እና የእናትነት ሚና

ዶናልድና ኖርማ በትዳር ሕይወታቸው መጀመሪያ አካባቢ በጣም ጥሩ መግባባት ነበራቸው። እያንዳንዳቸው «ስለማንኛውም ነገር በፍጹም ነፃነት ማነጋገር የምችለውን የትዳር ጓደኛ ማግኘት እንዴት አስደሳች ነው! ዕድለኛ ነኝ» የሚል ስሜት ነበራቸው።

ልጆች ከተወለዱ በኋላ ግን ኖርማ ለልጆቹ እንክብካቤ በማድረግ ስትወጠር ዶናልድ ደግሞ ለእነርሱ እንክብካቤ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት በሥራ ተጠመደ። ለልጆች ጉዳይ ከሚገባው በላይ አትኩሮት በመስጠታቸው እርስ በርሳቸው የሚያደርጉትን መግባባት ቸል አሉ። ጓደኝነታቸው መቀዝቀዝ ጀመረ። በዚህ ደረጃ የትዳር ሕይወታቸው በአንድ ቤት ውስጥ አብረው እየኖሩ ልጆችን ከማሳደግ ፈቀቅ የማይል ሆነ።

እንደዚህ ዓይነት ትዳር ሁለቱም የትዳር ጓደኛሞች ክርስቲያን በሆኑባቸው ቤቶች እንኳ የተለመደ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ እንዳልሆነ ግን እርግጥ ነው። አንድ ባል ከሚስቱ ጋር መነጋገር እስኪያቅተው ድረስ ገንዘብ ለማግኘት በሥራ መጠመድ የለበትም። ሚስትም ከባለቤቷ ጋር ያላትን ግንኙነት ቸል እስክትል ድረስ በእናትነት ሥራ መጠመድ የለባትም።

| ልጆች በፍቅር እርስ በርስ የሚግባቡ ወላጆች ያስፈልጓቸዋል። |
|---|

## በደል

ከሁሉ የከፋ የመግባባት ዕንቅፋት በደል ነው። ለትዳር ጓደኛሞች እርስ በርስ መበዳደል በጣም ቀላል ነው።

ሩት በአውቶቡስ መቆሚያ አጠገብ ሆና አውቶቡስ ስትጠብቅ አዊን ጠዋት ተናግሮ ያስቀየማት ነገር ትዝ አላት። ነገሩ ትንሽ በደል ብቻ ነበር። ያስቀየማት ቃሎቹ ሳይሆኑ የንግግሩ ቃና ነበር። ስለ ጉዳዩ ባሰበች መጠን ቅያሜዋ አደገ። የሌላ ጊዜ ቅያሜዋን ሁሉ አስታወሰች።

ከሥራ ወደ ቤቷ ስትመለስ ሩት «ስለዚህ ጉዳት ምን ማድረግ አለብኝ?» በማለት እራሷን መጠየቅ ጀመረች። መርሳት ልሞክርን? በፍጹም ይህን ካደረግሁ ከአዊን ጋር በዚህ ምሽት የሚኖረን ንግግር በግማሽ ልብ ይሆናል። በውስጤ ቅያሜው ሳይወገድ ይቀጥላል። ወይም ምናልባት ይቅርታ እስኪለኝ መጠበቅ ይገባኛል። ይህም አይሆንም፤ ምክንያቱም እንደጎዳኝ አይገባው ይሆናል። መልሱ አንድ ብቻ ነው። ስለ ጉዳዩ ከእርሱ ጋር መነጋገር አለብኝ። ምን እንደተሰማኝ ልነግረው ይገባል። እውነቱን በጥሩ መንፈስ መንገር አለብኝ።

በዚያ ምሽት እርሷና አዊን ብቻቸውን ለመሆን ዕድል እንዳገኙ ሩት በፈገግታ እንዲህ አለችው፦ «ውዴ፥ በዛሬ ጠዋት አነጋገርህ እንዳሳዘንከኝ ልነግርህ የሚገባኝ ይመስለኛል። ቀኑን ሙሉ አዝኜ ነው የዋልኩት። አውቀህ እንዳልሆነ ገብቶኛል። ይህ ትንሽ ነገር ቀኑን ሙሉ አእምሮዬን ይዞ መዋሉ አሳፍሮኛል።»

አዊንና ሩት ይህን ጉዳት ተነጋግረው ሲጨርሱ እንዴት ቅርበት እንደሚሰማቸው አስቡ። ምን ዓይነት ግሩም ምሽት እንዳሳለፉ ማሰብ ይቻላል።

ሩት ጉዳቷን ለመሸፈን ብትሞክር ኖሮ ምን ዓይነት ምሽት (የመኝታ እረፍት ጊዜ) ይኖራቸው ነበር?

ለሳሊ የጻፍነው ደብዳቤ

ይህ ምዕራፍ የጀመረው ከባለቤቷ ጋር መልካም መግባባት እንደሌላት በጻፈችው በሳሊ ደብዳቤ ነበር። የእኛ ምላሽ ከዚህ የሚከተለው ነበር።

ሳሊ፥ የምንመክርሽ ከባለቤትሽ ጋር በግልጽ እንድትነጋገሩ ነው። የተሻለ ግንኙነት እንደምትፈልጊ ይወቀው። በአክብሮት ከዚህ የሚከተለውን የሚመስል ነገር በዪው፦

«ማርቆስ፥ በቅርቡ መግባባታችን ከተሻሻለ የትዳር ሕይወታችን የተሻለ እንደሚሆን እያሰብኩ ነበር። የመጀመሪያው ዓመት የትዳር ሕይወታችንን ታስታውሳለህን፥ ስለ ሁሉ ነገር በመነጋገር እንዴት ደስተኞች እንደነበርን? አሁን ግን አንዳችን ለሌላችን እንግዳ የሆንን አይመስልምን? ጥፋቱ የአንተ ነው አላልኩም። ነገር ግን ጉዳዩን ለማሻሻል አብረን መሥራት እንደሚያስፈልገን አስባለሁ። ስለ አንተ ስለሚገደኝ በመካከላችን ጥሩ መግባባት እንዲኖር እንደምፈልግ እንድታውቅ እሻለሁ።»

ይህን ለማለት ትክክለኛውን *ጊዜና* ትክክለኛውን *ስፍራ* ለመምረጥ ተጠንቀቂ። ይኸውም ባለቤትሽ በራበው ወይም ድካም በተጫጫነው ጊዜ ሳይሆን ዘና ባለበት *ጊዜ* መሆን አለበት። *ቦታው* ጸጥ ያለና ሁለታችሁ ብቻችሁን ሆናችሁ ለመነጋገር በቂ ጊዜ የምታገኙበት መሆን አለበት።

ይህ ንግግር ባለቤትሽን በጣም ጥሩ ተግባቢ ሰው ያደርገዋልን? እንደሚረዳው ተስፋ እናደርጋለን። ነገር ግን አንቺ የምትፈልጊውን ያህል ጥሩ በመነጋገር የሚግባባ ሰው ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር ኃያል ስለሆነ

በጸሎት ይሠራል፥ ነገር ግን ይህ ማለት የትዳር ጓደኛሽ ፍጹም ይሆናል ማለት አይደለም።

ስለዚህ ባልሽ *አንቺ የምትፈልጊውን ያህል ጥሩ በንግግር የሚግባባ* ባይሆንም እንኳ መቀበልና መውደድ እንዳለብሽ አትርሺ (ደግሞም አንቺም ፍጹም እንዳልሆንሽ ባለቤትሽ ከነድካምሽ ተቀብሎ አንቺን የመውደድ ኃላፊነት እንዳለበት አስታውሺ)።

ሳሊ፥ በመጨረሻ የምንሰጥሽ አሳብ ከባለቤትሽ ሌላ አሳብሽን የምታካፍያቸው ጓደኞች ይኑሩሽ የሚል ነው። እያንዳንዱ ሰው ከትዳር ጓደኛው ሌላ ጓደኞች ያስፈልጉታል። የአንቺ ባለቤት ደግሞ ገና በመነጋገር መግባባትን እየተማረ ያለ ሰው ስለሆነ ሌሎች ጓደኞች በጣም ያስፈልጉሻል።

ለምሳሌ፥ ከዘመዶችሽ አንዱ ሞቶ በጣም አዝነሻል እንበል። በእርግጥ የተሰማሽን ጥልቅ ኃዘን ለባለቤትሽ መንገር ይገባሻል። ተረድቶሽ ኀዘንሽን በከፊል ይካፈል ይሆናል። ነገር ግን ፍላጎትሽን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሟላ አትጠብቂ። ከባለቤትሽ ጋር ከተነጋገርሽ በኋላ ወደ አንድ የሴት ጓደኛሽ ሄደሽ የተሰማሽን ስሜት አጫውቺያት። በዚያ መንገድ አሳብሽን የሚካፈልልሽን የማግኘት ፍላጎትሽን በከፊል በባልሽ፥ በከፊል ደግሞ በሴት ጓደኞችሽ ይሟላል። (ልብ በይ ያልንሽ የሴት ጓደኛ ነው። ጥሩ አድማጭ የሆነ የወንድ ጓደኛ ብታገኚ በዝሙት ትፈተኚ ይሆናል።)

ሳሊ፥ በአጭሩ የምንሰጥሽ አሳብ፦

ሀ) ከባለቤትሽ ጋር እውነት የሰፈነበት ንግግር ይኑርሽ።

ለ) ባለቤትሽ በጣም ጥሩ የአሳብ ተካፋይ ባይሆንም እንኳ በፍቅር ተቀበዪው።

ሐ) ባለቤትሽ አሳብሽን የሚካፈልልሽን የማግኘት ፍላጎትሽን ሁሉ እንደሚያሟላ አትጠብቂ። ሌሎች የቅርብ የሴት ጓደኞች ይኑሩሽ።

## ለሁሉም የሚጠቅሙ የመጨረሻ አሳቦች

ይህን መጽሐፍ ለምታነቡ ሁሉ የሚከተለውን እንላለን። ይህን እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ ምዕራፍ ማንበብ ጨርሳችኋል። አሁን *የትዳር ጓደኛችሁ ይህን አብሮ/አብራ እንዲያነብ/እንድታነብ ለምን አትጠይቁም?* አንዳችሁ ለሌላችሁ በየተራ አንብቡ። ደግሞም የሚከተሉትን በመሳሰሉ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርጉ። የአሳብ ልውውጥ ደረጃችን 1ኛ፥ 2ኛ ወይስ 3ኛ ደረጃ ላይ ነው? ወደ ሚቀጥለው ደረጃ እንዴት እንደርሳለን? ንግግራችንን እንዲያቅብ የፈቀድንለት ዕንቅፋት አለን?

ቀጥሎ ከትዳር ጓደኛችሁ ጋር መግባባታችሁን ለማሻሻል ተግታችሁ መሥራት አለባችሁ። ግንኙነታችሁ ከማንም ጋር ካላችሁ ግንኙነት የተሻለ እስኪሆን ድረስ ገንቡት።

እግዚአብሔር እንደሚረዳችሁ እመኑ። በሚቀጥለው ምዕራፍ ካሮልና እኔ በትዳር ሕይወታችን ውስጥ የነበረውን የአሳብ ልውውጥ ችግር ለማቃለል እግዚአብሔር እንዴት እንደሠራ እንነግራችኋለን።

ምዕራፍ 5

# ጥቂት ስለ ራሳችን ትዳር

ብሩስ፡- ካሮልን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁበት ሁኔታ ፈጽሞ አይረሳኝም። ባለ ሰማያዊ ቀለም ልብስ ለብሳ በጣም ታምር ነበር!

ክርስቶስን የተቀበለችው በአንድ የወጣቶች ካምፕ በተደረገ ፕሮግራም ላይ ነበር። ከዚያም በቤተ ክርስቲያናችን መካፈል ጀመረች። ደጋግሜ ባየኋት ቁጥር የበለጠ እየወደድኋት ሄድሁ። ፍንድቅድቅ ተጫዋች ሕይወት የምላባትና በኢየሱስ በጣም ደስተኛ ነበረች።

ካሮል፡- ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት ስጀምር የወጣቶች ሊቀመንበር የሆነ አንድ ረጅም ወጣት ተመለከትኩ። ስሙ ብሩስ ነበር። ለክርስቶስ የነበረውን ፍቅር አደነቅሁ። ትናንሽ ልጆችንም እንደሚወድ ተመለከትኩ። ለራሴ እንዲህ አልኩ «ይህ ወጣት ጥሩ አባትና ጥሩ ባል ይሆናል....ለታደለችው!»

የቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች በትምህርት ቤቶችና በየቤቶቹ በመመስከር እግዚአብሔርን በሚያገለግሉበት ወቅት እኔና ብሩስ ወዳጅነታችን እየጨመረ አንዳችን በሌላችን እየተሳብን መምጣት ጀመርን።

ትውውቃችን ለሦስት ዓመታት ከዘለቀ በኋላ እንደሚወደኝና ሊያገባኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ። ከፍተኛ የደስታ ስሜት ተሰምቶኝ ለራሴ እንዲህ አልኩ፡- «እንደ ሌሎች ብዙ ትዳሮች የእኛ ፈጽሞ አይቀዘቅዝም፤ እንዋደዳለንና!»

ብሩስ፡- የሚያሳዝነው እያደግሁ በመጣሁ መጠን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ የሚናገረውን አላጠናም ነበር። በዚህ ፈንታ ስለ ትዳር ያሉኝን አሳቦች በሙሉ ያገኘሁት የዘመዶቼንና የጎረቤቶቼን ትዳር በማየት ነበር። ወጣት ወንዶች ሊያገቧት ተስፋ ለሚያደርጓት ሴት ብዙ መልካም ነገሮችን እንደሚያደርጉ፤ ነገር ግን ባሎች ደግሞ ሚስቶቻቸውን ቸል በማለት በጣም የተመናመነ ርኅራኄ እንደሚያሳዩአቸው ተመለከትሁ።

በዚህ ዓይነት «ወንድ ማለት እንደዚያ እንደሆነና ሚስቱንም የሚይዘው በዚህ ሁኔታ እንደሚሆን ታየኝ»።

ካሮል፡- እንደ ማንኛውም ልጃገረድ ጋብቻ እንዴት ደስተኛ እንደሚያደርገኝ የቀን ሕልሜን አልም ነበር። ብዙ ጊዜ ልሰጠው ስለሚገባ ደስታ ሳይሆን ልቀበል ስላለው ደስታ አስብ ነበር።

ብዙ ጊዜ «ጋብቻ 50/50 ነው» (አንካ በአንካ) ሲሉ እሰማ ነበር። ያንንም አምኜ ተቀብዬ ነበር። ደስተኛ የጋብቻ ሕይወት ይኖረኝ ዘንድ ከምቀበለው ይልቅ ለመስጠት መዘጋጀት እንዳለብኝ አልተገነዘብኩም ነበር።

ብሩስ፡- የሠርጋችን ቀን ውድ በሆኑ ነገሮች ባያሸብርቅም ግሩም ቀን ነበር። ከሠርጉ በኋላ የመጀመሪያው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችን እጅግ አስደሳች ነበር።

ሆኖም ግን ወራት በተቆጠሩ መጠን የትዳር ሕይወት ደስታችን እየጠፋ ሄደ። አንዱ ችግር ካሮልን በሕይወቴ ልዩ ሰው አድርጌ መያዜን ወዲያውኑ አቆምኩ። «አሁን አግብቻለሁ ስለዚህ ከእንግዲህ እንደ ወንድ እንጂ እንደ አፍላ አፍቃሪ መታየት የለብኝም» በማለት አሰብኩ።

ካሮል፦ ከሠርጋችን በፊት ብሩስ በተገናኘን ቁጥር ብሩኅ ፈገግታውን ይመግበኝ ነበር። መልካም ነገሮች ለእኔ ማድረግ ይወድ ነበር።

ከሠርጋችን በኋላ ግን ተለወጠ። ከእኔ ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ለዘመዶቹ፥ ለቤተ ክርስቲያን አባላት መልካም ማድረግ ጀመረ። ለእኔ ግን ምንም መልካም ነገር አያደርግልኝም። አንድ ቀን በጣም ተናደድኩና ዘጋሁት።

ብሩስ፦ ካሮል ስትዘጋኝ በጣም ደነገጥሁ። ምን ችግር እንደተፈጠረ ስጠይቃት፥ እንደ ቀድሞው በጥሩ ሁኔታ ስለማትይዘኝ ነው አለችኝ።

አዝናለሁ፥ ይቅርታ አድርጊልኝ አልኳት። በልቤ ግን ምን ማለቷ ነው? ወንድ ሚስቱን እንዴት ይያዝ ብላ ይሆን የምታስበው? አልኩ።

ካሮል፦ ለብሩስ የሚሰማኝን ነገር ሁሉ መንገር ነበረብኝ። «አሁን ተጋብተናል ከዚህ ቀደም በምታደርግልኝ መልካም ተግባርና ወዳጅነት በሞላበት አነጋገር ፍቅርህን መግለጽ እንድትቀጥል እፈልጋለሁ» ልለው ይገባኝ ነበር።

ይህንን ልለው ሲገባኝ ነገር ግን አላልኩትም።

በዚህ ምትክ «እርሱ ለእኔ መልካም እስካልሆነ ድረስ እኔ ለእርሱ ለምን መልካም እሆናለሁ? አልሆንም» የሚል ዝንባሌ አደረብኝ።

ብሩስ፦ ካሮልን ፍቅር በሞላበት ርኅራኄ መንከባከብ እንዳቆምኩ አልታወቀኝም። ለእኔ ጎልቶ የታየኝ አብሯት ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ሰው እየሆነች መምጣትዋ ነበር። ጭራሽ የምትዘጋኝ ቀናት እየበረከቱ መምጣት ጀመሩ። «አነጋግሪኝ ወይም ከዚህ ቤት ውጭ» ልላት ምንም ያህል አልቀረኝም ነበር።

ካሮል፦ ወደ ስዋዚላንድ ተዛውርንና ብሩስ በዚያ የሳይንስ ትምህርት ማስተማር ጀመረ። በዚያ ዓመት ሴት ልጃችን ስትወለድ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ ወንድ ልጅ ተጨመረልን። ያገኘነው የልጆች በረከት ትዳራችንን ያሻሽለዋል ብዬ ባስብም እንኳ ሳያሻሽለው ቀረ።

ብሩስ፦ ከካሮል ጋር የማሳልፈው ጊዜ አስደሳች መሆኑ በየጊዜው እየቀነሰ መጣ። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜዬን በሥራዬና በቤተ ክርስቲያን የኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ማጥፋት ጀመርኩ።

ካሮል፦ በትዳር ሕይወታችን መጀመሪያ አካባቢ ብሩስ ብዙውን ጊዜ ከእኔ ጋር ያሳልፍ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን አዘውትሮ ወደ ሌላ ስፍራ ይሄድ ነበር። እኔም ብቻዬን ከልጆቼ ጋር በቤት አሳልፋለሁ።

በዚህም ከፍተኛ የመጣልና የብቸኝነት ስሜት ይሰማኝ ነበር።

ብሩስ:- በእነዚህ ቀናት «በቤት የምቆይበት ምን ምክንያት አለኝ? በቤት በምሆንበት ወቅት በሆነ ነገር ትበሳጭና ትዘጋኛለች» በማለት ለራሴ እናገር ነበር።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሕይወታችን እየቀነሰ መጣ። እንዲያውም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የምንፈጽመው እጅግ አልፎ አልፎ ሆነ።

ካሮል:- ብሩስ የሚፈልገኝ ለፍትወት ስሜቱ ብቻ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር።

ብሩስ:- እንደ ክርስቲያን ከፈታኋት በእግዚአብሔር ላይ ማመፄ እንደሆነ አውቅ ነበር። ስለዚህ ፍቺ የማይሆን ነገር ነው፥ ልወዳት ይገባኝ ነበር። ነገር ግን እንዴት?

ካሮል:- እጅግ በከፋ ሁኔታ ትዳራችን ለመቀዝቀዙ ከፊል ምክንያቱ እኔ እንደሆንኩ ለረጅም ጊዜ ሊገባኝ አልቻለም ነበር።

ብሩስ:- ከፊል ምክንያቱ እኔው እንደሆንኩ ለማየት አልቻልኩም ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ማስተማርና በተለያዩ ቦታዎች መስበክን ሥራዬ አድርጌ ተያይዤው ነበር። ቤቴ ግን እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነት አልነበረም!

መጋቢያችን «የእግዚአብሔር ቃል ስለ ፍቅር ምን ይላል?» በሚል ርእስ ለስድስት ሳምንት ወጣቶችን የሚያስተምር ሰው እንደሚፈልግ ነገረኝ።

ይህ ትምህርት የራሴን ሕይወት ምን ያህል ሊለውጠው እንደሚችል ሳላውቅ ለማስተማር ተስማማሁ።

መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና ፍቅር በትክክል ምን እንደሆነ ተረዳሁ። *ፍቅር፥ ባለቤቴን በልዩ መንገድ እንድንከባከባት ፍላጎት እንዲኖረኝ የሚያደርግ ስሜት አይደለም። ፍቅር ቢሰማኝም ባይሰማኝም ባለቤቴን በልዩ መንገድ መንከባከብ ነው።*

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባለቤቴን ልወዳት ወሰንኩ። በሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ ልረዳት በጥንቃቄ ማሰብ ጀመርኩ። አእምሮዬ ምን መልካም ነገር አደረገችልኝ ብሎ እንዲያስብ ከመፍቀድ ይልቅ ለእርሷ መልካም ነገር ማድረጉ ላይ አተኮርሁ።

በእኔ ሕይወት የታየው ይህ ለውጥ ካሮልም እንድትለወጥ ረዳት። የበለጠ ፈገግተኛ እየሆነች መጣች። የበለጠ ያኔ ባገባኋት ጊዜ የነበረችው ዓይነት አስደናቂ ሴት ሆነች።

በእርግጥ ለትዳር ሕይወታችን በአብዛኛው መቀዝቀዝ ምክንያት የእኔ ስሕተት መሆኑን እንድገነዘብ ይህ ሁኔታ ዓይኖቼን ከፈተልኝ። ለዚህ ያበቃን ካሮልን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል ከመውደድ ይልቅ የእኔዋ «ሴት» እንደሆነች መቁጠሬ እንደነበር ተረዳሁ (ኤፌ. 5፡25)።

ካሮል:- አንድ ቀን የመጋቢያችን ባለቤት እንዲህ ሲሉ ሰማሁ።

ጋብቻ የእንካ በእንካ ጉዳይ አይደለም።

ይልቁኑም ሁለቱም ወገኖች እያንዳንዳቸው ለመስጠት ፈቃደኞች የሆኑ፥ የሚሰጡና በዚህም ያለማቋረጥ የሚተጉ መሆን አለባቸው። ይህንንም ሲያደርጉ «የምሰጠውን ያህል እየተቀበልኩ ነውን?» ሊሉ ፈጽሞ አይገባም።

በዚያን ቀን ብዙ ጊዜ ብሩስ 50% እንዲሰጠኝ እንደምጠብቅ ከምቀበለው በላይ ልሰጥ ፈቃደኛ እንዳይደለሁ ተገነዘብኩ።

ቀጥሎ «የትዳራችን ችግር የብሩስ ስሕተት ብቻ አይደለም ማለት ነውን?» የሚል አዲስ አሳብ ወደ እኔ መጣ።

ይህ አሳብ ከዚህ በፊት ፈጽሞ ወደ ውስጤ ያለመግባቱ የሚያስደንቅ ነው።

ብሩስ፡- ለካሮል ላስብላትና ደግ ልሆንላት በእውነት ብፈልግም እንኳ ብዙ ጊዜ ላደርገው አልቻልኩም። ሳይሳካልኝ ሲቀር የተለመደውን የቀድሞውን «ኩርፊያ» እንደገና ታመጣብኝ ነበር።

ካሮል፡- በሴቶች ስብሰባ ላይ አንዲት ሴት ባለቤቷን አኩርፋ ለብዙ ቀናት ሳታነጋግረው እንዴት ትኖር እንደነበር ስትናገር ሰማሁ። ከዚህ ድካሟ እንድትወጣ እግዚአብሔር እንዴት እንደረዳት መሰከረች።

በእርሷ በኩል እግዚአብሔር በቀጥታ እንደተናገረኝ አወቅሁ። በዚያ ቀን «ጌታ ሆይ፥ በአንተ ርዳታ እለወጣለሁ። ብሩስ እኔ የምፈልገውን ያህል መልካም በማይሆንልኝ ጊዜ እንኳ ፈገግተኛና ደግ ልሆንለት እጥራለሁ። ፍቅርን ባልቀበል እንኳ እሰጣለሁ። በማዝንበትና በምጎዳበት ጊዜ ከማኩረፍ ይልቅ የሚሰማኝን ስሜቶች በቅንነት እነግረዋለሁ» ብዬ ቃል ገባሁ።

ብሩስ፡- ካሮል ሳታኮርፈኝ ሳምንታት ሲያልፉ ሳይ በጣም ደስተኛ ሆንኩ። ይህ መሻሻል ጊዜያዊ እንዳይሆን ግን ሰጋሁ። ፈገግተኛነቷና ተጫዋችነቷ ላይ ወደኋላ እስከ ማይመለስ፥ ለውጡ ይህን ያህል የበረታ ይሆናል ብዬ ተስፋ ለማድረግ ድፍረት አልነበረኝም። ታዲያ በትክክል የሆነው የፈራሁት አልነበረም፤ ትዳርን የሚያቀዘቅዘውን ያንን ቀዝቃዛ ኩርፊያ ደግሜ ሳላይ ወራትና ዓመታት አለፉ።

ብሩስ፡- አሁን ትዳራችን ምድራዊ ገነት ነውን? አይደለም አንዳንድ ጊዜ አሁንም እንጣላለን። ጠባችን ግን ከቀድሞ የተለየ ነው።

በቅርብ ጊዜ ከነበረን ጠብ አንዱን እንንገራችሁ።

ካሮል፡- በቅርቡ ለብሩስ እንዲህ አልሁት፥ «በቤታችን ሌላ አንድ ተጨማሪ ክፍል ብንሠራ ምን ይመስልሃል? በተለይ እንግዶች በሚኖሩን ወቅት መመገቢያ ክፍል በጣም ያስፈልገናል።»

ብሩስ፡- እንዲህ በማለት መለስኩላት «ምን ያህል ገንዘብ እንደሚፈጅ አታውቂም? በዚህ ጊዜ ቤት መሥራት በቀላል ወጪ የምንወጣው አይደለም።»

ካሮል፡- «ጎረቤቶቻችን ቤታቸውን አስፍተውታል፤ ግን ብዙ ገንዘብ አልፈጀባቸውም።»

ብሩስ፡- «ጎረቤታችን ቤቱን ራው እራሱ ነው። እኔ ግን የሕንፃ ሥራ ባለሙያ አይደለሁም።»

ካሮል፡- ከመጋባታችን በፊት የብሩስን የገንዘብ አያያዝ አደንቅ ነበር። ቤታችንን ለማስፋት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ግን ብሩስ ስስታምና ለእኔ ፍላጎት የማይገደው ነው ብዬ አሰብኩ።

ብሩስ፡- ካሮል «ስለ ቤት» ጉዳይ መጀመሪያ ስትናገር «ያዘጋጀሁት የመኖሪያ ቤታችን የማይረባ ነው ብላ የምትተቸኝ» መሰለኝ።

ስለ ጉዳዩ መነጋገራችንን ስንቀጥል ግን እንዴት እንዳልተወደደች እንደተሰማት ተረዳሁ። ለትልቅ ቤት ስላላት ፍላጎት ምንም እንደማይገደኝ ነበር ያሰበችው።

በተለይ ያለማቋረጥ አዳሪ እንግዶች ይመጡብን ስለነበር ቤታችን በጣም ትንሽ እንደሆነ አውቅ ነበር። ካሮል በቤታችን እንግዶች የምታስተናግድበትን መንገድ ሁልጊዜ አደንቃለሁ። ሰው ሁሉ እንደ ቤቱ እንዲሰማው ታደርግ ነበር። በጣም ድሆች የሆኑ ሰዎች እንኳ ሁልጊዜ ጥሩ ምግብና መኝታ እንደምትሰጣቸው ያውቁ ነበር።

ሆኖም ግን በዚህ ቤት ላይ ብዙ ገንዘብ ማውጣት አልፈለግሁም።

ካሮል፡- በችግሩ ላይ እየተወያየን ሳለ በብሩስ ላይ የፈረድኩት ያለአግባብ መሆኑን ተረዳሁ። እርሱ ስሜቶቼን ተረድቶም ተጠንቅቆልኝም ነበር።

ከዚህ ውይይት በኋላ ብሩስ ቅርቤ መሆኑ ተሰማኝ። ቤቱን ላለማስፋት በወሰነው ውሳኔ ተስማማሁ።

በቀጣዩ ቀን ጠዋት እየጸለይን ሳለ ለእግዚአብሔርም ቅርብ እንደሆንኩ ተሰማኝ።

ብሩስ፡- ሰባት የሰዎች ስም ዝርዝሮችን ይዘን በሳምንቱ በእያንዳንዱ ቀን በአንዱ ዝርዝር ላይ እንጸልያለን። በአንድ ዓመት ውስጥ ለሁሉም የዓለም አገሮች ጸልየን ለመጨረስ እንድንችል በየዕለቱ ለአንድ አገር እንጸልያለን። በጸሎት ጊዜያችን መጨረሻ አንዳችን ለሌላችን እንጸልያለን።

ካሮል፡- በዚያ ዕለት ጠዋት ብሩስ ጸሎቱን ሲያጠቃልል እንደዚህ አለ «እንግዶችን በቤታችን በግሩም ሁኔታ የምታስተናግድ ሚስት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ።» ይህም ጸሎት ልቤን ነካው።

ብሩስ፡- ካሮል በጸለየችው በሚቀጥለው ጸሎት እንዴት እንደተደሰትኩ አስታውሳለሁ። «አባት ሆይ፥ ሕይወትን ከአንተ ጋር እንዲህ በጠበቀ ግንኙነት ማሳለፍ ለእኛ አስደናቂ ነው። እንዲሁም በመካከላችን ስላለው ወዳጅነትና ቅርበት፥ ስለምትሰጠን ነገር ስለቤታችንም በየዕለቱ እንድናመሰግንህ እርዳን።»

ከጸሎታችን በኋላ በአሳብ ያለመስማማታችንን ያስተናገድንበት መንገድ ከብዙ ዓመታት በፊት ካደረግነው ፈጽሞ የተለየ መሆኑን ተረዳን።

ካሮል፡- አዎን፥ እግዚአብሔር ይህን በአሳብ ያለመስማማት እንድንነጋገርና እንድንግባባ ባይረዳን ኖሮ ውጤቱ የተለየ ይሆን ነበር። በቤታችን ጥበት የተሰማኝ የውጥረት ስሜት ከብሩስ ጋር ከመነጋገር ይልቅ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ባኮርፍ በመጨረሻ ምን ሆነሻል? ብሎ መጠየቁ የማይቀር ነበር። ምናልባት እንዳነጋግረው በመፈለግ ብቻ ቤቱን ለማስፋት ይስማማ ነበር (ይህንንም እንኳ እጠራጠራለሁ)። ምናልባት ደግሞ ቤቱን የማስፋት አሳቡን ሳይቀበል ቢገፋበት ኖሮ ብዙ እንዳንገናኝ አብዛኛውን ጊዜውን ከቤት ውጭ ያጠፉ ነበር። ስሜቶቻችንን ሳንነጋገርና ስለ ጉዳዩም አብረን ሳንጸልይ እንቀር ነበር።

ብሩስ፡- ከዓመታት በፊት ካሮል ስለ ቤቱ ጥበት አማርራ ቢሆን ኖሮ «ሚስቶች ሁሉ ይህ ነገር የለኝም፥ ያ ነገር የለኝም ማለት ልማዳቸው ነው። እንደ ባል ነገሩን እንደ አመጣጡ መመለስ አለብኝ» የሚል ዝንባሌ ይኖረኝ ነበር።

በመጨረሻ ባለቤቴን ፍቅር በተሞላው ርኅራኄ መንከባከብ እንዳለብኝ እንድገነዘብ ስለረዳኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ይህን ማለት የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ልገዛላት እችላለሁ ማለት አይደለም። ነገር ግን ስሜቶቿን ተረድቼ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ ማለት ነው። ስለ ሐዘኗና ስለ ተስፋ መቁረጧ ይገደኛል። እካፈላታለሁም ማለት ነው።

ካሮል፡- በነገራችን ላይ በስዋዚላንድ የሚገኘውን ቤታችንን ብትጎበኙ አስፍተን እንደሠራነው ትመለከታላችሁ። ውዱ ባለቤቴ አንድ ክፍል ሳይሆን ሁለት ተጨማሪ ክፍሎችን አክሎበታል!

ብሩስ፡- አዎን፥ አንድ ቀን ለራሴ እንዲህ አልኩኝ፥ «መገንባት አትችልም የሚል ማን ነው?»

ብሎኬቶችን እንዴት እንደሚደረደሩ አንድ ጓደኛዬ አሳየኝ። በሲሚንቶ መሥራት የመጀመሪያ ጊዜዬ ቢሆንም እንኳ በታላቅ ደስታ ፈጸምኩት። ከሁሉም በላይ በዚህ ሥራ የተደሰተው ግን ልጃችን ነበር። በዚህ ፕሮጀክት ከአባቱ ጋር መሥራትን እጅግ ወድዶት ነበር!

ካሮል፡- ሴት ልጃችን ዕድሜዋ አሥራ ስድስት ዓመት በሆናት ወቅት አንድ ቀን እንዲህ አለችን። «ትዳር በምመሠርትበት ጊዜ ከባለቤቴ ጋር የሚኖረኝ ግንኙነት በሁለታችሁ መካከል ያለው ዓይነት እንዲሆን እፈልጋለሁ።»

ይህ ለእኔና ለብሩስ ያሳየን እግዚአብሔር በትዳራችን ውስጥ ያደረገውን አስደናቂ ተግባር ነው።

ብሩስ፡- ታሪካችንን እየተናገርን ሳለን ካሮልና እኔ በትዳር ሕይወታችን ውስጥ መራርነት እንዳልነበረን በማሰብ ተደንቃችሁ ይሆናል። እውነታው ግን በተጋባንበት ወቅት ክርስቲያኖች የነበርን ቢሆንም እንኳ ክርስቶስ በሕይወታችን ለውጥ ሊያመጣ የሚገባበት ብዙ ክፍል ነበረን።

ካሮል፡- ታላቅ እህቴ፥ «ካሮል፥ ክርስቲያን መሆን አለብሽ» በማለት የሚያስገርም ንግግር የተናገረችኝ የ15 ዓመት ልጃገረድ በነበርኩ ጊዜ ነበር።

እኔ ሁልጊዜ የማስበው ክርስቲያን እንደሆንኩ ስለሆነ እንዴት እንደዚህ ልትለኝ ቻለች?

የተጠምቅሁት ገና ሕፃን እያለሁ ነበር። በየእሑድ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። ትልቅ ኃጢአትም ሠርቼ አላውቅም።

ለራሴ እንዲህ አልኩ «ክርስቲያን መሆኔ እርግጥ ነው! እንዴት ክርስቲያን መሆን አለብሽ ትለኛለች? እርሷስ ማን ነኝ ብላ ነው ስለ ራሷ የምታስበው? እንደ እርሷ እኔም ጥሩ ሰው ነኝ!»

እህቴ ተስፋ አልቆረጠችም። ስለዚህ ወደ ወጣቶች የካምፕ ፕሮግራም ወሰደችኝ። በዚያም ኃጢአተኛ መሆኔን ተረዳሁ። ይህ እንዴት እንዳስደነቀኝ ልገልጸው አልችልም። በእኔ አመለካከት የተጠመቅሁ ጥሩ ልጃገረድ ነበርሁኝ። በእግዚአብሔር ዓይን ግን ኃጢአተኛ ነበርኩ።

ይህንን እምኜ መቀበል ባልፈልግም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡ ስሰማ ግን መከራከር አልቻልኩም።

«ሁሉ ተሳስተዋል ... ቸርነት የሚያደርግ የለም።» ሮሜ 3:12

በዚያ የወጣቶች የካምፕ ፕሮግራም ስለ ኢየሱስ ማንነት ጥቂት ነገሮች ተማርኩ። ለምን ወደዚህ ምድር እንደ መጣ ተገነዘብኩ። የመጣው እንዴት ጥሩ ሰው መሆን እንደምችል ሊያስተምረኝ አይደለም። የመጣው ጥሩ ሰው ስላይደለሁ ነው። ስለዚህ ኃጢአቴን በሙሉ ሊወስድና ይቅርታን አገኝ ዘንድ በእኔ ፈንታ መከራን ሊቀበል መጣ።

ቀጥሎ ማንም ሰው ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ መልካም ነገር ማድረግ እንደማይችል ተገነዘብኩ። መልካም ተግባሬ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስደኛል ብዬ ከማሰብ ይልቅ ኃጢአቴን በመናዘዝ በእኔ ምትክ በሞተው በኢየሱስ ማመን እንዳለብኝ ተረዳሁ። በመልካምነቴ መታመንን በማቆም በኢየሱስ መታመን እንዳለብኝ አወቅሁ!

በዚያ የካምፕ ፕሮግራም ላይ ከዚህ ቀደም ለኢየሱስ ብዬ የማላውቀውን ነገር ተናገርሁ። «ጌታ ሆይ÷ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ! መቀጣት ይገባኛል። ነገር ግን ይቅርታን አገኝ ዘንድ አንተ ስለ እኔ መከራን እንደተቀበልክልኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረኛል። ዛሬ ኃጢአቴን ይቅር ትል ዘንድ በአንተ እታመናለሁ። እኔ ስላደረግኩት ማንኛውም መልካም ሥራ ሳይሆን አንተ ስላደረግኸው ሥራ አሁን መንግሥተ ሰማያት እንደምገባ አውቃለሁ።»

«ክርስቲያን ሆንኩኝ» በማለት ለእህቴ ስነግራት ይህ ነው የማይባል ደስታ ተሰማት።

ብሩስ፡- ስለሰጠን የዘላለም ሕይወትና በትጻራችን እየሠራ ስለሆነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

ዛሬ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችሁ እንድትቀበሉ እናበረታታችኋለን። እርሱ ይወዳችኋል። የሕይወት ዘመናችሁን እግዚአብሔርን በማገልገል አሳልፉ።

# ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አምስት እውነታዎች

በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሁሉን ነገር እንደሚያውቁ ያስባሉ። ሆኖም ግን ከአሳቦቻቸው አብዛኛዎቹ ትክክል አይደሉም። እውነታዎቹ ቀጥለው ቀርበዋል፦

## እውነታ 1፦ ባልና ሚስት ሁለቱም የፍትወት ፍላጎት አላቸው።

ባል የሚስቱን የፍትወት ፍላጎት ማርካት ያለበት ሲሆን፥ ሚስት ደግሞ የባሏን የፍትወት ፍላጎት ማርካት አለባት።

«ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማማታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።» (1ኛ ቆሮ. 7፡3–5)።

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ራስ ወዳድነት ሊኖር አይገባም። ከላይ የተመለከትነው ጥቅስ የሚናገረው ባል የራሱን ፍላጎት ለማርካት የሚስቱን ሰውነት በስግብግብነት መጠቀም እንደሌለበት ነው። ይልቁኑ የእርሷን ፍላጎት ስለማርካት ማሰብ አለበት። የእርሷም ዓላማ የእርሱን ፍላጎት ማሟላት መሆን አለበት።

እንደዚህ ሲሆን እርስ በርስ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት እርካታን በመስጠትና በመቀበል ደስታን ያገኛሉ።

## እውነታ 2፦ ባልና ሚስት ለአጭር ጊዜ ካልሆነ በስተቀር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ማቆም የለባቸውም።

ቀደም ሲል ከላይ እንደተመለከትነው ጥቅስ ባልና ሚስት «ለተወሰነ ጊዜ የበለጠ መጸለይ እንችል ዘንድ ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንከልከል» ቢሉ የተወሰነው ጊዜ እንደተጠናቀቀ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸውን እንደገና መቀጠል አለባቸው። የተወሰነው ጊዜ ረጅም እንዳይሆን መጠንቀቅ አለባቸው፤ አለበለዚያ ከጋብቻ ውጭ ለሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊፈተኑ ይችላሉ።

አንዳንድ ጊዜ መጋቢውና ባለቤቱ «እግዚአብሔርን በማገልገል ስለተጠመድን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አያስፈልገንም። ለዚያ ጊዜ የለንም» ብለው ሲወስኑ ይችላሉ። ጥቂት ቆይቶ መጋቢው ልጃገረዱን

አስረገዘ ሲባል ሰሚው ሁሉ ይደነቃል። ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን የጋብቻ መብቱን አይከልክለው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መስማትና መታዘዝ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።

## እውነታ 3፡- ባልና ሚስት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስታን ያገኛሉ።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ማንም ሰው በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስ እንዲለው አይፈልግም ብለው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ መደሰት ያለበት ባል ብቻ እንጂ ሚስት አይደለችም ይላሉ። *እውነቱ ግን እግዚአብሔር ባልና ሚስት ሁለቱም በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስ እንዲላቸው ይፈልጋል።*

መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን በተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ባል ለሚስቱ እንዲህ ይላታል፡-

«ወዳጄ ሆይ፥ እነሆ፥ ውብ ነሽ፤

እነሆ፥ አንቺ ውብ ነሽ፤

ዓይኖችሽም እንደ ርግቦች ናቸው።» (1:15)

«ፍቅርሽ እንዴት ምልካም ነው!

ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እንዴት ይሻላል!

የዘይትሽም መዓዛ ከሽቱ ሁሉ! (4:10)

«እግሮችሽ በጫማ ውስጥ እንዴት ውቦች ናቸው!

ዳሌዎችሽ በአንጥረኛ እጅ እንደተሠሩ

እንደ ዕንቍዎች ይመስላሉ። (7:2)

ሁለቱ ጡቶችሽ እንደ ሁለቱ መንታ

እንደ ሚዳቋ ግልገሎች ናቸው።» (7:4)

ሚስት ደግሞ ባሏን እንዲህ ትላለች፡-

«በአፉ መሳም ይሳመኝ፥

ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ መልካም ነውና (1:2)

«ውዴ ለእኔ በጡቶቼ መካከል እንደሚያርፍ

እንደ ተቋጠረ ከርቤ ነው» (1:13)

«ውዴ ሆይ፥ እነሆ፥ አንተ እኮ ውብ ነህ፥

መልከ መልካምም ነህ፤ (1:16)

«ግራው ከራሴ በታች ናት፥

ቀኙም ታቅፈኛለች።» (2፡6)

«እፉ እጅግ ጣፋጭ ነው፥

እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው፥

እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጂት ሆይ፥

ውዴ ይህ ነው፥ ባልንጀራዬም ይህ ነው (5፡16)

«ውዴ ሆይ፥ ና፥ ወደ መስክ እንውጣ

በመንደሮችም እንደር (7፡12)

«...በዚያ ውዴን እሰጥሃለሁ።» (7፡13)

እነዚህ ጥቅሶች በግልጽ የሚያሳዩን ባልና ሚስት አንዳቸው ለሌላቸው ፍቅርን በመስጠት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስ ይላቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ነው።

ብዙ ባልና ሚስቶች በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብዙ ደስታ ያለማግኘታቸው እንዴት አሳዛኝ ነገር ነው! አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸውን ለማነቃቃት ወይም ለማርካት ምንም ሙከራ አያደርጉም። «ጥሩ ሚስት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መደሰት የለባትም። እኔ ሳደርግላት እርሷ ዝም ብላ መተኛት አለባት» ይላሉ።

አንዳንድ ሚስቶች ደግሞ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስታ የሚሰጥ አይደለም ብለው ያምናሉ። ወደ አልጋቸው የሚሄዱት በሚከተለው ዝንባሌ ነው። «ልታደርገው የግድ ከሆነ ቀጥል አድርገው፤ ነገር ግን ፈጠን በል፥ መተኛት እፈልጋለሁ።» ሚስቲቱ ግራ እጁን ያንተርሰኛል በቀኝ እጁ ያቅፈኛል። ሁለንተናው የደስ ደስ አለው። ውዴ ይህ ነው፥ ባልንጀራዬም ይህ ነው። ካለችበት ጥቅስ እንዴት የራቀ ነው። (መኃ. 2፡6 ና 5፡16 ተመልከት)

## እውነታ 4፡- ከጋብቻ ውጭ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በጋብቻ ውስጥ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አስደሳች ነው ይላል።

«ሙሽራዬ ሆይ ....ነዪ! ....

ፍቅርሽ እንዴት መልካም ነው!

ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እንዴት ይሻላል!

ከከንፈሮችሽ ማር ይንጠባጠባል፤

ከምላስሽ በታች ማርና ወተት አለ...» (መኃ. 4፡8ና10 እና 11)

ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ግን እጅግ መራራ ኃጢአት ነው።

«ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና፥ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና፥ ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የመረረ ነው፥ ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው።» (ምሳ. 5:3–4)

«መንገድህን ከእርስዋ አርቅ፥ ወደ ቤትዋም ደጅ አትቅረብ» (ምሳ. 5:8)

«ከጉድጓድህ ውኃ፥ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ...ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ።» (ምሳ. 5:15፥18)

ከላይ የተሰጡት ጥቅሶች ላገቡ ሰዎች የተነገሩ ናቸው። ላላገቡ ወጣቶችስ? የፍትወተ ሥጋን ግንኙነት ለመፈጸም ተፈቅዶላቸዋልን? አልተፈቀደላቸውም። የእግዚአብሔር ሕግ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለጋብቻ ብቻ የታቀደ እንደሆነ ያረጋግጥልናል።

«ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።» (1ኛ ቆሮ. 6:18)።

ዝሙት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሁለት መንገድ አገልግሎት ላይ ውሏል።

ሀ) በአንዳንድ ጥቅስ «ዝሙት» የሚለው ቃል የሚገልጠው ከፍትወት ጋር የተያያዙ ኃጢአቶችን በሙሉ ማለትም አመንዝራነትና ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ይጨምራል። (1ኛ ቆሮ. 5:1 ና 6:9፤ ኤፌ. 5:3፤ 1ኛ ተሰ. 4:3፤ ዮሐ. 8:41)

ለ) በሌሎች ጥቅሶች ደግሞ «ዝሙት» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከጋብቻ በፊት የሚደረግን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ ነው። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ላላገቡ ሰዎች ስለማግባት ወይም ሳያገቡ ስለመኖር ሲጽፍላቸው እንዳላገባ ሰው ከዝሙት መራቅ እንዳለባቸው ይናገራል።

«ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው። ነገር ግን ስለ ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት።» (1ኛ ቆሮ. 7:1–2)።

ጥቅሱ የሚናገረው ያለማግባት መልካም ቢሆንም ዝሙትን ለማድረግ መፈተን ከባድ ስለሆነ ለብዙ ሰዎች ማግባት የሚመረጥ መሆኑን ነው።

ሳያገቡ መኖር መልካም የሆነው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ያላገቡ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል እራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ መስጠት ይችላሉ። (ወደ ኋላ የሚጎትታቸው የትዳር ጣጣ የለባቸውም) 1ኛ ቆሮ. 7:32–34ን ተመልከቱ።

ማግባት መልካም የሆነው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ፈተና ጠንካራ ስለሆነ፥ በመብዛት ምድርን ልንሞላት ስለሚገባና ያላገቡ ሰዎች ብቸኝነት የሚያጠቃቸው ስለሆነ ነው። (1ኛ ቆሮ. 7:9፤ ዘፍ. 1:28 ና 2:18ን ተመልከት)

ስለዚህ ማግባት መልካም ነው። ያለማግባትም መልካም ነው። እያንዳንዱ ሰው የመምረጥ መብት አለው።

ነገር ግን የምንመርጠው የትኛውንም ቢሆን የእግዚአብሔርን ሕግጋት መታዘዝ አለብን፡-

ሀ) ያገቡ ሰዎች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያለባቸው ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ብቻ ነው (ዕብ. 13:4)።

ለ) ያላገቡ ሰዎች ከማንም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የለባቸውም (1ኛ ቆሮ. 6:18 ና 7:1-2፤ 2ኛ ጢሞ. 2:22)።

## የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያለበት በጋብቻ ውስጥ ብቻ ነው።

እነዚህ ሕግጋት የተዘጋጁት በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አይደለም። እነዚህ የፈጣሪያችንና የፈራጃችን ሕግጋት ናቸው።

አንድ ወጣት እንዲህ በማለት ጽፎልን ነበር፡-

*እኔና የሴት ጓደኛዬ (እጮኛዬ) በጣም እንዋደዳለን። በሚቀጥለው ዓመት ለመጋባት ዕቅደናል። ላለፉት አሥር ወራት በየሳምንቱ መጨረሻ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንፈጽም። ነበር። በቅርቡ አንድ የመንፈሳዊ መነቃቂያ ፕሮግራም ተካፈልን በዚያ ንስሐ ገብተን ክርስቶስን ተቀበልን። አሁን መጠየቅ የፈለግነው እስክንጋባ ድረስ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችንን ማቆም አለብን?*

ይህ ወጣት *«ንስሐ ገብተን ክርስቶስን ተቀበልን»* ማለቱን አስታውሱ። ንስሐ መግባትና ክርስቶስን መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?

ኃጢአታዊ ፍላጎቶች ከሚገዛው ሕይወት መመለስ ማለት ነው። ወደ ክርስቶስ መመለስና እርሱን የሕይወት ጌታ ማድረግ ማለት ነው። ስለዚህ ለዚህ ወጣት ጥያቄ መልሱ፡-*አዎን ንስሐ ገብታችሁ ክርስቶስን ከተቀበላችሁ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን በማቆም እርሱን ታዘዙ የሚል ይሆናል። (ሉቃ. 6:46ን ተመልከቱ።)*

በዚህ መጽሐፍ ባልና ሚስት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስ እንዲሰኙ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ብዙ ጊዜ የምንናገረው ነገር ነው። የትዳር ጓደኞዎች በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አንዳቸው ለሌላቸው እርካታ እንዴት እንደሚተባበሩ እንገልጻለን። ነገር ግን ከጋብቻ ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት መሆኑን በፍጹም አንዘነጋም።

## እውነታ 5፦ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ዘር የመተካት ተግባርም ነው።

በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የእግዚአብሔር ተቀዳሚ ዓላማ ባልና ሚስትን አንድ ለማድረግና ከፍተኛ ደስታ ለመስጠት ነው። ነገር ግን ዓላማው ይህ ብቻ ሳይሆን በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ዘር ለመተካትና ለመራባት ልጆች እንዲወልዱም ጭምር ነው።

ልጆች አስደናቂ ስጦታዎች ናቸው። እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ሰዎች «ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት...» አላቸው (ዘፍ. 1:28)።

አንዳንድ ሰዎች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቸኛ ዓላማ ልጆችን መውለድ እንደሆነ ማሰባቸው ያሳዝናል። አንድ ሰው እንዲህ በማለት ጽፎልን ነበር፦

*ባለቤቴ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ተነቃቅታ አታውቅም። እንዲያውም መነቃቃትም አትፈልግም። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምንፈጽምበት ጊዜ ምን እንደሚሰማት ስጠይቃት ምንም አይሰማኝም ትለኛለች። ብዙ ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችን የተነቃቃና አስደሳች እንዲሆን የተለያዩ ሥልቶችን ባቀርብም ምንም ፍላጎት አታሳይም። «መውለድ እስከቻልኩ ድረስ ሴተኛ አዳሪዎች ስለሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የፍትወተ ሥጋ አፈጻጸም ሥልቶች ማሰብ የለብንም» ትለኛለች።*

*ሌሎች ሴቶችን ሳይ ብዙ ፍላጎት ቢያድርብኝም ክርስቶስ ስለሚመጣና የተደበቁ ኃጢአቶችን በሙሉ ስለሚገልጽ በዚህ ኃጢአት ወድቄ አላውቅም። ነገር ግን በዚህ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሕይወታችን ያለው ችግር እያደገ ነው። ሰይጣን «ፍታትና ሌላ በፍትወት የምትረካባት የተሻለች ሴት አግባ» በማለት ያንሾካሹክብኛል። ነገር ግን በሠርጋችን ቀን ሚስቴን እስከ ሞት ድረስ ለመውደድ ቃል ገብቻለሁ።*

*ባለቤቴ መልካም ሴት ናት። በፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችን የተነቃቃና የሚያስደስታት ልምምድ እንዲኖረን እመኛለሁ። ከእርሷ ጋር አብረን ልናነበው የምንችለው ደብዳቤ ልትጽፉልን ትችላላችሁን?*

የጻፍንላቸው ደብዳቤ እግዚአብሔር ጋብቻ እንዲያሟላ የሚፈልገው የጓደኝነት ደስታና የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ደስታ እንደሆነ የሚያበስር አስደናቂ እውነትን ያዘለ ነበር። በእግዚአብሔር ዕቅድ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ዓላማዎች አንዱ ዘርን መተካት ወይም ልጅ መውለድ ቢሆንም ይህ ግን *ብቸኛው ዓላማ አይደለም*። እግዚአብሔር ባልና ሚስት በፍትወተ-ሥጋ ደስ እንዲሰኙ ዕቅዷል።

በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛውን ደስታ የሚያገኙት ሴተኛ አዳሪዎችና ደንበኞቻቸው *አይደሉም*። በፍተወተ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛውን ደስታ የሚያገኙት እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚታዘዙ ናቸው!

እኅቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፥

የተዘጋም ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት።

(መኃ. 4፡12–15ን ተመልከት።)

ውዴ ወደ ገነቱ ይግባ፥ መልካሙንም ፍሬ ይብላ። (4፡16)

እኅቴ ሙሽራዬ ሆይ፥ ወደ ገነቴ ገባሁ፥...

እንጆሪዬን ከማሬ ጋር በላሁ፥ (5፡1)

እግዚአብሔርን የሚወዱና
እርስ በርስ የሚዋደዱ
ባልና ሚስት በፍትወተ ሥጋ
ግንኙነት የመስጠትና
የመቀበል ደስታን ከማንም
ይልቅ ይለማመዳሉ!



ምዕራፍ 7

# የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስልቶች

ውድ ብሩስና ካሮል

ባለቤቴን እወደዋለሁ፤ በጣም ጥሩ ክርስቲያን ነው። ችግሩ ወደ መኝታችን ስንሄድ ይስመኝና ጥቂት ይጫወታል፥ ነገር ግን በጣም ይፈጥናል። በስሜቴ ገና ከመነቃቃቴ በፊት ብልቱን ያስገባና የዘር ፍሬውን ያፈስሳል። ወደ መኝታው ተመልሶ በመሔድ ለጥ ብሎ ይተኛል። ከዚያ በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል ወይም ከዚያ በላይ ዓይኖቼን አፍጥጬ ምንም እርካታ በሌለው ስሜት እቆያለሁ።

በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አልፈልግም። አሁን ባለቤቴ በፍትወት ስሜት ደካማ ናት በማለት ማጉረምረም ጀምሯል።

«LOVE AND MARRIAGE» (ፍቅርና ጋብቻ) በሚለው መጽሐፋችሁ ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን የፍተወተ ሥጋ ፍላጎት ማርካት አለበት ብላችኋል። ጥያቄዬ እንዴት? የሚል ነው። ማለቴ አንዳችን ሌላችንን ማርካት እንዴት እንችላለን?

በክርስቶስ ፍቅር፥

አስቴር

ይህን መጽሐፍ መጻፍ ስንጀምር በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስልት ላይ የመጻፍ አሳብ አልነበረንም። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የግል ጉዳይ ነው። ብዙ ነገር በዚህ ርእስ ላይ መጻፍ መልካም አይደለም።

ሆኖም ግን ከላይ የጠቀስነውን የአስቴርን ደብዳቤ መሰል ደብዳቤዎች በየቀኑ ይደርሱናል። የመጀመሪያው «LOVE AND MARRIAGE» (ፍቅርና ጋብቻ) የሚለው መጽሐፋችን በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ ከ40,000 ቅጂዎች በላይ ይሸጣል። ይህን መጽሐፍ ካነበቡ በመቶ ከሚቆጠሩ ሰዎች የሚደርሱን ደብዳቤዎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስልትን መግለጽ የግድ እንዳለብን አመልክተውናል።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስልትን ማለት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አፈጻጸም እውቀት ማለት ነው።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቴክኒክን ማወቅ የጋብቻ ሕይወት ዋናው ነገር አይደለም። የጋብቻ ሕይወት ዋናው ነገር ፍቅር ነው። በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ባልና ሚስት እንዴት መዋደድ እንዳለባቸው ለመግለጽ የተጠቀምነው ስለዚህ ምክንያት ነው።

*በትዳር ሕይወት ፍቅር ከሌለ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስልት ፋይዳ የለውም!*

ባልና ሚስት ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ስልቶች እውቀት ሊኖራቸው ይገባል መባሉም ደግሞ እውነት ነው። የዚህ ምዕራፍ ዓላማ እንደ እስቴርና ባሏ ያሉ ሰዎችን የሚያስፈልጋቸውን እውቀት በመስጠት መርዳት ነው።

በግብረ ሥጋ ግንኙነት ስልት አምስት ደረጃዎች ያሉ ሲሆን እነርሱም ዝግጅት፥ የፍቅር ጨዋታ፥ ክርና መርፌነት (ወንዱ ወደ ሴቷ ሲገባ)፥ ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት መድረስ (ጡዘተ ወሲብ) እና ከዚያ በኋላ ዘና ማለት ናቸው። አምስቱንም ተራ በተራ እያንዳንዳቸውን እንመልከት።

## አንደኛ ደረጃ
## ዝግጅት

ባልና ሚስት ለግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚከተሉት መንገዶች መዘጋጀት አለባቸው:-

*ስሕተትን በመቀበል ይቅርታ ተጠያየቁ።* ከመኝታ ሰዓት በፊት የፀብ ጉዳይ መፈታት አለበት። ለምሳሌ ባልና ሚስት በቁርስ ሰዓት ተጣልተው እንደሆነ በጉዳዩ ጊዜ ወስደው በመነጋገር ስሕተትን መቀባበልና ይቅርታ መጠያየቅ አለባቸው። አለበለዚያ ጉዳቱ ቀኑን ሙሉ በልባቸው ይቆያል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«ቍጣችሁም ሳይወገድ ፀሐይ አይጥለቅባችሁ» (ኤፌ. 4:26ን ተመልከት)

ባልና ሚስት ለዚህ ጥቅስ በሚታዘዙበት ጊዜ አንዱ የአንዱን በደል በይቅርታ ስለተዉ ወዳጅነታቸው አሁንም እንደሞቀ መሆኑን ስለሚያውቁት ወደ መኝታቸው በደስታ ይሄዳሉ።

ከመኝታ ሰዓት በፊት ይቅርታ ለማይጠያየቁ ባልና ሚስቶች፥ የሚሆነው ነገር ፈጽሞ የተለየ ነው። በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመደሰት ተግተው ቢጥሩም በልባቸው ባለው መራራነት የተነሣ እውነተኛ ደስታ አያገኙበትም።

- *ንጹሕና የጸዳችሁ ሁኑ።* ኢዩኤል በሚሠራበት ቢሮ በጥሩ አለባበስ የተዋቡ ሴቶችን ያያል፥ ከሰዓት በኋላ ወደ ቤቱ ሲመጣ ግን ባለቤቱ እንደ ጽዳት ሠራተኛ ለብሳ ያገኛታል።

«ባለቤቴ በፍትወት ተቃጥሎ ሊፈጽም ፈልጎ በሚቀርብበት ጊዜ ሰውነቱ ጥሩ ሽታ ስለሌለው እንዳፈገፍግ ያደርገኛል» የሚሉ በርካታ ሚስቶች አሉ።

ባልና ሚስት በአጠቃላዩ የሚከተለውን ለመፈጸም ጠንቃቃ መሆን አለባቸው። ሁለቱም አንዱ ለሌላው

*«አንተ /አንቺ ለእኔ ስለምታስፈልገኝ/ጊኝ ከአንተ/አንቺ ጋር በሆንኩ ጊዜ ንጹሕና የጸዳሁ መሆን አለብኝ»* ማለት አለባቸው።

- *የመኝታ ቤት በር ይቆለፍ:-* አንዲት ሴት ከባሏ ጋር ተኝታ ባለችበት ጊዜ ማንም ሰው ከውጪ ወደ መኝታ ክፍሉ ሊገባ ይችላል ብላ ከፈራች

በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ አትደሰትም። ስለዚህ መኝታ ቤታችሁን ቆልፉ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በተዘጋጃችሁ ጊዜ ሁሉ መኝታ ቤታችሁን መቆለፋችሁን አረጋግጡ።

- *ልብሳችሁን አውልቁ።* የእግዚአብሔር ዕቅድ ባልና ሚስት ብቻቸውን በሚሆኑበት ጊዜ በመኝታ ቤታቸው ልብሳቸውን አውልቀው ራቁታቸውን ሆነው ደስ እንዲሰኙ ነው (ዘፍጥ. 2:25)። ራቁታቸውን ሲሆኑ ማፈር የለባቸውም። እንዲያውም ባልየው የሚስቱን ልብስ ረጋ ብሎ በማውለቅ ሊደሰት፥ እርሷም ተመሳሳዩን በማድረግ ልትደሰት ትችላለች። ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚደረጉ ዝግጅቶች ለፍትወት በጣም የሚያነቃቃው አንዱ የሌላውን (በባልና ሚስት) ልብስ የማውለቅ ሂደት ነው።

## ሁለተኛ ደረጃ
## የፍቅር ጨዋታ

የግብረ ሥጋ ግንኙነት እጅግ የሚያረካ የሚሆነው ወንዱ ብልቱን በሴቷ ብልት ውስጥ ከማስገባቱ በፊት በስሜታቸው በጣም የተነቃቁ ከሆኑ ነው። ስለዚህ ከዚህ በፊት በፍቅር ጨዋታ ረጅም ጊዜ ማጥፋት አለባቸው። «የፍቅር ጨዋታ» ማለት መርፌና ክር ከመሆን በፊት አንዱ የሌላው ስሜት ለፍትወት እንዲነቃቃ ማድረግ ማለት ነው።

ባልና ሚስት ይህን መነቃቃት በመሳሳምና በመተቃቀፍ ሊገነቡት ይችላሉ። አንዱ የሌላውን አካል ፍቅር በተሞላበት መንገድ በመደባበስ ሊተሻሹ ይችላሉ።

አስቴር በጻፈችልን ደብዳቤ ባሏ ለፍቅር ጨዋታ በቂ ጊዜ እንደማይሰጥና በጣም እንደሚፈጥን ገልጻለች። «ይስመኝና ጥቂት ተጫውቶ ከመነቃቃቴ በፊት ብልቱን ብልቴ ውስጥ ያስገባል። በጣም ፈጣን ነው» ብላለች።

ብዙ ባሎች ይህንን ስሕተት ይሠራሉ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ሲፈልጉ *ይጣደፋሉ!* በፍቅር ጨዋታ ጊዜ ሳይወስዱ ብልታቸውን በሴቷ ብልት በማስገባት በሁለት ደቂቃ ሁሉን ነገር ያጠናቅቃሉ። በውጤቱ ሚስቲቱ አትረካም፥ ባሏም የተስፋ መቁረጥ ስሜት ይታይበታል። ምክንያቱም እንዳልተደሰተች ስለሚገባው።

እንደዚህ ዓይነት በተከፈለ ልብ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የእግዚአብሔር ዕቅድ አይደለም።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ወንዱ ወደ ሴቷ ከመግባቱ በፊት በፍቅር ጨዋታ በቂ ጊዜ ወስደው ደስታን እንዲካፈሉ ነው። ባልና ሚስት በፍቅር ጨዋታ ስለሚያገኙት ደስታ የሚናገር ውብ ጥቅስ በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን።

«አንቺ እንደ ንጉሥ ልጅ የተዋብሽ ሆይ! እግሮችሽ በነጠላ ጫማ ውስጥ ሲታዩ እንዴት ያምራሉ! ዳሌዎችሽ በብልኀ አንጥረኛ እጅ የተሠራ የዕንቍ ጌጥ ይመስላሉ፤...

ቁመናሽ የዘንባባ ዛፍ ይመስላል፤ ጡቶችሽም የዘንባባ ዘለላ ይመስላሉ።

በዘንባባው ዛፍ ላይ ወጥቼ ፍሬውን መልቀም እወዳለሁ፤

ጡቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ እቅፍ ናቸው፤

የእስትንፋስሽ መዓዛ እንደፖም ፍሬ ሽታ ነው።

የአፍሽም መዓዛ እንደ መልካም ወይን ጠጅ ነው።»

(መኃ. 7፡1 እና 7–9ን ተመልከት።)

## አካሎቻቸው




ሴቶች የወንድን አካል በቀላሉ ይረዳሉ። ብዙ ወንዶች ግን የሴትን አካል አይረዱም።

በወንዶች አካል ለፍትወት ቀስቃሽ ስሜት ያለው አካል አንድ ብቻ ሲሆን ይህም ብልቱ ነው። ሚስቱ ብልቱን በምታሻሽው ጊዜ በቀላሉ ስሜቱ ይነሣሣል።

የሴት አካል ግን ቀላል አይደለም። ለፍትወት ስሜት እጅግ ንቁ የሆኑ ሁለት ክፍሎች ያላት ሲሆን እነርሱም ብልቷና የወንድ ብልት መሰል አካል የሆነው ናዝረ ብልቷ ናቸው። እጅግ የመነሣሣት ስሜት ያለው አካሏ ናዝረ ብልት (ቂንጥር) የሚባለው ነው።

የናዝረ ብልቷ ቅርጽ እንደ ወንድ ብልት ሲሆን በመጠን ግን እጅግ ትንሽ ናት። ከዚህ በታች የተሰጠው ሥዕል እንደሚያሳየው ናዝረ ብልቷ ከብልቷ ውጭ ያለ ነው። እንዲያውም ከብልቷ አፍ 4 ሴ.ሜ. ርቆ የሚገኝ ነው።




አንዳንድ ባሎች የሚስታቸውን ስሜት የማነቃቂያ ብቸኛ መንገድ ጣትን በብልቷ ውስጥ መክተት እንደሆነ ያስባሉ። ሆኖም ግን እውነቱ ሴት በፍትወት ስሜቷ የበለጠ የምትነሣሣው ናዝረ ብልቷን ጨምሮ በዚያ አካባቢ ያሉትን የሰውነት ክፍሎቿን በመደባበስና በማሻሸት ነው።

በፍቅር ጨዋታ ወቅት ባል የሴቲቱን ብልትና ናዝረ ብልቷን ማሻሸት አለበት። ለፍትወት ስሜት መነሣሣት ከሁለቱ የተሻለው ግን ናዝረ ብልቷን ማሻሸት ነው።

## በቂ ጊዜ አሳልፉ—አትጣደፉ

የወንድ ሰውነት ከሴቷ ይልቅ ፈጣን ነው። ሚስት የባሏን ብልት *ጥቂት ሰኮንዶች* እንኳ ብታሻሸው የፍትወት ስሜቱ በጣም ይነሣሣና ብልቱ ቆሞ የግብረ *ሥጋ* ግንኙነት ለመፈጸም የተዘጋጀ ይሆናል።

የሴት አካል ግን በፍትወት ስሜት ለመነሣሣት *አዝጋሚ* ነው። በፍትወት ስሜቷ ተነሣሥታ ለግብረ *ሥጋ* ግንኙነት እንድትዘጋጅ *ከአሥር እስከ ሃያ ደቂቃ* የፈጀ የፍቅር ጨዋታ ያስፈልጋታል።

ስለዚህ ባል የእርሱ ሰውነት የሚፈልገው ጊዜ ጥቂት ሰኮንዶች ያህል ብቻ ቢሆንም በፍቅር ጨዋታ በርካታ ደቂቃዎችን መውሰድ ይጠበቅበታል። መጣደፍ የለበትም። ብልቱን በሚስቱ ብልት ውስጥ ከማስገባቱ በፊት በፍቅር ጨዋታ በቂ ጊዜ ማሳለፍ አለበት።

የሚያሳዝነው ነገር ብዙ ባሎች ሴት ረዘም ያለ የፍቅር ጨዋታ እንደሚያስፈልጋት ስለማይገነዘቡ *ተፈጥሮአዊ ፍላጎታቸውን* ብቻ ይከተላሉ። የወንድ ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶች «ተመልከት፥ ሚስትህ ልብሷን አውልቃ ወደ መኝታ እየሄደች ነው። በጣም ውብ ናት! ፍጠን! በአልጋው ላይ አስተኛት፥ አንድ ጊዜ ሳማት፥ ከዚያም ግባባት፥ የዘር ፍሬህን አፍስስ፥ ብልትህን ከብልቷ አውጣና ለጥ ብለህ ተኛ» ይሉታል።

ይህንን ካደረገ ሚስቱ የፍትወት ስሜቷ ሊነሣሣ ጊዜ ስለማይኖራት አትደሰትበትም፥ በኋላም የእርካታ ስሜት አይኖራትም።

መልካም አፍቃሪ የሆነ ባል ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶቹን አይታዘዝም። በዚህ ምትክ ሚስቱ በሚገባ ስሜቷ እንዲነሣሣ ለማድረግ ጊዜ በመውሰድ ከመገናኘቱ በፊት ያዘጋጃታል። በሌላ አባባል ወደ እርሷ ከመግባቱ በፊት ፍቅሩን እየመገባት በቂ ጊዜ ይወስዳል ማለት ነው።

ቀጥሎ የፍቅር ጨዋታ እንዴት እንደሚፈጸም እንመልከት።

## የላይኛው የሰውነት ክፍሏ

ባል ማሻሸትና መደባበስ መጀመር ያለበት ከላይኛው የሰውነት ክፍሏ ነው። «የላይኛው የሰውነት ክፍል» ማለት ከወገቧ በላይ ማለት ነው። ብዙ ባሎች ግን የላይኛውን የሰውነት ክፍሏን ቸል በማለት የፍትወተ *ሥጋ* አካሏን ለመደባበስ ይጣደፋሉ። መልካም አፍቃሪ ባል ግን አይጣደፍም። የሚስቱን ሰውነት ላይኛውን ክፍል ለማቀፍና ለመሳም ጊዜ ይሰጣል። ከከንፈሮቿ በተጨማሪ አንገቷንና ጡቶቿን ሁሉ ይስማል።

ሁሉም ሴቶች አንድ ዓይነት አይደሉም። አንዳንዶች ጡቶቻቸው ሲተሻሹላቸው ደስ ይላቸዋል፤ ሌሎች ደግሞ አያስደስታቸውም። አንዳንድ

ሴቶች በተለይ በወር አበባ ዑደት አንዳንድ ቀናት ጡቶቻቸው ሲነኩ በጣም ሕመም ይሰማቸዋል።

ስለዚህ ሴቶች፥ ከባሎቻችሁ ጋር ተነጋገሩ! ፍቅርን እየሰጡ ሳለ የሚያስደስታችሁን ነገር ንገሩአቸው። ወይም አሳዩአቸው። በፍቅር ጨዋታ ወቅት ከባሎቻችሁ ጋር ለመነጋገር መፍራት አይገባችሁም። መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ምዕራፍ አራትን አንብቡ። በዚያ ስፍራ በፍቅር ጨዋታ ወቅት ባልና ሚስት በፍጹም ነጻነት ሲነጋገሩ ትመለከታላችሁ።

## የፍትወተ ሥጋ ብልቶቿ

ባል የሚስቱን ላይኛው የሰውነት ክፍሎች ለጥቂት ጊዜ ከደባበሰና ካሻሸ በኋላ የፍትወተ ሥጋ ብልቶቿን እንዲደባብስላት ወይም እንዲያሻሻት ሚስት ፍላጎት ያድርባታል። ይህን ዓይነት መደባበስና ማሻሸት በሚያመችበት ሁኔታ ስፍራዋን ማስተካከል ይገባታል። ለዚህ ተግባር የሚሻለው አቋም በጀርባዋ ተኝታ ጉልበቷን አጠፍ ማድረግ ነው። ባለቤቷ በዚህ ትብብሯ እጅግ ደስተኛ ይሆናል።

በዚህ ጊዜ በቀኝ ጎኗ በመተኛት ግራ እጁን ከራሷ ሥር በማድረግ በቀኝ እጁ የፍትወተ ሥጋ ብልቶቿን መደባበስና ማሻሸት ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ የፍቅር ጨዋታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል።

«ግራው ከራሴ በታች ናት፥ ቀኙም ታቅፈኛለች።» (መኃ. 2፡6)

በዚህ አቋም እጆቿ ነፃ ስለሆኑ የባሏን ቀኝ እጅ የት ቦታ ሊያሻሻት ወይም ሊዳብሳት እንደምትፈልግ ለማሳየት ልትጠቀምባቸው ትችላለች። የእርሱን ብልት ልታሻሽለትም ትችላለች።

ሴቲቱ የፍትወት ስሜቷ እየተቀሰቀሰ ሲሄድ በአብዛኛው ብልቷ ፈሳሽ ያመነጫል። ይህ ፈሳሽ ብልቷን በማርጠብ ስለሚያለሰልሰው ለፍቅር ጨዋታ ይጠቅማል። አንዳንድ ሴቶች ግን የሚያመነጩት ፈሳሽ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሣ ብልታቸው ደረቅ እንደሆነ ይቆያል። ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ባለቤቷ ብልቷን ማሻሸት ወይም መደባበስ ከመቀጠሉ በፊት ጣቶቹን በገላ ቅባት ማለስለስ ያስፈልገዋል። (የሚጠቀምበት ቅባት ውድ ዋጋ ያለው ባይሆን ይመረጣል። ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ቅባቶች የፍትወተ ሥጋ ብልቶችን ሊጎዱ የሚችሉ ሽቶዎች የሏቸውም።)

ባልየው ሊያሻሻቸው ወይም ሊዳብሳቸው የሚገቡ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸሚያ ብልቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም ብልቷና ናዝረ ብልቷ ናቸው። ናዝረብልቷ ከሁሉም የበለጠ የፍትወት ስሜት ቀስቃሽ ቢሆንም ብልቷን በማሻሸት ጀምሮ ወደዚያ ማለፍ ይሻላል።

ሚስቲቱ የምትፈልገው የመደባበስ ወይም የማሻሸት ዓይነት ለዘብ ያለ ይሁን ጠበቅ ያለ ማሳወቅ አለባት።

ባልየው ብልቷን በማሻሸት ጥቂት ደቂቃዎች ከወሰደ በኋላ ጣቶቹን ወደ ናዝረ ብልቷ ማስተላለፍ ይችላል። ይህ ናዝረ ብልት የሚገኘው ከብልቷ

ውጭ የውስጥ የብልት ከናፍርት የሚገናኙበት ነጥብ አካባቢ ነው። (ገጽ48 ተመልከት።) ሚስቲቱ ይህን ናዝረ ብልቷን እንዲያገኘው ባሏን መርዳት ትችላለች። እጁን በእጇ ይዛ ወደ ናዝረ ብልቷ በመውሰድ የምትፈልገውን የመደባበስ ወይም የማሻሸት ዓይነት ልታሳየው ትችላለች።

አንዳንድ ሴቶች ብልታቸውና ናዝረ ብልታቸውና በአንድ ጊዜ እንዲተሻሸላቸው ወይም እንዲደባበስላቸው ይፈልጋሉ። ስለዚህ ባሎቻቸው ጣቶቻቸውን ወደ ብልቶቻቸው ውስጥ በማንሻተት በእጅ መዳፎቻቸው ደግሞ ናዝረ ብልቶቻቸውን እንዲያሻሹ ይጠይቃሉ። ሌሎች ሴቶች ደግሞ ብልታቸው ውስጥ ጣት እንዲከተት አይፈልጉም። ስለዚህ ባሎቻቸውን ናዝረ ብልታቸውን ብቻ እንዲዳብሱ ወይም እንዲያሻሹ ይጠይቃሉ።

ለፍቅር ጨዋታ ዋና አስፈላጊው ነገር ንግግር ነው። ሚስት ታላቅ ደስታን የሚያጎናጽፉት ነገር ምን እንደሆነ ባል እንዲያውቅ ማድረግ አለባት። ባሏም መናገር አለበት። ለምሳሌ በፍቅር የወንድ የዘር ፍሬ ለማፍሰስ እንደቀረበ የሚሰማው ጊዜ አለ። በእነዚያ ጊዜያት ሚስቲቱ ብልቱን ማሻሸቱን እንድታቆም ሊጠይቃት ይችላል። ይህም ብልቱን ብልቷ ውስጥ ከማስገባቱ በፊት እንዳያፈስ ይረዳዋል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሌላ ዕረፍት እንደሚያስፈልገው እስኪነግራት ድረስ እንደገና ልታሻሽለት ትችላለች።

የፍቅር ጨዋታ ፀጥታ የሰፈነበት ሊሆን አይገባም። ባልና ሚስት በጣም ወይም በትንሽ የሚፈልጉት ነገር ምን እንደሆነ እርስ በርስ መነጋገር አለባቸው።

## ደስታን ለማግኘት ነፃ መሆን

በፍቅር ጨዋታ ወቅት ባልና ሚስት የሚፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ ነፃ ናቸው።

አንዳንድ ባልና ሚስት አንዳቸው የሌላቸውን መላ አካል በቅባት ማሻሸት ያስደስታቸዋል። ከሁለቱ የትዳር ጓደኞች አንዱ የሌላውን ጀርባ በመቀባት ይጀምርና ከፊት ለፊት ደግሞ ከአንገት እስከ እግር ጣት ይቀጥላል። በዚህ ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ብልትን መጨረሻ ላይ ለማድረግ ይዘላል። የትዳር ጓደኞች በዚህ ዓይነት የፍቅር ጨዋታ ከአንድ ሰዓት በላይ ሊቆዩ ይችላሉ። ይህ ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በፊት የሚፈጸም ደስታን የመስጠትና የመቀበል አስደናቂ ልምምድ ነው።

ሌሎች የትዳር ጓደኞች ደግሞ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመሳሳም ይደሰታሉ። ሌሎች የትዳር ጓደኞች ደግሞ በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ እርስ በርስ በመተጣጠብ ረጅም ጊዜ አብሮ መቆየት የሚያስደስታቸው አሉ።

በፍቅር ጨዋታ ወቅት ባልና ሚስት «የፍቅር ጨዋታችንን ሌሎች በሚፈጽሙት መንገድ እየፈጸምን ነውን? በትክክል እያደረግን ነውን?» የሚሉ ጥያቄዎችን እራሳቸውን በመጠየቅ መጨነቅ የለባቸውም።

ሌሎች እንዴት እንደሚያደርጉት በመጠየቅ ከመጨነቅ ዘና በማለት ደስታቸውን ሊያጣጥሙ ይገባል።

ሊከተሏቸው የሚገቡ ሁለት ብቸኛ ሕጎች፡-

**የሚያስደስታችሁን ነፃ ሆናችሁ ተነጋገሩ!**

## እርሷ በሚገባ እስክትዘጋጅ ድረስ የፍቅር ጨዋታን ቀጥሉ

የፍቅር ጨዋታው እየቀጠለ ሳለ የሚስት በፍትወት ስሜት መቀስቀስ በቀስታ ያድጋል። ሰውነቷ በሙሉ ይግልና ቶሎ ቶሎ መተንፈስ ትጀምራለች። የብልቷ የውስጥ ከናፍርት በመጠን ይጨምራሉ።

የፍቅር ጨዋታው ሚስት ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እስክምትዘጋጅበት ጊዜ ድረስ መቀጠል አለበት። የተዘጋጀች የምትሆነው የፍትወት ስሜቷ ግለት ከፍተኛው ደረጃ ላይ ሲቀርብ ነው። ይህ ከሆነ ወንዱ ብልቱን በብልቷ ውስጥ እንዳስገባ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት (ጡዘተ ፍትወት) ላይ ትደርሳለች።

## ሦስተኛ ደረጃ
## ወደ ብልቷ መግባት

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍጹም የሚሆነው ባልና ሚስት በአንድነት ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ማለትም ጡዘተ ፍትወት ላይ ሲደርሱ ነው።

ሴቲቱ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ስትደርስ ለአሥር ሰኮንዶች ያህል ታላቅ ደስታ ይሰማታል። የደስታው ስሜት በናዝረ ብልቷ ይጀምርና ወደ መላ ሰውነቷ ይሠራጫል። በዚህ አስደሳች ስሜት ወቅት ቶሎ ቶሎ ትተነፍሳለች፤ ፍጹም ታላቅ ደስታ እንዳገኘች የሚገልጥ የሲቃ ስሜት ልታሰማ ትችላለች። ከዚህ የእርካታ ስሜት በኋላ ትልቅ ደስታ ይሰማትና እርፍ ወይም ዘና ትላለች።

ወንዱ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ሲዳረስ እርሱም ለአሥር ሰኮንዶች ያህል ታላቅ ደስታ ይሰማዋል። በዚህ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ወቅት ወተት የመሰለ አንድ ማንኪያ የሚያህል ፈሳሽ ከብልቱ በፍጥነት ተፈትልኮ ይወጣል። ይህን ፈሳሽ ካፈሰሰ በኋላ ሰውነቱ ለጥቂት ጊዜ ከማንኛውም እንቅስቃሴ ገታ እንዲል ይፈልጋል።

## ወደ ብልቷ ውስጥ የማስገባት ሂደት

የፍቅር ጨዋታ ሚስት እጅግ ከፍተኛ የፍትወት ስሜት መነሣሣት እስከታሳይ ለሃያ ደቂቃ ወይም ከዚያ በላይ ይቀጥልና ሴቲቱ «አሁን ከፍተኛ የፍትወት ስሜት ላይ እየደረስኩ ይመስለኛል፥ ወደ እኔ ግባ» ትለዋለች።

የትዳር ጓደኛሞቹ የተጋቡት በቅርብ ከሆነ ሚስት ወደዚህ የስሜት እርካታ ደረጃ ስትቀርብ አታውቀው ይሆናል። ይህ ግን ችግር አይደለም። ምክንያቱም ሴቲቱ የወንዱን ብልት ለማስተናገድ የተዘጋጀችበትን ሰዓት ባለቤቷ የሚያውቅበት መንገድ አለ። ይኸውም የብልቷን የውስጥ ከናፍርትን መጠን ለማወቅ ጣቶቹን ይጠቀማል (ገጽ 48 )። እነዚህ ከናፍርቶች በመጠን እጅግ ሲጨምሩ ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት ቀርባለችና ብልቱን በብልትዋ ውስጥ ማስገባት አለበት።

ብልቱን ብልቷ ውስጥ ለማስገባት እርሱ ከላይ ይሆናል፥ ነገር ግን በሙሉ ክብደቱ አይተኛባትም። ክብደቱን በጉልበቶቹና በክርኖቹ ላይ ማሳረፍ አለበት። እርሷ ብልቱን በእጆቿ ይዛ ወደ ብልቷ ታስገባዋለች።

ከሚገባ በላይ ወደ ውስጥ አጥልቆ በማስገባት እንዳያሳምማት መጠንቀቅ አለበት። እርሷም የምትመርጠውን የጥልቀት መጠን ትነግረዋለች።

### ለአንድ ደቂቃ ጠብቅ

ወንዱ ብልቱን በሴቲቱ ብልት ውስጥ ካስገባ በኋላ መልካም ያልሆነው ነገር የወንድ የዘር ፈሳሹን በፍጥነት ማፍሰሱ ነው። ካልተጠነቀቀ በስተቀር በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ሊያፈስ ይችላል። ባለቤቱ ወደ ከፍተኛው የፍትወተ ስሜት እርካታ ላይ እንድትደርስ በቂ ጊዜ ስለሚያስፈልጋት ይህ በጣም ፈጣን ይሆንባታል።

ወንዱ የዘር ፍሬውን ፈጥኖ እንዳያፈስ የሚከተለውን ማድረግ ይችላል። ብልቱን ብልቷ ውስጥ ካስገባ በኋላ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት *ለአንድ ደቂቃ በፀጥታ ይቆያል*። በዚህ አንድ ደቂቃ ተነሣሥቶ የነበረው ስሜቱ እንዲበርድ ያለምንም እንቅስቃሴ ይሆናል። የተነሣሣው ስሜቱ እንዲበርድ የሚያስፈልገው የዘር ፍሬውን ሳያፈስ የመቆየቱ ጉዳይ እንዲሳካለት ነው።

ከአንድ ደቂቃ በኋላ የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴውን ይጀምራል። ተነሣሥቶ የነበረው ስሜቱ ስለበረደ የዘር ፈሳሹን ከማፍሰሱ በፊት *ለበርካታ ደቂቃዎች* እንቅስቃሴውን መቀጠል ይችላል። እነዚህ በርካታ ደቂቃዎች ሴቲቱ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት እንድትደርስ ስለሚያደርጋት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።

## አራተኛ ደረጃ

## ጡዘተ-ወሲብ (ከፍተኛው የእርካታ ደረጃ)

ባልና ሚስት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርጉባቸው ጊዜያት ሁሉ ከሚከተሉት ነገሮች አንዱ ይፈጸማል። ሀ) ወንዱ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ከመድረሱ በፊት ሴቷ ትደርሳለች። ወይም ለ) ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት (ጡዘተ-ወሲብ) በአንድ ላይ ይደርሳሉ። ወይም ሐ) ወንዱ አስቀድሞ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ይደርሳል።

*ሀ) ሚስት ቀድማ ስትረካ፡-* ሚስት ከባሏ ቀድማ ስትረካ መልካም ነው። ወደ እርካታዋ ስትደርስ በፊቷ ላይ በሚነበበው የደስታ ስሜት እርሱም ደስ ይለዋል። ከዚያ በኋላ ወንዱ የእርካታ ስሜት ላይ እስኪደርስ ድረስ ብልቱን የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴውን ይቀጥላል። እርሷ ወደ እርካታዋ ስሜት የደረሰች ቢሆንም ሕመም የሚያስከትልባት ስላይደለ በእንቅስቃሴው ደስተኛ ናት።

*ለ) በአንድ ላይ ወደ እርካታ ስሜት ሲደርሱ፡-* ይህም ሲሆን መልካም ነው። በዚህ ሁኔታ ደስታን በአንድ ጊዜ የሚሰጡና የሚቀበሉ ይሆናሉ።

*ሐ) ባል አስቀድሞ ሲረካ-* ባል አስቀድሞ ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት ከደረሰ መልካም አይደለም። እርሱ አስቀድሞ ከረካ ለእርሷ መርካት አስቸጋሪ ይሆናል። ለምን? ምክንያቱም እርሱ የወንድ ፈሳሹን ካፈሰሰ ብልቱ ይዝለፈለፍና ለስላሳ ይሆናል። የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴውን ልቀጥል ቢል ሕመም ይሰማዋል። እንደገና እንቅስቃሴውን ለመጀመር ለበርካታ ደቂቃዎች ማረፍ ያስፈልገዋል። በእነዚህ ደቂቃዎች የተቀሰቀሰው የሚስቱ ስሜት ይበርዳል። የሴት ስሜት ከበረደ በኋላ እንደገና ማነሣሣት አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ለበርካታ ደቂቃዎች ጠብቆ እንደገና ወደ እርካታ ስሜት እንድትደርስ ለማድረግ ቢሞክር አይሳካለት ይሆናል።

ወንዱ ሴቲቱ ከመርካትዋ በፊት የዘር ፈሳሹን ቢያፈስ ሴቲቱ እንድትረካ ለማድረግ የሚችልበት መንገድ ግን አለ። ይህም የወንድ ዘር ፈሳሹን ካፈሰሰ በኋላ ብልቱን ከብልቷ ሳያወጣ ጣቶቹን በመጠቀም ናዝረ ብልቷን ማሻሸት ወይም መደባበስ ነው (ገጽ 49)። ማሻሸቱን ወይም መደባበሱን ወዲያውኑ መጀመር አለበት። ይህም የተነሣሣው ስሜቷ ሳይበርድ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ እንድትደርስ ይረዳታል።

በዚህም ጊዜ መነጋገር በጣም አስፈላጊ ነው። ባል አስቀድሞ ከረካ ሚስት፡- «ፍቅሬ እባክህን ናዝረ ብልቴን በጣቶችህ አሻሽልኝ» ወይም ደግሞ «ይበቃል ዘና ማለት እፈልጋለሁ፤ በመርካትህ ደስ ብሎኛል፥ ዛሬ እኔ የግድ መርካት የለብኝም። ሁለታችንም ዘና እያልን ሳለ በክንዶችህ እቀፈኝ» ልትል ትችላለች።

አንዲት ሴት ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት መድረስ ሲያቅታት ያለመርካት ስሜት ቢኖራትም ይህ ስሜት ለረጅም ጊዜ አይዘልቅም። በባሏ ክንዶች ላይ አረፍ ብላ እያለ ያለመርካት ስሜቷ ቀስ በቀስ ይጠፋል።

## ማስታወስ የሚገባን አምስት ነጥቦች

አስቴር በጻፈችልን ደብዳቤ «ባሌ በጣም ፈጣን ነው፤ በፍትወት ስሜቴ በሚገባ ከመነቃቃቴ በፊት ብልቱን በብልቴ ያስገባና የዘር ፈሳሹን ያፈስሳል» ብላለች።

በሌላ አባባል የእነርሱ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሁልጊዜ «ባል አስቀድሞ የሚረካበት» ነው።

ቀጥሎ አስቴርና ባሏ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት አብረው እንዲደርሱ ወይም እርሷ አስቀድማ እንድትደርስ (ለአንተና ለባለቤትህም እንዲሁ) የሚረዳችሁ አምስት ነጥቦች ቀርበዋል።

♦ አንደኛ ነጥብ፦ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።

ባልና ሚስት እርስ በርስ ለመዋደድ ካልተጠነቀቁ በስተቀር ፍትወት አስደሳች ሊሆን አይችልም። ፍቅር ማለት አንዱ ለሌላው በአልጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ግንኙነት ደግና ርኅሩኅ መሆን ማለት ነው። ፍቅር ማለት ሚስት ሁሉን ነገር ስትሠራ ዝም ብሎ ከማየት ይልቅ ልጆች በጋራ እንክብካቤ በማድረግ መረዳዳት ማለት ነው። ፍቅር ማለት በቤት ውስጥ ባለ ኃላፊነት ሌላው ስሕተት በሚሠራበት ጊዜ እንኳ ጉዳዩን በጥሞና ማየትና ማለፍ ማለት ነው። ፍቅር ሰው ከወዳጁና ከጓደኛው ጋር እንደሚነጋገር ከትዳር ጓደኛ ጋር ችግሮችን መነጋገር ደስታን መካፈል ማለት ነው። ቀኑን ሙሉ ከፉና ራስ ወዳድ ሆኖ የዋለው ባል ማታ የሚያደርገው መደባበስና ማሻሸት ማለት አይደለም።

የትዳር ጓደኞችሁ ቀኑን ሙሉ ፍቅርን በመግለጽ ካሳለፈ የማታው የፍቅር ጨዋታ እንዴት አስደሳች ይሆናል!

ቅን ክርስቲያን የትዳር ጓደኞሞች የተከፈለ ልብ ካላቸው ክርስቲያን የትዳር ጓደኞሞች ይልቅ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ይደሰታሉ። ለምን? ምክንያቱም የተከፈለ ልብ ያላቸው ክርስቲያኖች ቀኑን ራስ-ወዳድና ትዕግሥት የለሽ በመሆናቸው ይህ የምሽት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸውን ያበላሽባቸዋል። ቅን ልብ ያላቸው ክርስቲያኖች የቻሉትን ያህል ቀኑን ሙሉ ደግ ለመሆን ስለሚጥሩ....መኝታቸው ውብና አስደሳች ይሆናል!

♦ ሁለተኛ ነጥብ፡- የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ አትቸኩል።

ለፍቅር ጨዋታ በቂ ጊዜ ውሰድ፤ ተደሰትበት! ፈጥነህ ወደ ግንኙነት አትሂድ። የሚስትህ መነሣሣት የእርካታው ጫፍ ድረስ ቀረብ እስኪል የፍቅር ጨዋታህን ቀጥል።

♦ ሦስተኛ ነጥብ፡- ብልትህን በብልቷ ውስጥ ካስገባህ በኋላ ለአንድ ደቂቃ ያህል በዝምታ ቆይ።

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ባል ብልቱን ሚስቱ ብልት ውስጥ ካስገባ በኋላ መልካም ያልሆነው ነገር በፍጥነት የዘር ፍሬውን ማፍሰሱ ነው። ስለዚህ የስሜቱ መነሣሣት እንዲበርድ ለማድረግ መሞከር አለበት። ይህን ለማድረግ ብልቱን በብልቷ ውስጥ ካስገባ በኋላ የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴ ሳያደርግ በፀጥታ ለአንድ ደቂቃ መቆየት አለበት። በዚያ አንድ ደቂቃ የተነሣሣው ስሜቱ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል። ይህም ፈጥኖ የዘር ፍሬውን እንዳያፈስ ይረዳዋል።

ለአንድ ደቂቃ በፀጥታ በሚጠብቅበት ጊዜ የሚስቱ የተነሣሣ ስሜት ይወርዳልን? ላይወርድ ይችላል። በዚያ የፀጥታ የአንድ ደቂቃ ቆይታ ውስጥ የፍትወት ስሜት የማነሣሺያ መንገድ ያገኙ የትዳር ጓደኞች በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ሚስት ስሜቷ እንዲቀሰቀስ (እንዲያድግ) በሚያስችል ሁኔታ ዳሌዋን ማንቀሳቀስ ትችላለች። ይህን ስታደርግ ባሏ የዘር ፍሬውን እንደማያፈስ መሆን አለባት። ባሏ የዘር ፍሬውን እንዲያፈስ የሚያደርገው ብልቱን የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴ ማድረጉ ነው። ስለዚህ የመግባትና የመውጣትን እንቅስቃሴ በማስወገድ ዳሌዋን በማሽከርከር ብልቱ የብልቷን ግድግዳዎች እንዲያሻሽ ማድረግ ትችላለች። በፒሲ ጡንቻዋ ብልቱን መጭመቅም ትችላለች (የብልቷን የፒሲ ጡንቻ በገጽ 129-130 ተመልከት)። መሽከርከርና መጭመቅ የእርሱን ስሜት ሳያነሣሣ የራሷን ስሜት ለማሳደግ ያስችላታል።

ባል የሚስቱ ስሜት በዚያ ደቂቃ ውስጥ ከፍ እንዲል ሊረዳት ይችላል። ብልቱ ያለ እንቅስቃሴ እንዲቆይ ሲያደርግ ናዝረ ብልቷን በጣቶቹ ማሻሸት ይችላል።

የትዳር ጓደኞች ይህን መጽሐፍ መከተላቸው የግድ አይደለም። እርስ በርሳቸው በነጻነት የሚነጋገሩ ከሆነ በዚያ የአንድ ደቂቃ ቆይታ የፍትወት ስሜቷን ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ የሚችሉበትን የተለያዩ መንገዶችን ያገኛሉ።

♦ አራተኛ ነጥብ፡- አሳባችሁ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚያስገኘው ደስታ ላይ ያተኩር።

በፍቅር ጨዋታና በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ሚስት መታጠብ ስላለባቸው የቆሸሹ ልብሶች ወይም ነገ መገዛት ስላለባቸው የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ማሰብ የለባትም። አንዲት ሴት ወደ ከፍተኛ እርካታ ስሜት

ለመድረስ እንድትችል ስሜቷ እንዲቀሰቀስ አሳቦቿን በፍቅርና በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚገኘው ደስታ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ አለባት።

♦ አምስተኛ ነጥብ፡- በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ተነጋገሩ

አንዳንድ ሴቶች የወንዱ ብልት እንቅስቃሴ ፈጣን እንዲሆን የሚፈልጉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በዝግታ መንቀሳቀሱን ይመርጣሉ። አንዳንድ ሴቶች የወንድ ብልት በጥልቀት እንዲገባ የሚፈልጉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ 10 ሴ.ሜ ድረስ ብቻ የወንዱ ብልት ሲገባ የበለጠ ያስደስታቸዋል። ባል ሚስቱ የምትመርጠውን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? *እርሱ ሊጠይቃት እርሷም ልትመልስለት ይገባል። መነጋገር አለባቸው!*

ባል ለግብረ ሥጋ ግንኙነት የተለየ አዲስ የአተኛኘት ዘዴ ይፈልግ ይሆናል። ነገር ግን «ሚስቴ አዲስ ነገር ለመሞከር የተዘጋጀ ስሜት አይኖራት ይሆናል?» ብሎ ቢያስብ፥ ይህን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? *በመጠየቅ ያውቃል፤ መነጋገር ያስፈልጋል!*

በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ለመነጋገር ብትፈሩም እንኳ ዛሬውኑ መነጋገር ጀምሩ። ብዙም ሳትቆዩ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት አንዳችሁ የሌላችሁን ድምጽ መስማት ስለሚያስደስታችሁ መናፈቅ ትጀምራላችሁ።

## አምስተኛ ደረጃ

## ዘና የማለት ወይም የዕረፍት ጊዜ

ወንድ ከፍተኛውን የፍትወት እርካታ ካገኘ በኋላ ተንጋሎ መተኛት ያምረዋል።

ለሴቷ ግን የተለየ ነው። ከፍተኛውን የፍትወት እርካታ ካገኘች በኋላ ለተጨማሪ ደቂቃዎች ባሏ እቅፍ አድርጓት እንዲቆይ ትፈልጋለች። ለተጨማሪ ጥቂት ጊዜያት «እወድሻለሁ» ሲል መስማት ትፈልጋለች።

ባለቤቷ ተንጋሎ ከተኛ «ምናልባት አይወደኝም ይሆናል» ብላ ታስባለች።

አንዲት ሚስት እንዲህ ብላለች፡- «የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸምን በኋላ ወዲያውኑ ጀርባውን ሰጥቶኝ ይተኛል። ጉዳቴ እንዳይሰማኝ እሞክራለሁ። ነገር ግን ‹ሰውነቴን የሚጠቀመው እራሱን ለማርካት ብቻ ነው። እንደ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር አይወደኝም›» ብዬ ሳስብ ራሴን አገኘዋለሁ።

ወንዶች የዘር ፍሬአችሁን ካፈሰሳችሁ በኋላ ወዲያውኑ አትተኙ። ተጨማሪ ጊዜ በመውሰድ ሚስታችሁን አቅፋችሁ እንዴት እንደምትወዱአት ንገሩአት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ለእንቅልፍ ትዘጋጁና በአንድነት መተኛት ትችላላችሁ።

# የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ችግር

ሪቻርድና ሚርያም ወደ መጋቢያቸው ለጋብቻ የምክር አገልግሎት ሄዱ። በመጋቢያቸው ቢሮ ተቀምጠው ሳለ ሪቻርድ እንዲህ አለ። «ፓስተር ፊት ለፊት እነግርሃለሁ... በጋብቻችን ውስጥ ያለው ችግር የፍተወተ ሥጋ ግንኙነት ችግር ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንድንፈጽም ደስተኛ አይደለችም።»

መጋቢው ምንም ነገር ሳይናገሩ ዓይኖቻቸውን ወደ ሚርያም አቅጣጫ መለሱ። መሬት እያየች ስትናገር ላለማልቀስ እየታገለች እንዲህ አለች «ፓስተር ባለቤቴ አይወደኝም። ለእናቱና ለእህቶቹ ርኅሩኅ ነው። ለእኔ ግን አይደለም። ከእኔ ጋር መነጋገር አያስደስተውም። ከእርሱ ጋር መነጋገር ስሞክር ብዙ ጊዜ መልስ አይሰጠኝም። ማታ ግን ልብሶቼን ሳወልቅ ሲያየኝ ያኔ ወዲያውኑ ትዝ እለዋለሁ። ለእኔ ምንም ስለማይጠነቀቅልኝ የፍትወት ስሜት የሚኖረኝ እጅግ አልፎ አልፎ ነው።»

መጋቢው ከሪቻርድ ጋር አንድ ወንድ ለሚስቱ የፍቅር ርኅራኄን እንዴት እንደሚያሳይና ከእርሷ ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚገባው ረጅም ውይይት ካደረጉ በኋላ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ችግራቸው ተቃለለ።

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው አራት ምዕራፎች ስለ ፍቅር ርኅራኄና ስለ መግባባት ገልጸናል። ምናልባት ብዙዎቻችሁ ያንን ምዕራፍ ዘላችሁት ይሆናል። ምዕራፍ 7ን አስቀድማችሁ ለማንበብ ወስናችሁ ማለት ነው። ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስልቶች በሙሉ ማወቅ ፈለጋችሁ። በዚህ አንወቅሳችሁም። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ከምዕራፍ አንድ እስከ አራት ያሉትን እውነቶች እስካልተረዳን ድረስ ስለ ፍትወተ ሥጋ ሁሉን ነገር ማወቅ አይጠቅምም። ስለዚህ የምንመክራችሁ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ የዚህን መጽሐፍ መጀመሪያ በተለይ ምዕራፍ 2ን እንድታነቡ ነው። ከዚያ በኋላ ብቻ በዚህ ምዕራፍ ያነበባችሁትን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስልቶች ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ።

ምዕራፍ 8

# የሠርግ ቀን ምሽት

የተወደዳችሁ ብሩስና ካሮል፥

በሚቀጥለው ወር ከአንድ አስደናቂ ልጅ ጋር እንጋባለን። እርሱ 24 ዓመቱ ሲሆን እኔ ደግሞ 22 ዓመቴ ነው። ሁለታችንም ጌታን እንወዳለን። ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸምንም...ኃጢአት እንደሆነ እናውቃለን።

ዋናው ፍርሃቴ የጋብቻችን ዕለት እኔና ባለቤቴ ወደ መኝታችን ስንሄድ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አለማወቁ ነው። ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ምንም አላውቅም። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። ክርስቶስን የተቀበልኩት በ12 ዓመቴ ሲሆን እስከ ሠርጌ ቀን ድረስ ለመቆየት በጥንቃቄ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቄአለሁ።

መልካም ክርስቲያን ሚስት መሆን እፈልጋለሁ። ባለቤቴን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ በሁሉም ነገር ላረካው እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ። ግን ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ስለማላውቅ ፍርሃት ይሰማኛል።

የእናንተው

ኤቪሊን

እንደ እውነቱ ከሆነ የኤቪሊን ችግር ትልቅ አይደለም። ከግብረ ሥጋ ግንኙነት አንጻር አንዳንድ ፍርሃቶች አሉአት። ነገር ግን አንዳንድ ልጃገረዶች ወደ ጋብቻ የሚገቡት ከዚህ በባሰ ፍርሃት ነው።

ለምሳሌ አንዳንድ ልጃገረዶች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከወንድ ጓደኞቻቸው ጋር ቀደም ብለው ይፈጽሙና ኋላ በሚያገቡበት ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በጣም ያስፈራቸዋል። ለምን? ምክንያቱም ከጋብቻ በፊት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርጉበት ጊዜ ሁሉ ከባድ ፍርሃት ነበረባቸው። *«ካረገዝኩኝ ይተወኝ ይሆንን?»፥ «ዛሬ ማታ ላረካው ካልቻልኩ ይተወኝ ይሆናል»* የሚል ፍርሃት ነበረባቸው። እነዚህ ልጃገረዶች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን የሚለማመዱት በፍርሃት ነው። በእነርሱ አእምሮ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትና ፍርሃት አብረው የሚሄዱ ናቸው። ስለዚህ ካገቡም በኋላ እንኳ ፍርሃታቸው በቶሎ አይጠፉም።

ኤቪሊን እንደዚህ አይደለችም። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንዲፈጸም በመጠበቋ መልካም አድርጋለች። የእርሷ ፍርሃት የእውቀት ጉድለት ብቻ ነው።

በዚህ ምዕራፍ ኤቪሊንና እንደ እርሷ ያሉ ሌሎች ሰዎችን መርዳት እንፈልጋለን። ስለ ሠርጋቸው ቀን ምሽት ፍርሃት ያላቸው ወጣት ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ፥ ብዙ ወጣት ወንዶችም ናቸው።

ውድ ብሩስና ካሮል፥

የ25 ዓመት ክርስቲያን ሰው ነኝ። "LOVE AND MARRIAGE" ወይም "ፍቅርና ጋብቻ" በሚል ርእስ ስለ ጻፉችሁት መጽሐፍ ላመሰግናችሁ ይገባኛል። አብዛኛዎቹ ጥያቄዎቼ ያን አስደናቂ መጽሐፋችሁን በማነብበት ጊዜ ተመልሰውልኛል። እንዲያውም ያነበብኩት ሦስት ጊዜ ነው።

ለሠርጊ ቀን የቀረው ስድስት ሳምንት ብቻ ነው። በድንግልና ስለ ቆየሁና የማገባት ልጃገረድም ድንግል መሆኗን ስለነገረችኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በጣም ደስተኛም ነኝ!

ብዙ ጊዜ ወንዶች ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሲናገሩ እሰማለሁ። የሚናገሩት ግን ብዙ ጊዜ አፀያፊ ቀልዶችና ኃጢአት የሞላባቸውን ታሪኮች ነው። በአንድ ወቅት ጥያቄ ስጠይቃቸው፦ «የጾታ ጉዳይ ትምህርት ከፈለግህ ልምድ ወደ አላት ጋለሞታ ሂድ» አሉኝ።

በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው ሊያደርገው የሚገባውን ነገር እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ። ባልና ሚስት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከመፈጸማቸው በፊትም ሆነ እየፈጸሙ ሳሉ ፍቅራቸውን እንዴት ሊገላለፁና ለተገቢ ስሜታዊ እርካታቸው ሊሠሩ ይችላሉ?

ላሳፍራችሁ እየሞከርኩ አይደለም። ነገር ግን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን አስደሳች ካላደረግሁላት ባለቤቴ ምን ታስብ ይሆን በማለት ስለምጨነቅ ነው። ስለዚህ በተለይ ወንድ ልጅ በሠርጉ ቀን ምሽት ምን ማድረግ እንዳለበት ጻፉልኝ።

በክርስቶስ የእናንተው

ሬይሞንድ

## በሠርጋችሁ ቀን ብቻ በመኝታ ቤታችሁ ለብቻችሁ ስትሆኑ

አንድ ድንግል ወንድና አንዲት ድንግል ሴት ከሠርጋቸው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በመኝታ ቤታቸው ብቻቸውን በሚሆኑበት ጊዜ የሚሰማቸውን ደስታና የሚፈጠረውን ችግር እንመልከት።

ወደ መኝታ ክፍላቸው በሚገቡበት ጊዜ ሲጠብቁት የነበረው ጊዜ በመድረሱ ልባቸው በታላቅ ደስታ ይሞላል። ከሠርጋቸው ቀን በፊት ብዙ ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ተፈትነዋል። ነገር ግን ለፍትወተ ሥጋ ፍላጎታቸው እምቢ በማለት የእግዚአብሔርን ሕግጋት መታዘዝ መረጡ። ይህን ቀን ሲጠባበቁ ነበር፤ አሁን ደረሰላቸው!

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከሠርጋቸው በኋላ በመጀመራቸው እግዚአብሔር ደስ እንደሚሰኝ ያውቃሉ። ቤተሰቦቻቸውም ይህንኑ አረጋግጠዋል። አእምሮአቸው ንጹሕ ስለሆነና ሕሊናቸው ስለማይከሳቸው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነቱ የላቀ ደስታ ይሰጣቸዋል።

በልባቸው ግን አንዳንድ ፍርሃቶች አሏቸው። ሴቲቱ ከባሏ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ብትፈልግም ያመኘ ይሆንን? ብላ ታስባለች።

ወንዱ ደግሞ «ላረካት ባልችልስ? እውነተኛ ወንድ መሆኔን ትጠረጥር ይሆንን?» በማለት ይጨነቃል።

በዚህ የመጀመሪያ ምሽት የሁለቱም ዓላማ የትዳር ጓደኛቸውን ፍርሃት ማስወገድ መሆን አለበት። አዲሱ ባል በአእምሮ ለሚስቱ *«እንዳያምሽ ለማድረግ በዝግታ እፈጽመዋለሁ። አንዳችን ለሌላችን መልካም አፍቃሪ መሆናችንን በመማር እጅግ ደስተኞች እንሆናለን።»*

የእርሷ ዝንባሌና የአእምሮ አሳቧ ደግሞ እንደሚከተለው መሆን አለበት። *«ዛሬ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ባልደርስ መጨነቅ የለብህም። አልወቅስህም ደግሞም አንድ ችግር እንዳለብህ አልቆጥርም። በፊታችን ባሉት ወራት አንዳችን ሌላችንን ማርካት እንማራለን።»*

እንደዚህ ዓይነት የፍቅር ዝንባሌዎች በሁለቱ በኩል ካለ ፍርሃታቸው ሁሉ ወዲያውኑ ይወገዳል። እርስ በርስ ለመነጋገር ነፃነት ያገኙና የሚሳዳንና ፍጹም ደስታን የሚያጎናጽፍ ነገራቸውን ሁሉ ይነጋገራሉ። ሁለት ድንግሎች ከሠርጋቸው በኋላ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሲጀምሩ እንዴት አስደሳች ነው!

ከጋብቻ በፊት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ወጣቶች ታሪክ ግን ፈጽሞ የተለየ ነው። ለምሳሌ ጆይስ የ16 ዓመት ልጅ እያለች የመጀመሪያውን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሳሙኤል ከተባለ ልጅ ጋር ፈጸመች። በፍቅር ጨዋታቸው ወቅት ስሕተት ከሠራ ለጓደኞቿ የማይረባ ፈዛዛ አፍቃሪ ነው ብላ እንዳትነግርበት ፈራ። ሁለቱ አላዋቂ እንዳይባሉ በመፍራት እንደ አዋቂ ለመሆን ሞከሩ። ከጥቂት የፍቅር ጨዋታ በኋላ ሳሙኤል ፈጥኖ ብልቱን ብልቷ ውስጥ አስገባና የዘር ፍሬውን አፈሰሰ። በቃ ይኸው ነበር...አጭር የስሜት መነቃቃትና ቀጥሎ የተመለከቱትን የመሳሰሉ ብዙ ፍርሃቶች፡—

ለማን ይነግርብኝ ይሆን?

ስለ እኔ ምን ብሎ ይናገር ይሆን?

አሁን ካረገዝኩ ምን አባቴ እሆናለሁ?

ሊወደኝ የሚችል አገኝ ይሆንን? ወይስ ይህ ልጅ እንዳደረገው ሁሉም ወንድ ገላዬን መጠቀሚያ ብቻ ያደርጉት ይሆን?

ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ምንም መልካም አይደለም። ሰዎች በፈጣሪያቸው ላይ ጀርባቸውን በማዞር እውነተኛ ደስታ ሊያገኙ አይችሉም።

ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸም እግዚአብሔርን የሚታዘዙ ወጣቶች ደስተኞች ናቸው! በሠርጋቸው ምሽት ልምድ የለኝም ብለው አይጨነቁም። ይልቁንም ሙሽራው፥ ሙሽሪት ምንም ዓይነት

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሞክራ የማታውቅ በመሆኗና ለሙሽሪትም ሙሽራው እንደ እርሷው በመሆኑ ሁለቱም ደስተኞች ይሆናሉ።

> ድንግል የሆነች ሙሽሪት እና በድንግልና የቆየው ሙሽራ ከማንም ሳይሆን አንዳቸው ከሌላቸው በመማር ፍጹም የተለየ፥ የተለየ፥ የተለየ ደስታን ይቀዳጃሉ።

## ለመጀመሪያው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መዘጋጀት

የተለያዩ ባሕሎች የተለያየ የሠርግ ልማድ አላቸው። በአንዳንድ አገሮች ሙሽሮች በሠርጋቸው የመጀመሪያ ምሽት ሳይነካኩ ያድራሉ። በአንዳንድ ባሕሎች ደግሞ በሠርጋቸው ምሽት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ አንዳችም ነገር ስለማይናገር ክርስቲያኖች የወደዱትን ሊከተሉ ነፃ ናቸው። የትኛውንም ባህል ይከተሉ ወዲያውኑ ወይም ጥቂት ቆይተው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸማቸው እርግጥ ነው። የመጀመሪያውን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንዴት መፈጸም እንደሚችሉ እንመልከት።

የሚከተለውን ዓይነት ጸሎት አብረው በመጸለይ እንዲጀምሩ እናሳስባለን «የተወደድከ እግዚአብሔር ሆይ፥ በጋብቻ ዘመናችን በሙሉ ልንታመንብህ፥ ልንታዘዝህና ከምትሰጠን ልጆቻችን ጋር ልናገለግልህ እንፈልጋለን። ለእኛና ኢየሱስን ለማመን ለመረጡ ሁሉ ስለሰጠኸው የዘላለም ሕይወት እናመሰግንሃለን።»

ከጸሎት በኋላ ኮስተር ማለታቸውን መቀጠል አያስፈልጋቸውም። በነጻነት መነጋገር፥ መቀለድና መሳሳቅ ጥሩ ነው። ስለ ምንም ሊጨነቁ አይገባም። ጥድፊያም አያስፈልግም። ዘና ሊሉና ሊደሰቱ የሚገባበት ምሽት ነው!

የመኝታ ቤታቸው በር መቆለፉን አንዳቸው ሊያረጋግጡ ይገባል። (በመካከል አንድ ሰው ሊገባ ይችላል የሚል ግምት ካላት ሴቲቷ በፍቅር ጨዋታ ወቅት ዘና ማለት አትችልም።)

አሁን አንዳቸው የሌላቸውን ልብስ የሚያወልቁበትንና እጅግ አስደሳች ከሆኑ ልምምዶች አንዱን ልምምድ ለማከናወን ይዘጋጃሉ። ድንግል ለሆኑ አዲስ ባልና ሚስት በአንድነት ብቻቸውን ሆነው አንዱ የሌላውን ልብስ የማውለቁ ልምምድ በጣም አስደሳች ስለሆነ በጥድፊያ መደረግ የለበትም።

ተቃቅፈው ከተሳሳሙ በኋላ አንዱ የሌላውን የመጀመሪያውን የውጪኛ ልብስ በየተራ ያውልቅ። እንደገና በተጨማሪ ከተሳሳሙ በኋላ ሙሉ ለሙሉ እርቃናቸውን እስኪሆኑ ድረስ አንዱ የሌላውን ልብስ ማውለቁን ይቀጥል።

ልብስ የማውለቁ ተግባር በጨለማ መፈጸም ያለበት ነገር አይደለም። ባልና ሚስት ስለሆኑ መተፋፈር ፈጽሞ የለባቸውም።

> «አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።» (ዘፍጥ. 2:25)

## የመጀመሪያው የፍቅር ጨዋታ

በገጽ 50 እንደ ተገለጸው የትዳር ጓደኛሞች የፍቅር ጨዋታን አንዱ የሌላውን የላይኛ የሰውነት ክፍል በመደባበስ ሊጀምሩ ይችላሉ።

ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ወደ ፍትወተ ሥጋ ብልቷ አካባቢ እጁን በመስደድ እንዲደባብሳት የምትፈልግበት ደረጃ ላይ እንደደረሰች ታሳውቀው። በሚዳብስበት ጊዜ ጫን ወይም ለዘብ እንዲያደርግላትና የትኛው ቦታ ላይ ቢያደርግላት እንደምትወድም ሊጠይቃት ይገባል። የፍትወት ስሜቷ እየተቀሰቀሰ እንዲሄድ የሚያደርግ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ሲፈጽም ስሜቷን ልትነግረው ይገባታል። ይህ በሚገባ ያበረታታዋል።

እንደዚህ ዓይነቱን ነገር ከሚስቱ መማሩ ያሳፍራልን? አያሳፍርም ይልቁኑ በጣም ውብ ነው!

ሚስቱ በሌላ ሰው እንዲለማመድ ትፈልጋለችን? በፍጹም! እርስ በርሳቸው መማማራቸው በጣም ግሩም ነገር ነው!

በገጽ 50 የፍቅር ጨዋታ ለ20 ደቂቃዎች መቀጠል አለበት ብለናል። ሆኖም ግን የመጀመሪያው የፍቅር ጨዋታ 30 ደቂቃ ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም ወጣት ሚስት ለብዙ ዓመታት በትዳር ከቆየች ሴት ይልቅ የረጅም ጊዜ የፍቅር ጨዋታ ያስፈልጋታል።

በመጨረሻ አዲሶቹ ባልና ሚስት እርሷ ለሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ዝግጁ የምትሆንበትን ጊዜ አብረው ይወስኑ። ሴቷ የፍትወት ስሜቷ ወደ ጫፍ አካባቢ መዳረሱን ለመገመት ትቸገር ይሆናል። እርሱም ውስጠኛው የብልቷ ከናፍርት በመጠን ጨምረው እንደሆነ ለማወቅ ሊያስቸግረው ይችላል።

ሮቤልና በርኒቄ በሠርጋቸው ምሽት በፍቅር ጨዋታ በቂ ጊዜ አላሳለፉም ነበር። የእርሷ የፍትወት ስሜት ጫፍ የደረሰ መስሎት ተገናኛት። እርሷ ግን ገና ነበረች። ውጤቱ ሮቤል ሚስቱ ጡዘተ-ፍትወት (ወደ ከፍተኛ የእርካታ ደረጃ) ላይ ሳትደርስ የዘር ፍሬውን በማፍሰሱ የጋለ ስሜቷ አሽቆለቆለ። ስለዚህ በዚያ ምሽት ከፍተኛውን የፍትወት እርካታ ስሜት ለማግኘት አልቻለችም። ግን ይህ ትልቅ ችግር አልነበረም። በልምምዱ ተደስተዋል፤ ተምረዋልና። ወንዱ ብልቱን ማስገባት ያለበት መቼ እንደሆነም ተምረዋል።

ፊልጶስና ሐና በሠርጋቸው ዕለት ምሽት ፊልጶስ ብልቱን ሳያስገባ በጣም ዘገየ። በብልቷ ዙሪያ በተለይ ናዝረ ብልቷን እያሻሸ ሳለ በድንገት ወደ ጡዘተ-ፍትወት ላይ ደረሰች፤ ጡዘተ-ፍትወቷ በጣም ከፍ እስኪል ድረስ ናዝረ ብልቷን ማሻሸቱን ቀጠለ። ከዚያም ብልቱን በማስገባት የዘር ፍሬውን አፈሰሰ።

በኋላ ፊልጶስ ሚስቱን፥ «ገና በብልትሽ ዙሪያ ሳሻሽ እንዴት ጡዘተ ፍትወት ላይ ደረስሽ? በብልትሽ ምንም ሳይኖር. . . እንዴት?» አላት።

እየተወያዩ ሳሉ የሴትን ከፍተኛ የፍትወት እርካታ የሚያመጣው ናዝረ ብልቷ እንጂ ብልቷ እንዳልሆነ ፊልጶስ ተረዳ።

## አትጨነቁ

በሠርጋችሁ ቀን ምሽት «በትክክል እንሠራ ይሆንን? በመጀመሪያው ምሽት አንዳችን ሌላችንን እናረካ ይሆንን?» በማለት አትጨነቁ።

ይልቅኑ ዘና በሉ። በሠርጋችሁ ቀን ምሽት ምንም ይሁን ምን ደስ ይበላችሁ። በፍጹም ውህደታችሁና አንዳችሁ ለሌላችሁ በምትሰጡት ደስታ ተመሰጡ። የሠርግ ቀን ምሽት ጅማሬ ብቻ መሆኑን አስታውሱ። በሕይወታችሁ ዘመን ሁሉ ደስታን መስጠትና መቀበልን የምትማሩበት ጅማሬ ነው። ወራት እየተቆጠሩ ሲሄዱ አንዳችሁ የሌላችሁን ስሜት እንዴት እንደምታነሣሡና አንዳችሁ ሌላችሁን እንዴት እንደምታረኩ ትማራላችሁ። ለአሥር ዓመታት በትዳር ከቆያችሁም በኋላ እንኳ አንዳችሁ ስለሌላችሁ ትማራላችሁ፥ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችሁም በተሻለ ሁኔታ እያደገ ይሄዳል!

ውድ ካሮል፥

እጮኛዬን እወደዋለሁ፥ ነገር ግን መጀመሪያ ስለምናደርገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳስብ እፈራለሁ። ሁሉም ሰው ሲናገር የምሰማው የመጀመሪያው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለሴት ልጅ ሕመም እንዳለውና እንድትደማ እንደሚያደርጋት ነው።

ሎይድ

ውድ ሎይድ

ከባለቤትሽ ጋር የምትፈጽሚውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፍራት የለብሽም።

ሁሉም ሴቶች ባይሆኑም እንኳ ብዙዎቹ ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በሚፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መድማታቸው እውነት ነው። ይህ ግን ከፍተኛ ችግር አይደለም።

ሴት ልጅ የምትደማው ክብረ ንጽሕናዋ በሚደፈርበት ጊዜ ነው። «ክብረ ንጽሕና» የምንለው በሴት ብልት መግቢያ ላይ ያለ ስስ የሥጋ ሽፋን ነው።

ሁሉም ልጃገረዶች አንድ ዓይነት አይደሉም። ልጃገረዶች ሊኖሯቸው የሚችሉት የክብረ ንጽሕና ዓይነቶች አራት ናቸው

*1) ስስ የክብረ ንጽሕና ሽፋን፡-* ብዙ ሴቶች በክብረ ንጽሕናቸው ሽፋን መካከል ላይ 2 ሴ.ሜ. ወረድ ያለ ቀዳዳ አላቸው። በመጀመሪያው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ይህ ስስ ሽፋን ሥጋ የወንድ ብልት በሚገፋው ጊዜ ይለጠጣል ወይም ይበጠሳል። ይህ ትንሽ ሕመምና መድማት ሊያስከትል ይችላል።



ስስ የክብረ ንጽሕና ሽፋን

*2) የክብረ ንጽሕና ሽፋን የሌላቸው፡-* አንዳንድ ልጃገረዶች፡- ያለዚህ ሽፋን ይወለዳሉ። ስለዚህ በመጀመሪያ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ሕመም ወይም ደም አይኖራቸውም።

*3) የተበጠሰ የክብረ ንጽሕና ሽፋን፡-* የአንዳንድ ልጃገረዶች የክብረ ንጽሕና ሽፋን ከጋብቻ በፊት ይበጠሳል። ስለዚህ በሠርጓ ቀን ማታ ሕመም ወይም መድማት አይኖራትም። የልጃገረድ የክብረ ንጽሕና ሽፋን በሁለት ምክንያት ይበጠሳል። አንዱ ምክንያት እንደ ስፖርት ባሉ እንቅስቃሴዎችና በወር አበባ ወቅት በብልት ውስጥ የሚደረጉ ነገሮችን በመጠቀም ሲሆን ሌላው መንገድ ከጋብቻ በፊት በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው።



የተበጠሰ የክብረ ንጽሕና ሽፋን

ባል *«ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ስንፈጽም ለምን አልደማሽም? ከማን ጋር ነው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረግሽው?»* በማለት በሚስቱ ላይ ሊፈርድ አይገባም።

ይልቁኑ ክብረ ንጽሕናዋ በስፖርት ወይም በወር አበባ ወቅት በብልት ውስጥ በሚደረግ ነገር ሊገሰስ እንደሚችል መረዳት አለበት። ወይም ያለክብረ ንጽሕና ሽፋን ልትወለድ ትችላለች።

*4) ወፍራም የክብረ ንጽሕና ሽፋን (ጭንጫ)፡-* 10% የሚያህሉ ጥቂት ሴቶች በጣም ወፍራም የክብረ ንጽሕና ሽፋን አላቸው። እንደዚሁ ዓይነት ወፍራም የክብረ ንጽሕና ሽፋን ያላቸው ሴቶች በሚያገቡበት ጊዜ ባላቸው ብልቱን ለማስገባት ፈጽሞ ይቸገር ይሆናል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለች ሴት ጣቶቿን በመጠቀም የክብረ ንጽሕናዋን ሽፋን



ወፍራም የክብረ ንጽሕና ሽፋን

ቀዳዳ ልታሰፋ መሞከር ትችላለች። እንደዚያም ሆኖ ልትለጥጠው ካቃታት ወደ ሆስፒታል በመሄድ በሕክምና ዘዴ ሊለጥጡላት ይችላሉ።

ሎይድ ለአንቺ የሚሆን ምክር በአጭሩ ቀጥለን እናቀርባለን። ከሠርግሽ ቀን ሁለት ወር ቀደም ብለሽ ወደ ሆስፒታል ለምርመራ ሂጂ። ነርሷ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች (የአባላዘር በሽታዎች) (ገጽ 153 ን ተመልከቺ) ምርመራ ስታደርግልሽ በዚያው የክብረ ንጽሕና ሽፋንሽን ጉዳይ ታረጋግጥልሻለች። ይህ የክብረ ንጽሕናሽ ሽፋን ወፍራም ሆኖ ካገኘችው እንዴት እንደሚለጠጥም ታሳይሻለች። ወፍራም የክብረ ንጽሕና ሽፋን ያላቸው ሴቶች ጥቂት ስለሆኑ ምናልባት የአንቺ ምንም ችግር የለውም ትልሽ ይሆናል። እናም በሠርግሽ ቀን ማታ ትንሽ ልትደሚና ጥቂት ሕመም ሊሰማሽ ይችላል። ነገር ግን አትጨነቂ፤ ምክንያቱም በባልሽ ከመወደድ ጋር ሲወዳደር ሕመሙ ጥቂት ነውና።

### አዲስ ባሎች ሊያውቁት የሚያስፈልግ ጉዳይ

ሚስትህ የሚለጠጥ ወይም የሚበጠስ የክብረ ንጽሕና ሽፋን ሊኖራት ስለሚችል በመጀመሪያው የግብረ ሥጋ ግንኙነታችሁ ወቅት ብልትህን በዝግታ አስገባ። ተፈጥሮአዊ ፍላጎትህ በፍጥነት እንድትገፋ ቢጠይቅህም እንኳ ምንም በማያሳምም ወይም ጥቂት ብቻ ሕመም ባለበት ሁኔታ ብትፈጽመው ለሚስትህ ያለህን ፍቅር ታሳያለህ። በዝግታ ለማስገባት የሰውነት ቅባት ማለስለሻዎችን ተጠቀም። ይህ በተለይ ለመጀመሪያው ምሽት በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ሴቲቱ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት የጋብቻ ቀናት የምታመነጨው የተፈጥሮ ማለስለሻ በጣም አነስተኛ ሊሆን ስለሚችል ነው።

## ግንኙነት (ብልት የማስገባት ሂደት)

በሠርጉ ቀን ምሽት ወንዱ ብልቱን ወደ ሴቷ ብልት ውስጥ ከማስገባቱ በፊት የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ እንዳለበት ተነጋግረናል፦

1) ረዘም ያለ የፍቅር ጨዋታ ሊኖር ይገባል።

2) በክብረ ንጽሕና ሥጋዋ ምክንያት ባልየው ብልቱን በሚያስገባበት ወቅት በዝግታ ላላ አድርጎ መሆን አለበት። ደግሞም ማለስለሻ ቅባት መጠቀም ይገባዋል።

አሁን ይህን የመጀመሪያ ግንኙነት አዲሶቹ የትዳር ጓደኞች እንዴት መፈጸም እንደሚችሉ እንመልከት።

የሚስት የፍትወት ስሜት በሚገባ ተነሣሥቶ ዝግጁ በምትሆንበት ጊዜ በቅባት የለሰለሰውን የባሏን ብልት በእጇ ወደ ብልቷ ታስገባለች። በዚህ ጊዜ የብልቱን የመጨረሻ ጫፍ መንካት የለባትም። ምክንያቱም ያ ክፍል በተለይ በደረቅ እጅ ሲነካ ያማል።

ባል ከሚገባው በላይ ብልቱን ወደ ውስጥ እንዳያስገባ መጠንቀቅ አለበት። ብዙ ሴቶች 10ሴ.ሜ. ያህል ብቻ ሲገባ ይመቻቸዋል። ሚስት የባሏ ብልት ከሚገባው በላይ በመጥለቁ ሕመም ከተሰማት 10 ሴ.ሜ. ያህል ብቻ ሲገባ የበለጠ እንደሚያስደስታት ልትነግረው ይገባል።

አንዳንድ ወንዶች ብልታችን ትንሽ ነው ብለው ይጨነቃሉ። ሆኖም ግን እውነቱ የሚስቱን ከፍተኛ የእርካታ ስሜት ወይም ጡዘተ ፍትወት ለማምጣት የባል ብልት ትልቅ መሆን የለበትም። ትንሽ ብልት ያለው ባል ሚስቱን ትልቅ ብልት ያለው ወንድ የሚያረካውን ያህል ማርካት ይችላል። ስለዚህ ትልቅ ብልት የተለየ ጥቅም የለውም።

አንዳንድ ጊዜ ሙሽራይቱ «የባለቤቴ ብልት ትልቅ ከሆነ ለብልቴ የሚስማማ አይሆንም» ብላ ትሰጋለች። እውነቱ ግን የሴቷ ብልት የወንዱን ብልት ምንም ያህል መጠን ይኑረው ለማስተናገድ በሚገባ ይለጠጣል። ስለዚህ ሚስት ስለዚያ መጨነቅ ፈጽሞ አያስፈልጋትም።

እንዲያውም በፍቅር ጨዋታ ወቅት ለሴቲቱ ስጋትን ማስወገድ ጠቃሚ ነው። ስጋት በብልት ዙሪያ ያለውን ጡንቻ ጭብጥ ስለሚያደርገው የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚያሳምም ያደርገዋል።

አንዲት ሴት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ሕመም ያለበት ሆኖ ካገኘችው ለባሏ ትንገረው፤ እርሱም በጣም የለሰለሰ ያድርገው። አሁንም ሕመም የሚሰማት ከሆነ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ያስተላልፉት።

ወንዶች ሆይ ስሙ፥ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለሚስቶቻችሁ የሚያሳምማቸው ከሆነ «ለዛሬ አንፈጽም፥ ልቆይ እችላለሁ፥ በሌላ ቀን እንደገና እንሞክራለን» በሉአቸው።

ይህንን በምትሉበት ጊዜ እውነተኛ *ፍቅራችሁን* ማሳየታችሁ ነው። *«ፍቅር»* ማለት ምን ማለት ነው? ከራስ ፍላጎት ይልቅ ለሚስትህ ፍላጎት የበለጠ አትኩሮት መስጠት ማለት ነው።

## ከግንኙነት በኋላ

ባል ወደ ሚስቱ ከገባ በኋላ ሚስቱ ሕመም ከሌላት የሚቀጥለው እርምጃ፥ እርሱ ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት ወይም ጡዘተ ፍትወት ከመድረሱ በፊት እርሷ እንድትደርስ ተረዳድተው የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ነው። ይህ ማለት የእርሷን ስሜት የበለጠ ማነሣሣት እና የእርሱ እንዲቀንስ ማድረግ ነው።

ባል የፍትወት ስሜት መነሣሣቱን ለመቀነስ ብልቱን ካስገባ በኋላ ለአንድ ደቂቃ የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴውን ማቆም አለበት። በዚያ ጊዜ የእርሷን ስሜት ከፍ ለማድረግ በሦስት መንገዶች መጠቀም ይችላሉ። 1) የእርሱ ብልት የብልቷን ግድግዳዎች እንዲጫን ዳሌዋን ማሽከርከር ትችላለች። 2) ናዝረ ብልቷን በጣቶቹ ሊያሻሽላት ይችላል። 3)

ብልቱን በፒሲ ጡንቻዎቻ ጨመቅ ጨመቅ ማድረግ ትችላለች (የፒሲ ጡንቻ የሴቷ ብልት ጡንቻዎቿ ናቸው። ገጽ– ተመልከት)።

ከዚህ አንድ ደቂቃ በኋላ የእርሱ የስሜት መነሣሣት ዝቅ ብሎ የእርሷ ስሜት ከፍ ሊል ይገባል። ይህ እርሷ ወደ ከፍተኛ የእርካታ ስሜት ወይም ጡዘተ ፍትወት በፍጥነት እንድትደርስ ስለሚረዳት መልካም ነው።

ባል የማስገባትና የማስወጣት እንቅስቃሴውን ሲጀምር ሚስት የፒሲ ጡንቻዎቿን ለመጠቀም ትፈልግ ይሆናል። ባል ብልቱን በሚያስወጣበት ጊዜ የፒሲ ጡንቻዎቿን ጨመቅ ታደርጋለች፥ ብልቱን በሚያስገባበት ጊዜ ደግሞ ጡንቻዎቿን ለቀቅ ታደርጋለች። አንዳንድ ሚስቶች ይህ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት እንዲደርሱ እንደሚረዳቸው ይናገራሉ።

ሚስት ጡዘተ ፍትወት ወይም ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ላይ ስትደርስ ለባሏ ልትነግረው ይገባታል። ምክንያቱም ይህ የራሱን ስሜት አቀዝቅዞ የመቆየት ጥረቱን እንዲያቆም ይረዳዋል። ይህ ከሆነ እርሷ ጡዘተ ፍትወት ውስጥ እያለች ወይም ደርሳ ብዙ ሳትቀዘቅዝ የዘር ፍሬውን ያፈሳል። ከዚያም ሁለቱም እርካታቸውን እንዳገኙ አብረው ዘና ሊሉ ወይም ሊያርፉ ይችላሉ።

ሆኖም ግን የትዳር ጓደኛሞች አብረው በሆኑበት የመጀመሪያ ምሽት ሁሉም ነገር ከላይ በጠቀስነው መንገድ ላይሄድ ይችላል። በዚህ ምትክ ከሚከተሉት ሦስት ውጤቶች አንዱ ሊፈጸም ይችላል።

ሀ) ባል በፍቅር ጨዋታ ወቅት ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ይቀዳጃል።

አንዳንድ ጊዜ ባል ሚስቱ በፍቅር ጨዋታ ወቅት እየዳበሰችው ሳለ በድንገት የዘር ፈሳሹን ያፈሳል። ይህ ኃጢአትም ትልቅ ችግርም አይደለም።

በሚቀጥለው የፍቅር ጨዋታ ጊዜ ቀድሞ የዘር ፍሬውን እንዳያፈስ ለሚስቱ እንዲህ በማለት ይንገራት፡– «ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ቀርቤአለሁና ለጥቂት ደቂቃዎች መደባበስሽን አቁሚ»። ከእነዚያ ደቂቃዎች በኋላ አረፍት እፈልጋለሁ ብሎ እስኪነግራት ድረስ መደባበሱን ልትቀጥል ትችላለች።

ይህንኑ የመደባበስ. . .ማረፍ. . . የመደባበስ... ማረፍ ሁደት (ድግግሞሽ) ለረጅም ጊዜያት መደጋገም ጥሩ ነው። ባል ከግንኙነት በኋላ እጅግ አስደሳች የሆነ የዘር ማፍሰስ ሂደት እንዲፈጽም ያደርገዋል። በተጨማሪ ግንኙነት ከጀመረ በኋላ በፍጥነት የዘር ፍሬውን እንዳያፈስም ይረዳዋል።

ለ) ሚስት በፍቅር ጨዋታ ወቅት ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ላይ ልትደርስ ትችላለች።

አንዳንድ ጊዜ ሚስት ወዳልታቀደ የከፍተኛ ፍትወት እርካታ ላይ ልትደርስ ትችላለች። ይህም ባል ብልቱን ከማስገባቱ በፊት ናዝረ ብልቷን በጣቶቹ በሚያሻሽበት ወቅት ይሆናል። ይህም የሚያስጨንቅ አይደለም።

እንዲያውም እጅግ ሊደሰቱበት ይችላሉ። በሚቀጥለው ጊዜ ግን ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ከግንኙነት በኋላ እንድትደርስ ቶሎ ብልቱን ማስገባት አለበት። ይህም ደግሞ የበለጠ እርካታን ያጎናጽፋል።

ሐ) ባል ብልቱን በሚያስገባበት ወቅት ጡዘተ–ፍትወት ላይ ሊደርስ ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ባል ብልቱን በሚያስገባበት ጊዜ በድንገት የዘር ፍሬውን ያፈሳል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ማቆም ይፈልጋል። ከዚያ በኋላ የትኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ቢሞክር የሚያም ይሆናል። ለሚስቱ የዘር ፈሳሹን ያፈሰሰ መሆኑን በመግለጽ የዳሌዋን እንቅስቃሴ እንድታቆም መንገር አለበት። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ከመቀጠላቸው በፊት ቢያንስ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ማረፍ አለበት።

ችግሩ ግን በእነዚያ ደቂቃዎች የተነሣሣው የሚስት ስሜት ይበርድ ይሆናል። ነገር ግን ባል የሚስቱ ስሜት እንደተነቃቃ እንዲቆይ ሊረዳት ይችላል። ብልቱን በብልቷ ውስጥ እንዳለ እንዲቆይ በማድረግ ናዝሬ ብልቷን በጣቶቹ ሊያሻሽላት ይችላል። ይህም ብልቱን ማስገባት ማስወጣት ከመጀመሩ በፊት የተነቃቃ የሚስቱ ስሜት እንዳያሽቆለቁል ይረዳል። በዚህ መንገድ ምናልባት እርሷ የመጀመሪያውን ጡዘተ ፍትወት እርሱም ሁለተኛውን ሊያገኙ ይችላሉ።

ባወቅን ቁጥር ደስታችን ይጨምራል

በመጀመሪያ ምሽት አንድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ከፍተኛ የፍትወት እርካታን የመስጠቱ ጉዳይ ለብዙዎቹ ላይሳካላቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ባል ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ይደርሳል፤ ሚስት ግን አትደርስም። እንዲያውም 90% የሚሆኑ ደናግል ሙሽሮች በሠርጋቸው ቀን ምሽት <u>ጡዘተ ፍትወት</u> ላይ አይደርሱም።

ስለዚህ ሚስት በመጀመሪያው ምሽት ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት ባትደርስ ባልም ሆኑ ሚስት «እንግዲህ በሰውነታችን አንድ ችግር ይኖረን ይሆናል» ብለው ማሰብ የለባቸውም። ባል እውነተኛ ወንድ ለመሆኑ መጠራጠር የለበትም። ሚስትም «ለፍትወት የሚያነሣሣ ስሜት ስለሌለኝ እንግዲህ ጥሩ ሚስት መሆን ፈጽሞ አልችልም» በማለት ማሰብ የለባትም። በዚያ ምትክ አንዳቸው ለሌላቸው፡–

የምንማረው ብዙ ነገር አለ፥

በምንማራቸው ነገሮችም እንደሰትባቸዋለን? በማለት ይገባቸዋል።

በግልጽነት ከተነጋገራችሁ ፈጥናችሁ ትማራላችሁ

መማር ሁሌም ጊዜ የሚጠይቅ ነው። በአንድ ቀን መራመድ መቻልን የተማረ ሕፃን የለም። በመጀመሪያው ምሽት ፍጹም የተሳካ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙ ባለትዳሮች የሉም። አንዱ ሌላውን ማርካትን መማር

ሳምንታት (ወይም ወራት) ይወስዳል። ስለዚህ በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ዕድሜ ሳምንታት ያሉት የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች በጣም አርኪ ያልሆኑላቸው ባለትዳሮች ተስፋ መቁረጥ አይገባቸውም። በመጠኑ ጊዜ ሊወስድ ይችላል!

አንዳንድ ባለትዳሮች ከሌሎች ፈጥነው መማራቸው እውነት ነው። ፈጥነው የሚማሩት ባለትዳሮች የትኞቹ ናቸው? *በግልጽነት የሚነጋገሩት* ናቸው!

ለምሳሌ አዊንና ዶሪስ እያንዳንዳቸው *«ከትዳር ጓደኛዬ መማር አለብኝ። ስለ ጉድለቴና ፍላጎቴ እንዲማር (እንድትማር) የትዳር ጓደኛዬን መርዳት አለብኝ። እንደ ባልና ሚስት እርስ በርስ በግልጽነት መነጋገር አለብን»* የሚል ዝንባሌ ስለነበራቸው ፈጥነው ተማሩ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፊኒዮስና ሚልድሬድ ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ ተነጋግረው ፈጽሞ አያውቁም። በመሆኑም አንዱ ሌላውን ማርካትን አልተማሩም። ፊኒዮስ ለራሱ እንዲህ ይላል፦ «እኔ ወንድ ነኝ ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ»። ሚስቱን እንዴት መደባበስና መተሻሸት እንደምትፈልግ ጠይቆአት አያውቅም። ሚልድሬድም ናዝሬ ብልቷ የት እንደሚገኝ ወይም እንዴት መተሻሸት እንደምትፈልግ ነግራው አታውቅም። «ጥሩ ክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነት ነገር አይነጋገሩም» የሚል እምነት ነበራት።

እውነታው ግን ባልና ሚስት ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመነጋገር ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው። መነጋገር የመማር ሂደትን ያራምዳል!

በመጨረሻ ከእግዚአብሔር ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ችግሮችን ጨምሮ ማንኛውንም ችግር በተመለከተ ልትነጋገሩ እንደምትችሉ አትርሱ! እርዳታውን ጠይቁ!

በቅርብ ጊዜ የብዙ የተለያዩ አገሮች ነዋሪ ባለትዳሮችን የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቅን፦

*«የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን የላቀ ደስታ የሚገኝበት እንዲሆን የትዳር ጓደኛህ ምን ማድረግ ይችላል?»*

የተሰጡት መልሶች የሚከተሉት ናቸው፦

ባሎች እንዲህ ብለዋል፦ ባለቤቴ የሚከተሉትን ብታደርግ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የላቀ ደስታ አገኝበታለሁ።

* ጥሩ ክርስቲያን ሴቶች በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መደሰት አያስፈልጋቸውም የሚለውን አስተሳሰቧን ብታቆም።
* ተነቃቅታ እየተነቃነቀች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን አስደሳች ለማድረግ በተለያየ አቅጣጫ ብትሞክር።
* ሙሉ በሙሉ ልብሷን ብታወልቅ ወይም ስስ የሆነና ለፍትወት የሚጋብዝ የሌሊት ልብስ ቢጃማ ብትለብስ።

* የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንድናደርግ ብትጠይቀኝ (ሁል ጊዜ እኔ ከምጠይቃት)።

* የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በመከልከል ወይም በተከፈለ ልብ በመፈጸም ባትቀጣኝ።

* በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ብታናግረኝ ምን እንደሚያስደስታትም እንዳውቅ ብታደርገኝ።

ሚስቶች እንዲህ ብለዋል፡- ባለቤቴ የሚከተሉትን ነገሮች ቢያደርግ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የላቀ ደስታን ማግኘት እችላለሁ።

* ከእርሱ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ጨምሮ ማንኛውንም ነገር በግልጽነት ለመነጋገር እንድችል ጓደኛ ቢያደርገኝ።

* እንደሚወደኝ በአልጋ ላይ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ቢነግረኝ።

* ሁለታችን ብቻ በአንድ ላይ የምንጸልይበትን ጊዜ በየቀኑ ቢያመቻች።

* እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ጓደኛ ቢንከባከበኝ።

* በፍቅር ጨዋታ ወቅት ምን ባደርግለት እንደሚወድ ቢነግረኝ።

* በፍቅር ጨዋታ ወቅት ሊስመኝ፥ ናዝሬ ብልቴን ሊዳብሰልኝና ሊያሻሽልኝ ጊዜ ቢሰጥ።

* የወንድ ዘር ፈሳሹን ቶሎ እንዳያፈስ ቢሞክር።

* ከመኝታ ሰዓት በፊት ቀኑን ሙሉ ደግ ቢሆንልኝ።

* አሳቦችንና ስሜቶቻችንን በሙሉ ለመወያየት እንድንችል ከእኔ ጋር መነጋገር የሚያስደስተው ቢሆን።

* ለልጆቻችን ያለው መልካም አባትነት እጅግ ቢጨምር።

* አልኮል መጠጣት ቢያቆም (ጠጥቶ ሲመጣ ከእርሱ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አልወድም)።

* ከእኔ በስተቀር ከማንም ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽም ባይሆን።

# ደብዳቤዎች
# እና
# መልሶቻቸው

ዮሴፍ፡-ዕድሜዬ 24 ዓመት የሆነ ወንደላጤ ነኝ። በቅርቡ ባገባች አንዲት ሴት ፍቅር ተነድፌያለሁ። የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል ከመሆናችን ሌላ ሦስት ሰው ባለበት የመዘምራን ጓድ ውስጥ አብረን እንዘምራለን። ብዙ ጊዜ ከአእምሮዬ ላወጣት ብሞክርም ፈጽሞ አልቻልኩም። ባየኋት ቁጥር ፍስስ እላለሁ።

ትናንትና «ስለ እርሷ ምን እንደሚሰማኝ ብነግራት ከዚያ በኋላ ልረሳት እችላለሁ» ብዬ አሰብኩና ወደ ቤቷ ሄድኩ። የሚሰማኝን ጉዳይ እየነገርኳት ሳለሁ ከቁጥጥር ውጭ ሆኜ አቅፌ እስማት ጀመርሁ። እርሷም የበለጠ በጥልቀት እየሳመችኝ ምላሿን ሰጠችኝ። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ግን አልፈጸምንም።

ዛሬ ደግሞ «ትላንትና ስለሳምኩሽ የማይገባ ነገር አድርጌብሻለሁና ይቅርታ አድርጊልኝ?» እላታለሁ በማለት ወደ ቤቷ ሄድኩ። ነገር ግን እንደገና ከንፈር ለከንፈር ስንግጠጥና የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ስሜታችንን የሚያነሣሣ መደባበሶች ስናደርግ ቆየን።

እርሷን ከማፍቀር እንዴት ልገታ እችላለሁ? ያለኝ ዕቅድ አንድ ጊዜ ብቻ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብናደርግ ለእካሷ ያደረብኝ ጥማት ይበርድልኝና ሁሉ ነገር ይቀር ይሆናል እያልኩ እያሰብኩ አለሁ።

ውድ ዮሴፍ፥

አሁን እያሰብክ ባለህበት መንገድ ብትቀጥል ከባለቤቷ፥ ከቤተክርስቲያንህና ከፈጣሪህ ጋር ከባድ ችግር ላይ ትወድቃለህ።

ከእርሷ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አትፈጽም። እንዲያውም አጠገቧ አትድረስ። እግዚአብሔር ከክፉ የወጣትነት ምኞት እንድንሸሽ አዝዞናል። (2ኛ. ጢሞ. 2፡22 ተመልከት።)

ዮሴፍ፥ አንተ ግን እየሸሸህ አይደለህም። ፈተናው እጅግ ጠንካራ ወደሆነበት ወደ ቤቷ እየሄድክ ነው።

አድምጥ ዮሴፍ ዛሬ መሸሽ ጀምር! ከዚህ በኋላ ወደ ቤቷ ፈጽሞ አትሂድ። ከእርሷ ጋር ብቻችሁን ልትሆኑ የምትችሉበት ሁኔታ ውስጥ እራስህን አትክተት። ከእርሷ ጋር በመዘመር የምትሰጠውን አገልግሎት አቁም።

እነዚህን ጠንካራ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚከተለውን ስለተናገረ ነው፡-

«በጉያው እሳትን የሚታቀፍ፥

ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው?

...ወደ ሰው ሚስት የሚገባም እንዲሁ ነው፤

የሚነካትም ሁሉ ሳይቀጣ አይቀርም።» (ምሳ. 6:27፥29)

«ከክፉ የጕልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ» (2ኛ ጢሞ. 2:22)

ዮሴፍ፥ ከደብዳቤህ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደምትሄድ ተገንዝበናል። ነገር ግን እውነተኛ ክርስቲያን ስለመሆንህ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመላለስ ሰው ብቻ ስለመሆንህ በአእምሮአችን ጥያቄ ተፈጥሮብናል። ክርስቶስን የግል አዳኝህና ጌታህ አድርገህ ተቀብለሃልን? እስካሁን ይህን ውሳኔ ካላደረግህ ዛሬ ይህን ልታደርግ ትችላለህ።

አሁኑኑ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገር። ኃጢአቶችህን ተናዘዝ። ክርስቶስ በአንተ ምትክ መከራን እንደተቀበለልህ እመን። ወደ ሕይወትህ ጋብዘው...

ማስታወሻ፦ ለጆ እንዴት ክርስቲያን መሆን እንደሚችል የሚገልጽ ረዘም ያለ ደብዳቤ ጽፈንለታል። የዚህን መጽሐፍ ገጽ – ተመልከት)

ኤውጂን፦–ሚስቱ በማመንዘሯ ምክንያት የወንድሜ ትዳር እየፈረሰ ነው። በዚህ ምክንያት ትዳር መመሥረት አፈራለሁ። የተመሰቃቀለ ትዳር ከሚኖረኝ ብቻዬን መኖር እመርጣለሁ። ሰዎች የሚያመነዝሩት ለምንድን ነው? ሴቶች የሚያመነዝሩበት ምክንያት ከወንዶቹ ጋር አንድ ነው ወይስ እነርሱ የተለየ ምክንያት አላቸው?

ዝሙትን እንዴት መከካለከል እንደሚቻል መጠየቅም እፈልጋለሁ።

ውድ ኤውጂን፥

የመጀመሪያውን ጥያቄህን ለመመለስ ለዝሙት የተለመዱትን አራት ምክንያቶች ቀጥለን እናቀርባለን።

1) አዲስ የመፈቀር ስሜት፦ ሴቷ እንዲህ በማለት እራሷን መጠየቅ ትጀምር ይሆናል «ባለቤቴ አሁንም ይወደኛል? ከብዙ ጊዜ በፊት ፍቅርን ያሳየኝ ነበር። በዚያን ጊዜ ምንኛ ደስተኛ ነበርኩ! አስደናቂ የሆነ ስሜት ይሰማኝ ነበር...ያኔ ድሮ። ያ ስሜት አሁንም ቢኖረኝ መልካም ነበር።»

ከዚያም በጉርብትና የሚኖር ሌላ ወንድ በእርሷ ላይ ያለውን ፍላጎት ማሳየት ይጀምራል። ወዲያው እንደገና እንደተወደደች ይሰማታል። ያ አስደናቂ የሆነው የቀድሞ ስሜቷ ወደ ልቧ ይመለስላታል። ይህን ስሜት የመለሰላትን ሰው በፍትወተ ሥጋ ለማርካት ትፈተናለች።

2) አዲስ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት፦ ብዙ ሴቶች የሚፈተኑት «በአዲስ የመፈቀር ስሜት»፥ ብዙ ወንዶች የሚፈተኑት ደግሞ «በአዲስ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት» ነው። ብዙ ወንዶች እንደዚህ ብለው ያስባሉ «ከሌላ ሴት

ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አስደሳች አይደለምን!» ክርስቲያን ወንዶች እንኳ ሌላ አዲስ ሴት የመሞከር ፈተና አለባቸው።

3) አድናቆት፡- ባለትዳር የሆነ ሰው (ወንድም ሆኑ ሴቶች) *«የሚያዳምጣቸውን... አስተሳሰባቸውን ወይም አመለካከታቸውን የሚጋሩአቸውን፥ ጎበዝ የምታምርና አስደሳች ነህ/ነሽ»* የሚላቸው ሰው ሲያጋጥማቸው ሊፈተኑ ይችላሉ።

ሁላችንም እንደዚህ ዓይነቱን አድናቆት እንፈልጋለን። እንዲያውም ሰው አድናቆትን ከፍትወተ ሥጋ ፍላጎት በላይ ሊሻው ይችላል። የሌላ ሴትን ባል በሚጣፍጥ ንግግራቸው የሚያማልሉ ሴቶች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም።

ለራሳቸው ሚስት አንዳችም አድናቆት ሳይኖራቸው ሌሎች ሴቶችን በማድነቅ የተዋጣላቸው ወንዶች መኖራቸውም እርግጥ ነው። ይህን ሲያደርጉ ከእነርሱ ጋር ዝሙት ለመፈጸም ተስፋ በማድረግ ነው።

4) ዘመናዊ ዝንባሌዎች፡- ብዙ ፊልሞች፥ መጽሔቶች፥ ጋዜጦችና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች *«የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከሚስትህ (ወይም ከባልሽ) ጋር ብቻ መፈጸም ለምን ያስፈልጋል? ከሌላ አዲስ ሰው ጋር ደግሞ ሞክሩ። ማንም የሚያደርገው ነው!»* ይላሉ። እነዚህ ዘመናዊ ዝንባሌዎች የብዙ ባሎችና ሚስቶችን ታማኝነት ይፈታተናሉ።

ኤውጂን፥ ለዝሙት ታዋቂ ምክንያቶች ከላይ የተጠቀሱት አራቱ መሆናቸውን ልብ በል።

ሌላው ጥያቄህ ዝሙትን እንዴት መከላከል ይቻላል? የሚል ነው። መልሱ ባሎችም ሆኑ ሚስቶች ከላይ ከተጠቀሱት አራት ምክንያቶች መጠበቅ አለባቸው የሚል ነው። ይህም ማለት፡-

1) ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ! ሚስቶቻችሁን በሚገነቡ ቃሎችና በመልካም ተግባራት ያለማቋረጥ ፍቅርን ልታሳዩአቸው ከተጠነቀቃችሁ ሚስቶቻችሁ አዲስ የመፈቀር ስሜትን አይራቡም።

2) ሚስቶች ሆይ፥ በጋብቻችሁ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎትን የማርካት ልምምድን አስደሳች አድርጉት። በተከፈለ ልብ የሚፈጸም ተግባር አታድርጉት። ባሎቻችሁ ሌላ አዲስ የፍትወተ ሥጋ ልምምድ የማድረግ ጠንካራ ፈተና ውስጥ እንዳይገቡ በጋብቻችሁ ውስጥ የሚፈጸመውን ይህን ልምምድ እጅግ አስደሳች አድርጉት። በቤቱ የመርሴዲስ መኪና ያለው ሰው ብስክሌት የመስረቅ ጠንካራ ፈተና ሊገጥመው አይችልም!

3) ለትዳር ጓደኞቻችሁ አድናቆታችሁን አሳዩ። ስለ እነርሱም በአድናቆት ተናገሩ። ይህን ካላደረጋችሁ በዚህ ፊንታ ክፉ ጠባሳ በሚያስቀር መንገድ የትዳር ጓደኞቻችሁን በማሳረፍ የምትደሰቱ ከሆነ ወደ ዝሙት ክፉ እጆች ገፈታትራችሁ ታስገቧቸዋላችሁ።

4) በፊልሞች፥ በመጽሔቶችና በጋዜጦች የሚቀርቡትን የዓለም «ዘመናዊ ዝንባሌዎች» ከመከተል ተቆጠቡ። ምንም ይሁን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ወስኑ።

ስማ፥ ኤውጂን ትዳር ለመመሥረት መፍራት የለብህም። ወደ እውነተኛዋ ክርስቲያን እህት እግዚአብሔር እንደሚመራህ እመን። በጋብቻችሁ በዓል ቀን እርስ በርስ ለመዋደድና የፍትወተ ሥጋ ልምምድንም በጋብቻ ውስጥ ብቻ በመፈጸም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቃል ኪዳን ግቡ።

ራሔል፡— ክርስቲያን ባል ፈተናዎችን ተቋቁሞ ማሸነፍ አይችልምን?

ባለፈው ዓመት ሙያው መምህር የሆነው ውድ ባለቤቴ ከመኖሪያችን ራቅ ብሎ ወደሚገኝ ትምህርት ቤት ተቀየረ። ወደ ቤቱ መምጣት የሚችለው በወር አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አሁን ትምህርት ቤቱ ባለበት አብረን እንድንኖር ጠየቀኝ። ችግሩ አሁን በአለሁበት ስፍራ በጣም ጥሩ ሥራ አለኝ። ትምህርት ቤቱ ወደሚገኝበት ስፍራ ብሄድ ምን ዓይነት ሥራ እንደሚያጋጥመኝ አላውቅም።

ብሩስና ካሮል ዓለማዊ የሆኑ ባሎች ከሚስቶቻቸው በሚለዩበት ወቅት ወደ ሌሎች ሴቶች እንደሚሄዱ አውቃለሁ። ባለቤቴ ግን ክርስቲያን ነው። መንፈስ ቅዱስ ፈተናዎችን የማሸነፍ ኃይል እንደሚያቀዳጅ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርምን?

ውድ ራሔል፥

ዝሙት ጠንካራ ፈተና ስለሆነ ባልና ሚስት አንዱ ሌላውን በፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ማርካት እንዳለበትም እኮ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (1ኛ ቆሮ. 7:5)።

ስለዚህ ክርስቲያን ባልና ሚስት ከአቅም በላይ የሆነ በቂ ምክንያት ከሌላቸው በስተቀር ለረጅም ጊዜ ተለያይተው መቆየት የለባቸውም።

ባለቤትሽ በሥራው ቦታ አብራችሁ እንድትኖሩ ባቀረበው አሳብ እኛም እንስማማለን። እግዚአብሔር ባለቤትሽ ባለበት ስፍራ ሥራ እንዲሰጥሽ ጸልዩ። እግዚአብሔር ሥራ ካልሰጠሽ በባለቤትሽ ደመወዝ መኖርን እወቂበት። የትኛው ይሻላል፡—

ብዙ ገንዘብና ዝሙት ያለበት ቤት ወይስ

ጥቂት ገንዘብ ኖሮ ከዝሙት የጸዳ ቤት?

«...አንዱ የሌላውን የጋብቻ መብት አይከልክል።» (1ኛ ቆሮ. 7:5፤ ከ1980 ዓ.ም. ትርጉም የተወሰደ)

መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤

ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።

አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥

ያላችሁም ይበቃችሁ፤

እርሱ ራሱ፦

አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና...»

(ዕብ. 13፡4–5 ተመልከት።)

ዳዊት፦ ባለሁበት ሕንፃ ከቤቴ በላይ ባለው ፎቅ የሚኖር አንድ ሰው ባለፈው ወር ሚስቱንና ልጆቹን አባሮ የሴት ጓደኛውን (የከንፈር ወዳጁን) አገባ። እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት ሲፈጽም ይህ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ጎረቤቶቻችን ነገሩኝ። ይህ ለሦስተኛ ጊዜ የፈጸመው ፍች ነበር።

እኔና ባለቤቴ ሁለት በአሥራዎቹ (በጉርምስና) የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ልጆች አሉን። በዚህ ሰው እጅግ የከፉ ባሕርይ ተጽዕኖ እንዳይኖርባቸው እንፈራለን።

ውድ ዳዊት፥

መጨነቅ አያስፈልግም። ከዚህ ሰው የከፉ ባሕርይ ልጆች የሚማሩት ነገር አላቸው።

ያለማቋረጥ ሲያዋራት፥ አብሯት ሲጫወትና ሲሳሳቅ በመጀመሪያ ልጆችህ ባገባት አዲሷ ሚስቱ ደስተኛ የሆነ ይመስላቸዋል።

እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት ግን ለረጅም ጊዜ አይቆይም።

ወራት ሲያልፉ ስሕተቶቿን ማየት ይጀምራል። እናም ይጣላሉ። ምናልባትም ይቅርታ አድርጎላት ሊቀበላት አይፈቅድም ይሆናል። (ከዚህ ቀደም የነበሩትን ሚስቶቹን እንዳልተቀበላቸውና ይቅርታ እንዳላደረገላቸው ሁሉ።)

የሕይወት ውጣ ውረድና ጣጣም ይቀጥላል። የመኪናዋ ማስቸገር፥ የሥራ ቦታ ችግር፥ የገንዘብ ችግር፥ ወዘተ...። ብዙም ሳይቆይ *ጀመርኩኝ ብዬ ያሰብኩት አስደሳች ሕይወት ምን ነካው?* በማለት እራሱን መጠየቅ ይጀምራል።

ቀጥሎ ምን ያደርጋል? ሌላ አዲስ ሴት መፈለግ ይጀምራል። በፍጹም ራስ ወዳድነት ለራሱ እየተጠነቀቀ ከራሷ አስበልጣ ልዩ እንክብካቤ የምታደርግለትን ሴት ይፈልጋል። እርሱ በምንም ዓይነት መንገድ ይያዛት ሁልጊዜ በፍትወተ ሥጋ ፍላጎቱ ፍጹም እርካታ የምትሰጠውን ሴት ይፈልጋል።

ብዚህ መንገድ የተለያዩ ሴቶችን ሲቀያይር እጅግ የተጎዱ መራሮች የሆኑ ብዙ ፈት ሴቶችን ያፈራል። ምንም እንኳ የአባታቸውን ፍቅር ቢራቡም ፈጽሞ የማያገኙ ልጆችንም ያፈራ ይሆናል። በአጭሩ ክርስቶስን ማግኘት ያስፈልገዋል! አንተ ዳዊት ስለ ክርስቶስ ልትመሰክርለት የምትችልባቸውን

መንገዶች መፈለግ አለብህ። ንስሐ ከገባ በጣም ግሩም ነው። ንስሐ ለመግባት ሳይፈቅድ ከቀረ ግን ቢያንስ ልጆችህ የሚከተለውን ይማራሉ፦

**በኃጢአት የሚኖር ሰው ዘላቂ ደስታ ሊያገኝ ፈጽሞ አይችልም። ይልቁኑ በቤተሰቡ ላይ ብዙ ኃዘን ያመጣል።**

ጁሊያ፦ ብሩስና ካሮል፥ መጽሐፎቻችሁ በእርግጥ ታላቅ በረከት ሆነውልኛል። እግዚአብሔር ትዳሬን እንዴት እንደታደገው ልመሰክርላችሁ ይገባኛል።

ከሁለት ዓመት በፊት ነው፥ አንድ ቀን ወደ ቤቴ ስመጣ ባለቤቴ ከአንዲት ሴት ጋር ተኝቶ ደረስሁበት። እንዲህ ዓይነት ቅሌት ውስጥ ይገባል ብዬ ገምቼም አላውቅም! ኋላም እንደሚወደኝ፥ ነገር ግን ያቺንም ሴት እንደሚወዳት ነገረኝ።

እንባዬን ለመቆጣጠር አልቻልኩም! በእርሱም ሆነ በሴቲቱ ላይ እጅግ በምሬት ተቆጣሁ። ቀጥሎም የንዴቴ አቅጣጫ ተቀየረና በራሴ ላይ ተቆጣሁ። እራሴን ጠላሁ። እንዲህ በማለት አሰብኩ። «ጥፋቱ የራሴ ነው! እጅግ ከፉ ሚስት ሆኜበታለሁ። የሚገባኝን ያህል በፍትወት ስሜት የማረካ ሆኜ አልተገኘሁም፥ ባለቤቴንም በሚገባ አልተንከባከብኩም።»

ስለዚህ እራሴን ለወጥኩ። ደስተኛ አደርገው ዘንድ የምችለውን ጥረት ሁሉ ፈጸምሁ። ይህም ሆኖ ከልጅቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ቀጠለ።

ምን ማድረግ እንደሚገባኝ በየዕለቱ እግዚአብሔርን መጠየቅ ቀጠልሁ ከብዙ ሳምንት በኋላ ከሚገባው በላይ እንደታገሥኩት ተሰማኝ። አንድ እርምጃ የመውሰጃ ጊዜ እንደሆነም ገባኝ። ስለዚህ ለመጋቢዬ ሁኔታውን አጫወትኩት። ጥፋቱ የእኔ ነው ብዬ ማሰቡን ማቆም እንዳለብኝ ነገረኝ። ከእኔና ከልጅቱ መምረጥ እንዳለበት ባለቤቴን እንድጠይቀው መከረኝ። ምርጫው እኔ እሆን ዘንድ መለመን እንደሌለብኝም አስጠነቀቀኝ። ወንድ ለፍቅር የምትለምነውን ሴት እንደሚንቅም ገለጸልኝ።

ባለቤቴ ምርጫውን እንዲያደርግ ለመንገር ፈራሁ። ልጅቱን ይመርጥ ይሆናል ብዬ እጅግ ሰጋሁ። ቢሆንም ይህን ማድረጌ ግድ እንደሆነ ወሰንኩ።

በባለቤቴ ፊት ይህን ማለት ስላቃተኝ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፍኩለት።

*በጋብቻ በቆየንባቸው ባለፉት ዓመታት እወድህ ነበር፥ አሁንም እወድሃለሁ። በሠርጋችን ቀን እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ልትሆንልኝ ቃል ኪዳን ገብተህልኝ ነበር። አሁን ግን እንቺንም፥ ሌላይቱንም ልጅ እወዳችኋለሁ ብለሃል። ከወዳጆችህ አንዷ ብቻ ለመሆን እንደማልችል ልነግርህ ይገባኛል። እኔና አንተ ባለ ቃል ኪዳን ባልና ሚስት ነን።*

*ስለዚህ እንደ ቃል ኪዳናችን እንዳችን ለሌላችን ታማኝ ልንሆን አለበለዚያ ልንለያይ ይገባል።*

*በፍጹም የተዋጣለት ሚስት እንዳልሆንኩልህ አምናለሁ። ነገር ግን አልማገጥኩም፤ ታማኝ ነበርኩ። ከእኔና ከልጅቱ ጋር መተኛትህን ልትቀጥል አትችልም። ይህ ጋብቻ ሊባል አይችልም።*

*ልጅቱን ብትመርጥ እጅግ ስለምወድህ መጎዳቴ አይቀሬ ነው። ነገር ግን ባለቤቴ ሆነህ እንድትቀጥል ማስገደድ አልችልም። እርሷን ከመረጥክ ልለይህ ይገባኛል። እንደዚህ ከሆነ ሕይወት ቀላል እንደማይሆንልኝ አውቃለሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅልኝ አምናለሁ።*

*ልፈርድብህ አይደለም፤ ነገር ግን ዘላለማዊ ነፍስ እንዳለህ አንድ ቀን ስለምርጫዎችህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልስ እንደምትሰጥ ማስታወስ አለብህ።*

ባለቤቴ ልጅቱን ለመተው ውሳኔ አደረገ። በጻፍኩት ደብዳቤዬ አድናቆቱን ገለጠልኝ! እኔም እጅግ ደስ አለኝ።

አሁን የጋብቻ ሕይወታችን ታድሷል። ይቅርታ ላደርግለት እጅግ ከብዶኝ ነበር። ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ይቅር እንድለው እግዚአብሔር ረዳኝ።

ታማኝ ያልሆነው ባለቤቴ ሆኖ ሳለ የእኔ ጥፋት እንደሆነ ለምን እንዳሰብኩ አሁን ነገሩን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳየው እደነቃለሁ። አንዲት ሴት ስለ ባሏ ኃጢአት እራሷን መውቀሷ የተለመደ ነውን?

ውድ ጁሊያ፥

አዎን፥ ሴት ስለ ባሏ ኃጢአት እራሷን መውቀሷ በጣም የተለመደ ነው። አንድ ወንድ ከሚስቱ ውጭ ከሌላ ሴት ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሲጀምር ሚስቱ የተሻለች ሚስት ሆና እንዳልተገኘች እራሷን መቁጠሯ የተለመደ ነው።

አንዲት ሴት በባሏ ላይ ስታመነዝር ባለቤቷ የሆነ ችግር አለብኝ ማለቱ የተለመደ ነው። እውነቱ ግን ጥፋተኛው ከትዳሩ ውጭ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመው ወገን መሆኑ ነው። ጥፋቱ የትዳር ጓደኛው ሳይሆን የራሱ/የራሷ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «አታመንዝር» ይላል። የትዳር ጓደኛህ/ሽ ካመነዘረ/ች ምክንያቱ በአንድ ወይም በሌላ አንተ ነህ/አንቺ ነሽ አይደለም።

ጁሊያ፥ ባለቤትሽ ከአንቺ ወይም ከልጅቱ ምርጫውን እንዲወስን መጠየቅሽ ትክክል ነው። ታማኝ ያልሆነ ሰው ሊነቃና በቤተሰቡ ላይ እየፈጸመ ያለውን ተግባር ልብ ሊል ይገባዋል። ደብዳቤሽ ባለቤትሽን በማንቃት ትልቅ ተግባር ፈጽሟል!

በእርግጥ አንቺን ትቶ ልጅቱን ሊመርጥ ይችል ነበር። ብዙ ወንዶች እንዲህ ያደርጋሉ። ነገር ግን እንዲመርጥ ማድረግሽ አሁንም ትክክል ነው

እንላለን። ከዓመት ዓመት ከእንቺና ከሌላ ሴት ጋር ከሚተኛ ትቶኸም ቢሆን እንኳ የተሻለ ነበር።

ፍሬድ፡- ትዳር ከመሠረትኩ አምስት ዓመት ሆኖኛል። በእነዚህ ዓመት ባለቤቴ በርካታ ወዳጆችን ቀያይራለች። በመጀመሪያ እንድትወደኝ ለማድረግ በመተቶች ተጠቀምሁ። ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆኑ አልረቡኝም። ባለቤቴ እስከ አሁን ለትዳሯ ታማኝ አይደለችም።

ባለፈው ዓመት ወንድሜ ክርስቲያን ሆነ። ለእኔም ስለ ክርስቶስ መሰከረልኝና ሕይወቴን ለጌታ ሰጠሁ። በመተት መጠቀም እንደሌለብኝ አሁን ተረድቻለሁ። መታመን ያለብኝ በክርስቶስ ነው።

ብዙ ጊዜ ለባለቤቴ ስለ ጌታ እነግራታለሁ። እርሷ እኔ «ክርስቲያን ነኝ» ብትልም ተግባሮቿ ግን ይህን አያሳዩም።

ባለቤቴን እወዳታለሁ። ለትዳሯ ታማኝ እንድትሆን እፈልጋለሁ። ምን ባደርግ ይበጀኛል?

የተወደድክ ፍሬድ፥

አንድ ሰው ክርስቶስንም ጠንቋይንም በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ ያለመቻሉን መረዳትህ ትክልል ነው። ደግሞ ክርስቶስን በመምረጥህ ከሁሉ የላቀውን አድርገሃል!

አሁን ለባለቤትህ የሚከተሉትን ሦስት ተግባራት በመፈጸም ፍቅርህን ግለጽላት።

1) በጎ የሆኑ ነገሮችን በማድረግ። ራስ ወዳድ አትሁን። ለሚያስፈልጋት ነገር አስብ። በቤት ውስጥ ሥራ አግዛት። በሕይወቷ የምታሳየውን መልካም ተግባርና ብርቱ ጎኗን በመለየት አድንቅላት። ስሜቶቿን እንድትናገር አበረታታት። ስትናገር አድምጣት! አስተሳሰብህንና ስሜቶችህን አካፍላት። ይህ በእውነት እንደምትጠነቀቅላት ያሳያታል።

2) አስፈላጊውን እርዳታ በማቅረብ። ለጸሎትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከባለቤትህ ጋር በየሳምንቱ የሚገናኙ ሁለት ክርስቲያን እህቶችን እንዲመርጥልህ መጋቢህን ጠይቀው። ባለቤትህ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆን ውሳኔ እንደምታደርግ ተስፋ እናደርጋለን (ገላ. 6፡1)።

3) ለመምረጥ እንድትወስን በማስገደድ። ባለቤትህ ከትዳሯና ከውስልትናዋ አንዱን መምረጥ እንዳለባት በትሕትና ንገራት። ሁለቱንም በአንድ ላይ ማስተናገድ አትችልም። ሁለቱ አብረው አይሄዱም። ውስልትናዋን የምትመርጥ ከሆነ ቤትህን ትታ ወደ ወላጆቿ ቤት ብትመለስ ይሻላታል። ነገር ግን ታማኝ ሚስትህ ለመሆን እንደምትወስን ተስፋ አለን።

ሊና፡- ባለቤቴ በሚቆጣበት ጊዜ ሁሉ እኔንና ልጆቼን ይደበድባል። ባለፈው ሳምንት የሁለት ዓመት ዕድሜ ያለው ልጃችን ከጠረጴዛ ላይ ወጣና

ሬዲዮኑን ሰበረው። ባለቤቴ ወደ ቤት እንደተመለሰ ያለማቋረጥ እኔንና ልጆችንን ይደበድበን ጀመር። ሁለታችንንም ሊገድለን ነው ብዬ ነበር።

ለትዳሬ ፍጹም ታማኝ ብሆንም እንኳ ሁልጊዜ ይጠረጥረኛል። ከማንኛውም ወንድ ዘመዶ ቢሆንም እንኳ ስነጋገር ሲያየኝ እጅግ በጣም ይቆጣል።

እኔን በመደብደቡ አንዳችም ስሕተት እንደሌለበት ይናገራል። አስቆጥተሽ ለዱላ ስለምትጋብዥኝ ጥፋተኛ አንቺው ነሽ ይለኛል።

ከደበደበኝ በኋላ የዱላውን ምልክት ለመሸሸግ ስል ለተወሰኑ ቀናት በቤት እቆያለሁ።

ክርስቲያን ስለሆንኩ ታገሽ እንደምትሉኝ አውቃለሁ፥ ነገር ግን እኔ ዱላ ሰልችቶኛል። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።

የተወደድሽ ሊና፥

እንድትታገሺ አይደለም የምንነግርሽ።

ብዙ ጊዜ ለባሎችና ለሚስቶች ትዕግሥት እንዲያደርጉ መናገራችን እውነት ነው። ነገር ግን መታገሥ አያስፈልግም፥ እርምጃ ውሰዱ የምንልባቸው ሁኔታዎችም አሉ።

ለምሳሌ፥ አንድ ባል ወይም ሚስት ወደ እኛ ዘንድ መጥተው የትዳር ጓደኛዬ አመነዘረብኝ ብለው ቢነግሩን ሁልጊዜ የምንላቸው ይህን መታገሥ አያስፈልግም፥ በአስቸኳይ እርምጃ ውሰዱ ነው።

አንዲት ሚስት ዱላ ቀለቧ ሲሆንም ታገሺ አንላትም።

አመንዝራንና ሚስቱን የሚደበድብ ሰውን ትዕግሥት አይለውጠውም። ብዙ ጊዜ ለውጥ የሚያመጣው ተግባራዊ እርምጃ ነው።

ስለዚህ ሊና የምንልሽ «እርምጃ ውሰጂ» ነው።

ለምትወስጂው እርምጃ የሚመሩሽ ሦስት ተግባራዊ ቅደም ተከተሎች ቀጥለው ተመልክተዋል።

1. ጉዳዩን ለቤተ ክርስቲያን (እና ወይም) ለቤተ ዘመድ አሳውቂ (ማቴ. 18፡15—17)።
2. እነርሱን ሊሰማቸው ሳይወድ ቢቀርና መደባደቡን ቢቀጥል ትተሽው ውጪ። በቤተ ዘመድ ቤት ወይም ከቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአንዱ ቤት ቆዪ።
3. ወደ ባለቤትሽ ፈጥነሽ አትመለሺ። መለወጥ እንዳለበት ለመገንዘብ በርካታ ሳምንታት ወይም ወራት ይፈጅበት ይሆናል።

እንደዚህ ዓይነት ተግባር ወንዱ ቆም ብሎ «ምን ዓይነት ባል ነኝ?» ብሎ እንዲያስብና «እንዴ ውድ ሚስቴን ላጣት ነውን?» እንዲል ያደርገዋል።

በእርግጥ አንዳንድ ባሎች እጅግ ክፉና ልበ ደንዳና ከመሆናቸው የተነሣ ሚስቶች ምንም ዓይነት እርምጃ ቢወስዱም ለውጥ ለማምጣት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ይቀራሉ። ብዙ ጊዜ ተግባር ከትዕግሥት ይልቅ ስኬታማ መሆኑ እርግጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ብርቱ ቅጣት ክፋትን ከልብ አውጥቶ ይጥላል» ይላል (ምሳ. 20:30)።

ስለዚህ ሊና፥ እነዚህን ሦስት ቅደም ተከተል የጠበቁ እርምጃዎችን ስትወስጂ ባለቤትሽ መሳሳቱን አውቆ እንዲለወጥ እንጸልይልሻለን።

ነገር ግን ከመሻሻል ይልቅ የመባባስ ሁኔታ ካሳየ ለዘለቄታው ልትተዪው ያስፈልግ ይሆናል።

ምንም ነገር ይድረስብሽ የሰማዩ አባትሽ እንደሚወድሽና ከአንቺ ጋር እንደሆነ አትዘንጊ። መዝሙር 31ን ብታነቢ ልብሽን የሚያበረታታና የሚያጸና ይሆናል።

> **ማስታወሻ፦** ወላጆች ልጆቻቸውን ለመቅጣት በትር መጠቀም እንደሚችሉ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይናገራሉ። *ነገር ግን የትዳር ጓደኛን በበትር መምታት ስለመቻሉ የተነገረ አንድም ጥቅስ የለም።*
>
> አብያተ ክርስቲያናት ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደ ጓደኛ እንዲቆጥሩ ማስተማር አለባቸው (1ኛ ጴጥ. 3:7)።
>
> ደግሞም አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሊና ያሉትን እህቶች መርዳት አለባቸው።

ጆሴፊን፦ ገና ወጣት ልጃገረድ በነበርኩበት ወቅት እናቴን ስለ ፍትወተ ሥጋ አንዳንድ ጥያቄዎችን እጠይቃት ነበር። እርሷ ግን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ፈጽሞ ፈቃደኛ አልነበረችም። ታዲያ ምን ማድረግ እችል ነበር? በመጨረሻም ስለ ፍትወተ ሥጋ ጉዳይ ከመጽሔቶች አነበብኩ፥ ጓደኞቼንም በርካታ ጥያቄዎች ጠየቅኋቸው። ከእነርሱ ካገኘኋቸው በርካታ ዓይነት መረጃዎች አብዛኞቹ የተሳሳቱና የተጣመሙ ነበሩ።

አሁን ዕድሜዬ 22 ዓመት ሆኖአል። ባለፈው ዓመት ወንድ አያቴ በመሞቱ የሴት አያቴ በአሁኑ ጊዜ ከእኛ ጋር አብራ ትኖራለች። ከእርሷ ጋር ብዙ አስደሳች ነገሮችን ተጫውተናል። እርሷ ወጣት በነበረችበት ዘመን እያንዳንዷ ልጃገረድ በፍትወተ ሥጋ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከእናቷና ከአክስቷ ትምህርት ታገኝ እንደነበር ነገረችኝ። በዚህ መሠረት የሚከተሉትን ነገሮች ያስተምሩ እንደነበር ገልጻልኛለች፦

* የሴት ልጅ አካል እንዴት እንደሚያድግ። የወር አበባ ለምን እንደሚጀምር።

* ሴት ልጅ እስከ ጋብቻ ዕለት ድረስ ክብረ ንጽሕናዋን ጠብቃ መኖር እንዳለባት።

* ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አንዳንድ መረጃዎች።

* እናት እያጠባች ባለችበት ወቅት ማርገዝ እንደሌለባት።

በዚያ ዘመን አባቶች ደግሞ ወንዶች ልጆቻቸውን የሚከተሉትን ነገሮች ያስተምሩ ነበር፡-

* ወንድ ለምን መሥራት እንዳለበት።

* ባሎች ሚስቶቻቸው ቶሎ ቶሎ እንዳያረግዙ ሊያደርጉ የሚችሉባቸውን መንገዶች፥

* ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ቢያመነዝሩ ስለሚቀበሉአቸው ቅጣቶች።

እነዚህ ትምህርቶች ተፈጥሮአዊ በሆኑ መንገዶች፥ በወላጆች ምሳሌነት፥ በተረትና ምሳሌ፥ በእንቆቅልሽ፥ በአሳዛኝና በአስቂኝ ታሪኮች የሚሰጡ ነበሩ።

በአሁኑ ጊዜ ግን ብዙ ወላጆች እነዚህን መረጃዎች ለልጆቻቸው ስለማይሰጡ የጾታ ትምህርት በትምህርት ቤቶች ሊሰጥ የሚገባ አይመስላችሁምን?

ውድ ጆሲፊን፥

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚሰጡ የጾታ ትምህርቶች ይልቅ የቀድሞው ባሕላዊ መንገድ እንደሚሻል እናምናለን። የፆታን ትምህርት ለመማር ከሁሉ የተሻለው ስፍራ መኖሪያ ቤት ነው።

እንደ ወላጆች ግባችን ደስታና ፍቅር የሰፈነበትን ቤት መመሥረት ነው። ከዚያም ልጆቻችን ሕፃናት ከየት እንደመጡ ሲጠይቁን ንጹሕና ቀላል የሆነ መልስ ልንሰጣቸው እንችላለን።

ምናልባት የጾታን ትምህርት በትምህርት ቤት መማር ያለባቸው መልካም ቤተሰብ የሌላቸው ልጆች ይሆናሉ።

ጆሲፊን፥ አንቺ ግን የሚከተለውን እንድታደርጊ እንመክርሻለን። ጥሩ ክርስቲያን ባል መርጠሽ አግቢ። ቤታችሁን እውነተኛ የክርስቲያን ቤተሰብ ለማድረግ ጣሩ። እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ልጆቻችሁን ውደዱ። ስለ እግዚአብሔርና እርሱ ለፍቅር፥ ለጋብቻ ለፍትወተ ሥጋ ፍላጎትና ልጆች ስለማግኘትና ስለማሳደግ ስላለው ዓላማ ጨምራችሁ አስተምሩ። እነዚህን ነገሮች ለልጆቻችሁ ለማስተማር ትምህርት ቤት ጥሩ ቦታ እንደሚሆን አታስቡ። ለልጆቻችሁ ምሳሌ በመሆን ስለ ሕይወት ገሃድ እውነታዎች ከእነርሱ ጋር ተነጋገሩ።

ቢጽትሪስ፡- ለሴት ልጄ የጾታ ትምህርት ማስተማር ያለብኝ በየትኛው ዕድሜ ላይ ነው?

ውድ ቢአትሪስ፥

ረጅም ጊዜ አትጠብቂ። ወደ ኮረዳነት ዕድሜ ከመድረስዋ በፊት ልትነግሪያት የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ።

ኮረዳነት የሚጀምረው ለሴቶች ከ10-12 ዓመት ባለው ጊዜ ሲሆን፥ ጉርምስና ለወንዶች የሚጀምረው ከ12-14 ዓመት ነው።

ስለዚህ ሴት ልጅሽ ዕድሜዋ 10 ዓመት ከመድረሱ በፊት የጾታ ትምህርትን ዋና ዋና እውነቶች መገንዘቧን አረጋግጪ።

ይህን ስንል ገና ጨቅላ ለሆነችው ሴት ልጅሽ በጾታ ትምህርት ሊካተቱ የሚችሉትን የፍትወተ ሥጋ ዝርዝር ጉዳዮችን መንገር አለብሽ ማለታችን አይደለም። እንደነዚህ ዓይነት ዝርዝር ጉዳዮችን ከማግባቷ ጥቂት ቀደም ብላ ልትማር ትችላለች።

ዕድሜዋ 10 ዓመት ከመድረሱ በፊት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መሠረታዊ ነገሮች ላይ ተነጋገሩ ማለታችን ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወደ እርግዝና እንዴት እንደሚመራና እግዚአብሔር በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ላይ የደነገገውን ሕግ ሁሉም ሊታዘዘው እንደሚገባ አስረጂያት። ልታጠቃልያቸው በሚገቡ ርእሰ ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉት መካተት አለባቸው።

ሀ) ወጣቶች እየጎረመሱ በሚመጡበት ወቅት በሰውነታቸው ውስጥ የሚታየውን ለውጥ። (ሴቶች ልጆቻችሁ ስለ *ወር አበባ* ወንዶች ደግሞ በእንቅልፍ ላይ ሆነው በሚያዩት ሕልም *የዘር ፍሬ ስለ መፍሰሱ* ሁኔታ ግንዛቤ ማግኘት አለባቸው።)

ለ) ጋብቻ፥ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትና እርግዝና። (ይህ ቀለልና አጠር ተደርጎ ይቅረብ።)

ሐ) በጉርምስና ወቅት ወጣቶች በሙሉ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት የሚኖራቸው የመሆኑ እውነታ ይጀምራል። ስለ ፍትወተ ሥጋ ፍላጎታቸው የጥፋተኝነት ስሜት ሊሰማቸው እንደማይገባ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ወጣት ከጋብቻ በፊት በሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚከተለውን ኃጢአት ለማስወገድ እራሱን/እራሷን የመግዛት ኃላፊነት አለበት/ባት።

መ) በጋብቻና በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ስለሚገኘው ደስታና እርሱን ባለመታዘዝ ደግሞ ስለሚከተለው ኃዘን።

ወላጆች ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ መረጃ ቢፈልጉ "Love & Marriage" ወይም "ፍቅርና ጋብቻ" የሚለውን መጽሐፋችንን መመልከት ይችላሉ። ወላጆች «ሔሎ ስዊት ቤቢ» (Hello Sweet Baby) (ተወዳጁ ልጃችን እንዴት ነህ) የሚለውን የእንግሊዝኛ መጽሐፋችንን እንዲያነቡ እናበረታታቸዋለን።

ካረን፡- ከወንዶች ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የጀመርኩት ገና የ14 ዓመት ልጅ ሳለሁ ነበር። ወላጆቼ ይህን አያውቁም ነበር። ጥሩ ልጅ እንደሆንኩ ያስቡ ነበር።

የፍትወተ ሥጋ ግኙነት በምናደርግበት ወቅት ወንዱ ኮንዶም የሚጠቀም ከሆነ ኃጢአት እንዳይደለ አስብ ነበር። በትምህርት ቤት አስተማሪያችን እንዲህ በማለት ነግሮን ነበር፡- «በድሮ ጊዜ ሴት ልጅ እስከታገባ ድረስ ክብረ ንጽሕናዋን ጠብቃ ድንግል ሆና መቆየት ነበረባት፥ በዘመናዊው ዓለም ግን ይህ ሁሉ ተቀይሯል።»

ለእኔ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማለት የሠለጠኑ ሴቶች ሁሉ ከወንድ ጋር የሚፈጽሙት አስደሳች ጨዋታ ነበር።

ዕድሜዬ 15 ዓመት በሞላ ጊዜ እናቴ እግዚአብሔር በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ላይ ስለደነገገው ሕግ፥ እኛ ክርስቲያኖች እስከ ጋብቻችን ቀን ድረስ ክብረ ንጽሕናችንን ጠብቀን በድንግልና መቆየት ለምን እንዳለብን በሰፊው አጫወተችኝ። ወላጆች እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሳይዘገዩ የማይነግሩን ለምንድን ነው?

> ማስታወሻ፡- የካረንን ደብዳቤ በቀጥታ ያወጣነው ወላጆች ለልጆቻችሁ የጾታን ትምህርት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጉዳዩን ጨምሮ ሳትዘገዩ መንገራችሁ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በሚገባ እንድታስታውሱ ነው። እስከ 15 ዓመታቸው ድረስ መቆየት በጣም መዘግየት ነው!

አንዲ፡- በዚህ በሠለጠነ ዓለም ለክርስቲያን ወጣቶች እስከ ጋብቻቸው ቀን ድረስ ክብረ ንጽሕናቸውን ጠብቀው በድንግልና መቆየት ይቻላል ብላችሁ ታምናላችሁን?

ውድ አንዲ፥

አዎን በእርግጥ እናምናለን! በዚህ ዘመን ፈተናው እጅግ ከባድ እንደሆነ እናምናለን። ሆኖም ግን እግዚአብሔር በፈተና ሁሉ ድል የማድረጊያን መንገድ እንዳዘጋጀ ቃል ገብቶልናልና (1ኛ ቆሮ. 10፡13) ዘወትር ድል መንሣት ይቻላል።

በዓለም ላይ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ *በርካታ* ወጣቶች እራሳቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ ቆርጠው በመነሣታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር እርዳታ ማሸነፋቸውን እናውቃለን!

በእኛ ቤተሰብ እኔና ባለቤቴ ብቻ ሳንሆን ልጆቻችንም እራሳቸውን በንጽሕና ጠብቀዋል «በዚህ በሠለጠነ ዓለም።»

ጌዴዎን፡- በአገራችን ያሉ ልጆች ምን ነካቸው? በዕድሜ የገፉ አዋቂዎችን ማክበር አቁመዋል። አብዛኞዎቹ አልኮል ጠጪዎች፥ ከጋብቻ ውጭ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን የሚያደርጉና በአደንዛዥ ዕጾች የተለከፉ ናቸው።

በወላጅነት ባለብን ኃላፊነት ተግተን በመሥራት የትምህርት ቤት ክፍያቸውን እናሟላለን፥ ጥሩ ጥሩ ልብሶችን እንገዛላቸዋለን። የኪስ ገንዘብም እንሰጣቸዋለን። ነገር ግን እንዴት እንደሚያደርጋቸው ተመልከቱ! እንደ ወላጆች ምን ማድረግ አለብን?

ውድ ጌዴዎን፥

በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው! መልሱ እንደሚከተለው መሆን እንዳለበት እናምናለን። በዚህ ዘመን ያሉ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር አብረው ረጅም ጊዜ ማሳለፍ አለባቸው።

ልጆቻችን ገና ጨቅላዎች በነበሩበት ወቅት በየምሽቱ ታሪክ የሚነገርበት ጊዜ ስለነበረን በአንድነት እንሰባሰብ ነበር። እኔ ወይም ካሮል የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንነግራቸው ነበር። ልጆቻችን ታሪኮቹን በናፍቆትና በጉጉት ይከታተሉ ዘንድ በቂ ዝግጅት አድርገን በማሰብ በጥሩ ሁኔታ እንነግራቸው ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በኋላ ብዙ ጊዜ የሚከተለውን የሚመስሉ ነገሮች እነግራቸው ነበር፡- «በትምህርት ቤት በፈተና ላይ እያለ ለማታለል የሞከረ አንድ ልጅ ምን እንደደረሰበት ልነግራችሁ ይገባኛል።»

ያንን ታሪክ ተናግሬ ስጨርስ ባለቤቴ ደግሞ የሚከተለውን የሚመስል አንዳንድ ነገሮችን ትናገር ነበር፡- «ይህ ታሪክ ትንሽ ልጅ በነበርኩ ጊዜ እንዴት ወደ ችግር እንደገባሁ ያስታውሰኛል። ነገሩ ያቆጠቆጠው ስለ ....ጉዳይ መዋሸት በጀመርኩበት ጊዜ ነው...»

እንደነዚህ ዓይነት ታሪኮች ለመናገር ጊዜ ስንሰጣቸው ልጆቻችን «አባባና እማማ በእርግጥ ይወዱናል። ስለዚህ ችግር ላይ እራሳችንን እንዳንጥል ይፈልጋሉ» የሚል ግንዛቤ አገኙ።

ስለዚህ ለወላጆች የምንሰጠው ምክር «ከልጆቻችሁ ጋር ጊዜ ውሰዱ» የሚል ነው። መኪናችሁን አብራችሁ እጠቡ። በአትክልት ስፍራዎቻችሁ አብራችሁ ሥሩ። አብራችሁ በምትሠሩበት ጊዜ አነጋግሩአቸው። ፊታቸውን ከእግዚአብሔር በመመለሳቸው ምክንያት ሕይወታቸው ስለተበላሸባቸው ሰዎች የምታውቁትን እውነተኛ ታሪክ ንገሯቸው። እግዚአብሔርን በማገልገላቸው ታላቅ ደስታ ስለተጎናጸፉ ሌሎች ሰዎችም ታሪክ አጫውቷቸው።

ለሕፃናት ልጆቻችሁ ሰብከት አትስበኩ። የምትናገሯቸውን ታሪኮች የሚስቡ አድርጓቸው። አንዳንድ የሚያሳዝኑ ታሪኮችንና ደግሞም የሚያስቋቸውን ሌሎች አስደሳች ታሪኮች ንገሩአቸው። በዚህ ዓይነት ስትቀጥሉ ልጆቻችሁ «አባባና እማማ እባካችሁ ሌሎች ታሪኮች ደግሞ ንገሩን» ሲሉ ታገኟቸዋላችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለወላጆች እንዲህ በማለት ይናገራቸዋል፡-

«ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት

አትርሳ፤

እነዚህኑ ትእዛዛት ለልጆችህ አስተምራቸው፤
በቤት ስትቀመጥም ሆነ በመንገድ ስትሄድ
ዕረፍት በምታደርግበትም ጊዜ ሆነ
ሥራ በምትሠራበት ጊዜ ሁሉ
እነዚህን ትእዛዛት ዘወትር አሰላስል።»

(ዘዳግ. 6:6–7)

አንድ ቀን ሊጎበኘን ወደ ቤታችን የመጣ አንድ ወጣት እንዲህ አለ:– «ከልጆቻችሁ ጋር የምትነጋገሩበት አኳኋን አስደንቆኛል። እኔ ልጅ በነበርኩበት ወቅት አባቴ «አትጮኽ፥ ክብሪቱን አቀብለኝ፥ ይህን ኩባያ ወደኩሽና ውሰድ...ከመሳሰሉ ነገሮች በስተቀር ምንም ነገር ተናግሮኝ አያውቅም።»

ለዚህ ወጣት እንዲህ አልነው:– «አባት በምትሆንበት ወቅት ዘዳግ. 6:6–7 የሚለውን አድርግ። ከልጆችህ ጋር በቤትህ በምትቀመጥበት ጊዜ በመንገድ ላይ በምትሄድበት ወቅት፥ በምትተኛበትና በምትነሣበት ጊዜ ሁሉ ተናገር።»

አንዳንድ ወላጆች ገንዘብ ለማግኘት እጅግ ከመባከናቸው የተነሣ ለልጆቻቸው ጊዜ ማጣታቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ አባት በአንድ ከተማ እናት ደግሞ በሌላ ከተማ ይሠራሉ። ስለዚህ ከልጆቻቸው ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው። እራሳቸውን እንዲህ ብለው መጠየቅ አለባቸው:– «የላቀና አስፈላጊው ነገር የትኛው ነው? ሥራችን ወይስ ከልጆቻችን ጋር የምናሳልፈው ጊዜ?»

በስዋዚላንድ በአንድ ትምህርት ቤት አስተማሪ በነበርኩበት ወቅት አንድ ቀን አንድ መምህር እንዲህ አለኝ:– «ብሩስ፥ የማታ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ማስተማር አለብህ። እነዚህን አዳዲስ የቤት ዕቃዎችንና ምንጣፍ ተመልከት። እነዚህን ዕቃዎች በሙሉ የገዛሁት የማታ ትምህርት በማስተማር ካገኘሁት ትርፍ ገንዘብ ነው። ብሩስ አድምጠኝ፥ በአስተማሪ ደመወዝ ኑሮህ ፈቅ ሊል ወይም ሊሻሻል አይችልም፥ የማታ ትምህርት አስተምር። ባለቤትህም ሥራ እንድትሠራ አድርግ።»

ለካሮል ግን እንዲህ አልኋት:– «የማታ ትምህርት ካስተማርኩ ማታ ማታ ለልጆቻችን ታሪክ የምንናገርበት ጊዜ ችግር ይገጥመዋል። አንቺም ገቢ ለማስገኘት ብለሽ ሥራ ብትጀምሪ ተመሳሳይ ችግር ይገጥመናል። የቤት ዕቃዎቻችን አሮጌ ቢሆኑ፥ ወለላችንም ምንጣፍ አጥቶ ሸክላው ቢያፈጥም ምንም አይደለም። ልጆቻችን ጊዜያችንን ይፈልጉታል።»

አንዳንድ ጊዜ ልጆቻችን ከሁሉ የተሻለ ልብስ ባይለብሱም ጊዜያችንና ፍቅራችን የእነርሱ ነው። ዛሬ ልጆቻችን ደስተኛ የሆነ ቤተሰብ መሥርተው ለክርስቶስ ይኖራሉ።

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር አጥጋቢ ጊዜ ሳይኖራቸው ሲቀር ምን ይሆናል? ልጆቻቸው አባባና እማማ እባካችሁ ከእኛ ጋር ብዙ ጊዜ ይኑራችሁ ብለው ይጠይቁናልን? ፈጽሞ ይህን ከማለት ይልቅ በባዶነት ስሜታቸው እያደጉ

ይሄዳሉ። በሚጎረምሱበት ወቅት የባዶነት ስሜቶቻቸውን ለማርካት አልኮል መጠጣትና የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ይጀምራሉ።

ጌዴዎን፥ በደብዳቤህ «እኛ እንደ ወላጆች ምን ማድረግ አለብን?» ብለህ ጠይቀሃል፤ መልሱ መጽሐፍ ቅዱስን ታዘዝ ነው። ከልጆችህ ጋር ለመጫወት ጊዜ ውሰድ። [መዝ. 77(78)፡3–6 ና 12–72ን ተመልከት።]

እንደ ባልና ሚስት እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ(ኤፌ. 5፡25–33ና 1ኛ ጴጥ. 3፡1–7)። ልጆቻችሁ «አባባና እማማ ይዋደዳሉ....እኛን ይወዱናል!» በማለት ይደሰታሉ።

ጢሞቴዎስ፡– ከስድስት ዓመት በፊት የመጀመሪያ ልጃችን ሲወለድ ባለቤቴ ሥራዋን አቆመች። ልጆች በቤት የምትውል እናት ታስፈልጋቸዋለች ብላ ታምናለች። አንዳንዶች ይህን በማድረጋችን ሳቁብን። ደግሞም እርሷን እንደ ሰነፍ ቆጠሯት። ለእኔ ባለቤቴ ግሩም እናት ናት።

ውድ ጢሞቴዎስ፥

ባለቤትህ ከልጆችህ ጋር ጊዜ እንዲኖራት ስለፈለገች እግዚአብሔርን አመስግን። እርሷ ብቻዋን አይደለችም። በዚህ ዘመን ብዙ እናቶች በቤት መዋል እየመረጡ ነው። ለምሳሌ አንድ ትሪንካ የምትባል ታዋቂ የፋሽን ሞዴል የሆነች ሴት ለልጆቿ ጊዜ ለመስጠት ሥራዋን እንዳቆመች ጋዜጦች በቅርቡ ይፋ አድርገዋል።

ትሪንካ እንዲህ ብላለች «እኔና ባለቤቴ ክርስቲያን ከሆንን በኋላ ሦስት ልጆቻችንን ከማሳደግ የሚበልጥ ሥራ እንደሌለ ተረድተናል። ከልጆቼ ጋር ቤቴ በመዋል ፍቅሬንና በእግዚአብሔር ያለኝን እምነቴን አካፍላቸው ዘንድ ደስ ያሰኘኛል። ከዚህ የበለጠ ምን ልሰጣቸው እችላለሁ?

ትሪንካና ባለቤቷ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ወጣት ባለትዳሮችን ሴቲቱ በቤት ከልጆቿ ጋር እየዋለች በባል ገቢ ብቻ እንዴት መኖር እንደሚቻል በማስተማር ያገለግላሉ።

ይህ ማለት ሴቶች ሁሉ ሥራቸውን ማቆም አለባቸው ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ሁኔታ የእናቶች መሥራት ግድ ይሆናል።

የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ እናቶች ባሎቻቸው በቂ ገቢ እያላቸው እንኳ መሥራት መፈለጋቸው ነው። የሚሠሩት «ቆንጆ ነገሮችን» መግዛት ስለሚፈልጉ ነው። ልጆቻቸው ምን ይሆናሉ? ጥቂት ፍቅር ብቻ ልትሰጣቸው በምትችል ተቀጣሪ ሴት እጅ ያድጋሉ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበትን ትምህርት ፈጽሞ አያገኙም። እነዚህ ልጆች በሚጎረምሱበት ወቅት ብዙዎቹ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ። ልባቸው የተሰበረባቸው ወላጆች «የገዛናቸው ቆንጆ ነገሮች ምንም ቆንጆ አይደሉም! ሰዓቱን አሥራ አምስት ዓመታት ወደ ኋላ መልሰን ከልጆቻችን ጋር የምናሳልፍበት ሁኔታ ምን ነው ባገኘን!» ይላሉ።

ጢሞቴዎስ፥ አድምጠን! ሚስትህ ሥራዋን ትታ በቤት በመዋሏ ስለ ሳቁ ሰዎች አትጨነቅ። ጎረቤቶችህ ያላቸውን አንዳንድ ቆንጆ ነገሮች ለመግዛት ባትችሉም አንተና ባለቤትህ ከልጆቻችሁ ጋር ስላሳለፋችሁት ጊዜ የምትጸጸቱበት ምንም ነገር አይኖርም።

ክሪስታቤል፡— እህቴ ከዩኒቨርስቲ ተመርቃ ስትወጣ «ልጆችን በዱላ መምታት ጊዜው ያለፈበት ጉዳይ ነው» ማለት ጀመረች፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

ውድ ክሪስታቤል፥

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡—

ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል፥
በበትር ብትመታው አይሞትምና።
በበትር ትመታዋለህ፥
ነፍሱንም ትታደጋለህ። (ምሳ. 23፡13–14)

በትርን የመጠቀሚያ ትክክለኛ ጊዜ ያለ ቢሆንም። ትክክለኛ ያልሆነም ጊዜ እንዳለ አትዘንጉ።

ትክክለኛው ጊዜ፡— በትርን መጠቀም ትክክለኛ የሚሆነው ልጅ ትክክለኛውን ነገር እያወቀ ትክክል ያልሆነውን ነገር ለማድረግ ሲመርጥ ነው። ለምሳሌ አንዲት እናት የሰባት ዓመት ልጇን «እባክህን ይህን ቆሻሻ አውጥተህ ጣል» ስትለው እምቢ ብሎ ጆርባውን ሰጥቶ ቢሄድ የግድ መጠቀም ያስፈልጋታል።

ትክክለኛ ያልሆነው ጊዜ፡— አንድ ልጅ አንድ ነገር ማድረግ ሲረሳ ወይም ስሕተት ሲያደርግ በበትር መቀጣት የለበትም። ለምሳሌ አንድ ልጅ ሳህን በድንገት ወድቆ ቢሰበርበት እናቲቱ ነገሩ ቢያስቆጣትም እንኳ ልጇን በዱላ መምታት የለባትም። ምክንያቱም አውቆ አላደረገውም። የተሰበረውን ዕቃ እንዲተካ ተጨማሪ ሥራ ልታሠራው ትችላለች፥ በዱላ መቅጣት ግን የለባትም።

በዱላ የመቅጣት ጉዳይ አንድ ልጅ ትክክለኛውን ነገር እያወቀ ትክክል ያልሆነውን ለማድረግ በሚመርጥበት ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል መሆን አለበት።

ዱላን ከልክ በላይ መጠቀም አያስፈልግም። ልጅን በኃይል መምታት አያስፈልግም። ሁለት ጊዜ ቀለል አድርጎ በአርጩሜ ማቅመስ ልጆች ወላጆቻቸውን መታዘዝ እንዳለባቸው ያስታውሳቸዋል።

አውስቲን፡— ከልጅነቴ ጀምሮ አባቴን በጣም እፈራው ነበር። አሁን እንኳ ስለ እርሱ ሳስብ ዱላውን አስታውሳለሁ። በቅርቡ ትዳር እመሠርታለሁ። ምን ዓይነት አባት ነው መሆን ያለብኝ እያልኩ እራሴን ደጋግሜ እጠይቃለሁ። አባት አምባገነን መሆን አለበትን?

ውድ አውስቲን፥

በፍጹም። አባት ለልጁ ፍቅርን ማሳየት አለበት። ይህንንም ከልጆቹ ጋር የእግር ጉዞን በማድረግ፥ በመነጋገር፥ ኳስ በመጫወት፥ ወዘተ... ሊያደርገው ይችላል። መቅጣት ሲያስፈልገው እንኳ በፍቅር ሊያደርገው ይገባል። ለምሳሌ አንድ አባት ልጁ ለአዋቂ ሰው ያለአግባብ ሲናገር ቢሰማ ልጁን ገለል አድርጎ «ልጄ ስማ፥ እንደዚህ እንድትናገር አልፈቅድም። ሰዎችን ማክበር ካልተማርክ ከአስተማሪዎችህና ከአሠሪዎችህ ጋር የማያቋርጥ ችግር ውስጥ ትገባለህ። ሰዎችን ማክበር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንድታስታውስ አሁን የምቀጣህ ስለምወድህ ነው።» ሊለው ይገባል።

ልጆች መቅጣት ግድ ሆኖበት በፍቅር የሚቀጣን አባት አይፈሩም።

ግላዲስ፦ LOVE AND MARRIAGE (ፍቅርና ጋብቻ) በሚለው መጽሐፋችሁ ብዙ ወጣቶች የማይረቡና ዋጋ የሌላቸው እንደሆኑ ስለሚያስቡ ሌሎች የማያውቁት ኃዘን በውስጣቸው ታምቆ መኖሩ የሚያሳዝን ነው ብላችኋል።

የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ አለኝ። ጥያቄዬ አንድ ልጅ እራሱን የማይረባና ዋጋ ቢስ አድርጎ እንዲቆጥር የሚያደርገው ምንድን ነው? ልጄ እንደዚህ ዓይነት ስሜት እንዳይኖረው እንዴት ልረዳው እችላለሁ?

ውድ ግላዲስ፥

> እኔና ባለቤቴ በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ስንገኝ የሚከተለውን የሚመስል ንግግር የሚናገሩ ጎረምሶች ያጋጥሙናል፦
>
> «አዎን፦ የማልረባና ዋጋ የሌለኝ እንደሆንኩ ይሰማኛል። ለምን? ምክንያቱም በትምህርት ጎብዝ አይደለሁም። በትምህርት ቤት ወንድሜም ሆነ እህቴ ሁልጊዜ ከእኔ የተሻለ ነጥብ ያመጣሉ።
>
> በስፖርትም ቢሆን ተሰፋ የለኝም።
>
> ከሁሉ የባሰው አስከፊ ነገር ግን አስቀያሚነቴ ነው። በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት ሰዎች በተለያዩ የቅጽል ስሞች እየጠሩ ይሳለቁብኛል። እውነተኛ ጓደኞች የሉኝም።
>
> አንዳንድ ጊዜ ምነው ባልተወለድኩ ኖሮ እንዴት ይሻለኝ ነበር እላለሁ። እውነት ለመናገር የእኔ መወለድ ስሕተት ነው። ወላጆቼ ሳይፈልጉኝ የተፈጠርኩ ነኝ ማለቴ ነው።»

ወጣቶች ውጪያቸውን ስናየው ደስተኞች ይመስላሉ። ከጓደኞቻቸው ጋር ይጫወታሉ። ምንም የሚያስጨንቃቸው ነገር ያለባቸው አይመስልም። ይሁን እንጂ በውስጣቸው ብዙ ይጨነቃሉ። በክፍል ውስጥ በትምህርታቸው በአንደኝነት የሚመሩት እንኳ ሌሎች ልጆች ጎበዞች እንደሆኑ እነርሱ ግን እንዳይደሉ በማሰብ ይጨነቃሉ።

ምንም ያህል ቆንጆ ቢሆኑም እንኳ በአጠቃላይ ሁሉም ማለት ይቻላል፥ እኔ በጣም ወፍራም፥ ወይም በጣም ቀጭን፥ በጣም ረጅም ወይም በጣም አጭር፥ ወይም በጣም.... ነኝ በማለት እራሳቸውን ይጠላሉ።

ስለዚህ ግላዲስ፥ «ልጄ እንደዚያ ዓይነት ስሜት እንዳይሰማው እንዴት ልረዳው እችላለሁ?» የሚለው ጥያቄሽ ትክክል ነው።

ቀጥሎ አንድ ወላጅ ኀረምሳ የሆነ ወንድ ወይም ሴት ልጁን እንዴት ሊረዳ እንደሚችል የተሰጠውን ምሳሌ መመልከት ይጠቅማል።

*ወላጅ ይጠይቃል፡-* በክፍላችሁ ውስጥ በጣም ደስተኛው ልጅ ማን ነው?

*ኀረምሳው/ዋ ይመልሳል/ትመልሳለች፡-* ምናልባት ስምዖን።

*ወላጅ፡-* ብዙ ጊዜ ይስቃልን?

*ልጅ፡-* አዎን፥ በጣም!

*ወላጅ፡-* የሌሎችን ልጆች አለባበስ ወይም የራስ ቅል ቅርፅ እያየ ማሳቅ ይወዳልን?

*ልጅ፡-* አዎን እንዴት አወቅህ?

*ወላጅ፡-* እስኪ ንገረኝ፥ ስምዖን እንደዚያ የሚያደርገው ለምን ይመስልሃል? ከውስጥ ልቡ ኃዘንና ራስን የማጣጣል ስሜት ስለሚሰማው ሊሆን ይችላልን?

*ልጅ፡-* በፍጹም፥ ስምዖን እንደዚያ ሊሆን አይችልም። ሁልጊዜ ደስተኛ ነው።

*ወላጅ፡-* እርግጠኛ ነህን? በጥንቃቄ ተከታተለው። በሌሎች ልጆች ደካማ ጎን የሚስቀው ለምን እንደሆነ ጥቂት አስብ።

ይህ ውይይት ኀረምሳው ልጅ ጥቂት ማሰብ እንዲጀምር ያደርገዋል፡- «በክፍሌ ውስጥ ያሉ በርካታ ልጆች ዋጋ ቢስነት ይሰማቸዋልን? ብዙ ጊዜ ደስተኛ መስለው የሚስቁት እንኳ እንደዚህ ሊሆኑ ይችላሉን?»

በሌላ ቀን የሚከተለውን ዓይነት ውይይት ቀጥሉ።

*ወላጅ፡-* ልጆች በእድገት ሂደታቸው ተፈላጊ አይደለሁም በሚል ስሜት ውስጥ እንደሚያልፉ ትገነዘባለህን? እንዲያውም አሁን ወይም ጥቂት ቆይቶ አንተም እንደዚሁ ዓይነት ስሜት ይሰማህ ይሆናል።

*ልጅ፡-* እንደዚያ ዓይነት ስሜት ይሰማኝ ጀምሯል። ምን ማድረግ እችላለሁ?

*ወላጅ፡-* የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ሊረዱህ ይችላሉ።

ሀ) አእምሮህ ስለ ራስህ ማሰብ ትቶ ስለ ሌሎች እንዲያስብ አድርገው።

ዝም ብለህ ተቀምጠህ አትዘን። ለራስህ እንዲህ ብለህ ተናገር፡- «ስምዖንን መርዳት አለብኝ። በሌሎች ልጆች የሚስቀው እራሱ ዋጋ ቢስነት ስለሚሰማው ይሆናል። ላበረታታው መሞከር ይገባኛል!»

ቀጥሎ ስምዖን በሚገባ የሚያደርገውን ነገር ፈልግና አበረታታው። እግር ኳስ ሲጫወት ስሕተት ቢሠራ ከስሕተቱ ይልቅ በጨዋታው ክፍለ ጊዜ ያደረገውን ደኅና ነገር ጠቁም።

የአንተ ማበረታቻ የሚያስፈልገው ስምዖን ብቻ እንዳልሆነ ትገነዘባለህ። በክፍል ውስጥ ያሉ በርካታ ልጆች ይበረታቱ ዘንድ እግዚአብሔር ይጠቀምብህ ይሆናል። ይህንን በማድረግ ተግባር ውስጥ ስትጠመድ አንዳንዶቹ እውነተኛ ጓደኞችህ ይሆናሉ። አንተም ይህ እርዳታ በሚያስፈልግህ ጊዜ ከጎንህ በመሆን ያበረታቱሃል።

ለ) እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወድህ ፈጽሞ አትዘንጋ።

የፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ እንደሚወድህ አስብ! አንተን በግልህ ይወድሃል። በጣም ስለወደደህ ለኃጢአትህ ሥቃይን ይቀበል ዘንድ ልጁን ላከልህ። በክርስቶስ ስላመንክ የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶሃል። በተጨማሪ በምድር ላይ የምትሠራው ሥራ አዘጋጅቶልሃል። መልካሙን የኢየሱስ የምሥራች ወንጌል ወደ ወዳጆችህ እንድታደርስ ይፈልጋል። ዋጋ ቢስ አይደለህም! የሚያስፈልግህን ችሎታና ተሰጥዖ ሁሉ እግዚአብሔር ሰጥቶሃል።

ምናልባትም አንዳንዶች «ወላጆች ሳይፈልጉኝ የተወለድኩኝ ነኝ እንዲያው በአጋጣሚ የመጣሁ» በማለት ያስባሉ። አንተ ግን እንዲህ ብለህ ልትነግራቸው ትችላለህ፡- «ማንኛውም የሰው ልጅ አጋጣሚ አይደለም....እያንዳንዱ ጥንቃቄ በሞላበት በእግዚአብሔር ዕቅድ የመጣ ነው። ዋጋ ቢስ አይደለህም። እግዚአብሔር ይወድሃል። ኃጢአትህን ተናዝዘህ በኢየሱስ እንድታምንና በቀሪው ምድራዊ ዘመንህ እርሱን በማገልገል እንድታሳልፍ ይፈልጋል።»

ግላዲስ፥ ለልጅሽ ይህን እየተናገርሽ ባለሽበት ሰዓት ትክክለኛውን ቃል እግዚአብሔር እንደሚሰጥሽ በመተማመን አብዝተሽ ጸልዪ!

ሜሪል፡- በአንድ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብር እሠራለሁ። ሥራዬንም እወደዋለሁኝ። ሥራ አስኪያጄ ብዙ ጊዜ ሥራዬን በሚገባ እንደምሠራ ይነግሩኛል። ደንበኞቻችንም ለእኔ መልካም ሰዎች ናቸው።

ነገር ግን በየዕለቱ ከሥራ በኋላ ቤት ወደ ባለቤቴ መሄድ እጠላለሁ። ሁልጊዜ ይነቅፈኛል። ምንም ያህል ተግቼና ጠንክሬ ምግቡን ባዘጋጅለትም ሥጋው አልበሰለም፥ ጨው የለውም፥ ወዘተ... እያለ ያጉረመርማል።

አድናቆቱን እንዲገልጽልኝ ምን ላድርግ?

ውድ ሚሪል፥

ከባለቤትሽ ጋር ተነጋገሪ፦ ከእርሱ አድናቆትን ማግኘት በጣም እንደምትፈልጊ ይወቀው። ይህን ለእርሱ መንገር አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ ፍርሃት አያግድሽ።

ይህን በመልካም አነጋገር ግለጭለት። አድናቆትን መፈለግሽ ስሕተት አይደለም። ሁሉም ሰው ይፈልጋል።

አድናቆትን እንደምትፈልጊ ከባለቤትሽ ጋር ካልተነጋገርሽ የትዳር ሕይወታችሁ ቁልቁል ይሄዳል።

ለባለቤትሽ ያለሽን አድናቆት ግለጪ፦ አዎን፥ ባሎችም አድናቆትን ይፈልጋሉ። ብዙ ወንዶች አድናቆትን የማይፈልጉ ያስመስላሉ። ነገር ግን የሴቶችን ያህል ይፈልጉታል። (ገጽ ተመልከት)። ስለዚህ የባለቤትሽን ጠንካራ ጎን ማድነቁን እንዳትዘነጊ ተጠንቀቂ። ባለቤትሽ እንደምታደንቂው ከተረዳ አንቺንም ለማድነቅ ቀላል ይሆንለታል።

ኢሳይያስ፦ አንዳንድ ጊዜ የወንድ ብልት የተወሰነ ክፍል (በግርዘት ጊዜ የሚቆረጠው) በሆስፒታል ቀዶ ሕክምና የሚወገድ እንደሆነ እሰማለሁ። ይህ እውነት ነውን?

ውድ ኢሳይያስ፥

አዎን፥ አንድ ወንድ የብልቱን ንጽሕና በሚገባ ካልጠበቀ ከፍተኛ የመበከል ሁኔታ ሊያጋጥመው ይችላል። በዚያ ወቅት ብቸኛው ምርጫ ቀዶ ሕክምና ሊሆን ይችላል።

ማንኛውም ወንድ የብልቱን አካል ማጣት አይፈልግም። ስለዚህ እያንዳንዱ ወንድ ብልቱን *በየቀኑ መታጠብ* አለበት። ይህን የሚያደርገው *ሸለፈቱን ወደ ኋላ በመገልበጥ ለብ ባለ ውኃና በሳሙና በማጠብ ነው።*

ክርስቲን፦ አሁን ነፍሰ ጡር ነኝ። ሁለት ጥያቄዎች አሉኝ።

ሀ) ከባለቤቴ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ማቆም ያለብኝ መቼ ነው?

ለ) ከወለድኩ በኋላ ደግሞ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ምን ያህል ሳምንታት ልቆይ?

ውድ ክርስቲን፥

ሀ) የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በእርግዝና ወቅት፦ እስከ 8ኛ ወር መጨረሻ ቀጥይና 9ኛ ወር ላይ አቁሚ። ሆድሽ በገፋበት ጊዜ እንኳ ሕመም ሳይሰማሽ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ልትፈጽሙ የምትችሉበትን አተኛኘት ከባለቤትሽ ጋር መነጋገር ትችላላችሁ።

እስከ ስምንት ወራት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም መቻልሽ ባለቤትሽን ደስ ያሰኘዋል። አንቺም ደስተኛ ትሆኚያለሽ። የሴት ብልት ከንፈሮች በእርግዝና ወቅት ከሌላ ጊዜ የበለጠ ስለሚነዝሩ ሴቶች በእርግዝና ወቅት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም በጣም ያስደስታቸዋል።

*ለ) የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከወሊድ በኋላ፡-* በአብዛኛው ሴቶች ከወለዱ በኋላ ለአምስት ሳምንታት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም። ሆኖም ግን አንዳንዴ የሴቶች ብልት በወሊድ ጊዜ ይቀደዳል። እንዲህ ሲሆን ስድስት ወይም ከዚያ በላይ ሳምንታት መቆየት አለባቸው። ስለዚህ ሐኪምሽ /ነርስሽ የሚልሽን ማንኛውም ነገር አድርጊ።

ሚሪየም፡- የአምስት ወር እርጉዝ ነኝ። ከባለቤቴ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አልደፍርም። የዘር ፍሬው በማኅፀኑ ያለውን ሕፃን ይጎዳው ይሆናል ብዬ እፈራለሁ።

ውድ ሚሪየም፥




አትስጊ። አንዲት ሴት በምታረግዝበት ወቅት በማኅፀኗ መግቢያ ላይ የሚፈጠር መዝጊያ አለ። ይህ አካል የወንዱ ዘር ፍሬ ወደ ማኅፀኗ እንዳይገባ ይከላከላል።

ስለዚህ ሚሪየም ከባለቤትሽ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም አትፍሪ። የወንዱ ዘር ፍሬ ሕፃኑ ላይ ሊደርስ አይችልም።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረጉን እስከ 8ኛው ወር መጨረሻ ድረስ ቀጥይ። ከዚያም ከወለድሽ ከ5 ሳምንት በኋላ እንደገና ጀምሪ።

ብሬንዳ፡- ጡቶቼ ትናንሽ ናቸው፥ ወተቴም ቀጭንና ውኃ መሰል ነው። በሱቅ የሚሸጥ ወተት ከጡት ወተት ይሻላልን?

ውድ ብሬንዳ፥

አይሻልም። በሱቅ የሚሸጥ ወተት ከጡት ወተት *አይሻልም*። እንዲያውም ለልጅ ከእናት ጡት ወተት የሚሻል አንዳችም ነገር የለም።

በሱቅ ውስጥ የሚሸጡ የዱቄት ወተቶች በሙሉ የተሠሩት ከላም ወተት ነው። የላም ወተት ከሰው ወተት በጣም የተለየ ነው። አንድ ጥጃ ከተወለደ

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ቆሞ መሄድ መቻል አለበት። ስለዚህ የላም ወተት አጥንትንና ጡንቻን የሚገነቡ በርካታ ነገሮች አሉት።

በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ግን በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ከሁሉም በፍጥነት የሚያድገው *አእምሮ* ነው። *የእናት ጡት* ወተት ሕፃኑ *በአእምሮና በአካል* እንዲያድግ የሚረዱትን ፕሮቲኖች በሙሉ የያዘ ነው።

የእናታቸውን ጡት ከጠቡ ሕፃናት ይልቅ በጡጦ ሌሎች ወተቶችን የተመገቡ ሕፃናት በቀላሉ በበሽታ ይጠቃሉ። ምክንያቱም የእናት ጡት ወተት ሕፃናትን የሚጎዱ በሽታዎችን የመከላከል ኃይል አለው። (በጡጦ የሚወስዱ ሕፃናት ግን የላም በሽታዎችን ለመከላከል የተዘጋጁ ናቸው።)

*በዓለም ዙሪያ ያሉ የሠለጠኑ ሴቶች ልጆቻቸውን ጡት ማጥባትን መምረጥ ጀምረዋል። የእናት ጡት ወተት ከሁሉ የላቀ ነው!*

ጡጦ የሚያመርቱ ድርጅቶች እናቶች ልጆቻቸውን በጡጦ እንዲመግቡ ለማሳመን ይጥራሉ። እውነቱ ግን እናት የጡት ወተቷን ለልጁ ለመመገብ የማትችልበት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ልጁን በጡጦ የሚሰጡ ሌሎች ወተቶችን መመገብ አይገባትም።

በመጨረሻ፥ ብሬንዳ ስለ ጡቶችሽ መጠን አትስጊ። ትናንሽ ጡቶች የትላልቆቹን ያህል ወተት ሊያመነጩ ይችላሉ። የጡትሽ ወተት ቀጭን ቢመስልሽም አትጨነቂ። የጡት ወተት ደካማና ቀጭን ቢመስልም *ለሕፃንሽ ከሁሉ የላቀ ምግብ ነው።*

*ኢቴል፡—* ሕፃኔን አጠባለሁ። መብላት የሌለብኝ ምግብ አለን?

ውድ ኢቴል፥

የጡት ወተትሽ ጤነኛ እንዲሆን ኮምጣጣ የሆኑ ወይም ቅመም የበዛባቸው ምግቦች አትመገቢ። ቢራ ወይም ማንኛውም አልኮል አትጠጪ። ደግሞም ሲጋራ በፍጹም አታጭሺ።

ጄን፡— ባለቤቴ ክርስቲያን ነው። ነገር ግን ከእኔ ይልቅ ለጥንቸሎቹ የበለጠ እንክብካቤ ያደርጋል።

በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ጥንቸሎችን የሚያረባበት ትልቅ የንግድ ድርጅት አለው። ከሴት ጥንቸሎቹ አንዷ ወልዳ ግልገሎች ሲኖሩአት ወዲያውኑ እንድታረግዝ አይፈቅድላትም። «እንደገና ጉልበቷ እስኪጸና ጊዜ ያስፈልጋታል» ይላል።

እኔ ግን ጉልበቴ ሳይጸና ደግሜ ደጋግሜ እንዳረግዝ ያደርገኛል። በሦስት ዓመት ወስጥ ሦስት ልጅ የወለድኩ ሲሆን፥ አሁንም ነፍሰ ጡር ነኝ። እግሮቼን የሚያመኝ በየዓመቱ በማርገዜ እንደሆነ ነርሷ ነግራኛለች።

እህቴ አራርቆ የመውለዱን ዘዴ ትጠቀማለች። እርሷና ባሏ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉት ልታረግዝ በማትችልባቸው ቀናት ነው።

እኔ ግን ለባለቤቴ በዚህ ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብንፈጽም አረግዛለሁ፥ ስለዚህ እንለፈው ብል አይሰማኝም። በዚያም ቀን እንኳ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ይፈልጋል።

ምን ይበጀኛል ትሉኛላችሁ? ለአንዲት ሴት አራርቆ መውለድ አይጠቅማትምን?

ውድ ጄን፥

አዎን አንዲት ሴት ሁለት ዓመት ያህል አራርቃ ብትወልድ ይሻላታል። ለምን? ሁለት ምክንያቶች አሉ፦

ሀ) ለሁለት ዓመት ያህል አረፍ ማለት እናቲቱ ጤነኛ ሆና እንድትኖር ይረዳታል። አንዲት እናት ከዚህ ባነሰ ርቀት ደጋግማ የምታረግዝ ከሆነ ሰውነቷ ደካማ ይሆናል። በዚህም ምክንያት እንደ ሳንባ ነቀርሳ ባሉ በሽታዎች በቀላሉ ትጠቃለች።

ለ) በየሁለት ዓመት ርቀት የሚወለዱ ሕፃናት እያንዳንዳቸው ለረጅም ጊዜ ጡት እንዲጠቡ ስለሚረዳቸው ለእነርሱም መልካም ነው።

ባለቤትሽ ጤነኛ ሚስትና ጠንካራ ልጆች የሚፈልግ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ይህንን ለማድረግ አራርቆ የመውለድ ዘዴን እንድትጠቀሚ ዕድል መስጠት አለበት። ከእርሱ ጋር ይህን ተነጋገሩ። የምታነጋግሪው በአክብሮት ይሁን። ሊረዳሽ ካልቻለ ግን በአንድ ላይ ሆናችሁ መጋቢያችሁን ወይም ሐኪማችሁን እንድታነጋግሩ አሳብ አቅርቢለት።

ሳምሶን፦ እኔና ባለቤቴ ለአራት ዓመታት ልጅ አልወለድንም ነበር። በዚህ ዓመት ወንድ ልጅ ወለደችልኝ። እግዚአብሔርን በጣም አመሰገንን።

አሁን ልጃችን ሁለት ወራት ሆኖታል። ችግሩ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ስፈልግ «ሕፃኑ ጡቱን እስከጠባ ድረስ ይህን ማድረግ አንችልም» ትለኛለች።

የፍተወት ሥጋ ግንኙነት ከፈጸመች የዘር ፍሬው የጡቷን ወተት እንደሚመርዘው ብዙ ሰዎች ነግረዋታል። ይህ እውነት ሊሆን ይችላልን?

ሁለተኛው ጥያቄዬ፦ የቤተሰብ ምጣኔ መልካም ነው ወይስ መጥፎ?

ውድ ሳምሶን፥

የወንድ ዘር ፍሬ የጡት ወተትን ሊያበላሽ (ሊመርዝ) አይችልም። ሰዎቹ የነገሯት ውሸት ነው።

ልጅ ከወለዳችሁ በኋላ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሳታደርጉ መቆየት ያለባችሁ ለአምስት ሳምንታት ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እንደገና መቀጠል ትችላላችሁ።

ነገር ግን አንዲት ሴት በሁለት ዓመት ልዩነት አራርቃ የመውለዷን አስፈላጊነት መዘንጋት የለብህም። ስለዚህ ባለቤትህ መቼ ማርገዝ እንዳለባት

ተመካከራችሁ መወሰን አለባችሁ። ለምሳሌ አራርቀን የምንወልድበት ርቀት 3 ዓመት ይሆናል ብላችሁ ከወሰናችሁ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት እንዳታረግዝ መጠንቀቅ አለባችሁ።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እያደረጋችሁ እርግዝናን ልታቅቡ የምትችሉት እንዴት ነው? ለዚህ አንዱን ዓይነት የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ መጠቀም አለባችሁ። የቤተሰብ ምጣኔ በጣም መልካም ነው።

ኢሊየት፡- ዛሬ እኔና ባለቤቴ ከፍተኛ ሙግት ገጠምን። «ለሚቀጥለው ሁለት ዓመት አልጋ መለየት አለብን። ማርገዝ የምፈልገው ከዚያ በኋላ ነው» አለችኝ።

ያለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለሁለት ዓመት መኖር አልችልም። የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴን መጠቀም አይሻልምን?

የትኛውን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ እንድንጠቀም ትመክሩናላችሁ

ውድ ኢሊየት፥

የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎችን መጠቀም የተሻለ ነው። ባልና ሚስት ለሁለት ዓመት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈጽሙ ለመቆየት ከሞከሩ አንዳቸው ወይም ሁለቱም ሊያመነዝሩ ይችላሉ።

ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፥ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ (1ኛ ቆሮ. 7፡5)።

ስለዚህ ኢሊየት አንተና ሚስትህ ለሁለት ዓመት ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመታቀብ አትሞክሩ።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረጋችሁን ቀጥሉ። ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ባለቤትህ እንዳታረግዝ ከቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች አንዱን ተጠቀሙ። በእኛ አስተሳሰብ «ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ» ብትጠቀሙ ይሻላል።

ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴን በሁለት መንገዶች መጠቀም ይቻላል።

1) እርግዝናን ለማቀብ፡- ባልና ሚስት የሚቀጥለውን ልጅ ለማግኘት የወሰኑበት ጊዜ እስኪደርስ እርግዝና እንዳይኖር ይህን ተፈጥሮአዊ ዘዴ መጠቀም ይችላሉ።

2) እርግዝና እንዲኖር ለማድረግ፡- ሚስቲቱ ከዚህ በፊት ያልወለደች ከሆነ ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ እንድታረግዝ ይረዳታል።

ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ የሚደረገው ባጭሩ እንደሚከተለው ነው። በዕለቱ ሴቲቱ የብልቷ ከንፈሮች ረጥበው እንደሆነ ትመለከታለች። ይህ «ማርገዝ የሚቻልበትንና የማይቻልበትን» ቀን ያመለክታል።

> ማስታወሻ፡- ስለ ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ የበለጠ ለመረዳት ከገጽ 96–116 ያሉትን ደብዳቤዎች ተመልከት።

ሪያን፡- ባለቤቴ አላረገዘችም። ከተጋባን ሁለት ዓመት ሆኖናል። ሁለታችንም ልጅ በጣም እንፈልጋለን።

እርሷ የምትሠራው በሌላ ከተማ ስለሆነ በየሳምንቱ እንገበኛታለሁ። አብረን በምንሆንበት ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብናደርግም እስካሁን ግን ልጅ የለንም!

ውድ ሪያን፥

ምናልባት የሚከተሉትን ሁለት እውነታዎች አላወቅህ ይሆናል።

ሀ) በሴት ወርሃዊ የወር አበባ ዑደት ልታረግዝ የምትችልባቸው ቀናት ጥቂት ናቸው። እነዚህ ጥቂት ቀናት የመፀነሻ ቀናት በመባል ይታወቃሉ።

ለ) አንዲት ሴት እነዚህን የምትፀንስባቸውን ቀናት ለማወቅ መማር ትችላለች። ልብ ማለት ያለባት በእያንዳንዱ ወርሃዊ ዑደት ሰውነቷ ምን እንደሚያደርግ ነው።

> የአንተ ባለቤት ችግር ለማርገዝ ያለመቻል ነውና የመፀነሻ ቀናትን እንዴት ልብ ማለት እንዳለባት መማር አለባት። *በእነዚያ ቀናት* የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸማችሁን እርግጠኞች መሆን አለባችሁ።

አንዲት ሴት የመፀነሻዋን ቀናት ለማወቅ ልትረዳቻው የሚገቡ አንዳንድ እውነታዎች አሉ።

በየወሩ የሴት ብልት *ሁለት* ዓይነት ፈሳሾችን ያመነጫል። አንዱ ደም ሲሆን ሌላው ደግሞ ወፈር ያለ ውኃ መሳይ ፈሳሽ ነው።

እያንዳንዷ ሴት ስለ ደሙ ታውቃለች፥ ነገር ግን ብዙ ሴቶች ሌላኛውን ፈሳሽ ልብ ማለት ያቅታቸዋል። ይህ ፈሳሽ ቀለም የሌለው ሲሆን በጥሬ እንቁላል ውስጥ ያለውን ቀለም አልባ ፈሳሽ ይመስላል።

አንዲት ሴት በሰውነቷ ውስጥ የሚካሄደውን ነገር በጥንቃቄ ካስተዋለች የሚከተለውን ስለምትገነዘብ እንዲህ ትላለች፡-

«በየወሩ ጥቂት ደም የማይባቸው ቀናት አሉ፡- በዚያው ወር ዘግየት ብሎ ደግሞ ጥቂት ቀለም አልባውን ፈሳሽ የማይበት ቀናት አሉ። ይህን ፈሳሽ በማይባቸው ቀናት የብልቴ ከናፍርት ረጠብ ይላሉ። ፈሳሹን የማላየው በጣም ጥቂት ስለሆነ ነው። ነገር ግን መኖሩ ቀኑን ሙሉ ይሰማኛል። ስቀመጥ፥ ስራመድ...የብልቴ ከናፍርት የእርጥበትና የማሙለጭለጭ ስሜት አለው። የብልት ከናፍርቶቼ በእንቁላል ንጹሕ ፈሳሽ እንደተሸፈኑ ዓይነት ይሰማኛል። ይህ ፈሳሽ በብልቴ ከናፍርቶች ላይ ለጥቂት ቀናት ይኖራል። ከዚያ በኋላ

ይጠፉና ከናፍርቶቹ ለሁለት ሳምንታት ደረቅ የመሆን ስሜት ይኖራቸዋል። ከዚያ በኋላ የምደማበት ቀን ይጀምራል።»

ከላይ የተነጋገርነው የእርጥበት ስሜት በብልት *ውስጥ ሳይሆን* ከብልት *ውጭ በከናፍርቶች ላይ ያለው* ነው። የብልቷ ውስጠኛ ክፍል ሁሌም እርጥብ ነው። (ልክ የአፍ ውስጠኛ ክፍል እርጥብ እንደሆነ ማለት ነው።) ብልትን የሚሸፍኑት ከናፍርት ግን አንዳንድ ጊዜ እርጥብ አንዳንድ ጊዜ ደረቅ ይሆናሉ። እነዚህ የብልት ከናፍርት ሲረጥቡ ሴቷ «ቀለም የሌለው ፈሳሽ ከማይበቸው ቀናት አንዱ ነው» ትላለች።

እነዚህን ቀናት የምታውቅ ሴት ደስተኛ ናት። ለባለቤቷ እንደዚህ ልትለው ትችላለች። «ዛሬ ላረግዝ እችላለሁ። ይህ ቀን ከእነዚያ ጥቂት የመፀነሻ ቀናት አንዱ ነው።» ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ እንደዚህ ልትለው ትችላለች «ዛሬ ላረግዝ አልችልም፤ የማልፀንስበት ቀን ነው።»

የሚያሳዝነው ነገር ግን ብዙ ሴቶች እንደዚህ ዓይነት እውቀት የላቸውም። የሚያውቁት «በየወሩ ለጥቂት ቀናት እደማለሁ...በሌሎች ቀናት ከባለቤቴ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እችላለሁ። የመፀነሻ ቀን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። በየትኞቹ ቀናት ላረግዝ እንደምችል አላውቅም። ምናልባት አረግዛለሁ ወይም አላረግዝም ...እንጃ» ማለትን ነው።

ስለዚህ ሴቶች ማወቅ ያሻቸዋል። ስለ ቀለም አልባው ፈሳሽ፥ ስለ መፀነሻ ቀናትንና መፀነስ ስለማይቻልባቸው ቀናት ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

| እያንዳንዱ ሴት ማወቅ የሚያስፈልጋት ነገር |
| --- |
| ◆ የሴት የወር አበባ ዑደት በአምስት የመድማት ቀናት ይጀምራል። |
| ◆ ከዚያ በኋላ የብልቷ ከናፍርት ይደርቃሉ። ይህ የድርቀት ስሜት ለበርካታ ቀናት ይቀጥላል። |
| ◆ ከዚያ የብልቷ ከናፍርት የእርጥበት ስሜት ይሰማቸው ይጀምራል። ይህም የሚነግራት ቀለም የሌለው ፈሳሽ የምታይበት ቀን ተጀመረ ማለት ነው። ሰውነቷ ይህን ፈሳሽ ማመንጨቱን ለጥቂት ቀናት ይቀጥላል። |
| ◆ ከእነዚያ ጥቂት የእርጥበት ቀናት በኋላ የብልቷ ከናፍርት እንደገና ይደርቃሉ። የመድረቁ ስሜት ለሁለት ሳምንታት ይቀጥላል። |
| ◆ ከዚያ ተከታዩ የወር አበባዋ ዑደት በመድማት ይጀምራል። |

## ቀለም አልባው ፈሳሽ

እንዲት ሴት ይህን ቀለም አልባ ፈሳሽ የምታይባቸውን ቀናት ማወቅ ለምን ያስፈልጋታል? ምክንያቱም ይህ ነው። አንዲት ሴት በእነዚህ ቀናት

በቀላሉ ታረግዛለች። ይህም የሚሆነው የወንድ የዘር ፈሳሽ በቀለም አልባው ፈሳሽ ውስጥ በቀላሉ መንቀሳቀስ ስለሚችል ነው።

ስለዚህ አንድ ወንድ ሚስቱ ከእነዚህ ቀለም አልባ ፈሳሽ ከምታይባቸው ቀናት በአንዱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካደረገ የዘር ፍሬው በዚህ ፈሳሽ ውስጥ በቀላሉ አልፎ ወደ ሴቲቱ እንቁላል በመግባት ሊያስረግዛት ይችላል። ይህ ፈሳሽ የትም በሌለበት ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ካደረጉ ግን የዘር ፍሬው የትም ሊንቀሳቀስ ስለማይችል ልታረግዝ አትችልም።



የወንድ ዘር ፈሳሽ በደረቅ የሴት ብልት ውስጥ ለመዋኘት አይችልም



የወንድ ዘር ፈሳሽ በቀለም አልባው ፈሳሽ ውስጥ በቀላሉ ይዋኛል

## የመፀነሻ ቀናት

አሁን ዋናውን ጥያቄ ለመመለስ ዝግጁ ነን። «ባልና ሚስት ልጅ ያገኙ ዘንድ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ያለባቸው በየትኞቹ ቀናት ነው?» መልሱ ይህ ነው።

ሴት ልታረግዝ (ልትፀንስ) የምትችልባቸው ቀናት

ሀ) ቀለም አልባውን ፈሳሽ በምታይባቸው ቀናት በሙሉ፥ እና

ለ) ቀለም አልባውን ፈሳሽ ካየችበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት ቀጣይ ሦስት ቀናት።

አንዲት ሴት የመፀነሻዋን ቀናት ልብ የምትልበት ከሁሉ የላቀ መንገድ በእያንዳንዱ ቀን የብልቷ ከናፍርት እንዴት እንደሆኑ በጥንቃቄ በመፈተሽ ነው። ከዚያ በየምሽቱ አንድ ሠንጠረዥ አዘጋጅታ «ደረቅ» ወይም «ቀለም አልባ ፈሳሽ» እያለች መጻፍ ነው።

ከዚህ በታች ሩት በተባለች ሴት የተሠራውን ሠንጠረዥ ተመልከቱ። (የእያንዳንዱ ሴት ሠንጠረዥ የተለያየ ነው።)

ሩት ይህን ሠንጠረዥ የሠራችው ማርገዝ ስለምትፈልግ ነው




ሩት ለማርገዝ ከፈለገች ‹በመጸነሻ ቀናት› በተለይም ደግሞ በ(ዋና..... ቀናት) ግንኙነት ማድረግ አለባት።

ሩት ታረግዝ ዘንድ ከሚፀነስባቸው ቀናት በየትኞቹም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ትችላለች፥ በተለይ ከሁሉ የተሻሉ በተባሉት ሁለት ቀናት።

*አስታውሱ ሴት የምትፀንስባቸው ቀናት ቀለም አልባ ፈሳሽ በምታይባቸው ቀናት በሙሉና የመጨረሻውን ፈሳሽ ካየችበት ቀን በኋላ ያሉት ሦስት ቀናት ናቸው።* ከላይ በተሰጠው ሠንጠረዥ ሩት እነዚህን የሚፀነስባቸው ቀናት ብላ ለይታቸዋለች።

አንዲት ሴት በሚፀነስባቸው ቀናት በሙሉ ማርገዝ ትችላለች ነገር ግን አንዳንዶቹ ቀናት ከሌሎቹ ይሻላሉ። ከሁሉም የተሻሉ የሚባሉት ሁለት ቀናት፦ 1) ቀለም አልባ ፈሳሽ የታየበት የመጨረሻ ቀንና 2) ከዚያም ቀጥሎ ያለው ቀን ናቸው።

ከላይ በተሰጠው ሠንጠረዥ ሩት እነዚህን ሁለት ቀናት ለይታቸዋለች። ማርገዝ ስለምትፈልግ እርሷና ባለቤቷ *በእነዚህ ሁለት ቀናት* የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው።

በዚህ ወር ሩት የ27 ቀናት የወር አበባ ዑደት ነበራት። በሚቀጥለው ምናልባት 30 ቀናት....ወይም 20 ቀናት ይሆናል። ይህ ችግር አይደለም። በእያንዳንዱ ወር አዲስ ሠንጠረዥ በማዘጋጀት ከሁሉ የተሻሉት ሁለት ቀናት፦

*1) ቀለም አልባ ፈሳሽ ያየችባቸው የመጨረሻ ቀንና 2) የሚቀጥለው ቀን መሆናቸውን ታረጋግጣለች።*

አሁን ሪያን ይህን ደብዳቤ ስናጠቃልል አንተና ባለቤትህ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እንነግራችሁ።

- ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ባለቤትህ የሩትን ዓይነት በገጽ 100 እንደተመለከተው ሠንጠረዥ ታዘጋጅ።

ለአንዲት ሴት የመጀመሪያውን ሠንጠረዥ ማዘጋጀት ቀላል አይደለም። በአንዳንድ ቀናት የብልቴ ከናፍርት ደረቅ ናቸው ወይስ እርጥብ በማለት ግራ ልትጋባ ትችላለች።

ባለቤትህን ተስፋ እንዳትቆርጥ አበረታታት። ሠንጠረዡን መሥራት ትማራለች። በጣም ከባድ አይደለም።

ስለሆነም ሪያን ልትረዳት አንድ ነገር ማድረግ ትችላለህ። የመጀመሪያውን ሠንጠረዥ በምትሠራበት ጊዜ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከእርሷ ጋር አታድርግ። ለምን? የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የብልቷን ከናፍርት ስለሚያረጥበው «ዛሬ የብልቴ ከናፍርት የረጠበው ከቀለም አልባው ፈሳሽ ነው ወይስ ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት? ሠንጠረዤ ላይ ምን ልጻፍ?» በማለት እርግጠኛ አትሆንም። ስለዚህ ራያን የመጀመሪያውን ሠንጠረዥ በምታዘጋጅበት የመጀመሪያው ወር ከባለቤትህ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንዳትፈጽም እንመክርሃለን።

- ከዚያ የመጀመሪያ ወር በኋላ ባለቤትህ ሠንጠረዡን በየወሩ መሥራት ትቀጥላለች። «አሁን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንችላለን፥ ምክንያቱም ልፀንስ ወይም ላረግዝ የምችልበት ጊዜ ነው» ስትልህ ደስተኛ መሆን ትጀምራለህ። ከጥቂት ቀናትም በኋላ «ዛሬና ነገ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የግድ ማድረግ አለብን፥ ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ቀናት ለማርገዝ ከሁሉ የተሻሉ ቀናት ናቸው» ትልሃለች።

- የፍትወተ ሥጋ ግኙነት በምትፈጽሙበት ጊዜ ምንም ዓይነት ቅባት-ነክ ማለስለሻ አትጠቀሙ (እንደ የቆዳ ሎሽን ዓይነት ማለት ነው።) እንደዚህ ዓይነት ቅባት-ነክ ነገሮች ሴቷ የብልቷ ከናፍርት የረጠቡት ቀለም አልባ በሆነው ፈሳሽ ይሁን ወይም በእነዚህ ቅባት-ነክ ነገሮች መለየት እንዲያስቸግራት ያደርጓታል። ደግሞም አንዳንድ ቅባት-ነክ ነገሮች የወንዱን

ፈሳሽ ዘር ይገድላሉ። ቅባት- ነክ ነገሮች ከመጠቀም ይልቅ ረጅም ጊዜ የፍቅር ጨዋታ በመጫወት የሴቷ ሰውነት የራሱን ተፈጥሮአዊ ቅባት ነክ ነገር እንዲፈጥር አድርጉ።

• አንድ ላይ የምትቆዩበትን መንገድ ለማግኘት ሞክሩ። የምትገናኙት በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት ብቻ ከሆነ ከሁሉ በተሻሉ የመፀነሻ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም እንዴት ትችላላችሁ?

• በዚህ ዓይነት ለጥቂት ዓመታት ከሞከራችሁ በኋላ ባለቤትህ ማርገዝ ካልቻለች በዚህ ጉዳይ ብቃት ያለውን ሐኪም አማክሩ።

• አስታውሱ፡- ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህ ልጆችን ለማግኘት የሚቻለውን ሁሉ መንገድ መፈለግ ስሕተት አይደለም። እንዲያውም ጥሩ ነው። ነገር ግን ልጆችን የሚሰጥ እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ምንም ያህል ሠንጠረዡን በጥንቃቄ እንሥራ፥ ወደ የትኛውም ሐኪም እንሂድ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ እስካልሆነ ድረስ ልጆች ሊኖሩን አይችልም።

ሪያን ስማኝ፥ አንተና ባለቤትህ ልጆች ካገኛችሁ መልካም ነው እግዚአብሔር ይመስገን! ልጆች ባይኖሯችሁም እንኳ እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁና የእርሱ ፈቃድ ለእናንተ ከሁሉ የላቀ መሆኑን አስታውሱ። ስለ ፍች በፍጹም አታስቡ። በሕይወት እስካላችሁ ድረስ አንዳችሁ ለሌላችሁ ታማኝ ሆናችሁ ኑሩ (ማቴ. 19፡9)።

ሪያን፡- ስለ ደብዳቤያችሁ እናመሰግናለን። አሁን አንድ ጥያቄ ብቻ አለኝ። ለመፀነስ (ለማርገዝ) የሚቻልባቸው ቀናት፡-

ሀ) ቀለም አልባ ፈሳሽ በሚታይባቸው ቀናት፥ እና

ለ) ቀጥሎ ባሉት ሦስት ቀናት እንደሆኑ ነግራችሁናል።

ሁለተኛው ክፍል አልገባኝም። አንዲት ሴት ቀለም አልባ ፈሳሽ ካየችበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት እንዴት የማርገዝ ዕድል ሊኖራት ይችላል?

ውድ ሪያን፥

ለምሳሌ አንድ ገበሬ ወደ እርሻው በታ አምጥቶ ሊተክለው የሚፈልገው የሽንኩርት ችግኝ አለው እንበል። መሬቱ ደረቅ ከሆነ የሽንኩርት ችግኙ ይሞታል። ስለዚህ የዝናብ ወቅት ጠብቆ በየቀኑ ችግኙን ወደ እርሻው ማስተላለፍ ጀመረ። ዝናቡ ሲቆም ቀጥለው ላሉት ሦስት ቀናትም መትከሉን ቀጠለ። ለምን? ምክንያቱም መሬቱ ውስጡ ረጠብ ብሎ መቆየቱ የታወቀ ስለሆነ ነው።

የአንተ የዘር ፍሬ ልክ እንደዚህ ችግኝ ነው። ስለዚህ የዘር ፈሳሽህን ቀለም አልባ ፈሳሽ ባለቤትህ በምታይበት ቀንና ካየችበት ከመጨረሻው ቀን ጀምሮ

ባሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ብታደርግ የሚፈለገው ተፈጽሟል ማለት ነው (ቀለም አልባው ፈሳሽ ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ርዝራዥ ስለሚኖር ነው።)

> ማስታወሻ፡- በተከታዩ ዓመት እግዚአብሔር የሪያንን ቤተሰብ ወንድ ልጅ በመስጠት እንደባረከ የሚገልጽ አስደሳች ደብዳቤ ደረሰን። በዚህ ደብዳቤው ሪያን የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቀን።

*ሪያን፡- «ይህንኑ ዘዴ እርግዝና ሊኖር የማይችልበትን ቀን ለመለየት መጠቀም አይቻልምን?»*

*ሌላ ልጅ አንፈልግም ማለቴ አይደለም። ሌላ ልጅ መፈለጋችን እርግጥ ነው። ነገር ግን ልጃችን እስኪጠነክርና እስኪበረታ ለሦስት ዓመት ያህል ሌላ ልጅ ሳንወልድ መቆየት እንፈልጋለን።*

*ውድ ሪያን፥*

የተወሰኑ ዓመታት ሳትወልዱ የመቆየታችሁን አሳብ እንደግፋለን።

*አዎን፥* ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴን ባለቤትህ እንድታረግዝ ብቻ ሳይሆን እርግዝናን ለመከላከል (አራርቆ መውለድ ይቻል ዘንድ) ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ።

*መንገዱ* እንደሚከተለው ነው። ባለቤትህ ሠንጠረዡን በየወሩ መሥራቷን ትቀጥል። አሁን ግን ምልክት የምታደርግበት መንገድ የተለየ ነው። በሚቀጥለው ገጽ ናሙና ሠንጠረዥ ታገኛለህ። በሠንጠረዡ ላይ እንደምትመለከተው *ሁለት ዓይነት* ከእርግዝና ነፃ የሆኑ ቀናት አሉ። እነዚህም «ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት» እና «ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የኋለኞቹ ቀናት» ናቸው።

«ከእርግዝና ነፃ በሆኑ የኋለኞቹ ቀናት» ባልና ሚስት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በማንኛውም ጊዜ ለመፈጸም ነፃ ናቸው።

«ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የኋለኞቹ ቀናት» የተባሉት ግን የተለዩ ናቸው። ለእነዚህ ቀናት ያሉትን ሕግጋት ተመልከት፡-

ስለዚህ ሪያን አንተና ባለቤትህ መረዳት ያለባችሁ አራት ነገሮች ብቻ አሉ።

1) አንዲት ሴት *የወር አበባዋን ካየች በኋላ* ለተወሰኑ ቀናት የብልቷ ከናፍርት ደረቅ የመሆን ስሜት አላቸው። በምትሠራው ሠንጠረዥ ላይ እነዚህን ቀናት «ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት» በማለት ምልክት ታድርግባቸው። በእነዚህ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ብትችልም ለእነዚህ ቀናት የወጡትን ሦስት ሕግጋት መከተል አለባት።
2) ቀጥሎ የብልቷ ከናፍርት እርጥበት ሊሰማቸው መጀመሩን ትረዳለች። በእነዚህ ቀናት በሠንጠረዡ ላይ «ቀለም አልባ ፈሳሽ» እያለች ትጽፋለች። እነዚህ ቀናት 5 ወይም 6 ሊሆኑ ይችላሉ። *እርግዝና እንዳይኖር በእነዚህ ቀናትና ከእነዚህ ቀናት በኋላ በሚኖሩ ሦስት*

ተከታታይ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለባትም። «ቀለም አልባ ፈሳሽ» የምታይባቸው ቀናትና ከዚያ በኋላ ያሉት 3 ተከታታይ ቀናት እርግዝና የሚኖርባቸው ቀናት ናቸው።

3) ከዚያ በኋላ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመጀመር ትችላለች። እነዚህ *ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የኋለኞቹ ቀናት* ናቸው። ለእነዚህ ቀናት ምንም ሕግ የለም። በእነዚህ ቀናት እርሷና ባለቤቷ የፈለጉትን ያህል የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ።

4) *ከኋለኞቹ የእርግዝና ነፃ ቀናት* በኋላ የወር አበባዋን ደም የምታይባቸው ቀናት ይጀምራሉ።

ሩት ይህንን ሠንጠረዥ የሠራችው ማርገዝ ስለማትፈልግ ነው።




እርግዝናን ለመከላከል ሩት በመጸነሻ ቀናት ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ትታቀባለች። ከእርግዝና ነፃ በሆኑ የፊተኞቹ ቀናት የሚሠሩትን ሦስት ሕጎችም ትጠብቃለች።

### ከእርግዝና ነፃ ለሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት የተሰጡ ሕጎች

1ኛ ሕግ ፦ ከእርግዝና ነፃ በሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጠዋት ሳይሆን ማታ ብቻ አድርጉ። በጠዋት የሚደረግ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የሴት ብልት ከናፍርት እርጥበት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ቀለም አልባ ፈሳሽ የሚመጣበት ጊዜ መድረሱን ለመለየት ሴቲቱ ትቸገራለች።

2ኛ ሕግ፡- ከእርግዝና ነፃ በሆኑ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት በተከታታይ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አታድርጉ። ቢያንስ አንድ ቀን በመሀሉ ዝለሉ። ለምን? ምክንያቱም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በየቀኑ የምታደርግ ከሆነ የብልቷ ከናፍርት እርጥበት ስለሚሰማቸው ቀለም አልባ ፈሳሽ መምጫው መድረሱን ለማወቅ ያስቸግራታል።

3ኛ ሕግ፡-የወር አበባ በሚታይባቸው ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አታድርጉ፤ ምክንያቱም እርግዝና ሊኖር ይችላል።

የአንዲት ሴት ሠንጠረዥ በየወሩ ሊለያይ ይችላል። አንዳንድ የወር አበባ ዑደት ረጅም ሲሆን፥ አንዳንዱ አጭር ሊሆን ይችላል። ሲረዝም እስከ 32 ቀናት ሊደርስ ይችላል፥ ሲያጥር 24 ቀናት እና እያለ ይቀጥላል።

አንዲት ሴት የወር አበባ ዑደቷ ረጅም ወይም አጭር መሆኑ የሚያመጣው ለውጥ የለም። በየወሩ በወር አበባ ዑደቷ መሠረት ሠንጠረዥ ማበጀት ያስፈልጋታል። (ረጅምም ቢሆን አጭር ምንም አይደለም።) በሠንጠረዡ መሠረት እርግዝና ሊኖራቸው የሚችልባቸውን ቀናት ትለያለች።



በዚህ ወር የሩት የወር አበባ ዑደት ረጅም ነበር።
የመጀመሪያዎቹ ነጻ ቀናት
የመጸነሻ ቀናት
የመጨረሻዎቹ ነጻ ቀናት
የመድማት ቀናት
ደረቅ
ቀለም አልባ
3 ቀናት




በዚህ ወር የሩት የወር አበባ ዑደት አጭር ነበር።
የመጸነሻ ቀናት
የመጨረሻዎቹ ነጻ ቀናት
የመድማት ቀናት
ደረቅ
ቀለም አልባ
ቀናት3
የመድማት ቀናት

## ልጅ ከተወለደ በኋላ

አሁን ልጅ ከተወለደ በኋላ የሴት የወር አበባ ዑደት እንዴት የተለየ እንደሆነ እንመልከት።

አንዲት ሴት ልጅ ከወለደች ከአምስት ሳምንት በኋላ ብልቷ ወደ ቀድሞው ሁኔታ ስለሚመለስ ከባሏ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ትችላለች። ነገር ግን ነፃ ነው ወይ? ከወሊድ በኋላ ያሉት ቀናት ነፃ ቀናት ናቸውን?

መልሱ ከልጅ መውለድ በኋላ ሴት በርካታ ከእርግዝና ነፃ የሆኑ ቀናት ይኖሯታል። በእነዚህ በርካታ ቀናት የብልቷ ከናፍርት በየቀኑ ደረቅ ይሆናሉ። ከዚያ አንድ ቀን በድንገት እርጥበት ይሰማታል። ይህ ሲሆን ልታረግዝ የምትችልባቸው ቀናት ተጀመሩ ማለት ነው። በእነዚህ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ መታቀብ አለባችሁ። (እነዚህ ቀናት ቀለም አልባ ፈሳሽ የሚታይባቸውና ከዚያ ቀጥሎ ያሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ናቸው።) ከዚያ በኋላ እርሷና ባለቤቷ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የሚችሉት ከእርግዝና ነፃ በሆኑ የኋለኞቹ ቀናት ነው። ከዚያ ልጅ ከወለደች በኋላ የመጀመሪያውን የወር አበባ ማየት ትጀምራለች። ከዚያ የተለመደውን የወር አበባ ዑደቷን (በግምት 30 ቀን የሆነውን) ትጀምራለች።

ሩት እንዲህ ብላለች፣ «ልጄን ከወለድኩ በኋላ ለ76 ቀናት ምንም የርእጥበት ስሜት አልተሰማኝም ነበር። በ77ኛው ቀን እርጥበት ይሰማኝ ጀመር። ስለዚህ ሠንጠረዥ የሚከተለውን ይመስላል።




ከልጅ መውለድ ጀምሮ ቀለም አልባ ፈሳሽ እስከሚታይበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ በሙሉ ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት እንደሆኑ አስተውል። ስእነዚህ ቀናት ሩትና ባለቤትዋ ከእርግዝና ነፃ የሆኑ የመጀመሪያዎቹን ቀናት ሕግ መከተል አለባቸው።

ልጅ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ቀለም አልባ ፈሳሽ እስከታያት ቀን ያሉት ቀናት በሙሉ በእርግዝና የመጀመሪያዎቹ ቀናት እንደሆኑ በሠንጠረዡ ላይ ትመለከታለህ። ይህ ማለት በእነዚህ ቀናት በሙሉ ከእርግዝና ነፃ የመጀመሪያዎቹ ቀናት ሕግጋትን መከተል አለባት ማለት ነው።

ሪያን አሁን ባለቤትህ አዲስ ሕፃን ያገኘችበት ጊዜ ስለሆነ የሚከተለውን አሳብ እንሰጥሃለን። ሕፃኑ ሦስት ሳምንታት እንደሆነው ባለቤትህ ሠንጠረዡን መሥራት መጀመር አለባት። የመጀመሪያው ሠንጠረዥ ረጅም ሆኖ ታገኘዋለች። ምናልባት 50 ቀናት ወይም 100 ወይም ከዓመት በላይ ሊሆን ይችላል። የሚያጠቡ እናቶች ብዙ ጊዜ በጣም ረጅም ሠንጠረዥ ይኖራቸዋል። ልጆቻቸውን በጡጦ የሚመግቡ እናቶች ደግሞ አጭር ሠንጠረዥ ይኖራቸዋል።

ሁለተኛ እርግዝና በቅርቡ እንዲኖር ስለማትፈልጉ ከእርግዝና ነፃ በሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀናት ሦስቱን ሕግጋት ተከተሉ። የእርግዝና ቀናት በሚባሉት ጊዜያት ደግሞ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ አታድርጉ።

ሔለን፦ በወር አበባዬ ወቅት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ከእርግዝና ነፃ መሆን እችላለሁን?

ውድ ሔለን፦

አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በወር አበባቸው ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙ ሴቶች ያረግዛሉ። ስለዚህ በወር አበባ ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ከእርግዝና ነፃ መሆን አይቻልም።

ለምሳሌ፥ አንዲት ሴት በጣም አጭር የወር አበባ ዑደት ቢኖራት (24 ቀን ብንል) የእርግዝናዋ ቀናት የሚጀምሩት የወር አበባዋን በምታይበት ወቀት ነው። (በገጽ 105 ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከቱ።)

ዶሮቲ፦ የምጠቀመው ተፈጥሮአዊውን የቤተሰብ ምጣኔ ሲሆን ግን አንድ ጥያቄ አለኝ። አንዳንድ ጊዜ ልክ የወር አበባ ዑደት ሲጀመር ጥቂት እርጥበት ይሰማኝና «ምናልባት ቀለም አልባ ፈሳሼን የማይበት ጊዜ ጅማሬ ይህ ይሆናል » እላለሁ። ግን እርግጠኛ አልሆንም። በዚህ ዓይነት ጊዜ ምን ማድረግ አለብኝ?

ውድ ዶሮቲ፥

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥምሽ በሠንጠረዥሽ ላይ «ቀለም አልባ ፈሳሽ?» ብለሽ ጻፊ። ከባለቤትሽ ጋር ተስማምታችሁ ለተከታታይ ሦስት ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አታድርጉ። በእነዚያ ሦስት ቀናት «ቀለም አልባ ፈሳሽ» በእርግጥ መምጣቱንና ያለመምጣቱን ታያለሽ።

ለምሳሌ፦ ሩት ጥቂት እርጥበት በ8ኛው ቀን ተሰማትና ይህ የቀለም አልባ ፈሳሽ ቀን ጅማሬ ሊሆን ይችላል አለች። እናም በሠንጠረዡ ላይ «ቀለም አልባ ፈሳሽ» ብላ ጻፈች። ለባለቤቷ ጉዳዩን አማክራ ለሚቀጥሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሳያደርጉ ቆዩ። ሆኖም ግን ዘጠነኛውና አሥረኛው ቀን ደረቅ ሆነው አገኘች። ይህ የሚያረጋግጠው ቀለም አልባ ፈሳሹ ገና ያለመምጣቱን ነው። ስለዚህ በ11ኛው ቀን ከባለቤቷ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸውን ቀጠሉ። (ከእርግዝና ነጻ የሚኮንባቸውና የመጀመሪያዎቹ ቀናት ሕግን በመከተል) በ14ኛው ቀን እንደገና እርጥበት ተሰማት።




አንድ ሴት ቀለም አልባው ፈሳሽ መድረሱን ባለማወቅ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የምትታቀብባቸው ቀናት «እርግጠኛ ያልሆኑ» ቀናት ናቸው።

ለባለቤቷ ነገረችውና ከፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ታቀቡ። በዚህኛው ጊዜ የእርጥበት ስሜት *ለበርካታ ቀናት ቀጠለ። ይህም ልታረግዝ የምትችልባቸው ቀናት መግባታቸውን ያረጋግጣል።* ስለዚህ ቀለም አልባ ፈሳሽ የሚታዩባቸው ቀናት በሙሉና በሚቀጥሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ ታቀቡ።

> አንዲት ሴት ቀለም አልባ ፈሳሽ ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ሲያቅታት «ቀለም አልባ ፈሳሽ?» ብላ መጻፍ አለባት። ከዚያም ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ግንኙነት መፈጸም የለባትም። ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ደረቅ ከሆነች ቀለም አልባ ፈሳሽ ገና አልመጣም ማለት ነው። ነገር ግን በእነዚህ ሁለት ቀናት የእርጥበት ስሜት የሚሰማት ከሆነ ቀለም አልባ ፈሳሽ መምጣት ለመጀመሩ እርግጠኛ ትሆናለች።

ይህንን ገጽ የራሳችሁን ሠንጠረዥ ለማበጀት ተጠቀሙበት።







ይህንን ገጽ ፎቶ ኮፒ አድርጎ በነጻነት መጠቀም ይቻላል።

ይህንን ገጽ የራሳችሁን ሠንጠረዥ ለማበጀት ተጠቀሙበት።







ይህንን ገጽ ፎቶ ኮፒ አድርጎ በነጻነት መጠቀም ይቻላል።

ቤቲ፡- ባለፈው ወር ወንድ ልጅ በሰላም ተገላገልኩ። አሁን ጡቴን አጠባው ዘንድ ከሥራዬ ዕረፍት ወስጄ በቤት እገኛለሁ።

እኔና ባለቤቴ ሁለተኛው እርግዝና ፈጥኖ እንዳይሆን ተስማምተናል። ጥያቄያችን ጡት ማጥባት እርግዝናን ይከላከላልን ወይስ ሌላ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ መጠቀም አለብን?

ውድ ቤቲ፥

ልጅሽን ማጥባት ትችይ ዘንድ ዕረፍት መውሰድሽ በጣም ጥሩ አድርገሻል። ጡት ማጥባት ሕፃንን በጡጦ ከመመገብ ይሻላል። ምክንያቱም ማጥባት በሕፃናት ላይ የመወደድን ስሜት ያሳድራል። ደግሞም ሕፃኑ ጤነኛና ጠንካራ ይሆን ዘንድ የእናት ጡት ወተት ከሁሉ የላቀ ነው።

ቀጥሎ ጥያቄያችሁን እንመልሳለን። ሕፃኑን በከፊል በጡጦ እየመገቡ በከፊል ማጥባት በቀላሉ እርግዝናን ሊያመጣ ይችላል። ነገር ግን ሕፃኑን ጡጦ ከልከለሽ በቀን አሥር ጊዜና ከዚያ በላይ የምታጠቢ ከሆነ ከወሊድ በኋላ ከ6-12 ወራት ድረስ ጡት ማጥባቱ እርግዝናን ምናልባት መከላከል ይችል ይሆናል።

አስታውሱ «ምናልባት» ይሆናል ነው ያልነው። ጡት ማጥባት *ሁልጊዜ እርግዝናን አይከላከልም*። ስለዚህ እርግዝናን ለመከላከል በማጥባት መተማመን አይገባም። ከልጅ መወለድ በኋላ አንድ ዓይነት የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ለእርግዝና መከላከያ መጠቀም መልካም ነው። ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴን እንድትጠቀሙ እናበረታታችኋለን። ይህ ዘዴ ሠንጠረዥ በመሥራት ሊረገዙ ብሚችልባቸው ቀናት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አለማድረግ ነው (ገጽ 103-108 ይመልከቱ።)

ክሊመንት፡- በመጀመሪያ እኔና ባለቤቴ ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ለመጠቀም አልፈለግንም ነበር። በማንኛውም ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ነፃ መሆን ፈልገን ነበር። እርግዝና የማይኖሩባቸውን ነፃ ቀናት ብቻ የመጠቀምን አሳብ አልወደድነውም ነበር።

በመጨረሻ ተፈጥሮአዊውን መንገድ ለመሞከር ወሰንን። ይህ ዘዴ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሕይወታችንን እንዴት እንዳሻሻለው ስናስብ እንደነቃለን። አንዳንድ ጊዜ ጥቂት ቀናት ማሳለፍና መጠብቅ እንዳለብን እውነት ነው። ነገር ግን መጠበቁ የተሻለ ያደርገዋል።

ውድ ክሊመንት፥

አዎን፥ ተፈጥሮአዊውን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ የተጠቀሙ በርካታ የትዳር ጓደኞች መጠበቁ ራሱ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሕይወታቸውን የተሻለ እንዳደረገው ይመሰክራሉ።

ዴኒስ፡- ሆድ ብሶኛል። ባለቤቴ እንደገና አርግዛለች። ነገሩ በጣም ፈጠነብኝ። ምክንያቱም ገና የአምስት ወር ሕፃን ነው ያለን። ይህ እንዴት

እንደሆነ አልገባኝም። ሁልጊዜ የዘር ፍሬዬን ከማፍሰሴ በፊት ብልቴን ወደ ውጪ በማውጣት በጭኖቿ መካከል ሳፈስስ ነበር የቆየሁት።

ውድ ዴኒስ፥

አንድ ወንድ ከባለቤቱ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርግበት ወቅት ብልቱን ወደ ባለቤቱ ብልት ሲያስገባ ፈሳሽን በተመለከተ ሁለት ነገር ይሆናል።

ሀ) ቀጭን የመጀመሪያው ፈሳሽ፡- ብልቱን ወደ ብልቷ ካስገባ ብዙ ሳይቆይ ከብልቱ የንጹሕ ፈሳሽ ጠብታ ይወጣል። ይህ ፈሳሽ ቀጭኑ የመጀመሪያ ፈሳሽ በመባል ይታወቃል።

ለ)ወፍራም የዘር ፈሳሽ፡- ከጥቂት ደቂቃ በኋላ የዘር ፍሬ ፈሳሹን ያፈስሳል። በዚህ ጊዜ አንድ ማንኪያ ያህል መጠን ያለው ነጭ ወፍራም ፈሳሽ ከብልቱ ይወጣል።

የዘር ፈሳሽህን በብልቷ ውስጥ ላለማፍሰስ ብልትህን ከብልቷ በማውጣት ተጠንቅቀህ ይሆናል። ነገር ግን ልትረዳው የሚገባህ ነገር *ቀጭኑ የመጀመሪያው ፈሳሽ የተወሰነ የዘር ፍሬ የያዘ መሆኑን ነው።* ስለዚህ ይህ ፈሳሽ ሴቲቱ እንድታረግዝ ሊያደርጋት ይችላል።

የዘር ፈሳሽ ከማፍሰስህ በፊት ብልትህን ከብልቷ በማውጣት እርግዝናን መከላከል የማትችለው ለዚህ ነው። ከዚህ የተሻለ ዘዴ ያስፈልግሃል። እኛ ተፈጥሮአዊውን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ እንድትጠቀም እናበረታታሃለን። (ገጽ 103–108ን ተመልከት።)

ኦዊን፡- አንዲት ሴት ቶሎ ቶሎ የምትወልድ ከሆነ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎቷ በጣም አነስተኛ ይሆናል የሚባለው እውነት ነውን?

ውድ ኦዊን፥

ቶሎ ቶሎ ያረገዘች ሴት ሁልጊዜ ድካም ይሰማታል። ስለዚህ ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነትም ሆነ ለማናቸውም ነገር አቅም ታጣለች።

በተደጋጋሚ ማርገዟ ሰውነቷን ስለሚያደክማት እንደ ሳንባ ነቀርሳ ላለ ሕመም ትጋለጣለች።

አማኑኤል፡- የቤተሰብ ምጣኔ ለማኅበረሰባችን አዲስ ነገር አይደለም። አባቶቻችን አራርቆ በመውለድ የእናቶችና የሕፃናት ጤና የተሻለ እንደሚሆን ተገንዝበው ነበር። በዚያን ዘመን ተደጋጋሚ እርግዝናን ለማስቀረት የተለያዩ ዘዴዎች ነበሯቸው። ከዘዴዎቻቸው አንዳንዶቹ ሠርተዋል ሌሎቹ ደግሞ አልሠሩም።

በአሁኑ ጊዜ ያለው ችግር አራርቆ ለመውለድ ብዙ ወጣት ባሎች የሚጫወቱት አንዳችም ሚና ያለመኖሩ ነው። ምንም ዓይነት የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ አይጠቀሙም። በውጤቱ ብዙ እናቶችና ልጆች ደካሞች ናቸው

(ወይም ይሞታሉ)። ምክንያቱም በሚወለዱ ልጆች መካከል ያለው ርቀት አነስተኛ ነው።

ለሚስቶቻችንና ለልጆቻችን ስንል አራርቆ የመውለድን ውጤታማ ዘዴዎች መጠቀም አለብን።

አንዲት ነርስ «እርግዝና የሚኖሩባቸው ቀናት የተባለውን ዘዴ አትጠቀሙ። አይሠራም።» አለችኝ።

የትኛውን ዘዴ እንድንጠቀም ትመክሩናላችሁ?

ውድ አማኑኤል፥

ተፈጥሮአዊውን የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ እንድትጠቀሙ እናበረታታችኋለን። ይህ ነርሷ የነገረቻችሁ ዓይነት ከእርግዝና ነፃ የሆነ ቀን አይደለም።

«ከእርግዝና ነፃ የሆኑ ቀናት» ዘዴ ወይም «ተፈጥሮአዊ» ዘዴ በማለት ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ሁሉ ጽፈዋል።

ነገር ግን የሚያሳዝነው በአብዛኛው እነርሱ ከእርግዝና ነፃ የሆኑ ቀናት ወይም ተፈጥሮአዊ መንገድ የሚሏቸው አይሠሩም። እነዚህን መንገዶች ተጠቅመው ከእርግዝና ያላመለጡ ሴቶች አሉ።

ሆኖም ግን እኛ የምንልህ መንገድ ይሠራል። ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ የምንለውን ይህን መንገድ የተጠቀሙ የትዳር ጓደኞች 95% ውጤታማ ሆኖ ያገኙታል።

በተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ሴቲቱ ልትፀንስ የምትችልባቸውን ቀናት የምታውቀው የብልቷን ከናፍርቶች እርጥበት በመከተል ነው።

ይህ ዘዴ አዲስ አይደለም። በእስያ፥ በአውሮፓ፥ በአፍሪካም ሆነ በአሜሪካ የሚገኙ አንዳንድ ሰዎችን ብታነጋግሩ አንዳንዶቹ አዎን በባሕላችን ለሴት ልጆቻችን ስለ ብልት ከናፍርት መርጠብ እናስተምራለን ይሉአችኋል። እናቶች ለሴት ልጆቻቸው «የብልት ከናፍርት የሚረጥቡባቸውን ጊዜያት መለየት እወቂ፤ ይህ ካገባችሁ በኋላ ይጠቅማችኋል» ይሏቸዋል። ከዚያም ከጋብቻው ጥቂት ቀን በፊት እናት ለልጇ ማርገዝ ትችል ዘንድ የብልት ከናፍርትን እርጥበት እንዴት እንደምትጠቀምና እንዴት አራርቃ መውለድ እንደምትችል ትነግራታለች።

አማኑኤል አራርቆ ለመውለድ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል በማለትህ ትክክል ነህ። በርካታ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎች አሉ። ተፈጥሮአዊ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ አስተማማኝ ስለሆነ፥ በሚገባ ስለሚሠራ፥ የሚያመጣው ምንም ችግር ስለሌለና የሚያስወጣው ወጭም ስለሌለ የሚመረጥ ነው።

ካሌብ፦ በጣም የምንወዳቸው አራት ሴቶች ልጆች አሉን። ነገር ግን ወንድ ልጅ እንዲኖረንም እንፈልጋለን። ባለቤቴ ምን ችግር ኖሮባት ይሆን? ወንድ ልጅ እንድትወልድ የሚያደርግ መድኃኒት ይኖር ይሆን?

ውድ ካሌብ፥

ባለቤትህ ምንም ችግር የለባትም። እውነታዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሁለት ዓይነት የዘር ፍሬዎች አሉ። «ወንድ የሚያስገኝ የዘር ፍሬና» «ሴት የሚያስገኝ የዘር ፍሬ»። ከባለቤትህ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምትፈጽምበት ጊዜ ሁሉ ሁለቱንም ዓይነት በርካታ የዘር ፍሬዎች በማኅፀኗ ታስገባለህ። ሁሉም የዘር ፍሬዎች ወደ እንቁላሏ ለመዝለቅ *ቢሽቀዳደሙም* አንዱ ብቻ ይሳካለታል።

ካሌብ የእናንተ ችግር ወንድ ልጅ የሚያስወልዱ የዘር ፍሬዎች መሽቀዳደም ተስኖአቸዋል ማለት ነው።

ለዚህ የሚሆን መልካም ዜና አለን። ወንድ ልጅ የሚያስወልደውን የዘር ፍሬ እንዲዘልቅ የምታስችልበት መንገድ አለ። እርሱም የሚከተለው ነው።

ባለቤትህ በየወሩ ከዚህ በታች እንደተሰጠው ዓይነት ሠንጠረዥ እንድትሠራ ጠይቃት። ይህን ሠንጠረዥ ለመሥራት በየቀኑ ብልቷ በቀለም አልባ ፈሳሽ መርጠቡን ወይም ደረቅ መሆኑን መከታተል አለባት።

ከባለቤትህ ጋር ቀለም አልባ ፈሳሽ በምታይበት *በመጀመሪያ* ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ካደረጋችሁ ሴት ልጅ የሚያስገኘው የዘር ፍሬ ያሸንፍና ሴት ልትወልዱ ትችላላችሁ

ሩት እንደገና ማርገዝ ፈልጋለች። ይህን ሠንጠረዥ ያዘጋጀችው እርሷና ባለቤቷ የሚፈልጉትን ጾታ ያገኙ ዘንድ ነው (ሴት ወይም ወንድ)።

ሴት ልጅ ከፈለጉ ሩት የመጀመሪያውን ቀለም አልባ ፈሳሽ ባየችበት ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አለባቸው።

ወንድ ልጅ ከፈለጉ ደግሞ ፈሳሹ እየጠፋ በሄደበት ቀን ወይም ኃይለኛ እርጥበት በተሰማት ቀን ማድረግ አለባቸው።



ነገር ግን የምትፈልጉት ወንድ ልጅ ስለሆነ የሚከተለውን አድርጉ። በየወሩ ቀለም አልባ ፈሳሽ በምታይባቸው ቀናት ሁሉ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ ታቀቡና ቀለም አልባ ፈሳሽ በጠፋበት ቀን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አድርጉ። ይህንን ለበርካታ ወራት አድርጉ። ባለቤትህ በዚህ መንገድ ማርገዝ ካልቻለች የፍተወተ ሥጋ ግንኙነት ቀለም አልባ ፈሳሿ በጣም በሚረጥብበት ቀን አድርጉት። እነዚህን ወንድ ልጅ ሊረገዝ የሚችልባቸውን ቀናት ያለማቋረጥ ስትጠቀሙ ምናልባት ወንድ ልጅ ለማስረገዝ የሚችለው የዘር ፍሬ ያሸንፍ ይሆናል።

አንዲት ሴት ወንድ ልጅ እንድትወልድ ሊያደርግ የሚችል መድኃኒት ይኖር እንደሆነ ጠይቀሃል። ፈጽሞ እንዲህ ዓይነት መድኃኒት የለም። አንዳንዶች ለዚህ የሚጠቅም ነው ብለው የሚሸጡት መድኃኒት ቢኖርም ውሸት ነው።

አሁን «የሴት ልጅ/የወንድ ልጅ ቀን» እያልን የተናገርነው ዘዴያችን እንኳ ሁልጊዜ አይሠራም። ስለዚህ ይህን ዘዴ ተጠቅመህም እንኳ ሴላ ሴት ልጅ ብታገኙ እግዚአብሔርን አመስግኑ። አዎን፥ እግዚአብሔር ይወዳችኋል። ስለዚህ ከሁሉ የተሻለውን እንደሚሰጣችሁ በማመን በእርሱ ተደገፉ (ማር. 14፡36)።

ማርጋሬት፦ ማርገዝ እፈልጋለሁ፥ ነገር ግን ከባለቤቴ ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸምን በኋላ የዘር ፍሬው ከብልቴ ወጥቶ ይፈስሳል።

ውድ ማርጋሬት፥

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸማችሁ በኋላ ወዲያውኑ በጀርባሽ ተኚ። ከዳሌዎችሽ በታች ደግሞ ትራስ አድርጊ። በዚያ ዓይነት ለ15 ደቂቃ ያህል ቆዪ ። ይህ ለማርገዝ እንድትችዪ ይረዳሽ ይሆናል።

ኢራስመስ፦ ባለፈው ሳምንት ሕፃኑ ልጃችን ታምሞብን ነበር። ወደ ሆስፒታል ወስደነው መድኃኒት ሰጡትና ተሻለው።

አሁን ዘመዶቻችን በጣም እየተቹን ነው። «ሕፃን ልጃችሁን ወደ ነጮች ሆስፒታል መውሰዳችሁ ስሕተት ነው። ወደ ባሕል መድኃኒት አዋቂ ዘንድ መሄድ ነበረባችሁ» ይሉናል።

ምን እንደምትሉ መስማት እንፈልጋለን። እኛ ክርስቲያኖች ወደ ባሕል መድኃኒት አዋቂ ዘንድ መሄድ አለብን ወይስ ወደ ነጭ ሐኪሞች ቤት መሄድ አለብን?

ውድ ኢራስመስ፥

ክርስቲያን ማድረግ ያለበት የሚከተለውን ነው። በእግዚአብሔር እንጂ በየትኛውም መናፍስት መታመን የለበትም።

ለምሳሌ በአሜሪካ እራሳቸውን «መናፍስተኞች/ፈዋሾች» ብለው የሚጠሩ በርካታ ሰዎች አሉ። ጥያቄዎችን ለመመለስ፥ ለመተንበይና ለመፈወስ የመናፍስትን ኃይል ይጠቀማሉ። ማንኛውም ክርስቲያን ወደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች መሄድ የለበትም። ለምን? ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ከመነጋገር ይልቅ ከሌሎች መናፍስት ጋር ይነጋገራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

«ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ እንዳትረከሱባቸውም አትፈልጓቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።» (ዘሌ. 19:31)።

እኛ ክርስቲያኖች ወደ ባሕል መድኃኒት አዋቂዎች መሄድ እንችላለን ወይ በማለት ጠይቀሃል። መልሱ ማንኛውም ክርስቲያን (ከእስያ፥ ከአሜሪካ፥ ከአፍሪካ፥ ከአውሮፓ ወይም ከየትኛውም ሌላ ስፍራ ቢሆን) በሌሎች መናፍስት ወደ ማይደገፉ ሐኪሞች መሄድ ይቻላል። ነገር ግን ከመናፍስት ጋር ግንኙነት ወደ ሚያደርግ ሐኪም ጋ መሄድ የለብንም። መናፍስት ስንል ከእግዚአብሔርና ከመንፈስ ቅዱስ ውጭ የሆነ ማንኛውም መንፈስ ማለትም ክፉ መናፍስት የቀደምት አባቶቻችን መናፍስት፤ ወዘተ... ናቸው።

አንዳንድ «ነቢያት»ና «ፈዋሾች» የእኔ ኃይል ከመንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ። እውነቱ ግን ከሙታንና ከሌሎች መናፍስት ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ መሆናቸው ነው።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥

> «ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና።» (1ኛ ዮሐ. 4:1)
>
> እነርሱም፦ የሚጮኹትንና ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው የሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉ? (ኢሳ. 8:19)

ሮዝሜሪ፦ እኔና ባለቤቴ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ በቤት ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች ይሰሙናል ብዬ እሰጋለሁ። አልጋችን ይጮሃል። ባለቤቴ ሰው ይሰማናል የሚል ስጋት የለበትም፤ እኔን ግን ያስጨንቀኛል።

ውድ ሮዝሜሪ፥

ወንዱ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜ በቀላሉ አይረበሽም። ስልኩ ሊጮህ፥ ልጆች ሊያለቅሱ ይችላሉ፥ እርሱ ግድ የለውም።

ሴት ግን በዚህ ጉዳይ የተለየች ናት። የሚያለቅስ ልጅ ወይም የሚንጫጫ አልጋ ይረብሻታል።

ወንዶች ከሴቶች የተለዩ ስለሆኑ እያንዳንዱ ሴት ከባሏ ጋር ምን እንደሚሰማት እንዲያውቅ በግልጽ መነጋገርን መልመድ አለባት። ስለዚህ ሮዝሜሪ ለባልሽ በግልጽ እንደዚህ በይው «እኛ ሴቶች ከወንዶች የተለየን ነን። በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ ድምጽ ያውከናል። አልጋችን ባይንጫጫ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን በተሻለ ሁኔታ ልፈጽም እችላለሁ»

ወዲያውኑ አልጋውን ሊያሠራ ወይም አዲስ ሊገዛ ይችላል!

ማርቆስና ዶሪስ፡- በባለትዳሮች የአንድነት ቀን እንደዚህ ስትሉ ሰምተናል «በትዳር ሕይወት ውስጥ ባል ሴትን ምን እንደሚሰባት ማወቅ አለበት። ሚስት ደግሞ ወንድን የሚሰበው ምን እንደሆነ ማወቅ አለባት»።

እንደዚህ ስትሉ ምን ማለታችሁ ነበር?

ውድ ማርቆስና ዶሪስ፥

እንደ ባልና ሚስት ወንዶች ከሴቶች እንዴት የተለዩ እንደሆኑ ማወቅ አለባችሁ ማለታችን ነው።

ዶሪስ፡- ወንዶች በሚያዩት ነገር ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እንደሚሳቡ መረዳት ያስፈልግሻል። አንድ ወንድ በመንገዱ ላይ እየተራመደ ሳለ የሚስብ የሴት ልጅ ገላ ቢያይ ስለ ሴቲቱ ምንም ባያውቅም እንኳ ወዲያውኑ የፍትወት ስሜቱ ይቀሰቀሳል። አንዲት ሴት የሰውነቷን ቅርጽ የሚያሳይ ስስ ልብስ ለብሳ በማየቱ ብቻ ብልቱ ይቆማል.....የፍትወት ስሜቱ ይነሣሣል በስሜቱ ይወሰዳል! ስለዚህ ፈተና ‹እምቢ› ብሎ ለሚስቱ በታማኝነት ይቆይ ዘንድ እራሱን መግዛት ይጠበቅበታል።

ማርቆስ፥ ሴቶች የተለዩ መሆናቸውን መረዳት አለብህ። ሴት ልጅ ስሜቷ የሚነሣሣው ወንዱ ስሜታዊ ፍላጎቷን ሲያሟላላት ነው። በስሜቷ የምትወሰደው ደግ፥ የሚንከባከብና አሳቧን የሚረዳ ወንድ ስታገኝ ነው። በሚያምር ገላ ልትሳብ ትችላለች። ነገር ግን ይህ ለእርሷ ቁጥር አንድ ጉዳይ አይደለም። በስሜቷ እንድትወሰድ የሚያደርጋት የሚያነጋግራት የሚያደምጣት፥ የሚያደንቃት ለምትፈልጋቸው ነገሮች ግድ የሚለው ወንድ ነው። ባሏ ያልሆነ እንደዚህ ዓይነት ሰው ስታገኝ ‹እምቢ› ብላ ፈተናውን ለማሸነፍ እራሷን መግዛት ይጠበቅባታል።

በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ እንኳ ባልና ሚስት ወንድና ሴት በፍትወት ስሜታቸው የሚሳቡበትን ጉዳይ ልዩነት ባለማወቅ በመኝታ ክፍሎቻቸው ውስጥ ችግር ይፈጠራል። ለምሳሌ ሚስት ምንም የማይስብ አሮጌ ቢጃማ ለብሳ ወደ መኝታ ቤት ትገባለች። ባሏ የፍትወት ስሜቱን የሚያነሣሣ ዓይነት ቢጃማ እንድትለብስ....ወይም ምንም ልብስ እንዳትለብስ ነው የሚጠብቀው። ቆንጆዋን ሚስቱን ለማየት ፈልጎ ሳይሆን ሲቀር እጅግ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይሰማዋል።

አንድ ነገር አእምሮውን እንደያዘውና እንዳልተደሰተ ብትገነዘብም እንኳ የሆነውን አታውቅም።

በሚቀጥለው ቀን ከሥራ ወደ ቤቱ ሲመለስ ለባለቤቱ ጥቂት ነገር ብቻ ይናገራል። ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ማንበብ ይቀጥላል። ሚስቱ ወይም ልጆቹ እንዲያውኩት አይፈልግም። በአራት ሰዓት ሲገናኙ ለባለቤቱ ከአሥር ያነሱ ቃሎችን ወርወር ያደርጋል። አይጠላትም። ነገር ግን በራስ ወዳድነት የእርሷን ሳይሆን የራሱን ፍላጎት ብቻ በማሰብና በመዝናናት ያሳልፋል።

ከዚያ በምሽት የመኝታ ሰዓት ሲደርስ ባለቤቱ ከመታጠቢያ ቤት እያንጻንጿን የሰውነቷን ክፍል የሚያሳይ ስስ ቢጃማ ለብሳ ስትወጣ ሲያይ ለተግባር ዝግጁ ሆኖ ወደ አልጋው ላይ ዘሎ ይወጣል!

ባለቤቱ ግን «ስለ እኔ አያስብም። እራሱን ለማርካት ብቻ ነው ሰውነቴን የሚጠቀምበት» ትላለች።

የሚፈልገውን እንዳያደርግ አትከለክለውም። እንዲጠቀምባት ትፈቅድለታለች። ግን እንደሚወዳት አይሰማትም– እንደተጠቀመባት ብቻ ትቆጥራለች።

እርሱ እንዴት ይሰማዋል? ያዝናል፥ ይከፋዋል ምክንያቱም ለተሳካ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የሚያስፈልጉ ሥልቶችን ሁሉ ቢከተልም እንኳ እርሷ ስሜቷ ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አይነሣሣም። «ያጠፋሁት ነገር ይኖር ይሆንን? ብልቴ በመጠኑ አነስተኛ ሆኖ ይሆንን?» በማለት ራሱን ይነዘንዛል።

ስለዚህ የሚከተለው ሊነገረው ይገባል። «የብልትህ መጠን በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ላይ የሚያመጣው ምንም ለውጥ የለም። የባለቤትህን ስሜታዊ ፍላጎት ለማሟላት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርግ። ለባለቤትህ መልካም ለመሆን እስከ መኝታ ሰዓት ድረስ አትጠብቅ። ቀኑን ሙሉ አፍቃሪዋ ሁን። ከባለቤትህ ጋር እንደ ጓደኛ ተነጋገር። እንደ ሰው ለእርሷ እንደሚገድህ አሳያት።

ባለቤቱም የሚከተለው ሊነገራት ይገባል «ሌሎች ወንዶች በአንቺ እንዲፈተኑ የሚያደርግ አለባበስን አስወግደሽ እንዲህ ዓይነቱን አለባበስ ለመኝታ ቤትሽ (ለባልሽ) ብቻ አድርጊው። ለባለቤትሽ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎትን የሚያነሣሣ አለባበስ ልበሺለት። ይህ ድርጊት «እወድሃለሁ – ማንንም – አይደለም አንተን ብቻ!» የሚል መልእክት ያስተላልፍለታል።

> በዓለም ዙሪያ ያሉ ወንዶችና ሴቶች የሚከተለውን መረዳት አለባቸው:–
>
> . ወንዶች የፍትወተ ሥጋ ፍላጎታቸው የሚነሣሣው በሚያዩት ነገር ነው።
>
> . ሴቶች የፍትወተ ሥጋ ፍላጎታቸው የሚነሣሣው ስሜታዊ ፍላጎታቸው ሲሟላላቸው ነው።

ሺርሊ፦ ሥራ በጣም ይበዛብኛል። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተምራለሁ። ሦስት ትናንሽ ልጆች አሉኝ። በየምሽቱ ቤቱን አጸዳለሁ፥ ልብሶች እተኩሳለሁ፥ በመጨረሻ የመኝታ ሰዓት ደርሶ ወደ መኝታ ስሄድ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ እስከማልችል በጣም ይደክመኛል። ለራሴ እንዲህ ብዬ እናገራለሁ «የባለቤቴን የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ለማርካት መቻል አለብኝ» ነገር ግን ብዙ ጊዜ በቀጥታ እንቀላፋለሁ። አሁን ባለቤቴ ማጉረምረም ጀምሯል። እባካችሁን እርዱኝ!

ውድ ሺርሊ፥

ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከሁሉ የተሻለው ጊዜ እኩለ ሌሊት አይደለም። ከባለቤትሽ ጋር ተነጋገሪ። በአንድነት ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የተሻለ ጊዜ ፈልጉ። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በጠዋት ለማድረግ ሞክሩ። ወይም እሑድ ከሰዓት በኋላ ምን ይመስላችኋል?

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለራስሽ እንዲህ ብለሽ ተናገሪ «ዛሬ የቤት ውስጥ ሥራዬን ሁሉ ትቼ ጊዜዬን ለትዳሬ እሰጣለሁ»። በዚያ ምሽት ልጆች በጊዜ እንዲተኙ አድርጊ። ማጽዳቱን ተይው። ወደ መኝታ ክፍል ገብተሽ የሚስብ ቢጃማ ለብሰሽ ባለቤትሽን ጥሪው። *ያንን ምሽት ሊረሳው የማይችለው ምሽት አድርጊለት!*

እርግጥ ነው የቤት ሥራሽን በየቀኑ ሳይሠራ ልትተይው አትችይም። ነገር ግን አልፎ አልፎ ልታደርጊው ትችያለሽ። ልታደርጊውም ይገባል! ለምን? ምክንያቱም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለትዳር ሕይወት በጣም አስፈላጊ ነው።

> ባሎች ሆይ ስሙ! መጽሐፍ ቅዱስ ሴት ደካማ ስለሆነች ባል ሚስቱን ማገዝ አለበት ይላል (1ኛ ጴጥ. 3፡7)።
>
> ይህ ማለት ሚስትህን በቤት ውስጥ ሥራዋ እርዳት ማለት ነው። ወደ ቤት ስትመጣ ዝም ብለህ አትቀመጥ። ልጆችህን ተንከባከብ። አጥበህ ለመኝታቸው አዘጋጃቸው። ከባለቤትህ ጋር ዕቃዎችን እጠብ። (አንዳንድ ወንዶች መኪናቸውን እያጠቡ ዕቃ ማጠብ እንደማይችሉ ማሰባቸው የሚያስደንቅ አይደለም!)
>
> ባለቤትህን ለመርዳት ፈቃደኛ ካልሆንክ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አልፈቀድክም ማለት ነው። እናም ትዳርህ በጣም የሚያስደስት አይሆንም ምክንያቱም ባለቤትህ ሁልጊዜ ትደክማለች!

ሊዲያ፦ በመጀመሪያዎቹ ሦስት የትዳር ዓመታት ወደ ከፍተኛው ጡዘተ ፍትወት ደርሼ አላውቅም ነበር። «ባለቤቴ ምን ማድረግ እንዳለበት ለምን አያውቅም? በስሜቴ እንድግልና ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት እንድደርስ ለምን አያደርግም?» በማለት የፍቅርን ጨዋታ በምንጫወትበት ጊዜ ሁሉ እራሴን እጠይቅ ነበር።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ካደረግን በኋላ እርሱ ወዲያውኑ እንቅልፍ ሲወስደው እኔ ግን ገና ስላልረካሁ በጸጥታ አለቅሳለሁ።

በመጨረሻ ከባለቤቴ ጋር ይህን ጉዳይ መነጋገር አለብኝ ብዬ ወሰንኩ።

እየፈራሁም እንኳ አደረግሁት። የፍቅር ጨዋታን በምናደርግበት ወቅት እንዲደባብሰኝ የምፈልገውን ሰውነቴን አሳየሁትና በእጆቹ ሰውነቴን መነካካቱን እንዴት እንደምወድ እነግረው ጀመር።

ወዲያውኑ ወደ ከፍተኛ እርካታ ደረጃ መድረስ ጀመርኩ። በጣም ተደሰትኩ። ከሁሉ አብልጦ የተደሰተው ግን ባለቤቴ ነበር! «ሚስቴን እንዴት ማርካት እንደምችል አዩልኝ!» የሚል ስሜት አለው።

ውድ ሊዲያ፥

ደብዳቤሽ በዓለም ዙሪያ ያሉ ባሎችንና ሚስቶችን በሚከተለው መንገድ እንደሚያበረታታ እናውቃለን፡

> «የፍቅር ጨዋታ በሚጫወቱበትና የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ጊዜ በግልጽ እንዲነጋገሩ፣ እርስ በርስ በመማማርም እንዲደሰቱ ያበረታታቸዋል።

ቪክተር፦ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በመኝታ ላይ የምንጠቀምባቸው የተለያዩ የአተኛኘት አቋሞች የትኞቹ ናቸው? ክርስቲያኖች የትኞቹን መጠቀም ይችላሉ?

ወድ ቪክተር

ክርስቲያን ባለትዳሮች የትኞቹንም ዓይነት የአተኛኘት አቋሞች መጠቀም ይችላሉ። እንዲያውም የተለያዩትን መጠቀም መልካም ነው። ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አቋም ብቻ መጠቀም ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ቮርባን የመጠጣት ያህል ያሰለቻል።

ብዙ ባለትዳሮች «ወንዱ ከላይ የሚሆንበትን» የአተኛኘት አቋም ይመርጣሉ። ይህ የአተኛኘት አቋም ያለው ጥቅም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተግባሩን ወንዱ ስለሚቆጣጠር ወንዱ የዘር ፈሳሹን ያለጊዜው እንዳያፈስ ይረዳዋል።

ሌሎች ባለትዳሮች ደግሞ «ሴቷ ከላይ የምትሆንበትን» የአተኛኘት አቋም ይመርጣሉ። የዚህ ጥቅም ደግሞ ሴቲቱ በምትፈልገው መንገድ በመንቀሳቀስ እርካታዋን እንድትገነባ ያስችላታል።

ሌላው የተለመደው የአስተኛኘት ዓይነት ሁለቱም ጎን ለጎን የሚሆኑበት ነው። በዚህ ዘዴ የወንዱ ብልት የሴቷን ብልት ጎንና ጎን ስለሚያሻሽ ለአንዳንድ ሴቶች በጣም እንዲደሰቱ የሚያደርጋቸው ነው።

ሌሎችም ዓይነት የአፈጻጸም ዘዴዎች አሉ። መቀመጥ፥ መቆም ወዘተ...

አንዳንድ ባለትዳሮች በርከት ያሉ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አፈጻጸም ዘዴዎችን የሚያሳዩ የቪዲዮ ፊልሞችን በመመልከት ስሕተት ይሠራሉ።

የሚሻለው መንገድ ይህ ነው፡-

> ምንም ዓይነት መጽሐፍ ወይም ቪዲዮ አትጠቀሙ። የራሳችሁን አሳብ በመሞከር ብቻ ተዝናኑ። ተደሰቱ። ከሁለት አንዳችሁ የምታስቧቸውን ማንኛውንም አሳብ ሞክሩ። ሊሠራ የማይችል አስቂኝ የአፈጻጸም ዓይነት ተጠቅማችሁ ሳይሳካላችሁ ቢቀር በሳቅና በፈገግታ ሸኙት እንጂ አትማረሩ። አንዳችሁ በሌላችሁ ደስ ይበላችሁ! ስለ ፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሁሉን እንደሚያውቅ ሰው አትሁኑ። ይልቁን አብራችሁ ተጫወቱ! ተሳሳቁ! ተዋደዱ! በትዳር ሕይወት ስላለው ደስታ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

ኢለን፡- በእርግዝና ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የተሻለው የአተኛኘት አቋም የትኛው ነው?

ውድ ኢለን፥

ለአንቺ ሕመም እንዲሰማሽ የማያደርግ ማንኛውም የአተኛኘት ሁኔታ በሕፃኑ ምንም ችግር የሚፈጥር አይደለም። ቀጥሎ አንድ ሁለት አሳቦችን እንሰጣለን።

ሀ) ከኋላ፡- ባልና ሚስት ጎን ለጎን ሆነው እርሷ ጀርባዋን ሰጥታ ስትተኛ እርሱ ወደ እርሷ በመዞር ብልቱን ከኋላ የሚያስገባበት፡- በዚህ አተኛኘት ባል የሚስቱን ሆድ ስለማይገፋ ለእርግዝና ወቅት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አፈጻጸም ጥሩ አተኛኘት ነው። የዚህ አተኛኘት ጉዳት የወንዱ ብልት ለሴቷ የፍትወተ ስሜት ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውን ናዝረ ብልቷን ያለመንካቱ ነው። ሆኖም ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ እንድትደርስ ሊረዳት ይችላል። እንዴት? ብልቱን ወደ ብልቷ እያስገባ ለስሜታዊ እርካታዋ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውን ናዝረ ብልቷን በጣቶቹ በመዳበስ ነው።

ለ) በመቀመጥ፡- ባል በወንበር ላይ ይቀመጥና ሚስት በጭኖቹ ላይ ተቀምጣ ሁለት እግሮቿን በሰውነቱ ጎንና ጎን የምታደርግበት ሁኔታ ነው። ይህን አቋም በተለይ በእርግዝና የመጨረሻ ሳምንታት ላይ መጠቀም በጣም ጥሩ ነው፥ ምክንያቱም በዚህ አቋም የወንዱ ብልት ወደ ሴቲቱ ብልት በጣም ጠልቆ አይገባም።

እራሳችሁን ከላይ በተጠቀሱት ሁለት የአፈጻጸም ዓይነቶች ብቻ አትወስኑ። አንቺና ባለቤትሽ የምታስቧቸውን ሌሎች የአተኛኘት ዓይነቶች

መሞከር ትችላላችሁ። አዳዲስ የአተኛኘት ዓይነቶች መሞከሩ ለሁለታችሁም አዝናኝ ይሆናል። አስታውሺ መስጋት የለብሽም። ምክንያቱም ለሆድሽ ሕመም የማይፈጥር ማንኛውም ዓይነት የአተኛኘት ዓይነቶች በሕፃኑ ላይ ምንም ችግር አያመጣም።

ትሮይ፡- የባለቤቴ ብልት ሁልጊዜ ደረቅ ስለሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ በምንሞክርበት ጊዜ ብልቴን ማስገባት ያስቸግረኛል። ብልቴን ለማስገባት ከመሞከሬ በፊት የሚያለሰልስ ቅባታማ ነገር ብልቴን መቀባት ይሻለኛልን? ምን ዓይነት... ቫዝሊን ወይስ ምን?

ውድ ትሮይ፥

ብዙ ጊዜ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በፊት የሚደረገው የፍቅር ጨዋታ አስደሳች፥ ስሜትን የሚያነሣሣ ለረጅም ጊዜ የሚደረግ ከሆነ ብልቷ በተፈጥሮአዊ ፈሳሽ ይረጥባል።

ትሮይ ስለዚህ የፍቅር ጨዋታችሁን ለማሻሻል ባለቤትህን «የፍቅር ጨዋታችን አስደሳችና አነቃቂ እንዲሆንልሽ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አሳይኝ ወይም ንገሪኝ» በላት። በተጨማሪ በቂ ጊዜ ውሰዱ። በፍጹም አትጣደፉ። የፍቅር ጨዋታው ቢያንስ ለ20 ደቂቃ ያህል ይቆይ።

ይህን ስታደርግ ባለቤትህ በቂ ተፈጥሮአዊ ፈሳሽ ስለምታመነጭ ምንም ዓይነት ሌላ የሚያረጥብ ፈሳሽ የማያስፈልግበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በሌላ በኩል ግን ምንም ነገር ብታደርግም የባለቤትህ ብልት አልረጥብ ይል ይሆናል። አንዳንድ ሴቶች የሚያመነጩት ተፈጥሮአዊ ፈሳሽ በጣም አነስተኛ ሲሆን የሌሎች ሴቶች ደግሞ ከፍተኛ ይሆናል። ባለቤትህ በጣም አነስተኛ ከሚያመነጩት መካከል የምትመደብ ከሆነ አለስላሽ ቅባት መጠቀም ያስፈልግሃል። ቫዝሊን ጥሩ አይደለም። ከዚህ ይልቅ ሎሽን መጠቀም ይሻላል። ሽቶ የሌለበት ሎሽን ተጠቀም። ሽቶ ግን የፍትወተ ሥጋ ብልቶችን ይጎዳል።

ግሎሪያ፡- ባለቤቴና እኔ ክርስቲያን ነን። ችግሩ *እርሱ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው!* በየምሽቱ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ይፈልጋል።

እኔ ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ንቁ ያልሆንኩበት ምክንያት ተወዳጅ ያለመሆኔ ስለሚሰማኝ ነው። ባለቤቴ በፍትወተ ሥጋ እርካታው እንጂ በሌላ ጊዜ ስለእኔ አይገደውም። ከእኔ ጋር ለመነጋገር ፍላጎት የለውም። ጓደኛዬ ለመሆን ፍላጎት የለውም።

ውድ ግሎሪያ፥

አንዳንድ ሰዎች በአንድ መንገድ መወደድን ሲፈልጉ፥ ሌሎች በሌላ መንገድ ይፈልጉታል። ከደብዳቤሽ እንደተገነዘብነው ባለቤትሽ የሚፈልገው በፍትወተ ሥጋ እንዲወደድ ብቻ ነው።

አንቺ በፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ጉዳይ ንቁ ስላልሆንሽ ምናልባት እንዲህ ብሎ ያስብ ይሆናል። «ባለቤቴ አትወደኝም። በሰውነቴ አትረካም አትደሰትም። ምናልባት ብልቴን ትንሽ ነው ብላ ታስብ ይሆናል። እርሷን በመውደድ የሚገባኝን እያደረግኩ ነው። በፈለገች ጊዜ ሁሉ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ልናደርግ ፈቃደኛ ነኝ። ሰውነቷን (አካሏን) እወደዋለሁ። እኔ በምወዳት መንገድ እንድትወደኝ እንደተመኘሁ ነው።

ለእርሱ ፍቅር አካላዊ ነገር ነው!

ነገር ግን ለአንቺ ፍቅር ስሜታዊ ነገር ነው።

ባለቤትሽ አንቺን እንደ ተራ አካል አድርጎ ሳይሆን በስሜቶችሽ ላይ ትኩረት ኖሮትና በመንከባከብ እንዲወድሽ ትፈልጊያለሽ።

ባለቤትሽ ግን ልክ እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት ፍቅር የምትፈልጊ ይመስለዋል። እርሱ የሚፈልገው ዓይነት ፍቅር ፍትወትን የማርካት ፍቅር ነው።

አንቺ በእርግጥ የምትፈልጊውን ነገር አያውቅም።

መንገር አለብሽ።

ስለዚህ ጉዳይ ከእርሱ ጋር መነጋገር አስቸጋሪ ይሆንብሻል፤ ነገር ግን መነጋገር አለብሽ። ለትዳር ሕይወት በግልጽ ንግግር መግባባት በጣም አስፈላጊ ነው።

ወደ አንድ ስፍራ ለመሄድ ቸኩሎ ባለበት ጊዜ ሳይሆን በቤት የሚቆይበትን ፀጥ ያለ ሰዓት ምረጪ። ከዚያም፤

ሀ) የምትፈልጊው ምን ዓይነት ፍቅር እንደሆነ ግለጪለት። መወደድ እንዲሰማሽ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ በቂ እንዳይደለ ይወቀው። ይልቁኑ እንደ አንድ ልዩ ሰብዓዊ ፍጡር ቆጥሮሽ እውነተኛ ፍላጎት ለአንቺ ሲያሳይ፤ እንደ ቅርብ ጓደኛው ከአንቺ ጋር የአሳብ ልውውጥ ሲያደርግ የመወደድ ስሜት እንደሚሰማሽ አሳውቂው።

ለ) የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለእርሱ የመወደድ ስሜት እንደሚፈጥርለት እንደተረዳሽና ከዚህ በኋላ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ፍቅርሽን ለመግለጽ ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ ልትተገብሪው እንደተዘጋጀሽ ንገሪው።

ከዚህ የአንድ ጊዜ ንግግር በኋላ ሁለታችሁም ሙሉ ለሙሉ የመወደድ ስሜት ታገኛላችሁን? አታገኙም። ነገር ግን ቢያንስ ባለቤትሽ እንዴት ሊወድሽ እንደሚገባ ይረዳል። ደግሞም ስሜታዊ ፍቅሩን ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ መስጠት እንደሚጀምር ተስፋ ይኖራል። አንቺም ደግሞ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ልትወጂው የቻልሽውን ሁሉ እንደምታደርጊ ተስፋ እናደርጋለን።

በመንግሥተ ሰማያት ሙሉ የመወደድ ስሜት ይኖራል። በዚህ ምድር ግን ሰዎች በቂ ፍቅር እንዲሰጡሽ ሊሰማሽ ፈጽሞ አይችልም።

ግሎሪያ:- አንዳንድ ጊዜ የምትፈልጊውን ፍቅር ሁሉ የሚሰጥሽን ለማግኘት ባልሽን ትተሽ ሌላ ወንድ እንድትፈልጊ ልትፈተኚ ትችያለሽ። እውነታው ግን በምድር ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ስሜታዊ ፍላጎቶሽን በሙሉ ሊያረካ አይችልም። ያንን ሊያደርግ የሚችል ኢየሱስ ብቻ ነው። ስለ ስሜታዊ ፍላጎቶችሽ ይገደዋል። በእርግጥ ስለሚወድሽ ከእርሱ ጋር ብዙ ጊዜ እንድትነጋገሪ ይፈልጋል።

ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት እንዲህ አላት

«ምክንያቱም አምስት ባሎች ነበሩሽ» ዮሐ. 4:18

«ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላት:- «ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ውኃ ይጠማዋል፤ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ለዘላለም ከቶ አይጠማም፤ ምክንያቱም እኔ የምሰጠው ውኃ፥ ለሚጠጣው ሰው ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ ምንጭ ይሆናል።» ዮሐ. 4:13-14

ሳሙኤል:- ባለቤቴ በጣም ግሩም ሰው ከመሆኗ ሌላ እውነተኛ ጓደኛዬም ናት። የፍትወት ፍላጎቷም ደግሞ ከፍተኛ ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምንፈጽምበት ወቅት እጅግ እንረካለን። ችግሩ ግን እኔ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በተደጋጋሚ እንድናደርግ እፈልጋለሁ።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸምን በኋላ ሰውነቷ ለአንድ ሳምንት ያህል የረካ ይሆናል። የእኔ እርካታ ግን ለአንድ ቀን ብቻ ነው።

ለእርሷ ደግሞ ሳትፈልግ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንባት ይገባኛል። ግን ምን ማድረግ እችላለሁ። ብዙ ቀን ለፍትወት እራብና ረሃቤ ሳይጠግብ ይቀራል።

ውድ ሳሙኤል፥

1. ሚስትህን ውደድ! ለፍትወት ያለህ ረሃብ ሙሉ ለሙሉ ባይጠግብም እንኳ ለባለቤትህ ፍላጎቶች ተጠንቀቅ። ከእርሷ ጋር የሚነጋገርና ስለ ችግሮቿ የሚገደው ደግ ባል ትፈልጋለች። ከራስህ ፍላጎት ይልቅ ለእርሷ ፍላጎት መጠንቀቅ አለብህ። እርሷም ደግሞ የራሷን ብቻ ሳይሆን የአንተን ፍላጎት ለማሟላት መጣር አለባት። ፍቅር ማለት ይህ ነው (1ኛ ቆሮ. 13:7)።

2. ብዙ ጊዜ ፍትወትህን የማርካት ጥማት እንዳለብህ ከባለቤትህ ጋር በግልጽ ተነጋገሩ። 1ኛ ቆሮ. 7:3-5ን በአንድነት አንብቡ። ይህ ክፍል ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ማሟላት እንዳለበት ይናገራል።

ይህም ሆኖ ሳሙኤል የፍትወት ፍላጎትህ የማይሟላባቸው ቀናት እንደሚኖሩ ተገንዘብ። ይህም ምንም አይደለም። ከፍትወት የበለጡ ነገሮች በሕይወት ውስጥ አሉ። የምትፈልገውን ያህል የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ባትፈጽምም እንኳ ደስ ሊልህ ይችላል።

ማስታወሻ ለሚስቶች፦ ሚስት ለባሏ የሚከተለውን በማለት ፍቅሯን ማሳየት ትችላለች። «በዚህ ምሽት ፍትወት ለመፈጸም ምንም ፍላጎት የለኝም፥ አንተ ከፈለግህ ግን ልታደርገው ትችላለህ»። በዚህ ጊዜ ፍትወት ለመፈጸም አንዱ ምቹ የአተኛኘት ዓይነት ሚስት ወደ ጎን በጸጥታ ተኝታ ከጀርባ በኩል ባል ሲገናኛት ነው።

አግነስ፦ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መደሰት አልቻልኩም። ስሜቴ ቢነቃቃና ደስታን ባገኝ እወድ ነበር። ነገር ግን ፈጽሞ አልተሳካልኝም። በጣም ጥሩ ባል አለኝ። ፍትወተ ሥጋ ለመፈጸም የፍቅር ጨዋታ በምንጫወትበት ጊዜ ስሜቴ እንዲነቃቃ ለማድረግ ይጥራል። ነገር ግን በምንፈጽመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምንም እንዳልተደሰትኩ ሲመለከት ሁል ጊዜ ያዝናል።

ውድ አግነስ፥

ቀጥሎ ሊረዱሽ የሚችሉ አሳቦችን እንሰጥሻለን።

1) ትክክለኛውን አስቢ፦ የመኝታ ሰዓት ከመድረሱ በፊት አእምሮሽን ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አዘጋጂ። ገና ቀትር ላይ ከባልሽ ጋር በምታደርጊው የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ልታገኚ ስለምትችይው ደስታ አስቢ።

ከዚያ በኋላ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምትፈጽሙበት ጊዜ አእምሮሽ ምን እንደሚያስብ ተጠንቀቂ። ነገ ስለምታበስይው ምግብ ወይም መታጠብ ስላለበት ልብስ በማሰብ ስትጨነቂ እንዳትገኚ ተጠንቀቂ። በዚህ ምትክ የባልሽን ሰውነት በመደባበስ እርሱም የአንቺን ሰውነት በመደባበሱ ስለሚገኘው ጥልቅ ደስታ አእምሮሽ ያሰላስል።

2) ተነጋገሩ። ባለቤትሽ የፍትወት ስሜትሽን የበለጠ የሚያነቃቃው ምን ቢያደርግ፥ የትኛውን የሰውነት ክፍልሽን ቢዳብስ እንደሆነ ንገሪው። እንዲሁ በግምት አውቆ ያደርገዋል አትበይ።

3) ንቁ ሁኚ፦ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ባልሽ ለአንቺ የሚያደርገው ነገር አይደለም። አንዳችሁ ለሌላችሁ የምታደርጉት ነገር ነው። ስለዚህ ባልሽ ስሜትሽን የሚቀሰቅሱ ቦታዎችን ሲደባብስሽ አንቺም ለእርሱ እንዲሁ አድርጊ። የፍቅርን ጨዋታ በምትጫወቱበትና የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በምታደርጉበት ጊዜ ዝም ብለሽ አትተኚ። በንቃት ተሳተፊ። ባለቤትሽ ስሜትሽን በሚቀሰቅስ ሁኔታ ሰውነትሽን በሚደባብስበት ጊዜ ሰውነትሽን በሚገባ አንቀሳቅሺው።

4) ጀምሪ፦ አውራ ዶሮ ሴት ዶሮዎችን እንደሚያሳድድ ባለቤትሽ ሁልጊዜ እንዲያባርርሽ ትጠብቂያለሽን? አግነስ አንቺ ሰው እንጂ ዶሮ አይደለሽም። ሰው (ሴትም ሆነ ወንድ) ጽኑ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት አላቸው። (1ኛ ቆሮ. 7:3ን ተመልከቺ።) ስለዚህ በክርስቲያናዊ ጋብቻ ውስጥ ወንዱ አንዳንድ ጊዜ ዛሬ ማታ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብናደርግስ? በማለት

ይጀምራል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሴቷ በመናገር ወይም መፈለጓን የሚያሳይ አንዳንድ ድርጊት በመፈጸም እርሷ ትጀምራለች።

ስለዚህ አግነስ ባለቤትሽ በሚጀምርበት ጊዜ ተከተይውና የጋራ ደስታችሁን ተቋደሱ። በሌላ ጊዜ ደግሞ አንቺ እራስሽ ጀምሪው። ባለቤትሽ መፈለግሽን የሚያውቅበትን ንግግር ተናገሪ። ወይም ድርጊት ፈጽሚ፥ «ዛሬ እፈልጋለሁ..አሁን እስፈልጎኛል! »።

እንደዚህ ስታደርጊ ባለቤትሽ ደስተኛ ይሆናል። «ባለቤቴ በእርግጥ ትወደኛለች። እንደዚህ በጣም እንደምትወደኝ አላውቅም ነበር። ትፈልገኛለች! ገላዬን ትወደዋለች! ድንቅ ባለቤቴን እንዴት እወዳታለሁ!» የሚል ስሜት ይሰማዋል።

እዝራ፡- ባለቤቴ በአንዳንድ የአተኛኘት አቋሞች ወደ ጡዘተ ፍትወት ብትደርስም በሌሎች ደግሞ አይሳካላትም። ፊት ለፊት በምንተኛበት ጊዜ ይሳካላታል። ጀርባዋን ሰጥታኝ ከኋላ በምሞክርበት ጊዜ አይሳካላትም። ይህ ለምንድን ነው?

ውድ እዝራ፡-

የብዙ ወንዶች እምነት ሴት የፍትወት እርካታ የምታገኘው ወንዱ ብልቱን በብልቷ ውስጥ በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ እንደሆነ ያምናሉ። እውነቱ ግን ሴት ልጅ ወደ ከፍተኛ የፍትወተ እርካታ ስሜት ወይም ጡዘተ ፍትወት ልትደርስ የምትችለው ናዝረ ብልቷ በሚገባ በሚታሸበት ጊዜ ብቻ ነው (ገጽ 48)።

ወንዱ ብልቱን ከኋላ በማስገባት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት በሚፈጽምበት ጊዜ ብልቱ ናዝረ ብልቷን ሊነካ አይችልም። ፊት ለፊት በሚተኙበት ጊዜ ግን ብልቱ ናዝረ ብልቷን በመንካት ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት እንድትደርስ ያደርጋታል።

ብዙ ባልና ሚስቶች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ፊት ለፊት መተኛት የሚመርጡትም ለዚህ ነው።

ይህ ማለት ግን ባልና ሚስት ሴቷ ለወንዱ ጀርባዋን ሰጥታ ከኋላ የሚፈጸመውን ግንኙነት ማድረግ የለባቸውም ማለታችን አይደለም። በዚህ መንገድ በሚፈጸም ግንኙነት ሴቲቱ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት እንድትደርስ ባሏ ሊረዳት የሚችልበት መንገድ አለው። ከኋላ ሆኖ ብልቱን ብልቷ ውስጥ ካስገባ በኋላ እጆቹን ወደፊት በማምጣት ናዝረ ብልቷን በጣቶቹ በማፍተልተል በቀላሉ በጥቂት ደቂቃዎች ወደ ጡዘተ ፍትወተ እንድትደርስ ሊያደርጋት ይችላል።

አሞጽ፡- ባለቤቴ ወደ ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ደርሳ አታውቅም። ሆኖም ግን በፍትወተ ሥጋ ግንኙነታችን ትደሰታለች።

ውድ አሞጽ፥

ሴቶች ሁሉ አንድ አይደሉም። አንዳንድ ሴቶች በፍትወተ ሥጋ ግንኙነታቸው ወቅት ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ሳይደርሱ ሲቀሩ ያለመርካት ይሰማቸዋል። አንዳንድ ሴቶች ደግሞ «ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ባልደርስም እንኳ ባለቤቴ በክንዶቹ እኔን ሲያቅፈኝና ለእኔ ያለውን ፍቅር የሚገልጽበት ሁኔታ በጣም ያስደስተኛል» ይላሉ።

ስለዚህ ባለቤትህ ጡዘተ ፍትወት ላይ ሳትደርስ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ደስተኛ የምትሆን ከሆነ መልካም ነው። ስለዚህ ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት መድረስ አለብኝ ብላ እንድታስብ አታስገድዳት።

ኮርኒ፡- ከሁለት ሳምንት በፊት የመጀመሪያ ልጄን ወለድኩ። ወዳጆቼ «በምታጠቢባቸው ወራቶች ባልሽ ሌሎች ልጃገረዶችን ለማሽኮርመም መሄዱ አይቀርም»። ይሉኛል ምን ማድረግ እችላለሁ?

ውድ ኮርኒ፥

ባለቤትሽ ወደ ምንዝርና እንዳይሄድ ለመርዳት ልታደርጊያቸው የምትችያቸው ሁለት ነገሮች አሉ።

1) ለፍቅር ያለውን ፍላጎት ለማርካት ጥንቃቄ አድርጊ። አንዳንድ ሴቶች ልጆቻቸውን ከመጠን በላይ በመውደድ ባሎቻቸውን የመዘንጋት ስሕተት ይሠራሉ። ወዲያውኑ ባሎች «ባለቤቴ ለእኔ የምታደርገውን እንክብካቤ አቁማለች አሁን አትኩሮቷ በሕፃኑ ላይ ነው» በማለት ለራሳቸው ይናገራሉ። በዚያን ጊዜ ዝሙት ጠንካራ ፈተና ይሆንባቸዋል።

ስለዚህ ኮርኒ ሕፃንሽን ውደጂ፥ ባለቤትሽንም የበለጠ እንደምትወጂው አሳዩው።

2) ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ያለውን ፍላጎት ለማርካት ተጠንቀቂ። ልጅሽን ከወለድሽ ከአምስት ሳምንታት በኋላ ሰውነትሽ ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ዝግጁ ይሆናል። በእርግጥ ከሁለት ዓመት በፊት እንዳታረግዢ መጠንቀቅ አለብሽ። የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎችን በመጠቀም የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እየፈጸምሽ እንኳ እንዳታረግዢ ማድረግ ይቻላል። (ገጽ 97 እና 112 ተመልከቺ።)

ማስታወሻ ለባሎች፡- ካመነዘራችሁ እግዚአብሔር «ይህ የእናንተ ጥፋት አይደለም የሚስቶቻችሁ ጥፋት ነው» ሊለን ፈጽሞ አይችልም። *ካመነዘርክ ጥፋቱ የአንተ ነው* (ሕዝ. 18፡20-23)።

ቪንሰንት፡- የአንድን ሰው የፍትወት ፍላጎት የሚጨምሩ ንጥረ ነገሮች ወይም መድኃኒቶች የትኞቹ ናቸው?

ውድ ቪንሰንት፥

እንደነዚህ ዓይነት ነጥረ ነገሮች ወይም መድኃኒቶች የሉም። በየአገሩ ያሉት አንዳንድ ሰዎች ከፍተኛ የፍትወት ፍላጎት የሚያስገኙ ናቸው በማለት አንዳንድ መድኃኒቶችን ይሸጣሉ። እውነታው ግን የፍትወት ፍላጎትን የሚጨምር መድኃኒት ወይም ኬሚካል የሌለ መሆኑ ነው።

አንጀላ፦ በቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ሴቶች ስለ ሰውነት እንቅስቃሴ ሲናገሩ እሰማለሁ። «አንዲት ሴት ይህን የሰውነት እንቅስቃሴ ከሠራች እርሷና ባሏ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ ደስታን ያገኛሉ» ይላሉ። እንደዚህ ዓይነት የሰውነት እንቅስቃሴ በእርግጥ አለን?

ውድ አንጀላ፦

አዎ አለ። «የፒሲ የሰውነት እንቅስቃሴ» በመባል ይታወቃል። እያንዳንዷ ሴት ይህን የሰውነት እንቅስቃሴ መሥራት አለባት፥ ምክንያቱም በሁለት መንገዶች ይረዳል።

ሀ) ባልና ሚስት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የበለጠ እንዲደሰቱ ይረዳል።

ለ) የወሊድ ጊዜ ለእናቲቱም ሆነ ለሕፃኑ ከአደጋ ነፃ እንዲሆን ያደርገዋል።



ጠንካራ የፒሲ ጡንቻ

የሴቲቱን ብልትና ፊኛ የሚቆጣጠረው ጡንቻ «ፒሲ ጡንቻ» በመባል ይታወቃል።

ይህ ጡንቻ በጣም ጠቃሚ ነው።

አንዲት ሴት ጠንካራ ፒሲ ጡንቻ ካላት ብልቷ የባሏን ብልት በሚገባ ጥብቅ አድርጎ ይይዘዋል። ይህም በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ደስታ እንዲሰማት ያደርጋል። (በስተቀኝ ያለውን ሥዕል ይመልከቱ።)

የሴቲቱ ፒሲ ጡንቻ ደካማ ከሆነ ግን ብልቷ በጣም ሰፊና ልፍስፍስ ይሆናል። በዚህ ጊዜ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ከፍተኛ ደስታን ልታገኝ አትችልም። (ከታች የሚገኘውን ሥዕል ይመልከቱ።)

ብዙ ሴቶች በጣም ሰፊና ልፍስፍስ ብልት አላቸው። ለምን? ምክንያቱም የፒሲ ጡንቻዎቻቸውን እንዴት እንደሚያንቀሳቅሱት ስለማያውቁ ነው።




«በብልታቸው አካባቢ ያሉ ጡንቻዎች እንቅስቃሴ እንደሚያስፈልጋቸው» ቢነገራቸው እንኳ እንዴት እንደሚያሠሩት አያውቁም።

ለምሳሌ፥ ማርታ የፒሲ ጡንቻዎቿን ለማሠራት ስትጀምር የፒሲ ጡንቻ ያልሆኑትን ጡንቻዎች በማኮማተር ስሕተት ሠራች። «የፒሲ ጡንቻዬን እያኮማተርሁ ነው»። እያለች የምታኮማትረው ግን የጭኖቿን ጡንቻዎች ነበር።

ደግነቱ አንዲት ሴት በፒሲና በጭን ጡንቻ መካከል ያለውን ልዩነት የምትማርበት ቀላል መንገድ መኖሩ ነው። የፒሲ ጡንቻ ብልቷን ጠበቅ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የሽንት መፍሰስንም ያቋርጣል። ስለዚህ አንዲት ሴት የፒሲ ጡንቻዎች ማኮማተርን ለመማር በምትሸናበት ጊዜ መለማመድ ያስፈልጋታል።

የፒሲ ጡንቻዎችሽን ማኮማተር ተማሪ

ለሚቀጥሉት ሰባት ቀናት በምትሸኚበት ጊዜ ጉልበቶችሽን ከፈቺያቸውና ለጥቂት ሰኮንዶች ያህል መሽናትሽን ለማቆም ሞክሪ...እንደገና ቀጥዪ....ደግመሽ ለጥቂት ሰኮንዶች አቋርጪ። ይህን በየመካከሉ ሽንትሽን የማቋረጥና የመሽናት ተግባር ፊኛሽ ባዶ እስኪሆን ድረስ ቀጥይ። *ሽንትሽን እንደማቋረጥ ስትይ የፒሲ ጡንቻዎችሽን እያኮማተርሽ ነው ማለት ነው።*

ጉልበቶችሽን በደንብ መክፈት የሚያስፈልግሽ ለምንድን ነው? ምክንያቱም ጉልበቶች በተከፈቱ ጊዜ የሽንትን መፍሰስ ሊያቆም የሚችል ጡንቻ የፒሲ ብቻ በመሆኑ ነው። ጉልበቶችሽ ከተገጠሙ ግን ሽንትሽን በጭን ጡንቻዎች ማቆም ትችያለሽ።

ሽንትሽን ማቆም በምትለማመጂበት ጊዜ በፒሲና በጭን ጡንቻዎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳትን እየተማርሽ ትመጪያለሽ።

ከሰባት ቀናት በኋላ የፒሲ ጡንቻዎችሽን ማኮማተር ትማሪና በምትሸኚበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ጊዜ ማኮማተር ትችያለሽ። በዚህ ጊዜ የፒሲን ልምምድ ለመሥራት ተዘጋጅተሻል ማለት ነው።

## የፒሲ ልምምድ

ሀ. ፒሲሽን የቻልሽውን ያህል ፊንጢጣሽን ወደ ውስጥ በማፈን አኮማትሪው። ለሦስት ሰኮንዶች አፍነሽ ያዥው።

ለ. ለቀቅ አድርጊው። ለሦስት ሰኮንድ ያህል ላላ እንዳረግሽው ተይው።

**የፒሲ ልምምድን ለ40 ጊዜ ያህል በየዕለቱ ሥሪ።**

አንዲት ሴት በየዕለቱ 40 ያህል የፒሲ ልምምድ ማድረግ ይኖርባታል። ይህ ማለት በቀን 40 ጊዜ ያህል ለ3 ሰኮንድ አፈን፥ ኮምተር ለ 3 ሰኮንድ ለቀቅ ዘና አድርጋ በማፈራረቅ ትቆያለች ማለት ነው።

በየዕለቱ 40 ልምምዶችን ለመሥራት አስቸጋሪ አይደለም። እያንዳንዱ ልምምድ የሚፈጀው ስድስት ሰኮንዶች ብቻ ነው። (ሦስት ለማኮማተር ሦስት ደግሞ ለቀቅ ለማድረግ ነው።)

አንዲት ሴት ጠዋት ከአልጋዋ ላይ ከመውረዱ በፊት አሥር ልምምዶችን መሥራት ትችላለች። (ይህ የሚፈጀው 60 ሰኮንዶች ብቻ ነው።) ሌላ አምስት ልምምዶች ደግሞ ሽንቷን በምትሸናበት ጊዜ ልትሠራ ትችላለች። በቁርስ ወቅት ሌላ አምስት በምሳ ሰዓት አሥር ወዘተ... በዚህ ዓይነት በቀኑ መጨረሻ 40 እስከትደርስ ትቀጥላለች።

የፒሲ ጡንቻ በሰውነት ውስጥ የሚገኝ ስለሆነ በምታኮማትርበትና ለቀቅ በምታደርግበት ወቅት ማንም ሊያይ ወይም ሊያውቅ አይችልም።

ዶሮቲ፡- 40 የፒሲ ልምምድ በየዕለቱ ለመሥራት የማስታወስ ችግር ነበረባት። ስለዚህ ማስታወሻ ጽፋ በቤቷ ውስጥ በየቦታው አስቀመጠችው። እያንዳንዱ ማስታወሻ «ልምምድ» የሚል ጽሑፍ ነበረው። አንዱን ማስታወሻ በኩሽና የዕቃ ማጠቢያ አጠገብ፥ ሌላውን በልብሷ መተኮሻ አጠገብ፥ ወዘተ... አኖረቻቸው። አንድ ቀን እህቷ ማስታወሻዎቹን አይታ ምንነታቸውን ጠየቀች። ዶሮቲ ስለ ፒሲ ልምምድ ሁሉን ነገር ነገረቻት። ከሁለት ወራት በኋላ እህትየዋ ወደ እርሷ በመምጣት እንዲህ አለቻት «ባለቤቴ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የምደሰትበትን አዲስ ዘዴ ወዶታል። ምን መድኃኒት እንደሰጠሽኝ ማወቅ ይፈልጋል።»

የፒሲ ልምምድ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እርካታን የሚጨምረው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ጠንካራ የፒሲ ጡንቻ ያላት ሴት በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ወቅት የባለቤቷን ብልት በብልቷ ጨብጣ ጨምቃ መያዝ ስለምትችል ነው።

አሜሪካኖች በመጀመሪያ እንደደረሱበት ያስባሉ።

አንዳንድ የአሜሪካ ዶክተሮች የፒሲን ልምምድ ለማግኘት የመጀመሪያው እነርሱ እንደሆኑ ያስባሉ። እውነታው ግን በሌላው ዓለም ያሉ ሴቶች (ለበርካታ ትውልዶች) የፒሲ ጡንቻዎችን ልምምድ ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ፥ በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች አንዲት ልጃገረድ የብልቷን ጡንቻ (ፒሲ) በሚገባ ጨብጣ ወይም አኮማትራ) መያዝ ካልቻለች ልታገባ አትችልም ነበር። በአንዳንድ የእስያ አገሮች ደግሞ አንዲት ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ የብልቷ ጡንቿ (የፒሲ ጡንቻ ነው) የቀድሞ ጥንካሬውን መልሶ ያገኝ ዘንድ የፒሲን ልምምድ ታደርጋለች።

ዛሬ ብዙ ሰዎች የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስታን ይጨምራል በማለት መድኃኒቶችን ይገዛሉ። እንደነዚህ ዓይነት መድኃኒቶች እንደማይሠሩ እርግጥ ነው። የፒሲ ልምምድ ግን ለምትተገብረው ሴት ሁሉ ይሠራል። ደግሞ ነፃ ነው!

የፒሲ ልምምድ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እርካታን ከመጨመሩም ሌላ ወሊድ በሰላማዊ ሁኔታ እንዲፈጸም ያደርጋል።

በሁሉም ዓለም ለሚገኙ ሴቶች እንዲህ እንላለን፡-

*የፒሲ ጡንቻዎቻችሁን የመጨበጥ ወይም የማኮማተር*
*ልምምድን ተማሩ።*
*ከዚያም 40 የፒሲ ልምምድን በየዕለቱ አድርጉ።*

ቬሮኒካ፡- እኔና ባለቤቴ ከተጋባን 12 ዓመታት ሆኗል። አራት ልጆች አሉን። ለመጀመሪያዎቹ 10 ዓመታት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ደስታን እንለማመድ ነበር። ከሁለት ዓመታት ወዲህ ግን ኃይለ ፍትወቱ ደከመ። ምንም ያህል ብደባብሰው ብልቱ አይቆምም። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም በሞከረባቸው ጊዜያት ሁሉ ብልቱን በብልቴ ውስጥ ለማስገባት ያቅተዋል።

ወደ ሆስፒታል ሄዷል። ሐኪሙ «የኃይለ ፍትወትን ድክመት የሚያመጣ ምንም ዓይነት በሽታ ስለሌለብህ ሄደህ እንደገና ሞክር» አለው።

አሁንም ቢሆን የፍቅርን ጨዋታ በምንጫወትበት ጊዜ ብልቱ እንደተዝለፈለፈ ይቀራል። ቀጥ ብሎ አይቆምም። ስለዚህ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አልቻልንም።

በነገሩ ትልቅ ኀፍረት ስለሚሰማው በራሱ አልጋ ላይ መተኛት ጀምሯል።

ለሁለት ዓመታት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አልቻልንም። አንዳንድ ጊዜ ለማመንዘር እፈተናለሁ፤ ነገር ግን ጀርባዬን በአዳኜ በክርስቶስ ላይ መመለስ አቃተኝ።

ኃይለ ፍትወቱ የመድከሙ ምክንያት ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ውድ ቪሮኒካ፡

የኃይለ ፍትወት ድክመት በበሽታ ወይም በጭንቀት ሊመጣ ይችላል።

ሐኪሙ ባለቤትሽ በሽታ እንደሌለበት ስላረጋገጠ ምክንያቱ ጭንቀት ሊሆን ይችላል። እንዲያውም የብዙ ኃይለ ፍትወት መድከም ምክንያት ጭንቀት ነው።

ጭንቀት ኃይለ ፍትወትን እንዴት ሊያደክም ይችላል? አንድ ሰው (ዮሴፍ እንበለው) አንድ ማታ በከባድ ሥራ ደክሞ ውሎ በመምጣት አልጋው ላይ የመውደቅ ያህል ዘፍ ይላል። ባለቤቱ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ስለፈለገች ብልቱን ትደባብሰለት ጀመር። ነገር ግን ብልቱ አልቆም አለ። ዮሴፍና ባለቤቱ በጉዳዩ ተደናገጡ።

መደናገጥ ግን አልነበረባቸውም። ዮሴፍ ደክሞት ነበር። ማንኛውም ወንድ እጅግ በሥራ ከደከመ ብልቱ ላይቆምለት ይችላል። ዮሴፍና ባለቤቱ ግን ይህን አልተረዱም። እንደ ሌሎች በርካታ ሰዎች ሁሉ «እውነተኛ ወንድ» ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሁል ጊዜ የተዘጋጀ ነው በማለት የተሳሳተ አሳብ አላቸው።

በዚያ ምሽት ዮሴፍ መተኛት አልቻለም «ብልቴ ምን ችግር ኖሮበት ይሆን? ባለቤቴ ስለ እኔ ምን ታስብ ይሆን? ነገ ማታ ብልቴ ይቆም ይሆንን? ከዚህ በኋላ ተመልሶ ባይቆም ምን አባቴ እሆናለሁ?» በማለት ሲያስብ አደረ።

በሚቀጥለው ዕለት ማታ አቋሙን ለማረጋገጥ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ጠየቃት። የፍቅር ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜ ዘና ብሎ በመደባበሱና በመተሻሸቱ ከመደሰት ይልቅ ብልቱ ጠንክሮ ይቆም እንደሆነ ለማረጋገጥ በመጨነቅ ይጠባበቅ ጀመር። ከመጨነቁ የተነሣ ብልቱ ሳይቆም ቀረ።

ዮሴፍና ሚስቱ ማድረግ የነበረባቸው ነገር የሚከተለው ነበር። ብልቱ አልቆም ባለበት የመጀመሪያ ምሽት ባለቤቱ «ይህ ምንም የሚያሳስብ አይደለም። ዛሬ በሥራ እጅግ ደክመሃል። ከሰሞኑ በቂ ዕረፍት የምታገኝበትን ሌላ ምሽት እንጠብቅ» ልትለው ይገባ ነበር።

በዚህ ሁኔታ የብልቱ ያለመቆም ችግር ይረሳ ነበር። በሚቀጥለው ዕለት ምሽት ብልቱ ይቆም እንደሆነ መጠባበቅ አልነበረባቸውም። በዚያም ምትክ አንዱ ለሌላው በሚሰጠው እርካታ ላይ ማተኮር ነበረባቸው። እንዲህ ቢሆን የብልቱ መቆም ያላአንዳች ጥርጣሬ ወዲያውኑ ይሆን ነበር። ችግሩም በፍጹም አይከሰትበትም ነበር።

ከፍቅር ጨዋታ ጊዜ ማንኛውም ሰው ብልቴ ጠንክሮ ይቆም ይሆን ወይ? ብሎ መጨነቅ የለበትም። ያንን ረስቶ ሚስቱን በመውደድ ብቻ ሐሤት ማድረግ አለበት።

የወንድ ብልት የሚቆመው እንዴት ነው? ልክ ሰው እንቅልፍ እንደሚወስደው ነው። አልጋው ላይ ወጥቶ «ቶሎ መተኛት አለብኝ። ነገ ብዙ ሥራ አለብኝ። አሁን እንቅልፍ እየወሰደኝ ነው? መተኛት አለብኝ– *በግድ!»* በማለት ለራሱ የሚናገርን ሰው አስቡ።

በዚህ ዓይነት እንቅልፍ በፍጹም አይወስደውም። እንቅልፍ ይወስደው ዘንድ ዘና ማለት አለበት። ስለ እንቅልፍ መጨነቅ የለበትም። አእምሮው ሌሎች ነገሮችን እንዲያስብ ማድረግ ይገባዋል። ይህን ሲያደርግ ወዲያውኑ እንቅልፍ ይወስደዋል።

በተመሳሳይ መንገድ አንድ ሰው ስለ ብልቱ መቆም የሚጨነቅ ከሆነ ብልቱ ሊቆም አይችልም። ዘና ብሎ ሚስቱን በመደባበስና በማሻሸት ሊደሰት ይገባዋል። በዚያን ጊዜ ብልቱ ወዲያውኑ ይቆማል።

ቬሮኒካ፥ ባለቤትሽ ብልቴ ይቆም ይሆንን ወይስ ይከዳኝ ይሆን በማለት ከመጠን በላይ የመጨነቅ ስሕተት የሠራ ይመስላል። እኛ ግን መልካም ዜና አለን። አንቺና ባለቤትሽ በችግሩ ላይ ድልን ልትቀዳጁ ትችላላችሁ! ድል ማድረጊያው መንገድ የሚከተለው ነው:–

ሀ) ተነጋገሩ:– ምናልባት አንቺና ባለቤትሽ ስለዚህ ችግር ተነጋግራችሁ አታውቁም ይሆናል። በነጻነትና በታማኝነት ሁኔታውን ሁሉ ዛሬ መነጋገር ጀምሩ። ቬሮኒካ፥ ስለ ባለቤትሽ የኃይለ ፍትወት ድክመት የሚጎዳ ነገር ተናግረሽ እንደሆነ ይቅርታ እንዲያደርግልሽ ጠይቂው።

ለ) የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሳትፈጽሙ የፍቅር ጨዋታን ተጫወቱ። በመጀመሪያ ባለቤትሽ ስለ ብልቱ ያለመቆም ችግር መረጋጋት ቀላል ላይሆንለት ይችላል። ስለዚህ የምንሰጣችሁ አሳብ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት በየምሽቱ የፍቅር ጨዋታ ተጫወቱ። ነገር ግን የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አትፈጽሙ። ባለቤትሽ ይህን ካወቀ ጭንቀቱን ትቶ ዘና ሊል ይችላል። «ዛሬ ማታ ባለቤቴ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድንፈጽም አትጠብቂብኝም። በፍቅር ጨዋታ ብቻ ደስ እንሰኛለን።» ይላል።

በፍቅር ጨዋታ ጊዜ እንደምትወጂው ሰውነቱን መደባበስና ማሻሸት እንድሚያስደስትሽ ንገሪው። «በምንም ዓይነት ብልቱን እንዲቆም አደርጋለሁ» አትበይ። በዚህ ምትክ ዘና በይ። ሰውነቱን በሙሉ በቅባት በማሸት ተደሰቺ። እርሱም አንቺን በመደባበስና በማሻሸት ደስ ይበለው። ብልቱ ስለመቆሙ ወይም ስላለመቆሙ ማናችሁንም አይጭነቃችሁ። ብልቱ ባይቆምም እንኳ አንዳችሁ ለሌላችሁ እርካታን በመስጠት ቀጥሉ። እንደምትወጅውና ከልብሽ መሆኑን ሲረዳ ከባድ ሸክም ከትከሻው ላይ የተንከባለለ ያህል ይሰማዋል።

እነዚህ ዓይነቱን የፍቅር ጨዋታ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳትፈጽሙ ለሳምንት ወይም ለወርም ቢሆን እንኳ ቀጥሉ። ቢፈጥንም ቢዘገይም ሁለታችሁም በፍቅር ጨዋታ በመደሰት ስለ ብልቱ አለመቆም ችግር የማታስቡበት ጊዜ ላይ ትደርሳላችሁ። አንዳችሁ የሌላችሁን አካል

በመውደድ በሚገኘው እርካታ ትደሰታላችሁ። ከዚያም ብልቱን ስትመለከቱ ግትር ብሎ ታገኙታላችሁ። ከዚያም ብልቱን ያስገባል። ተግባሩ ይከናወናል፤ አቤት እንዴት ግሩም ይሆናል!

ይህ የኃይለ ፍትወቱ ድክመት መጨረሻ ይሆናልን? አይሆንም። ነገር ግን የድሉ መጀመሪያ ነው።

ለሁለት ዓመታት የቆየና ሥር የሰደደ ችግር በአንድ ቀን አይጠፋም። ስለዚህ ትዕግሥት ያስፈልጋል። አሁንም አንዳንድ ጊዜ ላይቆምለት ይችላል።

በፍቅር ጨዋታችሁ አዘውትራችሁ መደሰትን መቀጠል አለባችሁ። በዚህ ሁኔታ ብልቱ ቢቆም መልካም ነው። በማይቆምበት ጊዜ አትጨነቁ። ዘና ብላችሁ የፍቅር ጨዋታችሁን ቀጥሉ። የብልት ያለመቆም ችግር ሙሉ ለሙሉ እስኪወገድለት ሳምንታት ወይም ወራት ሊወስዱበት ይችላል።

ፖል፦ የኃይለ ፍትወት ድክመት ሲጋራ በማጨስና አልኮል በመጠጣት ሊመጣ ይችላልን?

ውድ ጳውሎስ፥

ሲጋራ ማጨስ፦ አዎን ሲጋራ ማጨስ ብዙ ጊዜ የፍትወትን አቅም ያደክማል። የወንድ ብልት በሚገባ ይቆም ዘንድ በብልቱ ደም መሙላት አለበት። በሲጋራ ውስጥ የሚገኘው ኒኮቲን የተባለ ቅመም ደግሞ በከፊል የደም ቧንቧዎችን ይደፍናል። ይህም ብልቱ በሚገባ ተገትሮ እንዳይቆም ያደርጋል።

ማጨስ ያቆሙ ወንዶች «አሁን በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ ደስታ አገኝቻለሁ!» ጨምረውም «ማጨስ ያቆምኩት ከብዙ ዓመታት በፊት ቢሆን እንዴት መልካም ነበር! እንዲያውም ልጀምረው አይገባኝም ነበር!» ይላሉ።

አልኮል፦ አዎ አልኮልም ኃይለ ፍትወትን ያደክማል። አደገኛ ጠጪ የሆነ ሰው ብልቱ ፈጽሞ ሊቆም ወደ ማይችልበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

ዳንኤል፦ ዕድሜዬ 64 ሲሆን የባለቤቴ ዕድሜ ደግሞ ወደ 63 እየተጠጋ ነው። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ማቆም አለብን ወይ? ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ዕድሜያችን አላለፈምን?

ውድ ዳንኤል፥

አንተና ባለቤትህ በሕይወት እስካላችሁ ድረስ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት የሚገኘውን ደስታ መቋደሳችሁን ቀጥሉ።

ቴዎፍሎስ፦ ካገባሁ አንድ ዓመት ሆነኝ። ችግሬ የዘር ፍሬዬን የማፈስሰው እጅግ ፈጥኜ ነው። እንዲያውም የዘር ፍሬዬን የማፈስሰው ብልቴን በማስገባበት ቅጽበት ነው። በፍቅር ጨዋታ ወቅት ለባለቤቴ

ብልቴን እንዳታሻሽ ሁልጊዜ እነግራታለሁ። ነገር ግን ብልቴን በማስገባበት ወቅት ብልቴ ብልቷን ሲነካ ወዲያውኑ የዘር ፍሬዬን አፈስሳለሁ።

ወንድ ልጅን በፍትወት ስሜት ቀዝቀዝ እንዲል የሚያደርግ መድኃኒት አለን?

ውድ ቴዎፍሎስ፥

በፍቅር ጨዋታ ወቅት ባለቤትህ «ብልትህን እንዳታሻሽ» የሚል አሳብ ያገኘሽው ከየት ነው?

እውነታው ግን ብልትህን ከማስገባትህ በፊት ባለው የፍቅር ጨዋታ ወቅት ልታሻሽልህ ይገባል። ለምን? ምክንያቱም ይህ ብልትህን ወደ ብልቷ ካስገባህ በኋላ ፈጥነህ የዘር ፈሳሽህን እንዳታፈስ ይረዳል።

የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን በላቀ የፍትወት ስሜት ለመፈጸም መንገዱ ይህ ነው። ብልትህን ወደ ብልቷ ከማስገባትህ በፊት አንተ እርሷን ልትደባብስ እርሷም አንተን ልትደባብስ ያስፈልጋል። በዚህ መተሻሸት ጊዜ የዘር ፍሬህን እንዳታፈስ ሞክር። ለረጅም ጊዜ ከተሻሻችሁና ከተደባበሳችሁ በኋላ ብልትህን ወደ ብልቷ አስገባ። ለረጅም ጊዜ ስትደባብስህ ስለቆየች ብልትህን ወደ ብልቷ ካስገባህ በኋላ ቶሎ የዘር ፍሬህን አታፈስም። ስለዚህ ሚስትህ ወደ ከፍተኛው የእርካታ ስሜት ለመድረስ በቂ ጊዜ ይኖራታል። ቀጥሎም አንተ የዘር ፍሬህን ልታፈስ ትችላለህ።

ከማስገባቴ በፊት ለረጅም ጊዜ ብልቴን ካሻሸችኝ በዚህ ጊዜ የዘር ፈሳሼን እንዳላፈስ እንዴት እችላለሁ? የሚለው ጥያቄ የተለመደ ጥያቄ ይሆናል።

መልሱ፡- በማሻሸቱና በመደባበሱ ወቅት ለባለቤትህ እንዲህ ብለህ ልትነግራት ትችላለህ። «ጥቂት ጠብቂኝ...የዘር ፈሳሼን ለማፍሰስ ቀርቤአለሁ...። ለጥቂት ደቂቃ ልረፍ።» በእነዚያ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አንተ እርሷን መደባበሱንና ማሻሸቱን ልትቀጥል ትችላለህ። እርሷ ግን ታቆምና ጥቂት ዕረፍት ትሰጥሀ። ደግሞ ጥቂት ልረፍ እስክትላት ድረስ እንደገና ማሻሸትና መደባበስ አሁንም ትቀጥል።

ብልትህን ወደ ብልቷ ከማስገባትህ በፊት ይህ ማሻሻትና መደባበስ- ማረፍ፥ ደግሞ መደባበስና ማሻሸት- ማረፍ ድግግሞሽ ለብዙ ጊዜ ይቀጥል። ከዚያም ብልትህን ወደ ብልቷ ካስገባህ በኋላ እራስህን እንዲህ ስትል ታገኘዋለህ «ተመልከቱ....በፍጥነት የዘር ፈሳሼን ሳላፈስ ብልቴን ብልቷ ውስጥ ማስገባትና መቆየት ችዬአለሁ። ይህ የመተሻሸት፥ የመደባበስ - የዕረፍት ድግግሞሽ በእርግጥም ይረዳል!»

ይህ የመተሻሸት የመደባበስና የዕረፍት ድግግሞሽ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጸም ስኬታማነቱ አነስተኛ ሊሆን ይችላልና ተስፋ አትቁረጥ። የዘር ፍሬህን የማፍሰስ ተግባር እንዲዘገይ ማድረግ በወራት የሚቆጠሩ ልምምድ

ይጠይቅ ይሆናል። ተስፋ አትቁረጥ። ብልትህን ወደ ብልቷ ከማስገባትህ በፊት በርከት ላለ ጊዜ ድግግሞሹን ተለማመድ።

ብልትህን ወደ ሚስትህ ከማስገባትህ በፊት እያሻሸችህና እየደባበሰችህ ሳለ በድንገት የዘር ፍሬህን ብታፈስ አትጨነቅ። ይህ ችግር ወይም ኃጢአት አይደለም። ዑደቱን የዘር ፍሬህን ሳታፈስ በተደጋጋሚ ለመፈጸም ብቻ ጥረት አድርግ። ይህ ጥረትህ ብልትህን ወደ ሚስትህ በምታስገባበት ወቅት ፈጥነህ እንዳታፈስ ይረዳሃል።

ስለ መድኃኒቶች ጠይቀህ ነበር። አንዳንድ ሰዎች የወንዱን ስሜት ያቀዘቅዛል እያሉ መድኃኒቶችን ይሸጣሉ። ለዚህ ጉዳይ የሚሠራ መድኃኒት ግን ፈጽሞ የለም።

ደግሞም ዕረፍት እያደረጉ ከሚስት ጋር መተሻሸትና መደባበስን የመሰለ አስደሳች ነገር እያለ መድኃኒት መጠቀም ለምን ያስፈልጋል?

አልፍሬድ፡- አልኮል መጠጣት የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን እርካታ ለመጨመር ይጠቅማልን?

ውድ አልፍሬድ፥

አንዲት ሴት በሰውነቷ ውስጥ አልኮል ካለ በፍትወት ስሜቷ በሚገባ ለመቀስቀስ የሚወስድባት ጊዜ ይጨምራል። ይህም ወደ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ወይም ጡዘተ ፍትወት የመድረሷን ነገር እጅግ አስቸጋሪ ያደርግባታል።

በሰውነቱ ውስጥ አልኮል ያለበት ወንድ ደግሞ ብዙ ጊዜ ከሚፈልግበት ጊዜ እጅግ ቀድሞ የዘር ፍሬውን ያፈስሳል።

**አልኮል የሚጠጡ ወንድና ሴት በፍትወት የሚያገኙት ደስታ አናሳ ነው!**

ሉቃስ፡- ብልቴ ትንሽ ነው። አሁን ትዳር ብመሰርት ሚስቴን በፍትወት ላረካት አልችልም የሚል እምነት ስላለኝ ማግባት እፈራለሁ። አንዳንድ ልጃገረዶች የበለጠ የፍትወት ደስታ የሚሰጠን ትልቅ ብልት ያለው ወንድ ስለሆነ ማግባት የምንፈልገው እንደዚህ ዓይነቱን ወንድ ነው ይላሉ ሲባል እሰማለሁ። ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ሳላገባ ልኑርን? ትዳር ብመሠርት ሚስቴ በደንብ እንዳታረካኝ ብልትህ ትንሽ ሆነብህ ትለኛለችን? በዚህ ምክንያት ትፈታኝ ይሆንን?

ይህ ፍርሃት የምትስማማኝን እስካገኝ ድረስ ሴቶችን ሁሉ ልሞክር ወይ ወደ ሚል አሳብ እየነዳኝ ነው። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ነገር የሰማይ አባቴን እንደሚያስቀይም አውቃለሁ። ስለዚህ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ውድ ሉቃስ፥

ትልቅ ብልት ያለው ወንድ ትንሽ ብልት ካለው ወንድ ይልቅ ለሚስቱ የፍትወት እርካታን ይሰጣል የሚለው አሳብ እውነት አይደለም። ለሴት ልጅ የፍትወት እርካታን እንድታገኝ የሚያደርጓት ዋና የፍትወተ ሥጋ ብልቶች ናዝረ ብልቷና ከብልቷ ደግሞ የመጀመሪያው 7ሴ.ሜ ነው። ስለዚህ የወንድ ብልት መጠን 7ሴ.ሜ ወይም 12 ሴ.ሜ ወይም ከዚያ በላይ ቢሆን እንኳ የሚያመጣው ለውጥ የለም። የብልቱ መጠን 7ሴ.ሜ የሆነ ወንድ የብልቱ መጠን 15 ሴ.ሜ ከሆነው እኩል የፍትወት ደስታን ለባለቤቱ መስጠት ይችላል።

የብልቱ መጠን ብልቱ በሚቆምበት ጊዜ ከ7.ሴ.ሜ የሚያንስበት ወንድ የለም። ስለዚህ የፍትወት እርካታ ለመስጠት እስከማይችል ድረስ በጣም ትንሽ ብልት ያለው ወንድ የለም።

በጋብቻ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግሮች ምክንያቶች በርካታ ሲሆኑ ከምክንያቶቹ ውስጥ ግን የብልት መጠን ግንኙነ ፈጽሞ የለበትም።

ብዙ ጊዜ ወንዱ «ብልቴ በጣም ትንሽ ስለሆነ ባለቤቴ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አትወድም» ሲል፥ ሚስቲቱ ደግሞ «የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን የማልወደው ሁልጊዜ እንደ ጓደኛ ሳይሆን እንደ ሕፃን ስለሚያየኝ ነው» ትላለች።

ሉቃስ ከተለያዩ ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ የምትስማማህን ለመምረጥ መሞከሩ አንተ እንዳልከው እግዚአብሔርን ያሳዝናል። እናም ፍተሻ ማድረግ አያስፈልግም። እግዚአብሔርን ብቻ ታዘዝ። ስለዚህ ትዳር ስትመሠርት ሚስትህን ውደድ፥ የቅርብ ጓደኛዋ ሁን። ስለ ብልትህ መጠን ፈጽሞ አትጨነቅ።

ሩት፡- ዕድሜዬ 23 ዓመት የሆነ ያላገባሁ ሴት ነኝ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። በቢሮዬ አብሬያችው ከምሠራው ሰዎች አብዛኞዎቹ «አክራሪ ሃይማኖተኛ» ወይም «ንክ» ነሽ ይሉኛል። ነገር ግን እስከ ጋብቻዬ ዕለት ድረስ በንጽሕና በመቆየት ጌታዬን ለመታዘዝ ከወሰንኩ ቆይቻለሁ።

ከሰው ሁሉ ወንድም ሆነ ሴት ጋር በቀላሉ የመግባባት ተሰጥዖ አለኝ። በዚህም ደስ ይለኛል። ነገር ግን ማንኛውም ወንድ ይህን ውሳኔዬን ለማፋለስ ሲመጣ ወጊድ ብዬ አባርረዋለሁ።

ሁል ጊዜ ለራሴ እንዲህ ብዬ እናገራለሁ። «በአንድ ስፍራ እግዚአብሔር ለእኔ ያዘጋጀው ባል አለኝ.... በድንግልና ንጽሕናዬ ደስ የሚሰኝ ባል።»

አሁን ይህ እየተፈጸመ ነው። በጣም ግሩም የሆነ ክርስቲያን ወንድም እንዳገባው ጠየቀኝ። እጅግ በጣም ተደሰትኩ! በደመና ላይ የምራመድ መስሎ ተሰማኝ። እርሱም በድንግልና ንጽሕና በመቆየቱ የተሳቀበት ሰው ነው።

የጋብቻ በዓላችን በሚቀጥለው ዓመት የሕክምና ዶክተር ሆኖ እንደተመረቀ ይፈጸማል።

ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን እናስፋፋ ዘንድ ወደ ማሊ ልትልከን ታስባለች። አገሬን ትቼ መሄድ ብፈራም እንኳ ኢየሱስ ከእኛ ጋር እንደሚሆን አውቃለሁ።

ክርስቲያን ያልሆኑ ሁለት እህቶች አሉኝ። ስለ እነርሱ በጣም አዝናለሁ! ሰላም የላቸውም፥ በየወሩ አረግዝ ይሆን ብለው ይሰጋሉ። በኤድስና በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች እንዳይያዙ ይፈራሉ።

«ወደ ክርስቶስ ዛሬ ተመለሱ። ኃጢአታችሁን ይቅር በማለት የዘላለም ሕይወት ይሰጣችኋል፥ በእርሱ መንገድ ተመላለሱ፥ መንገዱ ለሕይወት ከሁሉም የተሻለ ነው» እያልኩ እነግራቸዋለሁ።

ከባለቤቴ ጋር ወደ ማሊ ከመሄዳችን በፊት ንስሐ እንደሚገቡ ተስፋ አደርጋለሁ።

ውድ ሩት፥

አንቺና ባለቤትሽ ወደ ማሊ ስለምታደርጉት ጉዞና እህቶችሽም ወደ ክርስቶስ እንዲመለሱ እንጸልይልሻለን።

የምትበረታቺበትን ጥቅስ ቀጥሎ እንሰጥሻለን።

ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡— ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤ እንግዲህ ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ፤ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» (ማቴ. 28:18—20)።

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋ. 1:8)

ኤድጋር፡— ከስድስት ዓመት በፊት ገና በትምህርት ቤት ሳለሁ አንዲት ልጅ ወድጄ አስረገዝኳት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመንፈሴ ምንም ሰላም የለኝም። ከአንድ ዓመት በኋላ ልጇ ሞተብኝና በታላቅ ኃዘን ተዋጥሁ። ለተከታዩ ዓመት ልጅቷ እኔን ትታ ሌላ የወንድ ጓደኛ ያዘች። ይህም ለልቤ ታላቅ ስብራት ሆነ። ለሳምንታት መተኛት አልቻልኩም።

ከዚያ ቀጥሎ እወድሻለሁ በማለት ሌላ ልጃገረድ አሳሳትኩኝ። እውነት ለመናገር አልወዳትም ነበር። ኀዘኔን ለመርሳት ብቻ የፈጸምኩት ነገር ነበር። ከዚያም አረገዘችብኝ። የልብ ስብራት ውስጥ ስለነበርኩ ለእርግዝናዋ ተጠያቂ መሆኔን ካድኩ። ነገር ግን ቆርጥ እኔን የመሰለ ወንድ ልጅ ወለደች። ችግሩ ግን ባሕርይዋን ስለማልወደው ላገባት አልችልም። አሁን ለሕፃኑ ልብስ እንድገዛለት ትፈልጋለች። እኔ ግን ትምህርቴን መጨረስ እፈልጋለሁ።

ይህ ሁሉ ነገር የደረሰብኝ ለምንድን ነው? እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እንድገባ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነውን?

ማሳሰቢያ፡- ይህ ሰው ችግር ውስጥ የገባው በራሱ ኃጢአት ምክንያት ነው። ገና ትምህርት ቤት እያለ ከልጃገረድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸሙ ኃጢአትን አደረገ። ውጤቱም ከፍተኛ ኃዘን ነበር።

ኋላም ችግሮቹን ይረሳ ዘንድ አብሮአት ለመተኛትና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ብቻ በማቀድ ሌላዋን ልጃገረድ እወድሻለሁ በማለት ሸነገላት። የዚህ ኃጢአት ውጤት ለራሱ ለሴቲቱና ለሕፃኑ የባሰ ኀዘን ነበር።

አሁን እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እገባ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውን? በማለት ይጠይቃል።

ችግር ውስጥ የከተተው እግዚአብሔር አይደለም። ራሱን ችግር ውስጥ የከተተው ራሱ ነው። እንዴት? ኃጢአትን ለማድረግ በወሰደው ነፃ ምርጫ። እያንዳንዱ ችግር በራሱ ምርጫ ያደረገው የኃጢአት ውጤት ነው።

በጻፍንለት ደብዳቤ ለእግዚአብሔር እንዲህ በማለት እንዲናዘዝ መከርነው።

«ጌታ ሆይ፥ ኃጢአቶቼ ብዙ ችግሮች አምጥተውብኛል። ኃጢአቶቼ ወደ ገሃነም እንደሚያወርዱኝ ተገንዝቤአለሁ። ነገር ግን በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደምትሰጥ አምናለሁ። ዛሬ ኢየሱስ ለእኔ እንደሞተ ማመን መርጫለሁ። ዛሬም ልቤ በኃጢአት ለመኖር ከመፈለግ ተለውጦ በአንተ መንገድ ለመኖር እንዲፈቅድ መርጫለሁ።»

ለሕፃኑ ልብስ፥ ትምህርትና ፍቅር የመስጠት ግዴታ እንዳለበትም ነግረነዋል።

«ለራሱ ዘመዶች ይልቁንም ለቅርብ ቤተሰዎቹ የማያስብ ሃይማኖቱን የካደ ነው። እንዲያውም ከማያምን ሰው እንኳ የባሰ ክፉ ነው።» (1ኛ ጢሞ. 5፡8)

ሊዲያ፡- ዕድሜዬ 27 ዓመት የሆነ ክርስቲያን ሴት ነኝ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። በድንግልና ንጽሕናዬ እገኛለሁ። ከአራት ወር በኋላ አንድ ክርስቲያን ወንድ አገባለሁ።

በባሕላችን አንዲት ወጣት ሴት ከማግባቷ በፊት የብልቷን የክብረ ንጽሕና ክፍተት በጣቶቿ ማስፋት ልማድ ነው። እራሷ ይህን ማድረግ ካልፈለገች ከሴቶች አንዷ ይህንን ታደርግላታለች።

ማንም ሴት ድብቅ ገላዬን የመንካቷ ነገር ደስ ስላላሰኘኝ እራሴ ላደርገው ወሰንኩ።

ችግሩ ግን ጣቶቼን በዚህ አካሌ ላይ ሳሳርፍ አስደሳች የሆነ የፍትወት ስሜት ተሰማኝ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እጅግ የላቀ ጣፋጭ ስሜት ተሰማኝ። ይህ ከፍተኛው የፍትወት እርካታ ስሜት ማለትም ጡዘተ ፍትወት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ።

አሁን ከላይ የጠቀስኩት የክብረ ንጽሕናዬ ሽፋን በሚገባ ተለጥጧል። ነገር ግን ያለማቋረጥ እያሳሰበኝና እያስጨነቀኝ ያለው ነገር ከጋብቻ በፊት ጡዘተ ፍትወትን ስላገኘሁ እግዚአብሔር ተቆጥቶኝ ይሆናል በማለት ነው። ይህን የእርካታ ስሜት በመፈጸሜ ኃጢአት አድርጌ ይሆንን? በቤተ ክርስቲያን የመዘምራን አገልግሎቴ መቀጠል እችል እንደሆነ አላውቅም። ምን ትላላችሁ?

ውድ ሊዲያ፥

የፍትወተ ሥጋ ኃጢአት አልፈጸምሽም።

ኃጢአት ይሆን የነበረው ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸምሽ ቢሆን ነበር። በሌላ አባባል ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው። ከፍተኛ የፍትወት እርካታ ስሜት ማግኘት ግን ኃጢአት አይደለም። እግዚአብሔር በአንቺ አይቆጣም።

በመዘምራን ውስጥ መዘመርሽን ቀጥይ። አሁንም ሆነ ካገባሽ በኋላ ክርስቶስን በሙሉ ልብሽ አገልግይው።

ዳግላስ፦ ከሁለት ወር በፊት እኔና ባለቤቴ ክርስቲያኖች ሆንን። ክርስቶስ ይቅር እንዲለን ጠይቀነው እንደ ጌታችን አድርገን ተቀበልነው።

ሦስት ልጆች አሉን። በትዳራችን የወለድነው አንዱን ብቻ ነው። ሁለተኛው የእኔ ልጅ ነው። ከማግባቴ በፊት ከአንዲት ልጃገረድ የወለድኩት ነው። ሦስተኛዋ የባለቤቴ ልጅ ስትሆን ከጋብቻችን በፊት ከሌላ የወንድ ጓደኛዋ የወለደችው ነው።

ችግሩ ባለቤቴ የድሮ የወንድ ጓደኛዋን ትወደዋለች። ዛሬ በቤት የተወችለትን መልእክት አገኘሁት።

> የቦታ ርቀት ይለያየን እንጂ ሁሉም ነገር መልካም ነበር። ውዴ፥ የምትጎበኘኝ መቼ ነው? ጽፌልህ ነበር፥ መልስ ግን ነፈግከኝ።

ስለ ጉዳዩ ስጠይቃት «ስለቀድሞው የወንድ ጓደኛዬ እንዴት ትጠይቀኛለህ? አንተስ ብትሆን ከቀድሞዋ የሴት ጓደኛህ ጋር እንደምትገናኝ የማላውቅ መሰለህ?» በማለት ትመልስልኛለች።

እባካችሁ እርዱኝ! ትዳራችን በቀድሞ ወዳጆቻችን እየተመረዘ ነው። ተጋብተን አብረን እየኖርን እንኳ የቀድሞ ወዳጆቻችን ፍቅር አልለቀቀንም። ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ከእነርሱ ጋር መገናኘታችንን አላቋረጥንም።

ውድ ዳግላስ፥

በሠርጋችሁ ቀን አንተና ባለቤትህ

ሀ) እርስ በርስ ለመዋደድ

ለ) እርስ በርሳችሁ አንዳችሁ ለሌላችሁ *ታማኝ* ለመሆን ቃል ኪዳን ገብታችኋል።

ጋብቻችሁን የፈጸማችሁት በቤተ ክርስቲያን ወይም ቤት ሊሆን ይችላል። በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ጋብቻ ሁልጊዜ እነዚህን ሁለት ነገሮች ማድረግ ነው። ስለዚህ ዳግላስ አንተና ባለቤትህ እነዚህን ሁለት ቃል ኪዳኖች መጠበቅ አለባችሁ። ነገር ግን እንዴት?

ከገባችሁት ቃል ኪዳን እንጀምር ሀ) እርስ በርሳችሁ *ለመዋደድ*። እስከ አሁንም ሁለታችሁም ለቀድሞ ወዳጆቻችሁ የፍቅር ስሜት አላችሁ። ሆኖም ግን እነዚያ ስሜቶች ሊሞቱ ይችላሉ። እስኪሞቱ ድረስ ልታስርቡአቸው ትችላላችሁ። የፍቅር ስሜት ስንመግበው የሚያድግ፥ ስናስርበው ደግሞ የሚሞት ነገር ነው።

ለቀድሞ ወዳጆቻችሁ ያላችሁን ስሜት ለማስራብ ለእነርሱ መጻፍም ሆነ ከእነርሱ ጋር የመገናኛ ጊዜ ማመቻቸትን አቁሙ።

እነዚህን ስሜቶች እያስራባችሁአቸው እያላችሁ አንዳችሁ ለሌላችሁ ያላችሁን የፍቅር ስሜት ደግሞ መግቡት። ይህንንም በመልካም ቃሎችና ተግባራት በየዕለቱ ለትዳር ጓደኞቻችሁ ፍቅር በማሳየት ትፈጽሙታላችሁ።

ዳግላስ ለባለቤትህ ደግ መሆንን ስትመርጥ ለእርሷ ያለህ ስሜት ሲያድግ ታየዋለህ። ከቀድሞ ጓደኛህ ጋር ምንም ዓይነት የተቃራኒ ጾታ ቅርበት ባለማድረግ ለእርሷ የነበረህን ስሜት ታከስመዋለህ።

አሁን የገባችሁትን ሌላኛውን ቃል ኪዳን እንመልከት። ለ) አንዳችሁ ለሌላችሁ *ታማኝ* መሆን። የፍትወት ኃጢአት ከሌላው ኃጢአት በተለየ ሁኔታ በአካል ላይ የሚሠለጥን መሆኑን በመግለጽ እግዚአብሔር ያስጠነቅቀናል።

«ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ኛ ቆሮ. 6፡18-20)። «ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል» (1ኛ ቆሮ. 10፡13)።

በደብዳቤህ «ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ከእነርሱ ጋር መገናኘት ልናቆም አልቻልንም» ብለሃል። እግዚአብሔር እዚህ ነጥብ ላይ ከአንተ ጋር አይስማማም። ማቆም አለባችሁ ይላል። በምትፈተኑበት ጊዜ መውጫውን ስለሚያዘጋጅላችሁ ልታቆሙት ትችላላችሁ። ስለዚህ ድልን መምረጥ ትችላላችሁ። ከመረጣችሁት የእናንተ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን መታዘዝ ምረጡ። በሠርጋችሁ ቀን የገባችሁትን ሁለት ቃል ኪዳኖች ጠብቁ።

የምታደርጉት ምርጫ የትዳር ሕይወታችሁንም ሆነ የዘላለም ስፍራችሁን የሚወስን ይሆናል።

ማርታ፡- በትምህርት ቤት በነበርኩበት ወቅት ጠንካራ ክርስቲያን ነበርኩ። ሕይወቴን ለኢየሱስ ሰጥቼ እኖር ነበር። ከትምህርት ቤት ከለቀቅኩ በኋላ ወደ ኋላ መመለስ ጀመርሁ። በ19 ዓመቴ አረገዝኩ። በተከታዩ ዓመት ይኸው ሰው እንደገና አስረገዘኝ። ሰውዬው ክርስቲያን አይደለም።

አሁን ሁለት ነገሮች ተፈጽመዋል። በመጀመሪያ፥ ወደ ኢየሱስ ተመልሼ ቀሪውን ዘመኔን በእርሱ መንገድ ለመኖር ወስኛለሁ። ሁለተኛው ነገር፥ ይህ ሰው ሊያገባኝ ጠይቆኛል።

ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ላገባው ይገባልን? ሁሉን ነገሩን እወደዋለሁ። (ከእርሱ የማልወዳቸው ነገሮች ጠጪነቱንና ኢየሱስን ያለመውደዱን ነው)።

ካላገባሁት ልጆቼ ያለአባት ያድጋሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮ. 6፡14 እንደዚህ እንደሚል አውቃለሁ።

«ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? አንዳንድ ጊዜ ግን በመካከላችን ልጆች ስላሉ ተጣምረናል እላለሁ።

ውድ ማርታ፥

ለክርስቲያን ወጣቶች ሁልጊዜ እንዲህ በማለት እንመክራቸዋለን። «እናንተ ጌታን የምትወዱትን ያህል ጌታን የሚወድ ሰው አግቡ። አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በእርግጥ የማይወድ ሰው ሲያገባ በቤት ውስጥ ከፍተኛ ችግር ይኖራል።

የአንቺን ጉዳይ በተመለከተ ግን ከእርሱ የወለድሻቸው ልጆች ስላሉሽ ልትከተያቸው የምትችያቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡-

1ኛ መንገድ፡- እንዲህ በማለት ጸልዪ፥ «ጌታ ሆይ፥ ጀርባዬን ለአንተ በመስጠት በድዬሃለሁ። እባክህን ይቅር በለኝ። አሁን ለልጆቼ ብዬ ይህን ሰው ማግባት ያለብኝ ይመስለኛል። አንተን የሚወድ ባል ለሌላት ሴት ሕይወት ከባድ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ። ኃጢአቴ ሕይወቴን ከባድ አድርጎብኛል። ከአሁን ጀምሮ ለአንተ እኖራለሁ።»

2ኛ መንገድ፡- ወይም እንዲህ በማለት መጸለይ ትችያለሽ፥ «ጌታ ሆይ ወደ ኋላ ስለመመለሴ ኃጢአት በፊትህ እናዘዛለሁ። አንተን የማይወድን ይህን ሰው ላገባው እንደማይገባኝ አስባለሁ። ልጆቼ ያለአባት ማደጋቸው ከባድ እንደሆነ እረዳለሁ። እባክህን ለልጆቼ ጥሩ ወላጅ እንድሆን እርዳኝ።»

ማርታ በደብዳቤሽ ውስጥ የሚከተለው አባባልሽ እጅግ አስደስቶናል፥ «ወደ ኢየሱስ ተመልሼ የቀረውን የሕይወት ዘመኔን በእርሱ መንገድ ለመሄድ ወስኛለሁ።» በፍርዱ ቀን እግዚአብሔር እንዲህ ይልሻል። «ልጄ ማርታ፥ ኃጢአትሽ በክርስቶስ ደም ታጥቦልሻል። ወደ ዘላለም ሕይወት ግቢ።»

በምድር ላይ በምትኖሪበት ጊዜ የሠራሽው ኃጢአት በትዳር ሕይወትሽና በልጆች አስተዳደግሽ ተጨማሪ ችግር ሊያመጣብሽ ይችላል።

ኃጢአት ሁልጊዜ ችግር ያመጣል (ገላ. 6:7)። *ልጆችሽ እያደጉ ሲሄዱ ከጌታ ወደ ኋላ መመለስ የሚያመጣውን ችግር በመግለጽ አስጠንቅቂያቸው። በክርስትና ሕይወታቸው በግልጽ ወደፊት እንዲቀጥሉ አበረታቺያቸው። በፍጹም ወደ ኋላ እንዳይመለሱ!*

ኢያሱ፡- ያደግሁት በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ነው። በ12 ዓመቴ ክርስቶስን ተቀበልኩ። በጎረምሳነቴ ወቅት ወደ ኋላ ተመለስኩ። በርካታ የሴት ጓደኞች ነበሩኝ። ላገባት የወሰንኳት ሴት ግን አልነበረችም። እንዲሁ ለጊዜያዊ ደስታ የሚሆን ፍቅር ነበር። ሁለቱን አስረግዤአለሁ። የመጀመሪያዋ ያረገዘችው እንዳገባት ብላ ነበር። ሌላኛዋ ግን ያረገዘችው በድንገት ነበር።

ለአስተማሪነት ከሠለጠንኩ በኋላ ላገባት ከምፈልግ አንዲት ክርስቲያን ጋር ተዋወቅሁ። ከሌሎች የሴት ጓደኞቼ የወለድኳቸው ልጆች እንዳሉኝ አልነገርኳትም ነበር። ነገር ግን ጉዳዩን ከእናቴ ሰማችው። ከዚያም እነዚያን ሁለት ሴቶች ያስረገዝኳቸው እኔ እንደነበርኩ አመንኩላት። ከዚህ በኋላ ግን ይህን ከመሰለ ኃጢአቴ እንደተመለስኩና ደግሜም እንደማልፈጽመው ነገርኳት።

እርሷም እንዲህ በማለት መለሰችልኝ «እግዚአብሔር ይቅር እንዳለህ እርግጠኛ ነኝ፤ ስላለፈው ሕይወትህ ይቅር ልልህና ያለፈውን ሕይወትህን ልረሳው እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ በኋላ ስለቀድሞ ኃጢአቶችህ አናውራ።»

ከዚያም ተጋባን። ትዳራችን ደስታ የሞላበት እንደሚሆን ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ስጠይቃት ስላስረገዝኳቸው ሁለት ሴቶች ትጠይቀኝ ጀመር። እንዲያውም «ከእኔ ሰውነት ይልቅ የእነርሱን ትወድ ይሆናል» አለችኝ።

ከአንድ ሰዓት በላይ አንዳችን በሌላችን ላይ ስንከራከር ቆየን። በመጨረሻ «ከሁለቱ ሴቶች ጋር ስላደረግካቸው ኃጢአቶችህ ሁሉ ይቅር

ብዬሃለሁ። ከዚህ በኋላ የቀድሞውን ነገር ፈጽሞ አላነሣም» በማለት ቃል ገባችልኝ።

ስለገባችልኝ ቃል ኪዳን በጣም ደስ ብሎኝ ያን ቀን ለማስታወስ በማስታወሻዬ መዘገብኩት።

ነገር ግን ከዚያን ቀን ጀምሮ የጦፈ ክርክሮች ተነሥተዋል። ሁልጊዜ ስለ ቀድሞ የፍትወተ ሥጋ ኃጢአቶቼ ትከስሰኛለች።

ይቅርታ አድርጋልኝ ጉዳዩን ልትረሳ ያልቻለችው ለምንድን ነው?

ውድ ኢያሱ፥

ባለቤትህ ደስተኛነት ያልተሰማት ከሌሎች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለፈጸምክ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው እንደዚያ እንዲሰማቸው አድርጎ እንደሆነ መዘንጋት የለብህም። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥር አንድ የፍትወት ጓደኛ እንዲኖራቸው አድርጎ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ማቴ. 19:4-6፤ 1ኛ ቆሮ. 6:16)። ሰዎች እንደ እንስሳት አይደሉም። ሰዎች የትዳር ጓደኛቸው ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲያደርግ ያዝናሉ።

ኢያሱ ስለዚህ ለአንተ የምንመክርህ ሚስትህን እንድትታገሥ ነው። የቀድሞ ነገርህን ልትረሳ ብትችልም ጊዜ ይፈጅባታል። የቀድሞ ኃጢአቶችህ ጎድተዋታል፥ ጉዳት ደግሞ ለመፈወስ ጊዜ ያስፈልገዋል።

ልጆችህ ከትዳር ጓደኞቻቸው በስተቀር ከማንም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈጽሙ ምከራቸው።

ሻሮን፡- ከቤተ ክርስቲያኔ መጋቢ ጋር ፍቅር ይዞኛል። ለስብከት በሚቆምበት ጊዜ ሁሉ መልእክቱን ከማድመጥ ይልቅ አእምሮዬ ስለ እርሱ ያልማል። ስለ እርሱ ያለኝን ስሜት ሁሉ ለመቋቋም ብታገልም አልቻልኩም። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከዚህ ቀደም ካሰብኩትና ከተለማመድኩት በበለጠ አእምሮዬን ይሞላዋል።

ችግሩ እኔ ያላገባሁ ስሆን፥ እርሱ ግን ሚስትና ሁለት ልጆች አሉት። ስለ እርሱ ያለኝን ስሜት ነግሬው ባላውቅም፥ ለእርሱ ያለኝ ፍቅር ግን እያደገ ሄዷል። በቅርቡ እርሱን ለማየት ብቻ ብዬ የሐሙስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መካፈል ጀምሬአለሁ። እንደሚወደኝ ነግሮኝ ባያውቅም አመለካከቱ ግን ያስታውቅበታል።

ምን ማድረግ ይገባኛል? የሚሰማኝን ልንገረውና ምክር ይስጠኝን? አደራ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሂጂ እንዳትሉኝ። ወላጆቼ ለብዙ ዓመታት የኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ብተወው ሰዎች ምን ሆና ነው ብለው ይጠይቃሉ።

ውድ ሻሮን፥

የመጋቢሽን ቤተሰብ አታፍርሺ። እንደምትወጂው ትናገሪያለሽ። በእርግጥ የምትወጂው ከሆነ በኃጢአት እንዲወድቅ አትፈታተኚው። ለሚስቱና ለልጆቹ ኀዘንን አታምጪ።

ምን እንደሚሰማኝ ልንገረውን? ብለሽ ጠይቀሽናል። መልሳችን በፍጹም አትንገሪው ነው። አንድ መጋቢ አንዲት ሴት ወደ እርሱ ዘንድ መጥታ «አባክህን ጸልይልኝ፥ *በአንተ* ፍቅር በጣም ተማርኬአለሁ» ብትለው ሊፈተን ይችላል።

ሻሮን ብቻችሁን የምትሆኑበትን ሁኔታ በፍጹም አታመቻቺ።

እርሱን ለማየት ብቻ የጀመርሽውን የሐሙስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አቁሚ። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ውስጥ ግቢ። ምናልባት በቤት ውስጥ የሚደረጉ ቢሆኑ አይከፋም።

ለእርሱ ያለሽ ስሜት እየጠነከረ የሚሄድ ከሆነ ያንን ቤተ ክርስቲያን ትተሽ ወደ ሌላ ሂጂ። እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል የምታስተምር ሌላ ቤተ ክርስቲያን ፈልጊ። የወላጆቿን ቤተ ክርስቲያን ለምን ተወች ብለው ሰዎች ቢጠይቁም እንኳ አትጨነቂ።

*መጽሐፍ ቅዱስ* ከኃጢአት እንድንሸሽ ያስተምረናል (2ኛ ጢሞ. 2፡22)።

እንድርያስ፡— ላገቡ ሰዎች የሚሆን መኖሪያ በሌለበት አንድ ካምፕ ውስጥ እሠራለሁ። ስለዚህ አንዲት ክፍል ውስጥ ብቻዬን እኖራለሁ። ባለቤትና ልጆቼ ራቅ ባለ ስፍራ ይኖራሉ። ወደ ቤተሰቤ የምሄደው በወር አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

ጥያቄዬ እንደ ክርስቲያን ልትረዳኝ የምትችል የሴት ጓደኛ ልትኖረኝ ተፈቅዶአልን? ወይስ ይህ ኃጢአት ነው?

*ታላቅ ወንድሜ ሲናገር «በባሕላችን መሠረት የሴት ጓደኛ ያለው ወንድ በሚስቱ ላይ ኃጢአት አይሠራም። ኃጢአት የሚሠራው በልጅቷ አባት ላይ ብቻ ነው። ዝሙት የምትፈጽም ሴት ግን ኃጢአት የምትሠራው በባሏ ላይ ነው።»*

*ምን ትላላችሁ?*

*ውድ እንድርያስ፥*

*ወንድምህ የገለጸው ልማድ በአንተ ባሕል ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያለ ነው። በምድር ላይ ባሉ አገሮች በሙሉ ያመነዘረች ሴትን አቃልለው ሲያዩ ተመሳሳይ ጥፋት ለፈጸመው ወንድ ግን ብዙም ትኩረት አይደረግበትም። በመላው አውሮፓ፥ አፍሪካ፥ አሜሪካና እስያ ወንድ ሚስቱ የወንድ ጓደኛ በሚኖራት ጊዜ ይበሳጫል። ነገር ግን እርሱ የሴት ጓደኞች ቢኖሩትም ስለ ሴት ጓደኞቹ ሚስቱ ምንም መቆጣት እንደሌለባት ያስባል።*

*ሆኖም ግን፥ እግዚአብሔር ፈራጅ ነው። «አታመንዝር»፥ «... ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ።» ይላል።* (ዘጸ. 20፡14፤ ምሳ. 5፡15-18)

እንድርያስ አሁን መምረጥ ያለብህ የሰውን ልማድ ለመከተል ወይም የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመፈጸም ይሁን።

እባክህን በጥንቃቄ አስብና ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ውሰድ። አስታውስ በሕይወትህ መጨረሻ ፍርድ የሚሰጥህ በሰው ልማድ ሳይሆን በፈጣሪህ ሕግጋት ነው።

እግዚአብሔርን መታዘዝ ከመረጥክ ዛሬ ይህንን ጸሎት እንድትጸልይ እንጠይቅሃለን «ጌታ ሆይ፥ ያለ ሚስቴ መኖር እንዴት ከባድ እንደሆነብኝ ታውቃለህ። እባክህን በአንድነት የምንኖርበትን ሁኔታ አንተው አመቻችልን»

እግዚአብሔር ይህንን ጸሎት እንደሚሰማ እናምናለን። ምክንያቱም ቃሉ ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይመክራል (1ኛ ቆሮ. 7፡2–5)።

ጵርስቅላ፡— የኤድስ በሽታ የሚስፋፋበት ዋናው መንገድ የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መሆኑ እውነት ነውን?

ውድ ጵርስቅላ፥

ብዙ በኤድስ በሽታ የተለከፉ ሰዎች ሕመሙ የያዛቸው ቀደም ብሎ በበሽታው ከተለከፈ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረጋቸው ነው።

ኤድስ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍባቸው ሌሎች ጥቂት መንገዶች አሉ። ለምሳሌ፥ የኤድስ ቫይረስ ተሸካሚ የሆነች እርጉዝ ሴት በሽታውን ወደሚወለደው ሕፃን ማስተላለፍ ትችላለች። አንዳንድ ሰዎች ኤድስ የያዛቸው የተበከለ ደም ባለበት መርፌ በመጠቀም ነው። ሌሎች ደግሞ ኤድስ በሽታ ያለበትን ሰው ደም በመንካት ነው።

ሆኖም ግን፥ በኤድስ በሽታ ከተለከፉ ሰዎች 95% በሽታው የያዛቸው በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ነው።

የኤድስ ቫይረስ ወደ ሰውነት ብዙ ጊዜ የሚገባው በሴትና በወንድ ብልት፥ በፊንጢጣና በአፍ ነው።

ናኦሚ፡— ኤድስ ያለበት ሰው ምን ይሆናል? የሕመም ስሜት ሊሰማት ይጀምራልን፥ ወይስ ምን ይሆናል?

ውድ ናኦሚ፥

ለምሳሌ አንዲት ሴት ከተለያዩ ወንዶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብትፈጽም ከወንዶቹ አንዱ ኤድስ ቢኖርበት የኤድስ ቫይረስ ከብልቱ ወደ እርሷ ሰውነት ይገባል። ግን የሆነውን ነገር ምንም አታውቅም። ለረጅም ጊዜ ጤነኛ መስላ ጤንነት እየተሰማት ትኖራለች። የኤድስ ቫይረስ ለበርካታ ወራት ወይም ዓመታት በሰውነቷ ውስጥ *በጸጥታ* ይሠራል።

በአንድ ወቅት በድንገት የኤድስ ቫይረስ ከፉኛ ሊያጠቃት ይጀምራል። ክብደቷ ሊቀንስ፥ የማያቋርጥ ተቅማጥና ትኩሳት ሊኖራት ይችላል። በዚያን ጊዜ የኤድስ በሽተኛ መሆኗን ትረዳለች።

አብነር፡- እኔና ባለቤቴ ክርስቶስን እንወዳለን። ኤድስ ላለባቸው ሰዎች አንድ ነገር ማድረግ እንፈልጋለን። እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?

ውድ አብነር፥

እናንተ ልክ እንደ ኢየሱስ ናችሁ! እርሱ በጽኑ በሽታ ለሚሰቃዩ ሰዎች ሁሉ ወዳጅ ነበር። ማንም ሰው ሊደርስላቸው ለማይፈልጋቸው ሰዎች ፈጥኖ የሚደርስና የሚጎበኛቸው ነበር።

አብነር እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን? የሚል ጥያቄ በማቅረብህ እናመሰግንሃለን። መልሳችንን ስለ አንድ በኤድስ ስለተያዘ ሰው በመንገር እንጀምር። (ስሙን ዮሐንስ እንበለው)።

ዮሐንስ በአንድ ቢሮ ውስጥ ከበርካታ ሴቶች ጋር ይሠራ ነበር። ዓላማው ከእያንዳንዳቸው ጋር የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ነበር። ጓደኞቹ ስለ ኤድስ በሽታ እየነገሩ ባስጠነቀቁት ጊዜ ሁሉ «በዚህ መንገድ የኖርኩት ለብዙ ዓመታት ነው፥ ምንም ዓይነት በሽታ ይዞኝ አያውቅም» በማለት ይመልስላቸው ነበር።

ነገር ግን የማይቀረው ነገር ሆነ። ዮሐንስ በኤድስ ተለከፈ። ቫይረሱ የተላለፈበት ከአንድ ወፍራም ሴት ጋር ባደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነበር። «ኤድስ የሰውን ክብደት በመቀነስ ቀጭን የሚያደርግ ነው ። ይህች ወፍራም ሴት ኤድስ ሊኖርባት አይችልም» ብሎ ያስብ ነበር። ሆኖም ይህ ከመሆኑ ከስድስት ወር በፊት በኤድስ በሽታ ከተለከፈ አንድ ሰው ጋር በፈጸመችው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በቫይረሱ ተይዛ ነበር። በሽታው ከዚያ ሰው ወደ እርሷ ተላለፈ። ከእርሷ ደግሞ ወደ ዮሐንስ ተላለፈ።

ለተከታዮቹ ጥቂት ዓመታት ዮሐንስ በኤድስ ቫይረስ እንደተለከፈ ሳያውቅ ቆየ። ምንም የሕመም ስሜት አልነበረውም። ጥንካሬና ጤንነት አልተለየውም። ካገኛት ሴት ሁሉ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እየፈጸመ መኖሩን ቀጠለ። በተጨማሪ እራሱን እንዲህ በማለት ያታልል ነበር። «በኤድስ ልያዝ አልችልም»! ነገር ግን ይህን በሚልበት ጊዜ እንኳ በቫይረሱ ተይዞ ነበር። በተጨማሪ ቫይረሱን ለበርካታ ሴቶች እያስተላለፈ እንደነበርም አልተገነዘበም።

ከዚያች ወፍራም ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸመ ከአራት ዓመታት በኋላ ነበር ሕመም ይሰማው የጀመረው። ከሳምንት ወደ ሳምንት የማያቋርጥ ተቅማጥ ጀመረው። ትኩሳት ነበረው፥ ክብደቱም እየቀነሰ መጣ። በመጨረሻ ወደ ክሊኒክ ሄደ።

ሐኪሙ «አዝናለሁ፥ የኤድስ በሽተኛ ነህ። ከዚህ በኋላ ከማንም ጋር ያለኮንዶም የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳታደርግ። ደምህም ማንንም እንዳይነካ አድርግ» አለው።

ዮሐንስ እጅግ ተቆጣ! የኤድስ ቫይረሱን ያስተላለፈበትን ሰው ጠላ። ግን ማን መሆኑን መገመት አልቻለም። በዚህ ወቅት በርካታ የሴት ጓደኞቹ

በኤድስ ተይዘው ነበር። (ወፍራሟ ሴት ብቻ ሳትሆን ከእርሱ የተላለፈባቸው አንዳንድ ሴቶችም ጭምር ማለት ነው።)

ከአንድ ሳምንት በኋላ ዮሐንስ ከመቆጣት ይልቅ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማው ጀመር። *«እኔ የኤድስ ቫይረስ ያስተላለፍኩባቸው ሰዎች ስንት ይሆኑ? ቁጥራቸው በርከት ካለ ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜያለሁ። እነርሱም ለሌሎች አስተላልፈውት ይሆናል....ምን ያህል እንደሆኑ ማን ያውቃል?»*

የዮሐንስ ጤንነት ከዕለት ወደ ዕለት ወደ ከፋ ሁኔታ ተሸጋገረ። ብዙ ጊዜ በሕመም ይሰቃይ ነበር። አብዛኞዎቹ ዘመዶቹ ጀርባቸውን ሰጡት።

ዮሐንስ መሞት ፈለገ! ነገር ግን ፈጣሪውን ለመገናኘት ፈራ!

* * * * * * *

አብነር፥ አንተና ባለቤትህ እንደ ዮሐንስ ላሉ ሰዎች ምን ለማድረግ ትችሉ ይሆን? ልታደርጉት የምትችሉት ብዙ ነገር አለ! «በኤድስ ወደተያዘ ሰው መቅረብ ፈጽሞ አልፈልግም» ከሚሉ ሰዎች ይልቅ እንደ ዮሐንስ ከመሰሉ ሰዎች ለአንዱ ጓደኛ መሆን ትችላላችሁ። ስቃዩን የሚያስታግሡለትን መንገዶች ልትፈልጉለት ትችላላችሁ።

እንደ ዮሐንስ ያሉ ሰዎችን ለመርዳት በምታደርጉት ጥረት ኤድስ ሊይዛችሁ ይችል ይሆንን? መልሱ ኤድስ በመጨባበጥ፥ ተቃቅፎ ሰላምታ በመለዋወጥ፥ ከአንድ ገበታ ላይ አብሮ በመብላት፥ በአንድ ዓይነት ሽንት ቤት በመቀመጥ ፈጽሞ አይተላለፍም። ነገር ግን ደሙን ከነካችሁ ሊተላለፍባችሁ ይችላል።

ከኤድስ በሽተኞች ጋር የሚሠሩ ሐኪሞች ወይም ነርሶች ኤድስ ያለባቸውን ሰዎች እንዴት በሽታው ሳይተላለፍባችሁ ልትረዱ እንደምትችሉ ሊነግሯችሁ ደስተኞች ናቸው።

እንደ ዮሐንስ ያለን ሰው ለሥጋው የሚያስፈልገውን ነገር በማድረግ በምትረዱበት ወቅት የወንጌልን የምሥራች ለመንገር ዕድል ታገኙ ይሆናል። በኤድስ የተያዘ ሰው «በኃጢአቴ ምክንያት እግዚአብሔር ጀርባውን ሰጥቶኛል» ብሎ ለራሱ ይናገር ይሆናል። እውነቱ ግን፦

> *ሁላችንም ኃጢአትን አድርገናል። በኃጢአታችን ምክንያት ሁላችንም ወደ ገሃነም መሄድ አለብን። ነገር ግን ይቅርታን እናገኝ ዘንድ ኢየሱስ በእኛ ስፍራ መከራን ተቀበለ። ኢየሱስ ባደረገው ሥራ ምክንያት እርሱን እንደ አዳኝና ጌታ የሚቀበል ማንኛውም ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል።*

ይህ መልካም ዜና አይደለምን? ይህን የምሥራች በኤድስ የተያዙትን ሰዎች ጨምሮ ለሁሉም ሰው እንናገር።

ያዕቆብ፦ የዩኒቨርስቲ 1ኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። ኤድስ እንዳይዘኝ ማድረግ እንዴት እችላለሁ?

ውድ ያዕቆብ፥

አንዳንድ ሰዎች በኤድስ የሚያዙት በበሽታው የተለከፈን ሰው ደም በመንካት ነው። ስለዚህ አንድ ልንነግርህ የሚገባ ነገር የማንንም ደም እንዳትነካ ተጠንቀቅ ነው። በተጨማሪ ከማንኛውም በሽታ አስተላለፊ ሕዋስ ነፃ ባልሆነ መርፌ እንዳትወጋ ተጠንቀቅ።

ሆኖም ግን 95% በኤድስ የተያዙ ሰዎች በሽታው የያዛቸው በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ባደረጉት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። ስለዚህ ልንነግርህ የሚገባው ትልቁ ቁም ነገር ኤድስ ካለበት ከማንኛውም ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳትፈጽም ነው።

ችግሩ ግን አንድን ሰው በማየት «ይህ ሰው የኤድስ በሽታ እንደሌለበት እርግጠኛ ነኝ» ማለት ያለመቻሉ ነው። ብቸኛ ማረጋገጫው በሆስፒታል የሚደረግ የደም ምርመራ ነው።

ስለዚህ በኤድስ በሽታ ከተያዘ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳንፈጽም ልንጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው? ከሁሉም የተሻለው መልስ፦

*«የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሚገባህ ከትዳር ጓደኛህ ጋር ብቻ ነው። ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አትፈጽም። ከጋብቻ በኋላ ደግሞ ለሚስትህ ታማኝ ሁን።»*

እግዚአብሔር የሚለው በትክክል ይህንን እንደሆነ ትገነዘባለህ። ኤድስን የመከላከል ከሁሉ የላቀው መንገድ እግዚአብሔርን መታዘዝ ነው። አመንዝራነት ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነትና ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የሚደረግ ግብረ ሰዶምን ሙሉ በሙሉ አስወግድ።

«ምንጭህ ብሩክ ይሁን፤ ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ፥ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ፥ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ጥገብ። ልጄ ሆይ፥ ስለ ምን ጋለሞታ ሴት ትወድዳለህ? የሌላይቱንስ ብብት ለምን ታቅፋለህ? የሰው መንገድ በእግዚአብሔር ፊት ነውና፥ አካሄዱንም ሁሉ እርሱ ይመለከታልና። ኀጥአንን ኃጢአቱ ታጠምደዋለች፥ በኃጢአቱም ገመድ ይታሰራል። አልተቀጣምና እርሱ ይሞታል፤ በስንፍናውም ብዛት ይስታል።» (ምሳ. 5፡18–23)



«ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው። (ዘሌዋ. 20፡13)

«ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።» (1ኛ ቆሮ. 6፡9–11)።

ኤድስ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች አንዱ ብቻ ነው። እንደ ቂጥኝና ጨብጥ የመሳሰሉ ሌሎችም አሉ። እነዚህ በሽታዎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ (የአባላዘር) በሽታዎች ይባላሉ። ጨብጥና ቂጥኝ በመቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት በምድር ላይ ነበሩ። ኤድስ አዲስ በሽታ ነው። የጀመረው በ1972 ዓ.ም. (በ1980 እ.ኤ.አ ነው)።

አንድ ሕዝብ ለእግዚአብሔር ጀርባውን በመስጠት በግብረ ሥጋ ኃጢአት ውስጥ ሲኖር በርካታው ሕዝብ በእነዚህ በሽታዎች (በአባለዘር በሽታዎች) እንደሚጠቃ የታሪክ እውነት ነው። ኋላም ባሎችና ሚስቶች በአብዛኛው ታማኝ መሆን ሲጀምሩ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ይቀንሳሉ።

ዛሬ በምድር ላይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች (የአባለዘር በሽታዎች) በፍጥነት እየተስፋፉ ናቸው። የሕክምና ሳይንስም ሊገታቸው አልቻለም። ብቸኛው ተስፋችን ወደ እግዚአብሔር መንገድ መመለስ ይኸውም ከጋብቻ በፊት ንጽሕናን መጠበቅና በጋብቻ ውስጥም በታማኝነት መኖር ብቻ ነው።

ስለዚህ ያዕቆብ የምንልህ ነገር፡– *እግዚአብሔርን ታዘዝ። ከማግባትህ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አትፈጽም፥ ካገባህ በኋላ የግብረ ሥጋ ግንኙነትህ ከሚስትህ ጋር ብቻ ይሁን።*

ምናልባት እንዲህ ብለህ ይሆናል። «የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአቶችን ሁሉ ባስወግድ እንኳ የማገባት ሴት ኤድስ ሊኖርባት ይችል ይሆናል። ስለዚህ መያዜ አይቀርልኝም።» ስለዚህ ጉዳይ ልንል የምንችለው ሁለት ነገሮች አሉ።

ሀ) በጥንቃቄ ምረጥ፡– ሚስት በምትመርጥበት ወቅት በፍትወተ ሥጋ ኃጢአት ላይ በድል የኖረች እውነተኛ ክርስቲያን ሴት ምረጥ። በሚገባ ታውቃት ዘንድ ለበርካታ ወራት በጓደኝነት አብርሃት ቆይ፥ ራስህን እንዲህ በማለት ጠይቅ፥ «ከጋብቻ ውጪ ለሚቀርብላት የፍትወተ ሥጋ ኃጢአት ፈተና እምቢ ለማለት የሚያቅታት ሴት ናትን? እንደዚያም ዓይነት ሴት

እንዳልሆነች እርግጠኛ ልሆን የምችለውን ያህል እርግጠኛ ሆኛለሁን? በእርግጥ ያለጥርጥር በጉዳዩ ላይ መድረስ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን አስተውል ስለ አንዲት ሴት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን ከባድ እንደሚሆን ካሰብክ፥ አራት ወይም አምስት የፍትወት ጓደኞች ያሏቸው ሰዎች ከአራቱ ወይም ከአምስቱ የትኛቹም ኤድስ እንደሌለባቸው እርግጠኛ መሆን እንዴት ይችላሉ? አይችሉም! ስለዚህ ነው በርካታ የፍትወት ጓደኞች ያሉአቸው ሰዎች በኤድስ የመለከፍ ከፍተኛ አደጋ ላይ ያሉት።

ለ) የኤድስ ምርምራ አድርጉ፦ ከጋብቻ በፊት ሁለታችሁም ወደ ሕክምና ማቢያ በመሄድ ለኤድስና ለሌሎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ አድርጉ። ይህ ማለት እርስ በርሳችሁ አትተማመኑም ማለት አይደለም። ነገር ግን መልካም የጥንቃቄ እርምጃ ነው።

ቀጥሎ ለጥያቄህ የሰጠነውን መልስ በአጭሩ እንከልስልሃለን። ያዕቆብ እንደ ዩኒቨርስቲ ተማሪነትህ እንዳስተዋልከው በርካታ ተማሪዎች የሚከተሉትን አራት ሕግጋት አይከተሉም። በተለይ ደግሞ የመጀመሪያውን አይታዘዙም። በዚህ ፈንታ ኤድስን ለመከላከል የራሳቸውን ዘዴዎች ለመጠቀም ይሞክራሉ።

## ኤድስን የመከላከያ መንገዶች

1. ከጋብቻ በፊት ከምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመታቀብ እግዚአብሔርን ታዘዝ።

2. ድንግል የሆነች የትዳር ጓደኛ ለማግኘት ሞክር። ወይም ለትዳር ያሰብከው/ካት ሰው «በኃጢአት ስኖር ቆይቼ በቅርቡ ክርስቲያን ሆንኩ።» ካለችህ/ካለህ እንዴት እንደምትኖር/እንደሚኖር ለማየት ጊዜ ውሰድ/ውሰጂ። በፍትወት ኃጢአት የምትኖርን ሴት/የሚኖርን ወንድ በፍጹም አታግባ/አታግቢ። በተጨማሪ ሁለታችሁም ከጋብቻ በፊት ወደ ሕክምና ማቢያ በመሄድ የኤድስ ምርመራ አድርጉ።

3. ከጋብቻ በኋላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከትዳር ጓደኛህ ጋር ብቻ ፈጽም/ሚ– ከአመንዝራነትም ሆነ ከግብረ ሰዶም ተጠንቀቅ/ቂ።

4. የማንንም ደም ወይም (ደም ሊኖርበት የሚችል መርፌን) ከመንካት ተጠንቀቅ/ቂ።

ለምሳሌ፥ ግሬስ በርካታ የፍትወት ጓደኞች ያላት ሲሆን፥ ነገር ግን የኤድስን መተላለፍ ኮንዶሞችን በመጠቀም ለመከላከል ተስፋ ታደርጋለች። ኮንዶም በቦርሳዋ የምትይዝ ሲሆን፥ ከማንኛውም ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያለኮንዶም አትፈጽምም። ነገር ግን፥ ኮንዶም የኤድስ ቫይረስ እንዳያስተላልፍ የማድረግ አቅሙ 100% እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ ግሬስ ያለችው አደጋ ላይ ነው።

ማይክም በርካታ የፍትወት ጓደኞች ያሉት ሲሆን፥ ጥንቃቄው ግን ከግሬስ የላቀ ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽም በኮንዶም ከመጠቀም በተጨማሪ የኤድስ ቫይረሶችን ለመግደል የሚችል መድኃኒት በኮንዶም ውስጥ ይጨምራል። ሆኖም ግን ኮንዶም ከመድኃኒት ጋርም ቢሆን 100% ልንታመንበት አንችልም።

ሐና ደግሞ የበለጠ ጥንቁቅ ናት። ከማርቆስ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ከመስማማቷ በፊት «ከአሁን በፊት ከስንት ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመሃል?» በማለት ጠየቀችው። እርሱም «ከሁለት ብቻ» በማለት መለሰላት። ሐናም ለራሷ እንዲህ አለች «ከአምስት ሴቶች ጋር ፈጽሚያለሁ ቢለኝ ኖር እምቢ እለው ነበር። ነገር ግን ከሁለት ሴቶች ብቻ ስላለኝ ምናልባት እስካሁን በኤድስ አልተያዘም ይሆናል።» ቀጥላ መድኃኒት ያለበት ኮንዶም ሰጠችውና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸሙ።

ሐና በኤድስ የመያዝ አደጋ ውስጥ ወድቃለችን? አዎን። ይህን ሁሉ ጥንቃቄ አድርጋ እንኳ በኤድስ ከመያዝ አደጋ ሙሉ ለሙሉ ነፃ አይደለችም። በቅርቡ ደግሞ እንዲህ በማለት ማሰብ ጀምራለች *«አንድን ሰው የፍትወት ሥጋ ግንኙነት ታሪኩን መጠየቅና ኮንዶም ሰጥቶ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ብዙም አስደሳች አይደለም።»*

እነዚህ ሦስት ወጣቶች በሙሉ ኃጢአታቸውን ሊናዘዙና ንስሐ ገብተው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው ሊቀበሉ ይገባቸዋል።

ያዕቆብ አንተ ይህን እርምጃ ወስደሃልን? ካልወሰድክ ዛሬውኑ ይህን እርምጃ ውሰድ። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡—

> «በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያገኝም» (ዮሐ. 3፡36)።

ዲቦራ፡— የአራት ዓመት ልጄን ከኤድስ በሽታ ለመከላከል የምችለውን ጥረት ሁሉ እያደረግሁ ነው። ወደ ክሊኒክ በምወስደው ወቅት ሁሉ ለነርሷ እንዲህ እላታለሁ፡— «እባክሽን ከማንኛውም በሽታ አስተላላፊ ነፃ መሆኑ በተረጋገጠ መርፌ ተጠቀሚ።» ጥንቃቄዬ ገደብ አለፈን?

ውድ ዲቦራ፥

ጥንቃቄሽ *ከገደብ ያለፈ* አይደለም። ጥሩ እያደረግሽ ነው።

ሆኖም ግን በኤድስ የተያዙ በርካታ ሰዎች በሽታውን ያገኙት ከክሊኒክ ሳይሆን አስቀድመው በበሽታው ከተያዙ ሰዎች ጋር በሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው።

ስለዚህ ልጅሽ እያደገ በሄደ ቁጥር በኢየሱስ ላይ እምነቱን እንዲያደርግ እርጂው። እድሜው 12 ዓመት በሚደርስበት ወቅት የሚከተለውን እንዲል ጸልዩለት፦ «ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ ተቀብያለሁ። ለእርሱ መኖር እፈልጋለሁ። ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት እርሱ ያስቀመጠውን ሕግጋት ተረድቼያለሁና እፈጽመዋለሁ።»

ዶርቃ፦ ለብዙ ዓመታት በቤተ ክርስቲያናችን ሐሙስ ዕለት የሚካሄደውን የሴቶች ስብሰባ በሊቀመንበርነት መርቻለሁ።

ባለፈው ወር ባለቤቴ በኤድስ በሽታ ሞተ። ከእርሱ ሞት በኋላ ወዲያውኑ በጣም ስለታመምኩ ለዚያ ስብሰባ ከነበረብኝ ኃላፊነት እራሴን ማግለል ግድ ሆነብኝ። ቀጥሎም ሐኪሙ በኤድስ በሽታ እንደተለከፍኩ ነገረኝ።

እመኑኝ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ከባለቤቴ ጋር ካልሆነ በስተቀር ከማንም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም።

ሐኪሙ የሚለኝ በሽታው የተላለፈብኝ ከወሰድኩት የሌላ ሰው ደም ወይም ከባለቤቴ እንደሆነ ነው።

አሁን ከሁለት ሴቶች በስተቀር ማንም አይጎበኘኝም። እነርሱ ግን በየቀኑ ይመጣሉ። ያለ እነርሱ ምን እሆን እንደነበር አላውቅም። እራሴን እንዲህ እያልኩ ከመጠየቅ አላቋረጥኩም፥ «ሌሎች ጓደኞቼ ወደየት ጠፉ?» ዛሬ መልሱን አወቅሁት። አዲሷ ሊቀመንበር ለሴቶቹ እንዲህ እንዳለቻቸው ሰማሁ። «ዶርቃ ከአመንዝራነት እንድንሸሽ ሁልጊዜ ታስጠነቅቀን ነበር። አሁን ግን በስውር የፈጸመችውን ኃጢአት ፍሬ እያጨደች መሆኑ አስደንግጦናል።»

ምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት እንዳልፈጸምኩ እግዚአብሔር ያውቃል። አሁን ምኞቴ በክርስቶስ እህቶቼ የሆኑት እንዲጎበኙኝ ብቻ ነው።

ማሳሰቢያ፦ ይህ ደብዳቤ አፍቃሪ እንጂ ፈራጅ መሆን እንደሌለብን ያስታውሰን። ሰዎች በሚታመሙበት ወቅት እንርዳቸው። «ጥፋተኛ» ሆኑም አልሆኑም ልንፈርድባቸው አንሞክር፤ በፍቅር እናጽናናቸው፥ አብረናቸው እንጸልይ፤ ፍርዱን ለእግዚአብሔር እንተወው።

ኒሊ፦ ከኤድስ ሌላ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ሰውን ሊይዙ የሚችሉ በሽታዎች የትኞቹ ናቸው?

ውድ ኒሊ፥

በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በርካታ በሽታዎች አሉ። እነዚህን በሽታዎች «በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች» ወይም የአባላዘር

በሽታዎች በማለት እንጠራቸዋለን። ከኤድስ ሌላ በሚገባ የታወቁ በዚህ ክፍል የሚመደቡ በሽታዎች ቂጥኝ፥ ጨብጥ፥ ከርከርና ሄርፐስ ናቸው።

ሄርፐስ፦ ከፍተኛ *ሥቃይ* የሚያመጣ በሽታ ሲሆን፥ በሕክምና ሊድን አይችልም። ይህ በሽታ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ወደ ሌሎች የዓለም ክፍሎች እየተስፋፋ ነው።

ከርከር፦ በቆላማ አገሮች የሚገኝ ሲሆን፥ በሽታው በሕክምና ሊድን ቢችልም እንኳ በጊዜ ካልተደረሰበት የወንድ ብልትን ያበላሻል።

ቂጥኝ፦ በዓለም ዙሪያ ሁሉ የሚገኝ በሽታ ነው። ከበሽታው ፈውስን የሚሰጥ መድኃኒት ያለን ቢሆንም እንኳ ብዙ ሰዎች በዚህ በሽታ ይሠቃያሉ። የሚሞቱም እንኳ አሉ። ለምን? ምክንያቱ *በወቅቱ* ወደ ሕክምና ስፍራ *ያለመሄዳቸው* ነው።

ጨብጥ ሊድን ይችላል። ጨብጥ የያዘው ሰው ወደ ሕክምና መስጫ ስፍራ ሳይሄድ ለረዥም ጊዜ ቢቆይ የተዋልዶ አካላት ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ። በዚህ በሽታ ምክንያት መካኖች የሆኑ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ናቸው።

በተጨማሪ በጨብጥ በሽታ ተይዛ ከነበረች ሴት የተወለደ ሕፃን እንደተወለደ ወዲያውኑ ዓይኑ ላይ መድኃኒት ካልተደረገለት ሊታወር ይችላል።

**በግብረ *ሥጋ* ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ጥቂት ምልክቶች፦**

- በወንዱ ወይም በሴቷ ብልት ወይም በአፍ ላይ የሚወጣ ውኃ የቋጠረ ኪንታሮት መሰል ነገር ወይም ነጥብ። ሕመም ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል።
- ከወንድ ብልት የሚወጣ ቢጫ ፈሳሽ ሲሆን ፈሳሹም የውስጥ ሱሪን ያቆሽሻል። ሽንት በሚሸናበት ወቅት የማቃጠል ስሜት ይኖራል።
- በሴቶች ከብልታቸው የሚወጣ ያልተለመደ ፈሳሽ ይኖራል። ወይም በሆድ የታችኛው ክፍል ላይ ሕመም ይኖራል።

ከእነዚህ ምልክቶች አንዱ እንኳ የታየበት ሰው *በፍጥነት* ወደ ሕክምና መስጫ ተቋም መሄድ አለበት። ለሳምንት ወይም ለአንድ ቀንም እንኳ መዘግየት የለበትም። አብዛኛዎቹ በግብረ *ሥጋ* ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች በጊዜ የሕክምና እርዳታ እስከተደረገላቸው ድረስ ይድናሉ።

ከሁሉ የሚያሳዝነው ነፍሰ ጡር ሴት በእነዚህ በሽታዎች ስትለከፍ ነው። ብዙ ጊዜ ሕፃኑ ከጤናማ ሰው የተለየ ቅርጽ ይዞ ወይም ሽባ ሆኖ ይወለዳል።

እግዚአብሔር በእነዚህ በሽታዎች ፍርሃት እንድንኖር አይፈልግም። እኔና ካሮል በምንጋባበት ወቅት ሁለታችንም ድንግሎች ነበርን። ስለዚህ በግብረ *ሥጋ* ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች አልነበሩብንም። አሁንም የግብረ *ሥጋ* ግንኙነት የምንፈጽመው እርስ በርሳችን ብቻ ከሆነና እኔም ሆንኩ እርሷ

ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ካልፈጸምን በዚህ መልክ ከሚተላለፉ በሽታዎች በየትኛውም አንያዝም።

**በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች የፈጣሪያችን ዕቅድ ከሁሉ የተሻለ እንደሆነ ዓለምን ያለማቋረጥ ያስታውሳሉ።**

ጌሪ፦ በዛሬ ጊዜ ብዙ ባለትዳሮች ልጅ የማይወልዱ ናቸው። አንድ ቀን አንድ ሰባኪ እንዲህ ሲል ሰማሁት፥ «የወጣትነት ኃጢአቶች ብዙ ጊዜ ባለትዳሮችን ልጅ አልባ ያደርጓቸዋል።» ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

ውድ ጌሪ፥

እውነት ነው። ለምሳሌ እንዲት ተማሪ (ጄን እንበላት) ሴዝ ከሚባል ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸመች። ይህ ፍጹም ጤነኛ ሰው ይመስላል ብላ በማሰብና ምናልባት በሽታ የለበትም ይሆናል በማለት ድርጊቱን ፈጸመች።

ሆኖም ግን ሴዝ፥ ከጄን ጋር ከመገናኘቱ በፊት ከሌሎች ሁለት ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ ነበር። ከሴቶቹ አንዷ ጨብጥ በሚባል በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚተላለፍ በሽታ ተለክፋ ነበር። እናም ይህ በሽታ ወደ እርሱ ተላለፈ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሽንቱን በሚሸናበት ወቅት ሕመም ይሰማው ጀመር። በዚህ ሳምንት ሥራ በጣም ስለሚበዛብኝ ወደ ሕክምና መስጫ ስፍራ አልሄድም፤ በሚቀጥለው ሳምንት እሄዳለሁ ብሎ አሰበ።

በዚህ መካከል ከጄን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ በሽታውን አስተላለፈባት።

ጄን ለረጅም ጊዜ ወደ ሕክምና መስጪያ ስፍራ አልሄደችም። ለምን? ምክንያቱም በበሽታው እንደተለከፈች አልተገነዘበችም ነበር። ያልተለመደውን ከብልቷ የሚወጣውን ፈሳሽ አላስተዋለችም ነበር። ሕመም አይሰማትም ነበር። ሆኖም ግን የጨብጥ በሽታው በሰውነቷ ውስጥ በፀጥታ እየሠራ ነበርና የማኅፀን ቧንቧዎቿን አበላሻቸው።

ከአንድ ወር በኋላ ሕመም ስለተሰማት ወደ ሕክምና መስጫ ስፍራ ሄደች። ነገር ግን የደረሰችው በጣም ዘግይታ ነበር። ሐኪሙ ከጨብጥ በሽታዎች እንድትፈወስ የረዳት ቢሆንም «በሽታው የማኅፀን ቧንቧዎችሽን ስላበላሸ፥ ጄን ለመውለድ ዕድል የለሽም። አዝናለሁ። እባክሽን ለጓደኞችሽ በትምህርት ቤት ውስጥ የምትቆዩባቸውን ቀናት በማጥናት እንጂ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጨዋታ አታጥፉ ብለሽ ንገሪያቸው» አላት።

ዛሬ በዚህ ዓለም ላይ በጨብጥ በሽታ ምክንያት ልጅ የሌላቸው በርካታ ሴቶችና (ጥቂት ወንዶች) ይገኛሉ።

ጨብጥ የያዘው ወንድ ለመሽናት ይቸገራል። በተለይ ወደ ሕክምና መስጫ ጣቢያ በወቅቱ ካልሄደ የዘር ፈሳሽ ቧንቧዎቹን ሊያበላሽበት ይችላል። የዘር ፈሳሽ ቧንቧዎቹ ቢበላሹም የዘር ፈሳሹን ማፍሰስ ይችላሉ። ፈሳሹ ትክክለኛ ቢመስልም ግን የወንድ ዘር የለውም።

ስለዚህ ጌሪ *«የወጣትነት ኃጢአቶች ባለትዳሮችን ያለ ልጅ ለማስቀረት ይችላሉ»* በማለት ሰባኪው ሲናገር የሰማኸው በእርግጥ ትክክል ነበር።

በእርግጥ ልጅ ያለመውለድ ምክንያት ይህ ብቻ አይደለም። ስለዚህ ልጅ የሌላቸው ባለትዳሮችን «ኃጢአት አድርጋችኋል» በማለት ልንፈርድባቸው አይገባም። ይልቁኑ ልጅ የሌላቸው ባለትዳሮችን በእግዚአብሔር ታምነው እንዲያገለግሉት ልናበረታታቸው ይገባል!

ከዚህ ጋር በአንድነት ወጣቶችን፥ ኃጢአት መካንነትንና ሌሎች በርካታ ጎዘኖችን እንደሚያስከትል በመግለጽ ማስጠንቀቅ አለብን።

ናታን፦ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ። የሴት ጓደኛዬንም እወዳታለሁ። የእግዚአብሔርን ወይም የሴት ጓደኛዬን ስም ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ላጎድፍ አልፈልግም።

ከፍተኛ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ያለብኝ ሰው ነኝ። ክርስቲያን ከመሆኔ በፊት ለግብረ ሥጋ ግንኙነት የጠየቅኋት ሴት እምቢ ብትለኝ አስገድጄ እደፍራት ነበር። ከሁለት ዓመት በፊት ወንጌልን ሰምቼ ክርስቶስን ተቀበልኩ። ከዚያን ቀን ጀምሮ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። እዚህ በመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ማድረጌ ብዙ ጠቅሞኛል።

ችግሬ ኮርሱን ከጨረስኩ በኋላ ወደ ገጠር ትምህርት ቤት እላካለሁ። በእንደነዚህ ዓይነት ቦታዎች ሰዎች ሁሉ ብዙ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ። የሴት ጓደኛዬ ልትጠይቀኝ ከመጣች ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት እንዴት ልናመልጥ እንደምንችል አላውቅም። ልትጠይቀኝ ካልመጣች ደግሞ በዚያ አካባቢ ካሉ ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳልፈጽም እንዴት መኖር እችላለሁ? ከሴቶች መካከል የሚጋብዘኝ ሰው ቢገኝ እምቢ ማለት እችል ይሆን?

እባካችሁ፥ እባካችሁ እርዱኝ። ኃጢአትን ማድረግ አልፈልግም። በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፍ ማንኛውም በሽታ ነፃ መሆን እፈልጋለሁ። በቂ ዝግጅት ከማድረጌ በፊት ልጅ መውለድ አልፈልግም።

ውድ ናታን፥

ከፍተኛ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ያለው ሰው አንተ ብቻ አይደለህም። በምድር ላይ ያሉ ሰዎች በሙሉ ማለት ይቻላል ይህ ፍላጎት አላቸው።

እግዚአብሔር ለሰዎች ከፍተኛ የፍትወተ ሥጋ ፍላጎት የሰጠው ለምንድን ነው? ምክንያቱም እያንዳንዱ ባል ሚስቱን እንዲወድና ከእርሷ ጋር ብቻ በፍትወት ድርጊት ደስ እንዲሰኝ ስለሚፈልግ ነው።

በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት። (1ኛ ጴጥ. 5:9)

ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ሕግ ሰዎች እራሳቸውን እንዲቆጣጠሩና ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈጽሙ የሚከለክል ነው።

ሰይጣን ይፈትነናል፤ ነገር ግን በዓለም ዙሪያ ድል የጨበጡ ወንድሞች አሉ። ናታን አንተም የድሉ ተካፋይ መሆን ትችላለህ።

ወደ ገጠር ትምህርት ቤት ተመድበህ ስትሄድ ክርስቲያን ወንድሞችን ፈልግ። ለሁለት ወይም ለሦስት «በየሳምንቱ መገናኘት እንጀምር። እንደ ወንድሞች እርስ በርሳችን መበረታታት እንችላለን። በተገናኘንም ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በጸሎት፥ በምስክርነትና ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈተና በመሸሽ እንዴት እንደሆንን እንጠያየቅ» በላቸው።

እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው (1ኛ ተሰ. 5:11)።

እነዚህ ክርስቲያን ወንድሞች ትልቅ እርዳታ ሊሆኑህ ይችላሉ። አንተም ለእነርሱ ትልቅ እርዳታ መሆን ትችላለህ።

አቤሴሎም:- ከአንዲት እህት ጋር በፍቅር ከንፌ ነበር። ትታኝ እስከሄደችበት ቀን ድረስ የምትወደኝ ይመስለኝ ነበር። ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ባለመፈጸሜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ከዚያ የልብ ስብራት በኋላ በእግዚአብሔር መታመኔን ቀጥዬአለሁ።

ከዚያ በኋላ ከሳንድራ ጋር ተዋወቅን። በጣም እወዳታለሁ። እርሷም ኢየሱስንም ሆነ እኔን ትወዳለች።

በሚቀጥለው ዓመት ለመጋባት አስበናል። አሁን የመጀመሪያዋ እህት ትታኝ ስለሄደች እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እኔና ሳንድራ አንድ ልብና አንድ አእምሮ ሆነናል። አብረን ስንሄዝ ስንነጋገርና በችግሮቻችን ላይ ስንወያይ በጣም ደስ ይለኛል።

እስከ ጋብቻችን ቀን ድረስ ራሳችንን በድንግልና ንጽሕና ለመጠበቅ ወስነናል።

ገላዋን በፍጹም አልነካም። በጣም ውብ ናት። ልነካት ከጀመርኩ ልብሶቿን ለማወላለቅ ቀጥሎም.... እፈተናለሁ ብዬ እሰጋለሁ።

ጥያቄዬ መላ አካሏን እንደምወድ ላሳያት ምንም ያደረግኩት ነገር ስለሌለ ለእርሷ ያለኝ ፍቅር ጠንካራ ስለመሆኑ ትጠራጠር ይሆንን? በዚህስ ምክንያት አጣት ይሆንን?

ውድ አቤሴሎም፥

በእግዚአብሔር ታመን! እግዚአብሔር ከዚህ የላቀ ዓላማ ካልኖረው በቀር ሳንድራን አታጣትም (ኤር. 29፡11)።

አካሏን መንካት ወደ ጠንካራ ፈተና ይመራኛል ያልከው እውነት ነው። ስለዚህ ጉዳይ ከእርሷ ጋር ተነጋገሩ። እርሷን የማትነካበት ምክንያት ምን እንደሆነ ንገራት።

ስማ አቤሴሎም፥ ከሳንድራ ጋር ችግሮችን መነጋገርና መወያየት መውደድህ ጥሩ ነው። ካገባሃትም በኋላ እንደዚህ ማድረግህን ቀጥል። *ሚስትህን እንደምትወድ ሰዎች እንዲያውቁ ለማድረግ አትፍራ።* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሏ ምን ያህል እንደሚወዳት ሁሉም ሰው ማየት በመቻሉ ደስተኛ የሆነች ሚስት እናያለን።

> «ወደ ወይን ጠጅም ቤት አገባኝ፥ ያለው ዓላማውም በእኔ ላይ ፍቅር ነው።» (መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 2፡4)

**ጴጥሮስ፦** እኔና ባለቤቴ ክርስቲያኖች ብንሆንም እንኳ በትዳር ሕይወታችን የመጀመሪያ አምስት ዓመታት ብዙ ጊዜ እንጣላ ነበር።

እኔ እግር ኳስ መጫወት በጣም እወዳለሁ፥ በከተማችን ከሚገኙ በጣም ጥሩ ቡድኖች ለአንዱ እጫወታለሁ። በእነዚያ የመጀመሪያ አምስት ዓመታት ግን ባለቤቴ እንደምትቆጣ ስለማውቅ ከጫወታ በኋላ ወደ ቤቴ መመለስ በጣም እጠላ ነበር። ከሁሉ በላይ የምወደውን ስፖርት እንድጫወት ለምን እንደማትፈልግ ልረዳ አልቻልኩም።

ከዚያ አንድ ጓደኛዬ «*Love & Marriage*» «ፍቅርና ጋብቻ» የሚለውን መጽሐፋችሁን ሸጠልኝ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «ባለቤትህ ከምንም ነገር በላይ እንደሆነች ልታሳያት መንገዶችን ፈልግ» የሚል ዐረፍተ ነገር አነበብኩ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እራሴን እንዲህ በማለት መጠየቅ ጀመርኩ። «ባለቤቴ እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ የምታሳየው እግር ኳስ ጨዋታን ከእርሷ በላይ እንደምወድ እያሰበች ይሆንን?»

በሚቀጥለው ቀን ቡድናችን በጣም ወሳኝ ጨዋታ ስለነበረበት በጠዋት ከእንቅልፌ ነቃሁ። ከቤት ከመውጣቴ በፊት ባለቤቴ በጠና መታመሟን ተረዳሁ። በቤት ማንም አልነበረም፥ ስለዚህ ብቻዋን ትቼያት ለመሄድ አልፈለግሁም። ነገር ግን «ጨዋታው ሊያመልጠኝ አይገባም» በማለት ለራሴ አንሾካሾክሁ።

ወደ መኪናዬ መራመድ ከጀመርኩ በኋላ ተመልሼ ወደ ቤት ገባሁ። ባለቤቴን በሕመሟ በመንከባከብ ቤት ለመዋል ወሰንኩ።

በዚያን ቀን ባለቤቴ ከምንም ነገር በላይ (ከእግር ኳስ ጨዋታ ጭምር) እንደምወዳት መገንዘብ ጀመረች።

ከዚያን ቀን ጀምሮ ከምንም ዓይነት ስፖርት በላይ ለእኔ ውድ እንደሆነች ለማሳየት ዕድሎችን መፈለግ ጀመርኩ።

አሁን ቤታችን እጅግ ደስታ የሞላበት ነው። ከጨዋታ በኋላ ወደ ቤቴ ስመለስ ባለቤቴ በታላቅ ፈገግታ ትቀበለኛለች። በተመለከትኩት ለውጥ እጅግ ስለተደሰትኩ ልጽፍላችሁ ወሰንኩ።

ውድ ጴጥሮስ፥

ትላንትና በሚያስገርም ሁኔታ ከአንተ ደብዳቤ ጋር እጅግ ተመሳሳይ የሆነ ደብዳቤ ደረሰን። የጻፈልን አንድ ወጣት ሰባኪ ነው። እርሱም እንዲህ ብሎናል፡-

«ባለፈው ዓመት ባለቤቴ ብዙ ጊዜ መራርና ቁጡ ነበረች። በመጨረሻ ጥፋቱ የእኔ መሆኑን ተገነዘብኩ። በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ለመስበክ ወዲያና ወዲህ እል ነበር። በቤት ግን ባለቤቴን ፍቅር ባለው ርኅራኄ አልመለከታትም ነበር። እናም ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባሁ። «ጌታ ሆይ በአንተ እርዳታ ለባለቤቴ ደግ አሳቢና አጋዥ እሆናለሁ!»

ይህ በትዳራችንና በስብከቴ ላይ ያመጣው ለውጥ አስደናቂ ነው!

የምንቀበላቸው በመቶ የሚቆጠሩ ደብዳቤዎች በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ወንዶች የሚከተለውን እየተገነዘቡ መሆኑን ያመለክታሉ።

> ሚስቱን በመውደድ እግዚአብሔርን ብታዘዝ
> ቤቴ ደስታ የሞላበት ይሆናል።

ዮሐና፡- የትዳራችን ችግር እኔና ባለቤቴ የምንነጋገረው በጣም አልፎ አልፎ መሆኑ ነው። አንዳንድ ጊዜ ለምጠይቀው ጥያቄ እንኳ መልስ አይሰጠኝም። ትሕትና በሞላበት የፍቅር መንገድ ስቀርበው እንኳ ዝም ይላል። ሁለታችንም ክርስቶስን እንወዳለን፥ ነገር ግን የምንጸልየውና የእግዚአብሔርን ቃል የምናነበው በአንድነት ሳይሆን *ለየብቻችን* ነው።

ብቸኝነት ይሰማኛል። እኔና ባለቤቴ የምንኖረው በአንድ ቤት፥ የምንተኛው በአንድ አልጋ ላይ ሆኖ እያለ በጣም ብቸኝነት ይሰማኛል።

ብንለወጥና ጓደኞች ብንሆን ምኞቴ ነው። ነገር ግን ባለቤቴ ትዳራችን ምንም ችግር እንደሌለበትና ጤነኛ እንደሆነ ያስባል።

የግብረ *ሥጋ ግንኙነት* ልምምዳችን አስደሳችነቱ እየቀነሰ ነው። በተቻለኝ መጠን የተነቃቃ የፍትወት ስሜት እንዲኖረኝ እጥራለሁ። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ለባሌ ምንም ፍላጎት የለኝም። ለምን? ምክንያቱም የእርሱ ፍላጎት *ጓደኛዬ* መሆን ሳይሆን *የፍትወተ ሥጋ ግንኙነት አጋሬ* መሆን ነው።

ማሳሰቢያ፦ ይህ የዮሐና ደብዳቤ የሚያመለክተው በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነት ነው።

*ወንዱ ከሚስቱ ጋር የሚነጋገረው አልፎ አልፎ ቢሆንም እንኳ ከፍተኛ የፍትወት ፍላጎት ሊኖረው ይችላል።*

*ሴት ግን ከባሏ ጋር በጣም ጥሩ የሆነ የጓደኝነት ግንኙነት ከሌላት ብዙ የፍትወት ፍላጎት አይኖራትም።*

ለዮሐናና ለባለቤቷ በጻፍነው ደብዳቤ በጓደኛነትም ሆነ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ሊያገኙ ስለሚችሉት ደስታ ገልጸንላቸዋል። (ገጽ 11-58 ያለውን ይመልከቱ።)

አንቶኒ፦ ከተጋባን ስድስት ወራት ሆኖናል። ችግሩ ባለቤቴ ወጣት ስለሆነች ሚስት ስለመሆን የምታውቀው ነገር በጣም ጥቂት ነው።

በየምሽቱ ቤቱ ሥርዓት አጥቶ እራት ሳይዘጋጅ እደርሳለሁ። ዘመዶቼን ስንጠይቅ የምታነጋግራቸው በትሕትና አይደለም። ለማያስፈልጉ ነገሮች ገንዘብ ታጠፋለች። ምን ማድረግ እችላለሁ?

ውድ አንቶኒ፥

ባለቤትህ እንድትለወጥ ልትረዳት ትችላለህ። እንዴት «የፍቅር ዘዴ»ን ተጠቀም።

## የፍቅር ዘዴ

ትእዛዝ 1፥ *እንድትለወጥ በምትነግራት ጊዜ ሁሉ የምትጠቀምባቸው ቃላት ለስላሳና ይቅር ባይነት የሞላባቸው መሆናቸውን አረጋግጥ።*

ሚስትህን ቁጣ በተሞላባቸው ቃላት ከመኮነንክ አትለወጥም። «ባሌ አይወደኝም» በማለት እራሷን ታሳምናለች። እንዴት ልትለወጥ እንደምትችልና የተሻለች ሚስት እንደምትሆን ልታስብ አትፈልግም። በዚያ ፈንታ ታለቅሳለች ወይም መልሳ ትኮንንብሃለች።

ቃሎችህ ለስላሳና ይቅር ባይነት የሞላባቸው ከሆኑ ግን ፍቅርህ ይሰማታልና ለመለወጥ ዝግጁ ትሆናለች (ምሳሌ. 15:1)።

ትእዛዝ 2፥ *ለመናገር ቁጣህ እስኪበርድ ጠብቅ።*

ለምሳሌ ወደ ቤት ስትመጣ እራት ሳይዘጋጅ ደረስክ እንበል። ተናደድክ።

እንዴት መለወጥ እንዳለባት ልትነግራት ይህ ጥሩ ጊዜ አይደለም። ቁጣህ እስኪበርድ ድረስ ጠብቅ፤ ተቆጥተህ እያለህ ብትናገር ቃሎችህ ለስላሳና ይቅርታን የተሞሉ ሊሆን አይችሉም።

ትእዛዝ 3፡ *በምትናገርበት ጊዜ «አንቺ» እንዲህ አደረግሽ ወዘተ... ከማለት «ይሰማኛል» በል።*

ቀጥሎ በዚህ መንገድ እንዴት እንደምትናገር የሚያሳዩ ሦስት ምሳሌዎች ቀርበዋል።

ሀ) «እራት በጊዜው አዘጋጅተሽ አታውቂም፥ ምክንያቱም ብቃት የሌለሽ ሰነፍ ነሽ» አትበል። በዚያ ፈንታ እራት በጊዜው ተዘጋጅቶ የሚቀርብበትን ቀን ጠብቅ። በዚያ ቀን «እራት በጊዜው ተዘጋጅቶ ሲቀየኝ በእርግጥ ለእኔ እንደምታስቢ *ይሰማኛል*» በል።

ለ) «እናቴን የምታናግሪበት መንገድ ትሕትና የጎደለው ነው» ምክንያቱም በጥሩ ባሕል ያላደግሽ ያለአዋቂና ጋጠወጥ ስለሆንሽ ነው» አትበል። ይህ ነቀፋ ነው። ይህ ይጎዳታል እንጂ እንድትለወጥም አይረዳትም። በዚህ ምትክ «እንዴት *እንደሚሰማኝ* ልንገርሽ፥ በአንቺና በእናቴ መካከል ባለው ያለመግባባት ለሁለት የተሰነጠቅኩ ያህል *ይሰማኛል*። የሚበልጠው ፍቅር ግን ለአንቺ ነው። አንቺ ለእናቴ ደግና መልካም ስትሆኚ እንደምትወጂኝ *ይሰማኛል*።»

ሐ) «ገንዘብ በማይረባ ነገር ታጠፊያለሽ» ብለህ ከምትጮኽባት ቁጣህ እስኪበርድ ቆይና «ምንም ሳንመካከር በምትገዢያቸው ነገሮች *ቅሬታ አለኝ*። ምን መግዛት እንዳለብን ስንነጋገርና ስታደርጊው ለአንቺ የበለጠ ቀረቤታ *ይሰማኛል*።» በላት።

«*አንቺ*» በሚል ቃል የሚጀምር ዐረፍተ ነገር የሚጎዳና ነቀፋ የተሞላ ነው። ነገር ግን «*ይሰማኛል*» በሚል ከተጀመረ ጣትህን ወደ እርሷ ሳትጠቁም ስሜትህን ማካፈል ትችላለህ።

በሌላ አነጋገር «*ይሰማኛል*» በማለት የሚጀምር ንግግር ችግሮቹን ከሰውዬው ነጥሎ የማጥቂያ መንገድ ነው።

አንቶኒ፡- ሚስትህን የምትተች ከሆነ ከመሻሻል ይልቅ እየባሰባት ትሄዳለች። «የፍቅር ዘዴ»ን ከተጠቀምክ ግን ማሻሻሏ የማይቀር ነው።

ማሳሰቢያ ለሚስቶች፡- የፍቅር ዘዴ ለባሎችም እኩል ይሠራልና ሞክሩት!

ኢዩኤል፡- እኔና ባለቤቴ ክርስቲያኖች አይደለንም። በእግዚአብሔር ግን እናምናለን። እስካሁን ድረስ በትዳራችን ምንም ከባድ ችግር የለብንም።

ጥያቄያችን ትዳራችን ጤናማ ሆኖም እያለ ክርስቲያኖች መሆን አለብን ወይ?

ውድ ኢዮኤል፥

«ትዳራችሁ ካልተሳካ ወደ እኔ ኑ አላለንም።» ነገር ግን ለሁሉም ሰው ያደረገው ጥሪ «የዘላለምን ሕይወት እሰጣችሁ ዘንድ ወደ እኔ ኑ» ነው (ዮሐ. 3:13–18 እና እና 6:40ን ይመልከቱ።)

ኢዮኤል ስለዚህ ዋናው ጥያቄ ትዳራችሁ እንዴት ነው? የሚል ሳይሆን «የዘላለም መኖሪያችሁ የት ነው?» የሚል ነው።

እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን በመንግሥተ ሰማያት ከእርሱ ጋር እንድታሳልፉ ይፈልጋል። ችግሩ ኃጢአተኞች ናቻሁ (ኢሳ. 53:6)። ሰዎች በጣም ጥሩ እንደሆናችሁ ሊናገሩ ይችላሉ። በእግዚአብሔር የተቀደሰ ዓይን ግን ኃጢአተኞች ናችሁ። ይህንን ራሳችሁ ታውቃላችሁ።

የምስራቹ ቃል፦

«ኢዮኤል፦ እግዚአብሔር በጣም ስለ ወደደህ ልጁን ወደ ምድር ላከ። ክርስቶስ ስለ ኃጢአትህ በመስቀል ላይ ተሠቃየ። አሁን ኢየሱስን ጌታህና አዳኝ አድርገህ ብትቀበል የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ። (ዮሐ. 3:16ን ተመልከት)።



እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። (ማቴ.28:19–20)

ኢዩኤል አባክህን አድምጥ። ልታደርግ የምትችለው ከሁሉ የላቀ ነገር በኢየሱስ ማመን ነው። ኃጢአቶችህን ተናዘዝ። እንደሚያነጻህ በእርሱ ተደገፍ። የሕይወትህ ጌታ አድርገው።

ይህንን ስታደርግ ኢየሱስ የዘላለምን ሕይወት ይሰጥሃል። ከዚያም ይህን የምሥራች ከባለቤትህ ጋር ተካፈል።

በአንድ ላይ ሆናችሁ መጽሐፍ ቅዱስን በእውነት የምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ፈልጉ። የምስራቹን ለሕዝብህና ለቀረው የዓለም ሕዝብ በሙሉ በማስፋፋት ሥራ ከእነዚህ አማኞች ጋር ተባበር (ሉቃ. 24:46)።

ይህ ለሕይወትህና ለጋብቻህ ዓላማ ይሰጥሃል። ትዳርህም ከጤናማነት የላቀ አስደሳች ይሆናል።

አቤል፦ የሴት ጓደኛዬ ጠንካራ ክርስቲያን ናት፤ እኔም ክርስቲያን ነኝ። ከእጆቿ በስተቀር የትኛውንም የሰውነት ክፍሏን እንዳልነካት መከላከሏ አስገርሞኛል። ይህን ለምን እንደምታደርግ ስጠይቃት «የትዳር ሰው እንጂ የፍቅር ሬዘኛ አይደለሁም» አለችኝ።

አንድ ቀን ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ጠየቅኋት። እርሷም እምቢ አለችኝ። በሚቀጥለው ቀን «እንደዚህ ዓይነቱን ጥያቄ የሚቀጥል ከሆነ ተለዪው» ብላ እናቴ አስጠንቅቃኛለች አለችኝ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ ዳግመኛ ጠይቄአት አላውቅም።

ጥያቄዬ የድንግልና ክብረ ንጽሕናዋን የጠበቀች መሆኗን በምን አውቃለሁ? ይህንን ለማረጋገጥ አስገድጂያት አንድ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልፈጽምን?

ውድ አቤል፥

የምጽፍልህ እኔ ካሮል ነኝ። ልጄ ሆይ አድምጥ። ከብዙ ዓመታት በፊት ምን እንደደረሰብኝ እነግርሃለሁ። አንድ ቀን ታላቅ እህቴ እንዲህ አለችኝ። «ካሮል ክርስቲያን መሆን አለብሽ» በመጀመሪያ «እኔ ክርስቲያን ነኝ ክርስቲያን ሁኚ የምትለኝ እንዴት ነው? እንዴት ይህን ልትል ቻለች። ሁልጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ።» በማለት አስቤ ነበር። ክርስቲያን እንዳልነበርኩ በመረዳት መሆን እንዳለብኝ ተገነዘብኩ (ገጽ 34)።

አቤል ዛሬ ልነግርህ የግድ የሚገባኝ ነገር ክርስቲያን መሆን እንዳለብህ ነው።

እባክህን ይህን በማለቴ አትቆጣ። እኔ ክርስቲያን ነኝ የምትል ሰው እንደሆንክ ይገባኛል። ግን ቆም ብለህ አስብ እግዚአብሔርን፥ «እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። ኢየሱስ ያስፈልገኛል። ኃጢአቴ ይቅር ይባል ዘንድ መከራ እንደተቀበለልኝ አምናለሁ። እባክህን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ። ካዛሬ ጀምሮ አንተ ጌታዬ ነህ » ለማለት የቻልክበት ጊዜ ነበርን?»

ልጄ አቤል፥ ከእግዚአብሔር ጋር እንደዚህ ብለህ በተነጋገርክበት ቀን ክርስቲያን ትሆናለህ። ያኔ ጌታህ ምን እንድታደርግ እንደሚፈልግ ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ትፈልጋለህ። መጽሐፍ ቅዱስ ሴትን አስገድዶ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ፈጽሞ የማይገባ ነገር መሆኑን ያሳያል (2ኛ ሳሙ. 13፡11–33)።

ሌላ ልነግርህ የሚገባኝ ነገር አንዳንድ ሴቶች የድንግልና ሽፋን ስስ ሥጋ ሳይኖራቸው የሚወለዱ መሆኑን ነው። ስለዚህ አንዲት ሴት በንጽሕና የመቆየቷ ማረጋገጫ ከእርሷ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም አይገኝም (ገጽ 63)።

ቶም፡— ብዙ ባለትዳሮች በግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ፍቅራቸው መቀነሱ እውነት ነውን?

ውድ ቶም፥

ይበልጥ ትክክለኛው ካልክው ተቃራኒው ነው። ብዙ ባለትዳሮች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችግሮች የሚገጥማቸው እርስ በርስ መዋደዳቸውን ስላቆሙ ነው።

በሌላ አባባል በቀን ውኋቸው ደግና ታጋሽ መሆን ያቆማሉ፥ እናም በአልጋ ላይ ችግር ይጀማምራቸዋል።

ኤልያስ፡— «ማሪዋና» የተባለውን ዕፅ መውሰድ ወይም ማጨስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ችሎታን ያሻሽላልን?

ውድ ኤልያስ፥

በፍጹም። ማሪዋና የሚያጨሱ ወንዶች ብልታቸው ለመቆም ይከብደዋል ወይም ጨርሶ ይሳነዋል። ለሴቶች ደግሞ ማሪዋናን ማጨስ መካንነትን ያመጣል።

የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ማንኛውም ሱስ አስያዥ ነገር፥ የሚጤስ ዕፅ፥ አልኮል ወይም ምንም ዓይነት መድኃኒት ሊያሻሽለው አይችልም።

ቀጥሎ በሰፈረው መንገድ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያሻሻል መንገድ ያገኘ ማንም ሰው የለም።

ሚስትህን ውደድ፥

ለእርስዋ ታማኝ ሁንላት፥

ከእርስዋ ጋር ደስ ይበልህ!

(ከኤፌ. 5፤33ና ምሳ. 5፡18–21 የተወሰደ።)

ኤማንዳ፡— በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በዓለም ላይ እስካሁን የወደድኩትን ብቸኛ ሰው ላገባ ነው። ከወላጆቻችን ርቀን በአንድ ከተማ ውስጥ እንሠራለን። እኔም በምካፈልበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው ሰው ነው።

ዛሬ በቤቱ ውስጥ አብረን መኖር እንድንጀምር ጠየቀኝ።

ምን እንደምል አላውቅም። ከእርሱም ሆነ ከማንም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜ አላውቅም። እስከንጋባ ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የሌለብን ይመስለኝ ነበር።

አሁን እንጀምርን? ምን መልስ ልሰጠው?

ውድ ኤማንዳ፥

«ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥...» ይላል

(ቲቶ 2፡11–12)።

ይህ ጥቅስ ምን ማድረግ እንዳለብሽ በግልጽ ይነግርሻል። «እምቢ» በይ።

ይህ ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ ጌታውን እንዲታዘዝ ስለረዳሽው ያመሰግንሻል።

ኢየሱስ እንዲህ አለ «ስለ ምን፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም? (ሉቃ. 6፡46)።

ኤውንቄ፦ ባለፈው ዓመት አንድን ክርስቲያን ላገባው ቃል ኪዳን ገብቼለት ነበር። ቃል ኪዳን ከገባሁለት በኋላ ከእኔ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ፈቀድኩለት። «ያው ሊያገባኝ ስለሆነ ችግር የለውም» በማለት ለራሴ ተናገርኩ።

አሁን አርግዤ ከወላጆቼ ጋር እኖራለሁ።

አሁን ምን እያደረገ መሰላችሁ? በአዳዲስ የሴት ጓደኞች ተወጥሮአል!

ሴቶችን እንደ ሸሚዝ እንደሚቀያይር እሰማለሁ። እውነተኛ ክርስቲያን የነበረበት ጊዜ ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ።

ሊያገባኝ እንደማይፈልግ ግልጽ አድርጎልኛል። እንዲያውም ጋብቻ የሚባል ነገር አስቦ እንደማያውቅ እገምታለሁ። ብቻ ተጠቀመብኝ።

ትምህርትን ተምሬአለሁ። በእግዚአብሔር ላይ ፈጽሞ ጀርባዬን ከእንግዲህ አልመልስም።

በዚህ ሳምንት ኃጢአቴን ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያን አባላት ተናዘዝሁ። ይቅር እንደተባልኩም አምናለሁ። ነገር ግን በየዕለቱ ተስፋ የመቁረጥና የብቸኝነት ስሜት ይሰማኛል። የማነብባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ብትሰጡኝ?

ውድ ኤውንቄ፥

እንወድሻለን፥ እግዚአብሔርም ይወድሻል።

ይቅር እንደተባልሽ ማመንሽን ቀጥዪ። በእግዚአብሔር ላይ ፊትሽን ላለመመለስ በወሰንሽው ውሳኔም ጽኚ።

ቀጥሎ የሚያበረታቱሽን ታላላቅ ጥቅሶች እንሰጥሻለን። ከሁለት ወይም ከሦስት ክርስቲያን ሴቶች ጋር ተገናኝተሽ እነዚህን ጥቅሶች እንድታጠኚ እንመክርሻለን። [መዝ. (51)፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡9፤ መዝ. (103)፡12፤ 1ኛ ሳሙ. 12፡20–25፤ ምሳ. 28፡13፤ ዮሐ. 5፡14፤ የሐዋ 26፡20፤ ቆላ. 3፡5–19]።

ማሳሰቢያ፦ያለፉትን ሁለት ደብዳቤዎች ያገኘነው በተመሳሳይ ቀን ነው። አንዱን ከኤማንዳ፥ ሌላውን ከኤውንቄ።

በመጀመሪያ የኤማንዳን ደብዳቤ አነበብን። ልታገባው ከተስማሙት ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመጀመር ትፈልጋለች።

ቀጥሎ የኤውንቄን ደብዳቤ አነበብን። ልታገባው ተስማምተው ከነበረው ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸሟ ሕይወቷ እጅግ ከባድ ሆኖባታል።

ይህ የሚያሳስበን የእግዚአብሔር ሕግጋት ጥበብ የሞላባቸው መሆናቸውን ነው [መዝ. (19)፡ 7-11]።

ሔኖክ፡- እባካችሁን ንገሩኝ። ኩሽናችንን መቆጣጠር ያለበት ማን ነው? ሚስቴ ወይስ እናቴ? ሁለቱም የኩሽናውን ኃላፊነት ለመውሰድና ለመምራት በመፈለጋቸው ሁልጊዜ ይጣላሉ።

ዛሬ ለወንድሜ እንዲህ አልኩት «ቤታችንን ለቅቄ ሚስቴን ይዤ መውጣት እፈልጋለሁ። እኔና እርሷ ብቻ የምንኖርበትን ቤት መሥራት እሻለሁ።»

እርሱም እንዲህ አለኝ «የቤተሰባችንን ቤት ትተህ ከወጣህ ለወላጆቻችንና ለቅድመ-አባቶቻችን አክብሮት እንደሌለህ ታሳያለህ።»

እንደ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለብኝ?

ውድ ሔኖክ፥

በዓለም ዙሪያ በባለትዳሮችና በወላጆቻቸው መካከል ፀብ አለ። የእስያ ሕዝብ ስለ ባለትዳሮችና ስለ ወላጆቻቸው አንዳንድ ባሕል አሏቸው። በአውሮፓ ያለው ባሕል ደግሞ የተለየ ነው። አፍሪካና አሜሪካ የራሳቸው ባሕሎች አሏቸው። ግን የትኛውም ባሕል ችግሩን አላቃለለውም። በሁሉም ባሕል ውስጥ በሚስትና በባል እናት.... ወይም በባልና በአማች መካከል ግጭቶች ይኖራሉ።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ከሁሉ የላቀ ነው። ዕቅዱ በእስያ፥ በአውሮፓ፥ በአፍሪካ፥ በአሜሪካና በሁሉም ስፍራ ይሠራል። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ባልና ሚስት የሚለው የሚከተለውን ነው።

1) ወላጆችህን ትተህ ከሚስትህ ጋር ኅብረትን አድርግ። (ዘፍ. 2፡24፤ ማር. 10፡7፤ ኤፌ. 5፡31)

2) ወላጆችህን በፍቅር ተንከባከባቸው (1ኛ ጢሞ. 5፡3-8)።

ሔኖክ «እንደ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለብኝ?» በማለት ጠይቀሃል። መልሱ ከላይ የተሰጡትን ሁለት ነገሮች ማድረግ አለብህ ነው።

1) ሚስትህን ይዘህ ጎጆ ውጣ። ከሚስትህ ጋር ተጣበቅ ማለትም «ከማንም በላይ እርሷን ውደድ።»

2) እናትህን በፍቅር የምትረዳበትን መንገድ ፈልግ። ትረዳቸው ዘንድ ቤትህን በቤታቸው አጠገብ መገንባት ትችላለህ። ወይም በቤትህ እንዲኖሩ ልትጠይቃቸው ትችላለህ።

እናትህ በቤትህ የሚቆዩ ከሆነ አንተና ባለቤትህ ልትወዷቸውና ልትቀበሏቸው ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ አለባችሁ። ከእናንተ ጋር በመኖራቸው

ደስተኛ መሆናችሁን ግለጹላቸው። በወጥ ቤት ሥራ ሊረዱችሁ ሲፈልጉ በደስታ ተቀበሏቸው።

ተስፋ የምናደርገው የሚከተለው ዝንባሌ ይኖራቸዋል ብለን ነው። «ይህ የእኔ ቤት አይደለም፥ ነገር ግን ልጇና ባለቤቱ በፍጹም ርኅራኄ ተቀብለውኛል። ከፍቅራቸው በመነጨ አቀባበላቸው ልደሰት ይገባኛል እንጂ ቤታቸውን ወይም ኩሽናቸውን ለመቆጣጠር መጣር የለብኝም።»

በእርግጥ አስቸጋሪ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ እናትህ ባለቤትህንና ቤታችሁን ሊያዙበት ይፈልጋሉ። ያኔ ሔኖክ የቤተሰቦችህን ቤት እንደተውክና አሁን የራስህ ቤት ቁንጮ መሆንህን ማስታወስ አለብህ። እናትህ እንግዳ ብቻ መሆናቸውን በፍቅር አስታውሳቸው። ቤትህን ሊቆጣጠሩ አይገባቸውም።

በተጨማሪ፥ በሕይወትህ ቁጥር አንድ መሆኗን ለሚስትህ አሳያት። የወላጆችህን ቤት የተውከው ለምን ነበር? እግዚአብሔር ምክንያቱን ሲናገር *ከሚስትህ ጋር እንድትጣበቅ (ኅብረት እንድታደርግ) ነው ይላል* (ዘፍ. 2፡24)

ይህ ሁሉ ቀላል ይሆናልን? በምንም ዓይነት! ባለቤትህና እናትህ የሚጣሉበት ጊዜ አሁንም ሊኖር ይችላል። ደግሞም ወንድምህ አንዳንድ ልማዶችን አልተከተልክም ብሎ ሊከስህ ይችላል። ሕይወት ቀላል አይደለም።

ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ዕቅድ ከሁሉ የተሻለ ነው። የሰው ባሕሎች ከእግዚአብሔር ሕግ የተሻሉበት ወቅት የለም። ስለዚህ ሔኖክ እግዚአብሔር የሚልህን አድርግ፡- *«ወላጆችህን ትተህ ከሚስትህ ጋር ተባበር (ተጣበቅ)። ወላጆችህን በፍቅር እርዳ።* (ማር. 10፡7፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡3-8)።

ሜርሲ፡- እኔና ባለቤቴ እውነተኛ ክርስቲያኖች ነን። አንድ ልጅ አለን። ሁለተኛውን ደግሞ አሁን አርግዣለሁ። ችግሩ ከተጋባን ጀምሮ ከወላጆቹ ጋር እኖራለሁ። የራሳችንን ቤት እንድንሠራ ባለቤቴን ብጠይቀው፥ በዚያ ፈንታ የወላጆቹን ቤት አስፋፍቶ ከእነርሱ ጋር አንድ ቆይ እያደረገ ነው።

የሚሠራው ራቅ ባለ ስፍራ በማዕድን ማውጣት ተግባር ላይ ነው። በየሳምንቱ መጨረሻ ወደ ቤት ሲመጣ አብዛኛውን ጊዜ ከወላጆቹ ጋር ያሳልፋል። ወደ እኔ የሚመጣው በመኝታ ሰዓት ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ ብዙ ለመነጋገርና ለመጫወት በጣም የዘገየ ሰዓት ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ እንዴት ብቸኝነት እንደሚሰማኝ እገልጽለታለሁ። እርሱ ግን ወላጆቹ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ብቻ ይነግረኛል።

ወላጆቹ የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዳለ አውቃለሁ። ልረዳቸውም ደስተኛ ነኝ፥ ነገር ግን ትዳሬ ቀዝቃዛና ብቸኝነት የሞላበት ስለሆነ እጨነቃለሁ።

ባለቤቴን እወደዋለሁ። እንደ ጓደኛ ላናግረው እፈልጋለሁ። የራሳችን ቤት ያስፈልገናል።

አስተውሉ፦ የሚርሲ ባል ክርስቲያን ነው፥ ነገር ግን «እናትና አባትህን ተው ከሚስትህ ጋር ተባበር። (ተጣበቅ)። ወላጆችህን በፍቅር አግዝ» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አልተረዳም።

ይህ የሚያስረዳው ቤተ ክርስቲያን *መጽሐፍ ቅዱስን ለማስተማር* ተግታ መሥራት እንዳለባት ነው! በተለይ የሚከተሉትን ጥቅሶች ማስተማር አለብን፥ ዘፍ. 2:24፤ ማር. 10:6–8፤ ኤፌ. 5:28–31ና፤ 1ኛ ጢሞ. 5:3–8።

በአሜሪካ፥ በአፍሪካ፥ በእስያ፥ በአውስትራሊያና በአውሮፓ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ ይህ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። በእያንዳንዱ አገር ሕዝብ የራሱ ባሕል ቢኖረውም የእግዚአብሔር መንገድ ግን የላቀ ነው።

ቃሉን እናጥና! በቤተ ክርስቲያኖቻችን እናስተምረው! እንታዘዘው።

መጋቢ ኤን፦ ወጣት መጋቢ ነኝና የእናንተ ምክር ያስፈልገኛል።

ባለፈው ሳምንት አንዲት ሴት ወደ እኔ መጣች። ባሏ ሌላ ልጃገረድ በማስረገዙ ተንሰቅስቃ ታለቅስ ነበር።

ባሏን ላገኘው ሄድኩ። ድርጊቱ እውነት መሆኑን አመነ።

ትላንትና ለቤተ ክርስቲያን አባላት ተናዘዘ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ስለነበረ በፈጸመው ተግባር ሰው ሁሉ ተደነቀ።

አንዳንድ አባላት «ለሦስት ወራት ቤተ ክርስቲያንን እንዳይመራ መታገድ አለበት» አሉ።

ሌሎች ደግሞ «በቃ ይቅርታ እናድርግለት» አሉ።

ምን ምክር ትሰጡናላችሁ?

ውድ መጋቢ ኤን፥

ወደ ባለቤቷ ሄደህ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ኃጢአቱን እንዲናዘዝ በማበረታታትህ በጣም ጥሩ አድርገሃል።

ምክራችን ይቅር እንድትሉት፥ እንድትወዱትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ለአንድ ዓመት እንዳያገለግል እንድታግዱት ነው።

በሦስት ወር ምትክ አንድ ዓመት እንዳያገለግል አድርጉት ያልነው ለምንድን ነው? ምክንያቱም፦

ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ አመንዝራነትን አጥብቆ ይቃወማል። ስለዚህ፥ ቤተ ክርስቲያንም ልትቃወመው ይገባታል። ይህ ወንድም ለአንድ ዓመት እንዳያገለግል ቢቀጣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች

ክርስቲያኖች በሙሉ አመንዝራነትን ለፐብቀው እንደሚቃወሙ ይረዳሉ (1ኛ ቆሮ. 6:18፤ ኤፌ. 5:3፤ 1ኛ ጢሞ. 3:5)።

ለ) ይህ ወንድም እርዳታ ያስፈልገዋል። እንደገና በምንዝርና ኃጢአት እንዳይገኝ ዓመቱን ሙሉ እርዳታ ያስፈልገዋል። ቤተ ክርስቲያን ይህን ሰው ሊረዱ የሚችሉ ሁለት ታማኝ ሰዎችን እንድትመርጥ እናሳስባለን። ዓመቱን ሙሉ እነዚህ ሁለት ወንድሞች በየሳምንቱ ከእርሱ ጋር ይገናኙ። በየሳምንቱ በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በውይይትና በጸሎት ያንጹት። እነዚህ ጊዜያት ለሦስቱም ሰዎች አስደሳች እንደሚሆኑ እናምናለን።

«ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ
ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ
እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት
መንፈስ አቅኑት» (ገላ. 6:1)።

ለአንድ ዓመት ሲታነጽ ከቆየ በኋላ ይህ ወንድም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ለመሆን መዘጋጀት አለበት። ማንም ዝቅ አድርጎ አይመልከተው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ በኢየሱስ ደም ኃጢአቱ የታጠበ ወንድም አድርገው ሊቀበሉትና ሊወዱት ይገባል። «ስለዚህ ይህ ሰው በጣም ከማዘኑ የተነሣ ተስፋ እንዳይቆርጥ ይልቅስ ይቅርታ እንድታደርጉለትና እንድታጽናኑት ይገባል። እንዲሁም እርሱን የምትወድዱት መሆናችሁን ለማስረዳት እውነተኛ ፍቅራችሁን በሥራ አሳዩት (2ኛ ቆሮ. 2:7–8)።

ስምዖን፦ ባለፈው ዓመት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የመዘመራት መሪ የሆነው ሰው ሚስቱን ፈታ። ብዙዎቻችን ይህን ድርጊት እንዳይፈጽም ለማድረግ ብንመከረውም ሊቀበለን አልቻለም። ሚስቱ ለእርሱ ታማኝ ያልሆነችበት (ያመነዘረችበት) ወቅት ፈጽሞ አልነበረም። መጋቢያችን ፊት ለፊት እንዲህ ብሎት ነበር። «ሚስትህን ብትፈታ እያወቅህ እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ መርጠሃል።

ሆኖም ግን ፈታት፥ ቤተ ክርስቲያናችንንም ትቶ ሄደና ወጣት ሴት አገባ።

አሁን የሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖአል። ፈትቶ በማግባቱ ያች ቤተ ክርስቲያንም የመዘምራን ቡድን መሪ እንዳይሆን እንደከለከለችው በመናገር ያጉረመርማል ሲሉ እሰማለሁ።

ብሩስና ካሮል፥ ክርስቲያኖች ፍች ሲፈጽሙ ማየት ይረብሸኛል። የማያምኑ ሰዎች ቢፈቱና ቢያገቡ ያ ይገባኛል። የዓለም ናቸውና ከእነርሱ ምን እንጠብቃለን። መረዳት ያቃተኝ ነገር ግን ክርስቶስ ስለ ፍች የሰጠውን ትእዛዝ ክርስቲያን መታዘዝ የሚያቅተው እንዴት ነው?

ውድ ስምዖን፥

ከሠላሳ ዓመታት በፊት በክርስቲያኖች መካከል ፍች የሚባል ነገር አይታሰብም ነበር። ዛሬ ግን በተለይ በሰሜን አሜሪካ ፍች የፈጸሙ

ክርስቲያኖች ቁጥር በየጊዜው እያደገ መጥቷል። አደገኛው ነገር ይህ የፍች ባሕል ከሰሜን አሜሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት ሊስፋፋ መቻሉ ነው።

የእግዚአብሔር ሕግ ዛሬም ከሠላሳ ዓመት በፊት እንደነበረው ነው። በማቴ 19:9 ላይ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል።

«አንድ ሰው ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥...»

ሚልክያስ ምዕራፍ 2:13-16 እንዲህ ይላል:-

«ይህንም ደግሞ አድርጋችኋል፤ እግዚአብሔር ቍርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት፥ ከእጃችሁም በደስታ እንዳይቀበለው መሠዊያውን በእንባና በልቅሶ በኀዘንም ትከድናላችሁ። እናንተም:- ስለ ምንድር ነው? ብላችኋል። ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች አርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ፥ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፥ ልብሱንም በግፍ ሥራ የሚከድነውን ሰው እጠላለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ። »



*ጌታ ሆይ፥ እባክህን ባልና ሚስት የሚከተሉትን በማድረግ ይታዘዙህ ዘንድ ቤተ ክርስቲያኖቻችንን አነቃቃ እያልን እንጸልያለን።*

- እርስ በርስ በመዋደድ።
- አንዳቸው በሌላቸው ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ጉዳይ ታማኝ በመሆን።
- ከመፋታት ይልቅ ትዳራቸውን ለማሻሻል ርምጃ በመውሰድ ይመላለሱ ዘንድ። (ገጽ 10 እስከ 36 ን ይመልከቱ።)

ሲንቲያ፡- በሠርጌ ቀን ለባሌ ምንም ፍቅር አይሰማኝም ነበር። ለማግባት የወሰንኩት ቤተሰቦቼ ጠጪዎች ስለነበሩ ከዚያ ደስታን ከተራቆተ ቤተሰብ ለመሸሽ ብዬ ነበር።

ከሠርጋችን በኋላ ባለቤቴ ምን ዓይነት ስግብግብና አብሮ ለመኖር ፈጽሞ የማይመች ሰው መሆኑን ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም።

በመጨረሻ እራሴን እንዲህ በማለት ጠየቅኩ «እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ የሚያሳየው እንደማልወደው ስለሚሰማው ይሆንን?»

ስለዚህ ባለቤቴን ልወደው ወሰንኩ።

ለእርሱ ፍቅሬን የማሳይባቸውን መንገዶች መፈለግ ጀመርኩ። ከሥራው ተበሳጭቶ በሚመጣበት ወቅት ላረጋጋው ከፍተኛ ጥንቃቄ መውሰድ ጀምርኩ። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ፍላጎት እንዳለኝ ማሳየት ጀመርኩ። በፍትወት ስሜት በሚገባ እንድነቃቃ ለማድረግ እራሴን ማስለመድ ጀመርኩ። በጣም የሚወዳቸውን ምግቦች አበስልለት ጀመርኩ። አለመግባባት በመካከላችን በሚከሰትበት ወቅት በፍጹም አክብሮት አናግረው ጀመር።

ወዲያውኑ ከፍተኛ ለውጥ በእርሱ ውስጥ ተመለከትኩ። በእውነት በጣም ጥሩ ሰው ነው። በፍቅሩ ተጠመድኩኝ።

የምለው ነገር እንግዳ ሊሆን እንደሚችል ይገባኛል። ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር የያዛት ልጃገረድ ዓይነት ሆኜአለሁ።

ውድ ሴንቲያ፥

አሁን ስላለሽ የፍቅር ስሜት ምንም አልተደነቅንም። ፍቅር የሞላባቸውን ድርጊቶች ለባልሽ ማድረግ ጀመርሽ፥ ይህ በመጨረሻ የፍቅር ስሜት አጎናፀፈሽ። ይህ እንግዳ አይደለም። ተፈጥሮአዊ ነው። የፍቅር ተግባራትን በምናደርግበት ወቅት ሁሉ የፍቅር ስሜቶች ይከተሉናል።

አሁን ደስተኛ በመሆንሽም አንደነቅም። ባልሽን ለመውደድ ስትወስኚ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መምረጥሽ ነው።

«ምስክሩን የሚፈልጉ፥ በፍጹም ልብ የሚሹት ምስጉኖች ናቸው፤።» [መዝ. (119)፡2]

ሎይስ፡- በትዳር ጉዳይ ስላለኝ አቋም እርግጠኛ አይደለሁም። ፍላጎቴ አግብቼ ለመኖር ይሁን ወይም ሳላገባ ለመኖር እርግጠኛ አይደለሁም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክርስቲያን የግድ ማግባት አለበት?

ውድ ሎይስ፥

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክርስቲያን የሚከተለው አመለካከት ሊኖረው ይገባል፡-

በሕይወቴ ዘመን ሁሉ የክርስቶስ ወንጌል የምስራች በዓለም ሁሉ እንዲሰራጭ የምችለውን ሁሉ በማድረግ እኖራለሁ።

የራሴን ምቾት ብቻ ለመጠበቅ በስግብግብነት ከመኖር ይልቅ ለሰዎች መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጎት መሟላት እርዳታ ለማድረግ የምችለውን ሁሉ እፈጽማለሁ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች «ሳላገባ ብኖር እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ አገለግላለሁ። እንዳላገባ ሰው የባልና/ሚስት ወይም የልጆች ኃላፊነት አይኖርብኝም። ልቤን ሙሉ ለሙሉ ለክርስቶስ እሰጣለሁ።» (1ኛ ቆሮ. 7:32–35) ብለው ሊወስኑ ይችላሉ።

ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ክርስቶስን በእውነት የሚወድ ሰው በማግባት በጋራ እርሱን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል እችላለሁ። [መዝ. (34):3] ብለው ይወስናሉ።

ስለዚህ ሎይስ ይህን አድርግ።

- በሕይወትህ ሙሉ ክርስቶስን ለማገልገል ወስን።
- ትዳር መመሥረት ክርስቶስን በተሻለ ሁኔታ እንድታገለግል የሚያግዝህ ከሆነ ብቻ አግባ።

ዛሬ በዓለም ላይ የእነርሱን ቋንቋ የምትናገር ቤተ ክርስቲያን ያላዩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። እናም በክርስቶስ አላመኑም። ምክንያቱም የወንጌላትን የምሥራች የነገራቸው የለም።



«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።... እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ።»

(ኢሳ. 49:6 እና የሐዋ. 13:47)።

«ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ!» (ማቴ. 6:19)

በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል» (ሉቃ. 24:47)

# የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በሕይወቴ

በብሩስ ብሪተን

ከብዙ ዓመታት በፊት በአንድ የወጣቶች ካምፕ ፕሮግራም ላይ ክርስቶስ በልቤ ደጃፍ ላይ ቆሞ እያንኳኳ እንደሆነ ተገነዘብኩ።

እኔም የሚከተለውን መልስ ሰጠሁ። «ኃጢአቴን በማጠብ የዘላለምን ሕይወት ልትሰጠኝ የምትችል አንተ ብቻ ነህ፤ ስለዚህ ወደ ልቤ ግባ። በዚያም ኑር»።

ክርስቶስ ወደ ሰው ልብ ውስጥ ሲገባ በርካታ ክፍሎችን ያገኛል። ሳሎን፥ መኝታ ክፍል፥ የማንበቢያ ክፍል፥ የሥራ ክፍልና ምናልባት የተቆለፈ ክፍል። የእርሱ ፍላጎት በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አስደናቂ መሻሻሎችን ማድረግ ነው።

ክርስቶስ ወደ ልቤ በገባ ዕለት በቀጥታ ወደ ሳሎን ገባና «በዚህ ክፍል በየዕለቱ ከአንተ ጋር ማሳለፍ እፈልጋለሁ። ሁለታችን ብቻ በፍጹም አንድነት በምንነጋገርበት በዚህ ክፍል ታላቅ ደስታን እናገኛለን።»

አሳቡን በጣም ወደድኩት። በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር የምናሳልፈውን ጊዜ ማግኘት እንዴት አስደሳች ነገር ነው!

በየዕለቱ ጠዋት መገናኘት ጀመርን። መጽሐፍ ቅዱስን አብረን እያነበብን ሳለ ሕይወቴ መለወጥ ያለበት በየትኛው አቅጣጫ እንደሆነ አሳየኝ። ክርስቶስ ለእኔ ያለውን ታላቅ ፍቅር መገንዘብ ጀምርኩ። ልቤ ሞቀ። በእነዚያ ጊዜያት የማገኛቸው ደስታዎች አስደናቂ ናቸው!

ነገር ግን ቀናት እያለፉ ሲመጡ ከክርስቶስ ጋር የማሳልፈው ጊዜ እያነሰ መጣ ለምን? አላውቅም። በሥራዬ ተጠምጄ ይመስለኛል። የፈተና ጊዜ ነበር። ከዚያ በኋላ በሥራው ተጠመድኩ። በየምሽቱ ሁልጊዜ ማለት ይቻላል ኮምፒዩተር አጠና ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ወደ ሳሎኔ እርሱን ለመገናኘት ሳልሄድ ሳምንታት ያልፉ ጀመር።



አንድ ቀን ጠዋት ተቻኩዬ ከቤት ልወጣ በሳሎን በኩል ሳልፍ ቤቱ ክፍት ሆኖ አገኘሁት። ልብ ብዬ ስመለከት ክርስቶስ ብቻውን ቁጭ ብሎ አየሁት። ወዲያውኑ አንድ ነገር አስታወስኩ። እንግዳዬ እንደሆነ፥ ወደ ልቤ እንደጋበዝኩትና ነገር ግን ከእርሱ ጋር የማሳልፈው ጊዜ በጣም ጥቂት እንደሆነ ገባኝ!

ወደ ክፍሉ እንደገባሁ፥ «ጌታዬ፥ አዝናለሁ» አልኩት። «እኔ ባልመጣሁባቸው ቀናት እንኳ በየጠዋቱ እዚህ ነበርክ ማለት ነውን? አባክህ ይቅር በለኝ።»

በፍቅር ዓይኖቹ እየተመለከተኝ «አዎን» አለኝ። «በየቀኑ ጠዋት እዚህ የምመጣው በደስታ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት ብናገርህ የተሻለ ክርስቲያን እንደምትሆን አውቃለሁ። ጸሎትህ ፍቅሬን ለዓለም ሁሉ ለማሰራጨት በኃይል ሊሠራ እንደሚችል አውቃለሁ።»

*በዚያን ቀን ከክርስቶስ ጋር ከምንሆንበት ጊዜ የበለጠ አንዳችም ነገር እንደሌለ ተገነዘብኩ!*

የእግዚብሔርን ቃል የማጠናበትንና የምጸልይበትን ጊዜ በአስደናቂ ሁኔታ ለወጠው!

«እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።» (የሐዋ. 6፡4)።

## የመኝታ ክፍል

አንድ ቀን ጠዋት እኔና ክርስቶስ በሳሎን ውስጥ ቁጭ ብለን የሞቀ ጨዋታ ላይ ሳለን በፍቅር ዓይኑ እየተመለከተ እንዲህ አለኝ፥ «ዕቅድህ በቤትህ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻ ተወስኜ እንድቀር እንዳልሆነ ተስፋ

አደርጋለሁ። በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ብርሃንና ደስታን ማምጣት እፈልጋለሁ።»

«ድንቅ ነው! » ብዬ በመገረም ጮኽኩ። «በደስታ እቀበላለሁ» አልኩ።

ክርስቶስ በታላቅ ፈገግታ ተነሥቶ ቆመ። ወዲያውኑ በአንድ ላይ ወደሚቀጥለው ክፍል አዘገምን። እርሱም መኝታ ክፍሌ ነበር። ፊት ለፊት እየተመለከተኝ እንዲህ አለኝ። «ስሜትህ እንዴት እንደሆነ ይገባኛል። እንደ ወጣት፥ ብርቱ ሰውነትህ የፍትወት ፍላጎት ብዙ ጊዜ ይሰማዋል። የሴቶች ሰውነት ይስብሃል። አንዳንድ ጊዜ ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳታደርግ መቆየት የሚቻል ስለመሆኑም ትጠራጠራለህ። የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ለጋብቻ ብቻ ማቆየት ተፈጥሮአዊ ያልሆነና የማይቻል ይመስልሃል።»

ምንም መልስ አልሰጠሁም። ነገር ግን ክርስቶስ ስለ ስሜቶቼና ስለ ፈተናዎቼ ፍጹም የሆነ መረዳት እንዳለው ስመለከት ተደነቅሁ።

ክርስቶስ ንግግሩን በመቀጠል «በእኔ ኃይል ማንኛውም ወጣት (ወንድ ወይም ሴት) የፍትወተ ሥጋ ግንኙነትን ለጋብቻ ብቻ የማቆየትን ኃይል ሊጎናጸፍ መቻሉን አስታውስ። ሕዝቤ በኃጢአት ቢወድቅ ይቅርታ አደርግለታለሁ፥ ነገር ግን ማንኛውም ውድቀት ለራሳቸው ሕይወትና ለልጆቻቸውም እንኳ ኀዘንን ያመጣል። ስለዚህ *ከኃጢአት እንድትሸሽ* እመክርሃለሁ። በተፈተንክ ጊዜ ሁሉ መውጫውን ላዘጋጅልህ ቃል እገባልሃለሁ።»

ክርስቶስን ታማኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለፈተና መውጫውን በማዘጋጀት ሁልጊዜ ቃሉን ጠብቆልኛል። ክርስቶስ በሕይወቴ ውስጥ ስላለ እራሴን በንጽሕና በመጠበቅና በፍትወት ፈተና ላይ ድልን በመጎናጸፍ ለመኖር ችያለሁ።

«ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና
አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ
መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ
እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም
ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው
ጋር መውጫውን ደግሞ
ያደርግላችኋል።»
(1ኛ ቆሮ. 10:13)።

## የማንበቢያ ክፍል

መኝታ ቤቴን ካየ በኋላ ክርስቶስ እንዲህ በማለት ጠየቀኝ «ወደ ማንበቢያ ክፍል ልገባ እችላለሁን?

በፈገግታ «*በሚገባ* ትችላለህ፥ እንዲያውም የቪዲዮ ፊልም አብረን እንመለከታለን» አልኩት።

ክርስቶስ ወደ ቤተ መጻሕፍቴ እንደገባ ዓይኖቹ በጠረጴዛው ላይ ወዳሉት ጋዜጦችና መጽሔቶች ተመለከቱ። ቀጥሎም አረፍ ብሎ ከቪዲዮ ክሮቼ አንዱን ይመለከት ጀመር።

ወዲያውኑ እጅግ አፈርኩ።

እስከዚያ ቀን ድረስ ስለ ቤተ መጻሕፍቴ ምንም ወቀሳ ተሰምቶኝ አያውቅም። ክርስቶስ በገባ ጊዜ ግን እጅግ አፈርኩ።

በፍጥነት ቪዲዮውን አጠፋሁትና «ጌታ ሆይ ይህ ክፍል ታላቅ ለውጦች ያስፈልጉታል። ትረዳኛለህን?» አልሁት።

እርሱም መልሶ «በደስታ»፥ አከሎም «በአንድነት መልካም የሆኑ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን እንመርጣለን። ስለ ቪዲዮ ካነሣን ልታገኝ የቻልከው የተሻለው ይህን ነውን?» አለኝ።

እኔም መልሼ «እውነት ለመናገር ብዙ የተሻሉ ቪዲዮዎችን ማግኘት አልቻልኩም» አልኩት።

ክርስቶስም ሞቅ ባለ ፈገግታ መልሶ «ምንም አይደለም፥ ምክንያቱም እውነት ለመናገር ቴሌቪዥንና ቪዲዮን በማየት ብዙ ጊዜ አጥፍተሃል። እባክህን በሥራ ክፍልህ የምትሠራው ምን እንደሆነ ማየት እችላለሁ?»

# የሥራ ክፍል

እኔና ክርስቶስ ወደ ሥራ ክፍሌ ስንገባ መሣሪያዎቹ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ላይ እንዳልዋሉ ሁለታችንም አስተዋልን። ሁሉንም ነገር አቧራ ሸፍኖታል።

ለራሴ እንዲህ ስል ቆይቼ ነበር። «ጥሩ መሣሪያዎች ስለሌሉኝ ብዙ ሥራ መሥራት አልችልም›።

ክርስቶስ ዙሪያውን በመመልከት እንዲህ አለ «ይህ ክፍል በጣም ጥሩ መሣሪያዎች አሉት፤ ለመንግሥቱ ሥራ ምን እያደረግክ ነው?»

በከፊል የተከናወኑ የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች አሳየሁት።

ለዘመዶች መመስከር

እና ለሌሎች ሁለት

በወህኒ ቤቶች መስበክ

የእሁድ ትምህርት በ[illegible] ማስተማር

በደከመ ድምፅ እንዲህ አልኩት «በእነዚህ ፕሮጀክቶች ላይ መሥራት በማቆሜ አዝናለሁ፥ ችግሩ ግን ብዙ ችሎታዎችና ብቃቶች ማጣቴ ነው።»

እርሱም መልሶ «ከዚህ የተሻለ መሥራት በእርግጥ ትፈልጋለህን?» በማለት ጠየቀኝ።

በሞቀ ስሜት «አዎን እፈልጋለሁ» በማለት መለስኩለት።

ከዚያም እኔና ክርስቶስ አብረን መሥራት ጀመርን።

ከእርሱ ጋር መሥራት እንዴት ፍቅር የሚያስደይዝ ነው። አሁን በምመሰክርበት፥ በምሰብክበት ወይም የእሑድ ትምህርት በማስተምርበት ጊዜ ሁሉ በእርሱ ሕይወትን የመለወጥ ኃይል እታመናለሁ።

በአውቶቡስ በምሄድባቸው ጊዜያት ሁሉ በጸጥታ እንዲህ እያልኩ እጸልያለሁ። «ጌታ ሆይ፥ እግዚአብሔር በሚያስፈልገው ሰው አጠገብ

እንድቀመጥ እባክህን ምራኝ።» ብዙ ጊዜ ከአውቶቡሱ ስወርድ አጠገቡ ተቀምጦ የነበረው ሰው «ስለ ኢየሱስ ከአንተ ጋር በመነጋገሬ በጣም ደስ ብሎኛል» ይሉኛል።

እንደ እኔ ዓይነት ተራ በሆነ ሰው እንኳ ክርስቶስ የሚሠራበትን መንገድ እወደዋለሁ።

ከዚህ በኋላ ችሎታ ስለሌለኝ ምንም ማድረግ አልችልም ብዬ ፈጽሞ አልናገረም። ክርስቶስ በእርሱ ኃይልና በእኔ አናሳ ችሎታ ታላቅ ነገሮችን ያደርጋል።

«ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ»

(ፊልጵ. 4:13)

## መዝናኛ

ቅዳሜ ጠዋት ክርስቶስ እንዲህ በማለት ጠየቀኝ «መዝናናትና መጫወት ስትፈልግ ወደ የት ትሄዳለህ?»

መልስ አልሰጠሁትም። አንዳንድ ደስታ የማገኝባቸውን ነገሮች እንዲያውቅብኝ አልፈለግሁም።

በዚያን ዕለትም ቤቴን ለቅቄ ስወጣ «የምትሄድበት ቦታ አለን?» በማለት ጠየቀኝ።

መሬት መሬት እያየሁ «አዎን፥ የምሄድበት አለኝ» አልኩት።

«መልካም እኔም አብሬህ እሄዳለሁ አለኝ።»

በፍጥነት መልሼ «ቆይ፥ አሁን እኔ ወደምሄድበት መሄድ የምትፈልግ አይመስለኝም። ነገ ወደ ጸሎት ስብሰባ አብሬህ እሄዳለሁ። አሁን ግን የምሄደው....ማለቴ... ወደ አንድ ስፍራ ነው።»

ኃዘን በተሞላበት ፊት እንደዚህ አለኝ። «አዝናለሁ፥ ወደ ልብህ ስገባ የቅርብ ጓደኞሞች ሆነን ሁሉን ነገር በአንድ ላይ እንደምንሠራ ተስፋ አድርጌ ነበር።»

ምን እንደምመልስለት አላውቅም ነበር። ከቤቴ ስወጣ «እሺ ዛሬ ማታ ግን አይደለም ምናልባት...» በማለት አጉተመተምኩ። «ምናልባት በሌላ ጊዜ።»

በዚያ ምሽት ኃጢአት የሆነ አንዳችም ነገር አልፈጸምኩም፥ ነገር ግን በምሄድባቸው አንዳንድ ቦታዎችና በማደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ክርስቶስ እንደማይደሰት ተገነዘብኩ።

ወደ ቤቴ በተመለስኩ ጊዜ በቀጥታ ወደ እርሱ በመሄድ «ጌታ ሆይ፥ አዝናለሁ። ከአሁን ጀምሮ ግን ሁሉን ነገር አብረን እናደርጋለን» አልኩት።

እርሱም ፈገግ በማለት እንዲህ አለኝ። «ሕይወትህን ለማበላሸት እንደመጣሁ ፈጽሞ አታስብ። የመጣሁት ሕይወትህን የተሻለ ለማድረግ ነው እንጂ የከፋ ለማድረግ አይደለም። ሕይወትህ ምን ያህል የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ስታይ ትደነቃለህ!»።

ከዚያ እኔና ክርስቶስ ወደ ወጣቶች የሳምንት መጨረሻ መዝናኛ ካምፕ አብረን ሄድን። በጣም ጥሩ ጊዜ ነበር! በርካታ አዳዲስ ጓደኞችንም አገኘሁ።

አሁን ከቀድሞ ጓደኞቼ ማናቸውንም ሳገኝ ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ አነግራቸዋለሁ። በመጀመሪያ ሊያደምጠኝ የፈቀደ አልነበረም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ሁለቱ ንስሐ ገብተው ወደ እኛ የወጣቶች ካምፕ ተቀላቀሉ።

ከዝማሬ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከውይይት የምናገኘው ደስታ ታላቅ ነው። በሆስፒታሎችና በትምህርት ቤቶች የምናደርገውን የወንጌል ስብከት በጣም እየወደድነው ነበር። በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል በምናደርጋቸው የሳምንት መጨረሻ ጉዞዎች የሚሰማን የአንድነት ስሜት ታላቅ ነው።

ክርስቶስን ማገልገል በዓለም ከሚገኙ ደስታዎች በብዙ ሺህ እጥፍ የላቀ ነው። ሕይወቴን በእውነተኛ ደስታና ዓላማ ይሞላዋል።

«እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው
እንዲበዛላቸውም መጣሁ» (ዮሐ. 10:10)

# የተዘጋ ክፍል

አንድ ቀን ወደ ቤቴ ስደርስ ውጭ ቆሞ ሲጠብቀኝ ደረስኩ። ወደ ውስጥ እየዘለቅኩ ሳለሁ «በክፍሌ ውስጥ መጥፎ ሽታ አለ። አንድ ነገር እየገማ ነው። ሽታው የሚመጣው ከዚያ ከተዘጋ ክፍል ነው» አለኝ።

«የተዘጋ» የሚለውን ቃል ስሰማ ምን ማለቱ እንደሆነ ወዲያውኑ አወቅሁ። በቤቴ ውስጥ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ምሥጢራዊ የሆነ መራርነት የያዝኩበት ክፍል ነበር። ያንን ክፍል ሁልጊዜ አዘጋውና እቆልፈው ነበር። ማንም ሰው እንዲያውቀው አልፈልግም ነበር።

ክርስቶስ ወደተዘጋው ክፍሌ በቀጥታ ሲሄድ ተከተልኩት። «የሚሸተው ነገር ያለው እዚህ ክፍል ውስጥ ነው። እባክህን ቁልፉን ስጠኝ።» አለኝ።

አሁን ተቆጣሁ። «አሁንስ አበዛው የሚጠይቀው ብዙ ነው» አልኩ። ለራሴም እንዲህ አልኩኝ። «ወደ ሳሎኔ፥ መኝታ ክፍሌ፥ ማንበቢያ ክፍሌና መሥሪያ ክፍሌ እንዲገባ ፈቀድኩለት። አሁን ወደ ቀረኝ የመጨረሻ ክፍል ለመግባት ይፈልጋል። በቤቴ ውስጥ እንግዳ መሆኑን ረሳ መሰለኝ»

ምን እንደማስብ አውቆ ማዘኑን መመልከት ቻልኩ።

ከቁጣዬ በረድ አልኩ። ክርስቶስን ማስቀየም አልፈለግሁም ነበር። የጠየቀውን ሁሉ ማድረግ እፈልግ ነበር። ያ የገማ ነገር ቢወገድ ሕይወቴ የተሻለ እንደሚሆን በውስጥ ሰውነቴ በሚገባ አውቅ ነበር።

በእውነተኛ ልብ እንዲህ አልኩ «ጌታ ሆይ፥ የገማው ነገር ከሕይወቴ ቢወገድ ደስ ባለኝ ነበር፥ እመኛለሁም። ነገር ግን ላስወግደው አቅም አጣሁ።»

እርሱም መልሰ እንዲህ አለኝ «አቅም እንዳጣህ አውቃለሁ። ቁልፉን ብቻ ስጠኝ። ያንን ክፍል እንዳነጻው ፍቀድልኝ። አደርገዋለሁ።»

እጆቼ እየተንቀጠቀጡ ቁልፉን ሰጠሁት።

ክፍሉን ከፍቶ፥ የገማውን ነገር አውጥቶ ወረወረው። ክፍሉንም በሙሉ አጠበው።

ያ የገማ ኃጢአት ከሕይወቴ መወገዱ እንዴት አስደናቂ ነገር ነው!

«ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ
ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ፤
ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፥
በደሌንም አልሸፈንሁም፤ ለእግዚአብሔር
መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ፤ አንተም
የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ።»

[መዝ. (32)፡3፥5]

# የሕይወቴ ጌታ

ቀጥሎ አስደናቂ አሳብ ወደ አእምሮዬ መጣ። ጌታ ሆይ፥ አልኩ በጩኸት «ያንን የተዘጋ ክፍል እንዳደረግከ ቤቴን በሙሉ መግዛት ትፈልጋለህን?»

እርሱም መልሶ «አዎን ላደርግ የምፈልገው ያንን ነው። ነገር ግን እንግዳ ሆኜ ይህን ቤት ለመግዛት አልችልም» አለኝ።

ወዲያውኑ በፊቱ በጉልበቴ ተንበረከኩና «ጌታ ሆይ፥ እንግዳ ነበርክ፥ ባለቤቱ እኔ ነበርኩ። ከዛሬ ጀምሮ ግን እኔ አገልጋይ እሆናለሁ። አንተም የሁሉ ነገር ጌታ ትሆናለህ» አልኩት።

ወዲያውኑ ወረቀት ወስጄ የሚከተለውን ጻፍኩ።

> የእያንዳንዱ የልቤ ክፍል ገገር
> ክርስቶስ ነው።
> እርሱ ጌታዬ ነው፥
> እኔም የእርሱ አገልጋይ ነኝ።

ወረቀቱን ስሰጠው በታላቅ ደስታ ተሞላሁ!

ከዚያን ቀን ጀምሮ ሕይወቴን በሙሉ ተቀበለ። ችሎታዬን፥ ጊዜዬን፥ ገንዘቤንና ሁሉንም ነገር!»

ከዚያ በኋላ በቤቱ ውስጥ ከእርሱ ጋር መኖሬን መቀጠል ብቻ እንደሚያስፈልገኝ አሰበኩ።

ነገር ግን አይደለም!

ከቤት ወጥቶ ወደ መንገዱ ሲሄድ በማየቴ በጣም ደነገጥሁ!

«ጌታ ሆይ»፥ በማለት ጮኽኩ። «ሕይወቴን በሙሉ ሰጠሁ! ትተኸኝ የምትሄደው ለምንድን ነው?»

ወደ ኋላ ተመልሶ እያየኝ *«ትቼህ መሄዴ አይደለም፥ እየመራሁህ* ነው። እንሂድ፥ ና፥ ተከተለኝ» አለኝ ።

በመደነቅ *«እንሂድ?! የት* ነው የምንሄደው?» አልኩት።

እርሱም መልሶ «ወደ ዓለም ሁሉ» አለኝ። በመቀጠልም «በቤትህ አካባቢ የሠራኸው የወንጌል ሥራ መልካም ነው። አሁን ወደ ሌሎች ስፍራዎች እንድትሄድ እፈልጋለሁ...እሩቅ ስፍራዎች፥ አስቸጋሪ የሆኑ ስፍራዎች እንኳ! ኃይል ሁሉ የእኔ ነው፥ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። እንሂድ!» አለኝ።

ወደ እርሱ እየተመለከትሁ ቆሜ ቀረሁ። ወደ ቤቴ፥ ወደ ዕቃዎቼና ወደ ተረጋጋው ሕይወቴ ተመለከትኩ!! ራሴን በጸጥታ እንዲህ ብዬ ጠየቅኩ። «ይህን ሁሉ መተው እችላለሁን?»

ለረጅም ደቂቃ ካለሁበት አልተነቃነቅኩም።

ቀጥሎ ወሰንኩ!

ከዚህ ዓለም ደስታና ተድላ ፊቴን አዙሬ ወደ እርሱ ሮጥኩ።

በፈገግታ፥ እጆቼን ያዘና አብረን መጓዝ ጀመርን።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንገዱ ቀላል ነው ልል አልችልም። ክርስቶስ ወደ ሌላው ሕዝብ ሲመራኝ፥ ሥራዬን ትቼ ዘመዶቼን ስሰናበት በልቤ ታላቅ ሕመም ተሰማኝ።

ደስታው ግን ከየትኛውም የሕመም ስሜት እጅግ የላቀ ነው። በተለይም ደግሞ በክርስቶስ በኩል የዘላለም ሕይወት የመገኘቱን የምሥራች ወደ ሰዎች ሁሉ ማድረስ።

